# የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ

## ተልእኮውና ተግባሩ በተቃውሞ መካከል

በሰለሞን ከበደ ወ-ጻ

ታኅሣሥ 1999 ዓ.ም ታተመ

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ
ማባዛት ወይም ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው።

Copyright © 2006 Solomon Kebede
All right reserved.

ታዛዥነታቸውንና አክብሮታቸውን
ለወላጆቻቸው ላላጓደሉ ልጆቻችን
ለኤልፋዝ፣ ለእሴተ፣ ለጸባኦት እና
ለሳሌም የተበረከተ።

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ ግፊት ላደረጉት ለወንጌል ሐዲስ እና ለባለቤታቸው ለዮሴፍ ሽፈራው፣ ብዙ ጊዜ ሐሳቤን ለማላጋበት ለንጉሤ ቡልቻ፣ ለኅትመት እንዲበቃ መልካም ተሳትፎ ላደረጉት ለአሰይ አንተነህ፣ ለሜሪ ላቀውና ለተስፋዬ ሮበሌ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# መቅድም

ክርስቶስ የሰበሰበው ማኅበር መስመርና ግብ የሌለው የሕዝብ ክምችት አይደለም፤ ወይም የሕይወት አካሄዱንና መድረሻውን ከየጉዳናው የሚነጥቅ ዘርፎ አዳሪ ሠራዊት አይደለም፤ ወይም መሰብሰቡ ብቻውን ግብ የሆነለት የባልንጀሮች ክበብ አይደለም። ይልቁን ቍርጥ ያለ ጥሪና ርቱዕ አቅጣጫ የተሰጠው ሕያው ማኅበር ነው።

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ቤተ ክርስቲያኔ" ብሎ የጠራው ይህ በመስቀሉ ሞትና በትንሣኤው ኀይል ሕልውና ያገኘ ዐዲስ ኅብረተ ሰብ ዛሬ በብዙ ቦታ መንገዱ ተወሳስቦበታል፤ አካሄዱ ተደነቃቅፎአል፤ እይታው ተንሸዋርሮአል። ጌታውና አዳኙ የሚፈልግበትን የጽድቅና የሰላም ወኪልነት ለመፈጸም ከሚችገርበት ትልቅ ተግዳሮት ውስጥ ወድቆአል።

የአካሉን አንድነት የሚያላሉ ሥጋውያን ድክመቶች ነጋ ጠባ ብቅ እያሉ ጉልበቱን ይገዘግዛሉ፤ የድኅረ ዘመናዊው ዓለም ጥላ በላዩ ላይ እያንዣበበ ነጩን ከጥቁር ለመለየት እየተሣነው ያመነታል፤ ከየአቅጣጫው ከሚመጣው ጥቃት የተነሣ ከዋናው ተልእኮ የመዘናጋትና የተራ ማኅበርነት ፈተና ተጋርጦበታል።

ይሁን እንጂ በበዓለ ሃምሳ ቧት በታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ጉልበት፣ በመድኀኒታችን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መሠረት ላይ ተተክሎ የጀመረው ይህ ኅብረተ ሰብ አሁንም የማያሻማ ጥሪና ይህንኑ ጥሪ ያቀረበው ያ መልካም እረኛ አለለት። ለተልእኮው መላካት የሚያግዘው ያ ብርቱ የእግዚአብሔር መንፈስ አለለት። ይህን ቋሚ ቦታውንና ጥሪውን የሚያስገነዝቡን ድምጾች የሚፈለጉበት ጊዜ ላይ ነን።

በዚህ ረገድ አቶ ሰሎሞን ያቀረበልንን ይህን ሁለ ገብ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮና ተግባር ዳሰሳ አራት ጥንካሬዎች ልጠቃቅስ፦

ሁላችንም የምናውቃቸውን የተለመዱ አርእሰት አቶ ሰሎሞን ጥልቅ እይታ እየሰጣቸው "ለካ ነገሩ እንዲህ ነው" እንድንል ልቡናችንን ያነቃቃል። በያዝናቸውን ሠናያት እሴቶች እንድንደላደል ያበረታታናል።

ሰፊና ጥልቅ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮና ተግባር ለመያዝ በሚመች ሞዴል በማቅረብ ሚዛናዊና ሁለገብ የሆነ አመለካከት እንዲኖረን ያግዛል።

አቶ ሰሎሞን የመጽሐፍ ቅዱስን የማይሻር ብርሃን በሰፊው በአገልግሎቱ ላይና በሕይወት ትዝብቶች ካገኛቸው ተግባራዊ እውነቶች ጋር አሰናስሎ ለእምነትም ለተግባርም የሚሆን ጉዳና ያሳየናል።

ይህን ሁሉ ሲያደርግ ክርስቶስ ስለ ሠራው ዐዲስ ኅብረተ ሰብ ያለው መገደድና ይህ ኅብረተ ሰብ ከወንጌል ቢያፈነግጥ ሊከተል የሚችለው ጉዳት እያሳሰበው እንደ ሆነ ይታወቃል፤ ስለዚህም "አንተ ግን" የተሰኘውን ሥር ነቀል የሕይወት ዘይቤና የመንፈሳዊውን ጦርነት የከተት ዐዋጅ ያስተጋባልናል።

የዐዲሱ ኅብረተ ሰብ መሠረትና መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ወደ ጥሪያችን ግንዛቤና ወደ ኀይሉ ሙላት ይሳበን።

ንጉሤ ቡልቻ

# ማውጫ

## የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ተልእኮውና ተግባሩ


I. ሰው 2

II. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ምንነትና ተልእኮው 11

III. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ተግባራት 29

1. አምልኮና ጸሎት 31
   - ሀ) አምልኮ 31
   - ለ) ጸሎት 46
2. ኅብረት ... አንድነትን መጠበቅና መራመድ 85
   - 1) ኅብረት 85
   - 2) ይቅር መባባል 122
3. ወንጌል ስርጭት ... የንስሓና የእመኑ ጥሪ 132
4. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት 135
5. ምግባረ ሠናይ _ የምሕረት አገልግሎት 150
6. የጽድቅና የፍትሕ አገልግሎት 154

IV. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብን የሚገዳደሩ ተቃውሞዎች 161

1. አሮጌው ሰው እና የዓለም ሥርዐት 162
2. ዓለምና መልኮቿ 173
3. ሰይጣን - የጨለማ ኀይላት 191
   - 1) ሰይጣን ማን ነው 191
   - 2) የሰይጣን ማጥቂያ መንገዶች 194
   - 3) የማሳቻ ስልቶቹ 204

V. ድል በሰይጣን ላይ 226

1. ጌታ ኢየሱስ ዲያብሎስን እንዴት ድል አደረገ? 226
2. የክርስቲያን የአማኝ ድል በሰይጣን ላይ 232

VI. አንተ ግን 254

# የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ...
## ተልእኮውና ተግባሩ
## በተቃውሞ መካከል

## I. ሰው

እግዚአብሔር አምላክ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ የፍጥረተ ዓለም ጠንሳሽ፣ ጀማሪና አኗሪ፣ ባለቤት፣ ገዢም ነው።

እርሱ በፈጣሪነቱ መግዛት መብቱ ነው። በፍጥረቱ ላይ ባለ ሥልጣን መሆኑ ከፈጣሪነቱ የተነሣ ይመነጫል።

እርሱ ጊዜ መሰፈር ከመጀመሩ በፊት የነበረ፣ ጀማሪ የሌለው ጀማሪ ሰበብ የለሽ ሰበብ ነው።

ሰማይ፣ ሰማየ ሰማያት፣ ምድር ምድርንም የሞላው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከምድር ዐፈር እንዳበጀው የሕይወትንም እስትንፋስ እፍ ብሎበት ሕያው ነፍስ ያለው አድርጎ እንደ ሠራው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ እንደ ሠራቸው፤ 'አዳም' ብሎ እንደ ጠራቸው እናውቃለን (ዘፍ 5፥2)። አዳምና ሔዋንም እንዲበዙ እንዲባዙም የሚያስችላቸው ተፈጥሮአዊ ብቃትና ትዕዛዝ ተሰጣቸው (ዘፍ 1፥28)።

እግዚአብሔር ሰውን ሲሠራው፣ የራስ ሕልውና ግንዛቤ ያለው እንዲሆን እግዚአብሔር በፈቃዱ ለሰው የራሱ ፈቃድ ያለው ፍጡር እንዲሆን የማሰብ፣ የማስተዋል ችሎታ ሰጠው። ይሁን እንጂ ሰው በፍጡርነቱ ለእግዚአብሔር እንዲገዛ የፈጣሪና የተፈጣሪ እይይዝ ሕግ ግድ የሚለው ነው።

ሰው የራስ ሕልውና፣ ግንዛቤ ያለው፣ ፈቃድ ያለው፣ የማስተዋል



ችሎታ የተሰጠውም ቢሆን በራሱ ፍጹም ሕልውና የለውም። በሥጋዊም ሆነ በመንፈስ ሕይወቱ ከእርሱ ውጭ በሆኑ ነገሮች ላይ ተደጋፊ ነው።

በእግዚአብሔር ፍጥረት በምድር (ውሃ፣ ዐፈር፣ አየር፣ ዕፀዋት፣ እንስሳት) በፀሓይ በሕግጋታቸው በሌላ ሰው ላይ ወዘተ ... ላይ እንዲሁም በቀጥታ በመንፈስ ሕይወቱ ረገድ በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፍ ነው።

ሰው ከምንነቱና ከማንነቱ፣ ከየትነቱ የተነሣ ለእግዚአብሔር መገዛቱና እግዚአብሔርን የሚሻ መሆኑን ሊካድ የሚቻል ጕዳይ አይደለም። ሰው ለሕያውነቱ ተደጋፊ ሙጥኝ ባይ ነው።

ሰው ከምንነቱ፣ ከማንነቱ፣ ከየትነቱ የተነሣ ለሕያውነቱ ለሙላቱ

1. ለእግዚአብሔር መገዛትና
2. እግዚአብሔርን መታዘዙ የግድና ትክክል ነው።

«ለእግዚአብሔር መገዛት» ስንል በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ማደርን እናስባለን፤ እግዚአብሔር አምላክ ሲሆን፣ ሰው ግን እግዚአብሔርን አምላኪ መሆኑን እናጸናለን። በሁሉ እግዚአብሔር በላጭ፣ ሰው በእግዚአብሔር ተበላጭ፣ እግዚአብሔር ቀዳሚ ሰው ተቀዳሚ፣ ተመሪ፣ ለእግዚአብሔር ተጠሪ መሆኑን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መስተካከልና እኩልነት እንደማይኖር እንቀበላለን።

«እግዚአብሔርን መታዘዝ» ስንል እግዚአብሔር በግልጥ የሰጣቸውን መመሪያና ትእዛዝ ሰው ማክበር በተግባር የመግለጥ/የማዋል ግዴታና ተጠያቂነት እንዳለበት እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ

ሰው የእግዚአብሔር ንብረት ነው፤ የእግዚአብሔር ነው፤ እውነቱ ይሄ ነው።

ሰውን ሕያው ነፍስ ያለው፣ የራስ ሕልውና ግንዛቤ እንዲሁም ባለ
ፈቃድ ወይም ፈቃድ ያለው እንዲሆን አቡቃው ወይም አስቻ
ለው:: ይህ አቋም ሰው ራሱን የሚያውቅ፣ በራሱ የሆነ የራሱ
ፈቃድ ያለው እንዲሆን የስቈጠረው እንጂ፣ የሰው ማንነትና ምን
ነት በእግዚአብሔር በፍጥረቱ ክልል ውቅር ውስጥ የተቀናበረ
ነው፤ ከዚያ የወጣ ኢተደጋፊ ልዑል አይደለም::

እግዚአብሔር ሰውን ከምድር ዐፈር እንዳበጀው፣ የሕይወትንም
እስትንፋስ እፍ እንዳለበት ሰው ሕያው ነፍስ ያለው እንደ ሆነ
መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: የምድር ዐፈር የእግዚአብሔር ነው፤
እስትንፋሱም የእግዚአብሔር ነው፤ ስለ ሆነም በሰው ዘንድ
ያለው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው::

ይህ የፍጥረት ሥርዐት የሆነውን እውነታ ሰው በራስ ሕልውና
ግንዛቤ፣ በፈቃዱ ሲቀበለውና ሲያከብረው፣ ከአምላክ ጋር በሚ
ኖር ግንኙነት በኑሮው ሁሉ ሲያጸናው፣ በፍጥረት ሥርዐት ልክ
የሆነው በፍጡሩ በኩልም እንደዚያው ሲሆን፣ ለሰው ሕይወትና
ሰላም (ሻሎም) ይሆናል:: አለበለዚያ «ንፍረትና ሞት» ነው::

ተፈጥሮ በሥርዐተ ሕጉ በስተመጨረሻ በኀይል ግድ የሚባለው
ሰው ከወዲሁ በፈቃዱ ለእግዚአብሔር ልገዛለት ማለትን ቢቀበ
ለው፣ አሜን ቢል መልካም ነው:: ሰው ፈቃድ አልባ በሆነበት
መንኰራኵራዊ መስተጋብር ሳይሆን፣ የሰው ፈቃድ በተሰጠበት
መልኩ ሰው አዎንታዊ ምላሽ ቢሰጥ፣ የሰውና የእግዚአብሔር
ግንኙነት ታላቅ ውበት፣ ጥሩ ስምረት ያለው ይሆናል:: ይዐም
ማለት ሰው በፍጡርነቱ ግዳጅ ለእግዚአብሔር ተገዥ ከሚሆን
ይልቅ፣ በፈቃዱ ለእግዚአብሔር ተገዥ ቢሆን ከእግዚአብሔር
ጋር የሚኖረው ግንኙነት ውብ ይሆናል:: ሰው በፈቃዱ ለእግዚ
አብሔር ቢገዛ ሕይወቱና ሙላቱ ነው:: ሰው በፈቃዱ አሻፈ
ረኝ ለእግዚአብሔር አልገዛም ቢል ዐልፎት መሄድ ከማይችለው
ግድግዳ ጋር እንደሚላተምና ራሱን እንደሚያሠቃይ ሰው/እን



ስሳ ነው:: በሕይወት ምንጭና ሙላት ላይ መነሣትና ጥፋት
ነው:: የገዛ ሕይወትን ማቃረን፣ መጠናወት ነው:: ከእግዚአብሔር
ጋር በፈቃዳችን አለመስማማት ሕይወታችን ማወላከፍ፣ የሕይ
ወትን ሂደት መቃረን መጻረር ነው:: ("*እስራኤል ሆይ፣ በእኔ ላይ
ስለ ተነሣህ፣ ረዳትህንም ስለ ተቃወምህ ተጠፋለህ* (ሆሴ 13፥9)::

እንግዲያስ ለእግዚአብሔር አለመገዛትና እግዚአብሔርን አለመ
ታዘዝ ኀጢአት ነው:: ቅራኔ ሕይወት፣ ጸረ - ሕይወት ነው::
የገዛ ሕይወትንና ሰላምን መጻረር ነው::

እግዚአብሔር ለሰው በጎ መሆኑን ሰውን በፈጠረበት ጊዜ ገል
ጧል:: እግዚአብሔር አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ለሰው ሕይወት
የሚያስፈልገውን ነገር አዘጋጀ:: ፀሐይና ምድርን ፈጠረ፤ ምድ
ርም በራሷ ዛቢያ ላይ የምትሽከረከር በፀሐይም ዙሪያ ምሕዋ
ሯን ጠብቃ የምትዞር ለሁለቱም ዐይነት እንቅስቃሴዋ አቅጣ
ጫንና ፍጥነትን ተመነላት:: በምድርም ያሉትን ነገሮች ዐፈ
ሩን፣ ውሃውን፣ አየሩን፣ ዕፀዋቱን፣ እንስሳቱን በቅድሚያ ወደ
መኖር አመጣ:: ይኼ ሊሆን የቻለው አዳም እግዚአብሔርን
«እኔን ከመሥራት በፊት እነዚያ ለእኔ የሚያስፈልጉ ነገሮች
መኖራቸውን በቅድሚያ አረጋግጥ ብሎት አልነበረም:: እግዚአ
ብሔር ለሰው ዐሳቢነቱን፣ ተጠንቃቂነቱን፣ የስውን ምቾት ፈላ
ጊነቱን ከፍጥረት ቅደም ተከተሉ በግልጥ እንረዳለን::

እግዚአብሔር በፍጥረት አባትነቱ በጎ ነው:: ልንደገፈው፣ ልን
ታመንበት የሚበቃ ነው:: ለሕይወታችን እኛ ባለቤት ከመሆና
ችን በፊት፣ እግዚአብሔር የሕይወታችን ባለቤት ሆኖ እናየዋ
ለን:: እንዲያውም እኛ የራሳችን ሕይወት ባለቤት ለመሆን በም
ንነሣበትና በምናሳየው ሁኔታ ሁሉ በቅድሚያ እግዚአብሔር የሕ
ይወታችን ባለቤት መሆኑን መዘንጋታችንና እግዚአብሔርንም
ከባለቤትነቱ መጋፋታችን ነው:: ምንጊዜም እግዚአብሔር ለእኛ
በጎ ዐሳቢ ተጠንቃቂ መሆኑን በማያቋርጥ ሁኔታ ልናስተውልና

ልንታመንበት፣ ልንደገፍበት ፀሳባችንን ልንጥልበት የሚገባ ነው:: በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ማረፍ ነው:: ለእግዚአብሔር ተገዛንም ማለት በእግዚአብሔር በጎ አሳቢነቱ ላይ ፀረፍን የሕይወት ምንጫችንና ሙላታችን እርሱ ሆነ ማለት ነው::

ሰው በሥጋዊ ሕይወቱ ማለትም በፀጸደ ሥጋው በጊዜ ውስጥ የታጠረ ነው:: ሕይወቱም የአሁን ነው፤ ዕውቀቱም በዚህ ረገድ ከአሁንና እዚህ ካለ ነገር ጋር የተያያዘ ነው:: የዕውቀቱም መጠንና ጥራት በስፍራ እና በጊዜ ውስጥ የታጠረ፣ የተቀነበበ ነው:: ሰው በምድራዊ አካል ሕይወቱ በ«አሁንና በዚህ» ጥ ዳዮች የተያዘ ነው:: ከአሁን እዚህ ካለው ነገር ባሻገር ያለውን ነገር የማየትና የመረዳት ችሎታው የተገደበ ነው:: ይሁን እንጂ ሰው የነገው ነገር እንዲሁም እዚህ ካለው ባሻገር፣ እዚያ ማዶ ያለው ነገር ይገደዋል፤ ያሳስበዋል፤ ሥጋት ይጋርድበታል፤ ሕይወቱን ሰላሙን እንጥልጥል ያደርግበታል:: ስለ ሆነም ሰው ከአሁንና ከዚህ ባሻገር ስላለው ነገር ምቹነቱ ሕይወት የማይጠናወት መሆኑን ማረጋገጥ ይሻል:: ይህ ግን ሊረጋገጥ የሚቻለው በእምነት በኩል ነው፤ በጎነቱን በፍጥረት ቅደም ተከተል በገለጠ በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ብቻ ነው::

ሰው የእግዚአብሔርን ሥራ አስተውሎ በእግዚአብሔር ላይ ለዛሬም ሆነ ለነገ ሕይወት ካልተደገፈ በስተቀር ጥጥ፣ ሥጉ፣ ተጨናቂ፣ ርካታ ቢስ፣ ፈሪ፣ አገርጋሪ፣ ተተናኳይ፣ ተቅበዝባዥ ሟች ነው::

ጥረቱ መሄድ፣ መሄድ፣ መሮጥ፣ መሮጥ፣ የትም ሳለመድረስ መዝለል፣ መዝለል ምንም ሳለመያዝ፣ ሳለማውረድ እንዲያው መንጠራራት ነው:: ነገ ለመኖር በመታገል በመዘጋጀት ዛሬ የሕይወትን ወቅት በማሳለፍ የሕይወትን ዘመን መጨረስ ነው:: ከእግዚአብሔር እስከነ አካቴው መለየት ነው::



ሀ) ሰው የፈጣሪውን ሕግ ተሳለፈ

ኀጢአት በዔድን ገነት ጀመረ፤ ውድቀት መጣ::

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በዔድን ገነት መልካምና ምቹ ስፍራን እንዳዘጋጀ የሠራውንም ሰው ወደዚያ እንዳመጣውና ከፉና ደግን ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ በስተቀር ለማየትና ለመብላት መልካም የሆኑትን የዛፎች ፍሬ እንዲበላ እንዲመገብ ፈቀደለት::

አንድ ጊዜ አሳቹ የቀደመው እባብ ወደ ሄዋንና አዳም መጣ፤ ሄዋንን እንዲህ ብሎ ጠየቃት::

*"በርግጥ እግዚአብሔር፣ በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ' ብሎአልን?"* አላት (ዘፍ 3፥1):: አጠያየቁ በእግዚአብሔር ላይ አሉታዊ፣ አፍራሽ አመለካከት በሚያነሣሣ አቀራረብ ነው:: የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ በጎነት፣ ቸርነትን በሚያሳይ በሚያጐላ መንገድ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ከልካይ፣ ንፉግ፣ ስስታም፣ እንደ ሆነ በሚያስመስል አቀራረብ ነው የመጣው "እግዚአብሔር ምን ምን እንድትበሉ ፈቀደላችሁ/አዘዛችሁ" የሚል የእግዚአብሔርን ሰጭነት የሚያጐላ ጥያቄ አልነበረም ያቀረበው::

እርሷም እንዲህ ስትል መለሰችለት

*" ...በአትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት እንችላለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ ትሞታላችሁ' ብሎአል"* (ዘፍ 3፥2-3)::

እግዚአብሔር ሁሉን የፍራፍሬ ዛፍ ፈቅዶ አንድ ዛፍ ቢከለክል፣ ለራሱ ቢያስቀር ምን አለበት? ሁሉን ችሮ አንድ ለራሱ ለይቶ ቢያስቀር ቸርነቱ እንደሌለ ያስቈጥራል ወይ? ገነትንስ

ለአዳም እንዲያዘጋጅ የሚያስገድደው ምንድን ነው፤ አንድ ሰው መቶ ወንበሮች ሠርቶ ዘጠና ዘጠኙን ሰጥቶ አንዱን ቢያ ስቀምጥ ንፉግ ያሰኘዋል? ቸር እንዳልሆነ ያስቈጥረዋል? እንደ ዚያ አያሰኘውም፤ አያስቈጥረውም::

ይሁን እንጂ ሰይጣን እግዚአብሔርን በሰው ዘንድ እንደ ጨካኝ፣ የሰውን ሙሉነት መልካምነት እንደሚቀናቀን፣ እንደ ንፉግ አድርጐ ሲያቀርብ ራሱን ግን ለሰው ሙሉነትና መልካምነት እን ደሚቈረቈር እንደ ነጻ አውጭ ታጋይ አድርጐ ነው ያቀረበው::

ሄዋንም የእባቡን ቃል ሰማች፤ የሔዋን ችግር ያለማመን ችግር አልነበረም:: ችግሯ ማንን ማመን ነበር:: እርሷ ግን የእግዚአ ብሔርን ቃል ከማመን ይልቅ የሰይጣንን ቃል አመነች:: እግ ዚአብሔርን ከማመን ይልቅ ሰይጣንን አመነች:: የሰዎች ችግር በጥቅሉ ያለማመን ችግር ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ያለማመን፣ ቃሉን ያለማመን ችግር ነው::

ሰዎች እግዚአብሔርን ከማመን ይልቅ አሳቹን ያምናሉ ወይም የራሳቸውን ሀሳብ ያምናሉ፤ ሰይጣንም ጥረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንዳይታመን ነው እንጂ ሌላው እንዳይታመን አይደ ለም::

ከዚህ የተነሣ ኀጢአት ሆነ፤ ውድቀት መጣ:: ሰው እንደ እግ ዚአብሔር ለማወቅ ፈለገ፤ ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከልን ፈለገ፤ ከፍሬዋ ቢበሉ እንደማይሞቱ የሰይጣንን ቃል አመኑ::

ለእግዚአብሔር አለመገዛት ፍሬዋን ሲበሉ ባሰቡ ጊዜ ለእግዚ አብሔር መገዛት ለእግዚአብሔር ማደር ተጣሰ:: ፍሬዋን በበሉ ጊዜ ደግሞ በዚያን ወቅት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተግባር ተላለፉ፤ ስለዚህም ኀጢአት ሠሩ፤ በደለኞችም ሆኑ:: ኀጢአት ፈጸሙ፤ ለእግዚአብሔር የአለመገዛትና የአለመታዘዝ ርምጃ ወሰዱ::



ኀጢአት በመሠረቱ ለእግዚአብሔር አለመገዛትና እግዚአብሔ ርን አለመታዘዝ ሲሆን፣ በደል ደግሞ በኀጢአት ምክንያት የተጠያቂነት ዕዳ ነው:: ለመተላለፋችን የምላሽ ዋጋ የመክፈል ተጠያቂነት፣ ባለ ዕዳነት ነው::

ሰው በኀጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለየ እግዚአብሔር ከቅድስናው ከጽድቁ የተነሣ ከሰው ተለየ፤ ሁለት አቅጣጫ መለያየት ሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል (ኢሳ59፥1-2)::

በዘፍ. ምዕራፍ 3 እንደምንመለከተው ሰው በኀጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ሲለይ ከራሱ ተለየ፤ ራሱን መቀበል አቃተው፤ ከራሱ ሸሸ፤ ቅጠል አገለደመ፤ በሰውና በሰው መካከል መለያ የት ሆነ፤ ከተፈጥሮ በረከትም ተለየ፤ ከገነት ተባረረ፤ መሬት ተረገመች፤ እሾኽና አሜከላ የምታበቅል ሆነች፤ መብላት በድ ካም፣ በላብና በወዝ ሆነ፤ መውለድ በጭንቀት እንዲሆን ታወጀ:: የመጀመሪያ ኀላፊነቱ ገነትን መጠበቅና ማበጀት (የፈጠራ ሥራ ) ነበረ:: ኋላ ግን ለዕለት ምግቡ ደካሚ፣ ዋታችና በእሾ ኽም ተወጊ ሆነ(ዘፍ 3፥16-29)::

ለ) ሰው ከእግዚአብሔር ሲለይ

1. ሰው ከራሱ ተለየ (ሰው በራሱ ነገር አለመርካት የራሱን ክፍል ማፈርና መሸሽ)
2. ሰው ከሰው ተለየ (አዳምና ሄዋን፣ አቤልና ቃየን ወዘተ... )
   (ሰው ሰውን መብለጥ፤ ሰው በሰው ላይ መሰልጠን ይሻል፣ በሰው <u>መግባት</u>፣ ሰው ሰውን ይፈራል፣ ይጠራጠራል) (ወን ድም በወንድሙ ላይ፣ ሰው በሰው ላይ፣ ነገድ በነገድ ላይ፣ ወገን በወገን ላይ ቋንቋ በቋንቋ ላይ፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ ያምፃል፣ ይነሣል ... )
3. ሰው ከተፈጥሮ በረከት ተለየ

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከል መሻቱና ለዚሁም ብቃት ትእዛዝ ተላልፎ ከተከለለው ዛፍ ክልል ጥሶ ፍሬ ቀጥፎ መብላቱ ዐመፁ፣ ዐመፀኛነቱም ሆነ በዚህ ዐመፀኝነት አቋሙ ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር እግዚአብሔር አይሆንም አለ፤ ተቃወመ:: ስለዚህም ከገነት አስወጣው፤ መቼም በጥረቱ እንዳይደርስበት ከልካይ፣ የሕይወትን ዛፍ ጠባቂ አኖረ::

*ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ፣ "ሰው ... ሰውንም ካስወጣው በኋላ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባላዊ ሠይፍ ከዔድን በስተ ምሥራቅ አኖረ"* (ዘፍ 3፥22-24)::

ከዚህም ቃል በተጨማሪ የምናስተውለው ሰው አሁንም ቢሆን በስውር ልቡናው በኅቡዕ ማንነቱ እዚያ ማዶ የሕይወት ዛፍ የሕይወት ርካታ እንዳለ ያውቃል:: ወደዚያም የሕይወት እርካታ ለመድረስ ሕይወትን ለመጨበጥ የማያቋርጥ ጥረትና ጕዞ እንደሚያደርግ፤ ይሁን እንጂ ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ የሚያደርገው ሁሉ ከሕይወት ዛፍ መለስ በኪሩቤልና በየአቅጣጫው በምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ እንደሚታገድና ይጓጓ እንጂ፣ መቼም በራሱ ጥረት ወደ ሕይወት ሙላት መድረስ እንደማይችል ነው::

ከዚህም የተነሣ ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል(ሮሜ 5፥10):: እግዚአብሔር ግን በበኩሉ የዕርቅን መንገድ የሕይወትን መንገድ ለሰው አዘጋጅቷል፤ የተፈጥሮንም ጸጋ ሙሉ በሙሉ ከሰው ያራቀ አይደለም፤ ዝናብም ያዘንባል፤ ፀሓይን ለጻድቃንም ለኀጥአንም ያወጣል ወዘተ ...:: ወደ ሕይወት ዛፍ ሰው በራሱ ጥረት በራሱ መንገድ የሚያደርገውን ጥረት ከንቱ ያደርጋል፤ በጌታ ጸጋ በኩል እንጂ፣

*«ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስና በበሮቿም በኩል ወደ ከተማ*



*ይቱ ለመግባት መብት እንዲኖራቸው ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው»* (ራእ 22፥14)::

## II. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ምንነትና ተልእኮው

እግዚአብሔር የኪዳን አምላክ ነው፤ ሰውም የእግዚአብሔር የኪዳን ፍጡር ነው፤ ሰው ኪዳን መግባት የሚያበቃውን ፈቃድ እግዚአብሔር ሲፈጥረው አድሎታል::

እግዚአብሔር ከግለሰብም ሆነ ከማኅበረ ሰብ ወይም ከኅብረተ ሰብ ጋር ኪዳን የሚገባ አምላክ ነው:: ኪዳን ማለት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው:: ኪዳን የሚመሠረተው በሁለት ግለሰቦች ወይም ወገኖች መካከል በጋራ ፈቃድ፣ በጋራ መቀባበል ነው:: በኪዳን ውስጥ ሁለቱም ወገኖች ግዴታና መብት ይኖራቸዋል፤ ማለትም እያንዳንዱ ወገን የራሱ የሆነ መብት እንዲሁም በራሱ ላይ የተጣለ ግዴታ አለው::

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ወይም ከማኅበረ ሰብ ጋር ኪዳን ሲገባ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ የመመለክ፣ የማዘዝ መብት ሲኖረው ከእርሱ ጋር ቃል ተጋቢው ግለሰብ ወይም ማኅበረ ሰብ ደግሞ በእግዚአብሔር የመባረክ ወይም ለመጋቦቱ መብት አለው::

እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ኪዳን ገብቷል፤ ከሌዊ፣ ከሙሴ ... ወዘተ ጋር ኪዳን ገብቷል::

*"እንደ አዳም ቃል ኪዳን ተላለፉ*
*በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም"* (ሆሴ 6፥7)::

*"ከእርሱ ጋር የገባሁት ኪዳን የሕይወትና የሰላም ኪዳን ነበር፣*
*እነርሱንም ሰጠሁት፤ ይህም ክብርን አመጣ፤ እርሱም*
*አከበረኝ፤*
*ስሜንም በመፍራት ጸና"* (ሚል 2፥5)::

ብሉይ ኪዳን ስለ ቀደመው ኪዳን ታሪክ የሚያወሳ ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ ስለ አዲሱ ኪዳን ያወሳል። እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በገባው የተስፋ ቃል መሠረት ለአዲስ ኪዳን ያጨውን ኅብረተ ሰብ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት በኀያል ክንዱ ነጻ አወጣው።

*"በግብፅ ላይ ያደረግሁትን፣ በንስር ክንፍ ተሸክሜ ወደ ራሴ እንዴት እንዳመጣኋችሁ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል። አሁንም በፍጹም ብትታዘዙኝና ቃል ኪዳኔን ብትጠብቁ እነሆ ከአሕዛብ ሁሉ እናንተ የተወደደ ርስቴ ትሆናላችሁ፤ ምንም እንኳ ምድር ሁሉ የእኔ ብትሆንም፣ እናንተ ለእኔ የመንግሥት ካህናት የተቀደሰ ሕዝብ ትሆናላችሁ"* (ዘፀ 19፥4-6)።

*"ሙሴ ወደ ሕዝቡ ሄዶ የእግዚአብሔርን ቃሎችና ሕጎች ሁሉ በነገራቸው ጊዜ በአንድ ድምፅ ሆነው፣ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን አሉ"* (ዘፀ 24፥3)።

*"ከዚያም የኪዳኑን መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው፤ እነርሱም፣ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፤ እንታዘዛለን አሉ። ከዚያም ሙሴ ደሙን ወስዶ፣ ሕዝቡም ላይ ረጭቶ፣ ይህ እነዚህን ቃሎች በሰጠ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የገባው የቃል ኪዳኑ ደም ነው አላቸው"* (ዘፀ 24፥7-8)።

የቀደመውን የኪዳን ሕዝብ እግዚአብሔር ለኪዳን ከመጋበዙ በፊት ታላቅ ትድግና አደረገለት። ታላቅነቱንና በጎነቱን አሳየው። ከዚያም የኪዳኑን ረቂቅ በሙሴ አማካኝነት ለሕዝቡ አቀረበ፤ ሕዝቡም ተመልክቶ በአንድ ሀሳብ ተስማምቶ የኪዳኑን ቃል ተቀበለ። ከዚያም በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል ኪዳን ተመሠረተ፤ ይህንኑ ኪዳን የማጽኛ ምልክት ይሆን ዘንድ የመሥዋዕቱ ደም ተረጨ።



በዚህ ኪዳን መሠረት እስራኤል የተመረጠ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሆን፣ እግዚአብሔርም የእስራኤል አምላክ ሊሆን፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ሊታዘዝ፣ እግዚአብሔርም በበጎነት ሕዝቡን ሊከብ፣ ሊያጠግብ ስምምነት ተደረገ።

የኪዳኑ ቃል ይዘት ሁለት አቅጣጫ ያለው ነው፤ ይኸውም ሕዝቡ ሽቅብ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረው አምልኮአዊ ግንኙነት ወይም አምልኮተ እግዚአብሔርና እርስ በርስ ስለሚኖረው የሰመረ ግንኙነት የመተሳሰብና የመደጋገፍ ኑሮ ነበር።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ኪዳን የሕይወትና የሰላም (ሻሎም) ኪዳን ነበር። ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ መልካምና ንጹሕ ግንኙነትን ያመለክታል። ሕዝቡ በአንድ ልቡ፣ በሙሉ ኀይሉ፣ በሙሉ ነፍሱ እግዚአብሔርን ብቻ ሊያመልክ፣ እግዚአብሔርም በሕዝቡ መካከል የሻሎምን በረከት ሊሰጥ ነው። ሻሎም ሲል የግል፣ የልብ ሰላምን ብቻ የሚያመለክት አልነበረም። ሻሎም የሚለው የዕብራይስጡ ቃል የእርስ በርስ ሰላምን፣ ጭቆናና ብዝበዛ መወገዱንና የፍትሕ መስፈንን፣ የግብፅ በሽታ መታገድን ወይም ጤና መስፈንን፣ ጦርነት መታገድን፣ ብልጥግና ማለትም የግብርና ምርት መትረፍረፍን የሚያካትት ነው።

ይህን ኪዳን መተላለፍ ማለት የግዛ ሕይወትን የግልንም ሆነ የማኅበረ ሰብን ሕይወት ማደፍረስ፣ መጻረር ማለት ነው። የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ በክርስቶስ የተመሠረተ ነው።

" እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ"

የቀደመው የኪዳን ሕዝብ እስራኤል በወይን ተክል ይመሰል ነበር። እስራኤል በእግዚአብሔር የተተከለ የወይን ተክል ተብላ ትታወቅ ነበር። ይኸው እውነት በመዝሙር 80 ላይና በኢሳይያስ ምዕራፍ 5 ላይ ተገልጧል። የአዲስ ኪዳን ሕዝብ ደግሞ በገላትያ 6

ላይ 'የእግዚአብሔር እስራኤል' ተብሎ ተጠርቷል::

እግዚአብሔር ከቀደመው የኪዳን ሕዝብ ጋር ኪዳን ከመግባቱ በፊት እስራኤልን ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ለማውጣት ታላቅ የትድግና ሥራ እንደ ሠራ ሁሉ አዲሱንም የኪዳን ሕዝብ ለኪዳን ከመጥራቱ በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ መሥዋዕትነት ታላቅ የመቤዠት ሥራ ሠርቷል::

*"ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይሀ ነው"* (ማቴ 26፥28)::

የአዲሱ ኪዳን ሕዝብ ወይም ኅብረተ ሰብ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራል::

ቤተ ክርስቲያን ተግባሯና ተልእኮዋ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ተቀምጧል:: ይህን ፍሬ ሀሳብ በዚህ ጽሑፍ ላይ ለማየት ከመሞከራችን በፊት፣ አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያን ስንል ምን ማለታችን ነው?

ቤተ ክርስቲያን የሚለው የአማርኛ ቃል በግሪክ ኤክሊስያ ከሚለው ቃል የተተረጐመ ሲሆን፣ ፍችውም "ተጠርተው ወጥተው የተሰበሰቡ" ማለት ነው:: ይህ ቃል በጥንት ግሪካውያን ዘንድ ፈጽሞ መንፈሳዊ ትርጒም የሌለው ቃል ሲሆን፣ ቃሉም ትርጒም ላይ የዋለው ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ስብሰባን ወይም ሕጋዊ ሸንጎን ለመግለጥ ነበር:: እንግዲህ የቃሉ አመጣጥ እንዲህ ከሆነ፣ በአዲስ ኪዳን አማኞችን አስመልክቶ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሁል ጊዜ የሚያሳየው በእግዚአብሔር አብ ከዓለም ተጠርተው በኄታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት በማመን በመንፈስ ቅዱስ የሕይወት ለውጥ (ዳግም ልደት) ያገኙትን የአማኞች ስብስብ (ኅብረት) ነው:: አማኞቹ የወንጌል ስብከት ለመስማት፣ እንዲሁም ቅዱሳት ምስጢራትንና



ሃይማኖታዊ ሥርዐትን ለመፈጸም የሚሰበሰቡትን ቦታ (ሕንፃ) አይደለም::

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በመሰላቸው መስፈርት ወይም መለኪያ ተመራርጠውና ተጠራርተው የሚመሠርቷት ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ክበብ አይደለችም::

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በእግዚአብሔር አብ ቅዱስ አጠራር፣ ከዓለም ተጠርተው፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞግተውና ተወቅሰው፣ የክርስቶስን አዳኝነትና ጌትነት አምነው፣ ድነትን ተቀብለው፣ በዳግም ልደት የእግዚአብሔር አብ የጸጋ ልጆች ሆነው፣ በመንፈስ ቅዱስ አጥማቂነት ወደ ክርስቶስ አካል የተጨመሩ የአማኞች ኅብረት ናት::

1. አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት ድነት ያገኙ ናቸው::

   በደሙ:-

   ሀ. ከኀጢአትና ከበደል ሥርየት አግኝተው (ኤፌ. 1፥7)፣
   ለ. ከፍርድና ከኵነኔ፣ ነጻ የሚያደርገውን ጽድቅ ተቀብለው (ሮሜ 5፥18፤ 8፥1)፣
   ሐ. ከሕግ ርግማን፣ ከሕግ ሥራና ከከንቱ ኑሮ ተዋጅተው (ገላ3፥13)፣
   መ. ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅንና የጸጋ ልጅነትን ሥልጣን አግኝተው (ዮሐ 1፥12-13)፣
   ሠ. ለዘላለም ርስት ለክብር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የታተሙ ናቸው (ኤፌ. 1፥13-14)::

የመስቀሉን ማዕከልነት በድነታችን አንጻር ወሳኝ ነው:: ሮሜ 3፥21-23 እንዲህ ይላል፤ *"አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሠከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው*

የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኀጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለመተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፤ ራሱም ጽድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው" (ሮሜ 3፥21-23)።

"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌ 2፥8-9)።

የድነታችን ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲሆን፣ የድነታችን መሠረቱ ደግሞ የፈሰሰው የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ወይም በመስቀሉ ላይ የተከናወነው ሥራ ነው። የድነታችን መንገድ የእምነት መንገድ ነው። ይህም ድነት በሕይወታችን የሚተገበረው፣ የሚተረጐመው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። አራት ሐሳቦችን ነው ያነሣሁት፦

1) የድነታችን ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፤
2) መሠረቱ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ወይም በመስቀሉ ላይ የተከናወነው ሥራ ነው፤
3) መንገዱ የእምነት መንገድ ነው።
4) ኀይሉም የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው።

ይህንን ድነት የምንቀበለው በእምነት ነው። ይሁንና የእኛ እምነት ያመጣው ሳይሆን፣ የመጣው ከጸጋው የተነሣ ነው። ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል ይላል (ኤፌ 2፥8)። ደግሞ ይኽ በሕይወታችን የሚተረጐመው፣ የሚከሠተው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።



ከላይ እንደ ተጠቀሰው፣ «አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል» ቲቶም ይህንኑ ያጠናክርልናል፤ «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና» (ቲቶ 2፥11)። "ነገር ግን የመድኀኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለሀዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፣ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም። ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው። ቃሉ የታመነ ነው" (ቲቶ 3፥4-7)።

እነዚህ ክፍሎች የተጠቀሱትን አራት ዐሳቦች ይይዛሉ። የድነታችን ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የድነታችን መሠረት የክርስቶስ ኢየሱስ ደም፣ መንገዱም የእምነት መንገድ መሆኑን ነው። «ለሚያምኑ ሁሉ የሚሆን» ይላልና። ተግባራዊ የሚሆነውም የሚተረጐመው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው።

መቼም ስለ ጸጋ እናውቃለን። ግን ብዙ ጊዜ ጸጋ አይገባንም። ጸጋ ነጻ ስጦታ እንደ ሆነ ይህን በትርጒም አንጻር እናውቃለን። ግን በሕይወት አኗያ ለመረዳት ግን በጣም ይቸግረናል። ባህላችን የጸጋ ባህል ስላልሆነ የምናድግበት አካባቢ ሁሉ በዓለም ዙሪያ እንዲሁ ነጻ ስጦታ የሚባለው ነገር አይታይም።

አሁን እዚህ አንድ ሰው ድንገት መጥቶ ወድጃችኋለሁ ብሎ አንዳንድ ሚሊየን ዶላር ቢያድለን፣ እግዚአብሔር ይስጥልን ብለን ነው የምንቀመው ወይስ ጥያቄ እናነሣለን በውስጣችን? ለምንድን ነው የሚሰጠኝ? እንዴት ሊሰጠኝ ይችላል? ይሄ ነገር ከየት የተገኘ ነው? ጤናማ ነው? ወይስ ከኔ ምን ፈልጐ ነው? ከዚህ በኋላ እኔን ምን አድርግልኝ/ሁንልኝ ሊለኝ ነው? እንደ

ዚህ ዐይነት አያሌ ጥያቄዎች ይመጡብናል።

ጸጋ ብዙ ጊዜ ለእኛ እንግዳ ነው፤ ግራም ያጋባናል። ሌላው ቀርቶ እንኳን በክርስቶስ ሕይወት ስንመላለስ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው በጸጋ እንደሆነም ዐናስብም። ትምህርታችን ልማዳችንን ማሸነፍ ያዳግተዋል፤ ሲቆይም ትምህርታችን ይረሳና ልማዳችን ጸንቶ ይቆያል። በሥራ እንደ ሆነ ነው የምንቈጥረው። አሁን ሕይወታችን ስንቃኘው ትንሽ ያልጣፈጠን እንደ ሆነ፣ ምናልባት እዚያ ጋ አንጕል ተናግረን፣ ሰውን ዘልፈን ተሳድበን ከሆነ፣ እዚህ ጋ ተናደን ከሆነ ትንሽ ቀላምደን ወይም ሌላ ጥፋት አጥፍተን ከሆነ፣ በጸሎት ጊዜ ወደ ጸሎት መምጣት ይቸግረናል። እግዚአብሔር ጕድለት ስላለብን የሚቀበለን አይመስለንም፤ ስለ ሆነም የጥፋታችን ማካካሻ የሚሆን ጥቂት በጎ ሥራ ከሠራን በኋላ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንሞክራለን። እንዲህ ሲሆን ነው ቀለል ብሎን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው? ጥቂት መልካም ካደረግን፣ ጸሎት ሲባል ገፋ ገፋ ያደርገናል። ለምን? እግዚአብሔር በጎ ሥራችን እንደሚቀበለን ስለምንቈጥር ነው።

ወደ እግዚአብሔር እንዲሁ መግባትና ተናዞ ይቅርታ መጠየቅ መፍቀዱን መቀበል በጣም ያስቸግረናል። አንድ የሆነ ነገር እጅ መንሻ ለማምጣት እንፈልጋለን።

ትንሽ ሕይወታችን ከተበላሸብን፣ የማካካሻ ሥራ ሠርተን ከዚያ በኋላ ወደ ጸሎት ብንመጣ ይቀለናል፤ የዚያን ጊዜ ተቀባይነት እንደምናገኝ እንቈጥራለን። እንዲሁ ጕድለታችንን ዐውቀን፣ ጸጋውን ተስፋ አድርገን በክርስቶስ መሥዋዕትነት የሚገኘውን ይቅርታውን ተማምነን መምጣት እንደምንችል አይገባንም። በመጠኑም ቢሆን ለኀጢአታችን ማካካሻ ትንሽ ዋጋ መክፈል እንዳለብን እናስባለን። ተቀባይነት እንድናገኝ የራሳችንን ጽድቅ



ቈጥረን መምጣት እንሻለን፤ የቈጠርነው እንደሌለ ስናስብ ደግሞ ከጸሎትም እንሸሻለን።

በሉቃስ ወንጌል፣ ቤተ መቅደስ የሄዱትን ሁለት ሰዎች እናስታውሳቸዋለን። "ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑ ሌሎችን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል፤ "ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛው ቀራጭ ሲሆን፣ ፈሪሳዊው ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ እግዚአብሔር ሆይ እንደሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና አመጸኞች አመን ዝሮችም ወይም እንደዚሁ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግናለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት አወጣለሁ። ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዐይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳን አልወደደም ነገር ግን አምላክ ሆይ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ" (ሉቃ18፥9-14)።

ለቀራጩ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነበረ ተስፋው፤ ፈሪሳዊው ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረቢያ ትምክሕት ያከማቸው ጽድቅ ነበረ። የያዘው የምስጋና ጊዜ ነው። መቼም የምስጋና ጊዜ ጥሩ ጊዜ ነው። «ቀማኛ ስላልሆንሁ፣ ዐመፀኛ ስላልሆንሁ፣ አመንዝራ ስላልሆንሁ፣ ደግሞ እን ደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ፣ አመሰግንሃለሁ» ነው የሚለው። አንዳንዴ የምስጋናችን ጊዜ የመጸደቂያችን ጊዜ ይሆናል። ነገር ግን ከዚህኛው በጽድቅ ሥራው ከተመረኰዘው ሰው ይልቅ ቀራጩ በእግዚአብሔር ፊት በጸጋው ዋጋ አገኘ። ይሄ ዲስኩር ነው፤ ገድሉን ነው የሚናገረው። እርሱ ለእግዚአብሔር ያደረገውን ለእግዚአብሔር የሆነለትን፣ በእግዚአብሔር ፊት ምን ዐይነት ተቀባይነት እንዳለው ነው የሚናገረው፤ ያኛው ግን የማልበቃ ነኝ ብሎ ነው የሚጮኸው። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ቀራጩ ጻድቅ ሆኖ ተመለሰ። ይሄ ቀና ብሎ ማየት የማይችለው ምንም ትምክህት የሌለው፣ ጽድቅ

አድርጎ የሚቈጥረው ነገር የሌለው ቀራጭ ጸደቀ።

ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ መቼም ምንም እናድርግ ምንም፣ ምን ጊዜም ጸጋው ዐዲስ ነው። ስንመጣ ምን ጊዜም ጸጋውን ብቻ ተማምነን ነው መምጣት ያለብን። የዋጋ ባለ መብቶች ሆነን መምጣት የለብንም። ጸጋ ላደረግነው ነገር ክፍያ አይጠደለም። ጸጋ ደመወዝ ወይም ብልጫ ስላሳየን ሽልማትም አይደለም። ሽልማትም ከሆነ የሆነ አስተዋፅኦ አድርገናል ማለት ነው፤ ሌሎችን በልጠናል። ጸጋ በኋላ ልናከናውነው ላለነው ነገር የቅድሚያ ክፍያም አይደለም። አንዳንድ መሥሪያ ቤት ዐዲስ ጀማሪዎች ስንሆን እንደ መቋቋሚያ ብለው ደመ ወዛችንን ቀደም አድርገው ይከፍሉናል። ጸጋ እንደዚህም ያለ ክፍያ አይደለም።

ልክ ወደ ጌታ ስንመጣ በመጀመሪያ ቀን የሆነልን የጌታ ጸጋ ዐሥርም ዓመት ሃያም፣ ሠላሳም፣ አርባም ዓመት እግዚአብሔርን አገልግለን ባለንበት ወቅትም ጸጋው ዐዲስ ነው።

ገና መጀመሪያ ወደ ጌታ ስንመጣ በእውነት፣ በንስሓና በእምነት ስንመጣ ጌታም ሲቀበለን በእውነት ጸጋው ይታየናል። እንዴት እኔን ይቀበለኛል እንላለን። ውሎ ሲያድር፣ ስንቈይ ስንመስክር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ስናመጣ፣ ስንጸም፣ ስንጸልይ፣ ለዚም ለዛም ጸሎት ስናደርግ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን እንዳገለገልነው እንደሠራንለት እንቈጥራለን። የጸጋው ባለ ዕዳነታችንን እንደ ተወጣን እንቈጥራለን፤ ከእንግዲህ እግዚአብሔር ባለ ዕዳ እንደ ሆነ፣ እግዚአብሔርም ለእኛ ማድረግ ያለበት፣ ካደረግነው ነገር የተነሣ እንደ ሆነ እናስባለን። «ይሄን አድርጌ ያለሁ ይህን ሠርቻለሁ» ብለን እናስባለን። እንደዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ የጸጋ አስተሳሰብ ሳይሆን፣ የዋጋ ተማኝ፣ የአሠሪና የሠራተኛ፣ የሥራና የደመወዝ ተቀባይ አስተሳሰብ ነው።

ይኸ ድነታችን ግን ምን ጊዜም ምንጩ የእግዚአብሔር ጸጋ




ነው። ድነት ለእኛ ምን ጊዜም እንደ ሥራችን ያልተገባን ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ እንዲያው የቸረው፣ በእኛ ዘንድ ያለ ምንም ነገር የማይከፍለው ታላቅ ስጦታ ነው። የድነታችን መሠረቱ የክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ደም ነው። በመስቀሉ ላይ የተከናወነ ድነታችንን የሚያሳዩ ቍልፍ ቃሎችን፣ መግለጫዎችን እንመለከታለን።

## <u>የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል (ደም) - የድነት መሠረት</u>

| የከንውኑ መግለጫ ቃል | የድርጊቱ ማረፊያ (የፈውሱ ማረፊያ) | የቃሉ ዐውድ |
|---|---|---|
| 1. ሥርየት (ማቴ 26፥27) (ሮሜ3፥21-25) (ኤፌ1፥7) | ከኀጢአት - ከበደል | ቤተ መቅደስ |
| 2. ጽድቅ (ሮሜ 5፥9) | ከፍርድ ከኩነኔ | ፍርድ ቤት |
| 3. መዋጀት (ገላ 2፥16) (3፥13፥23-29) (4፥3-7) (1ጴጥ1፥18-19) (ራእ 5፥9-10) | ከባርነት<br>- ከከንቱ ኑሮ፣<br>- ከሕግ እርግማን<br>- ከሕግ ሞግዚትነት፣<br>- ከሕግ ሥራ | ገበያ |
| 4. ድል (ቈላ 1፥13) (ቈላ 2፥14-15) (ዕብ 2፥14-15) (ራእ 12፥11) (ገላ 1፥4፤ 6፥14) | በጠላት ላይ<br>- በጨለማ፣ በሰይጣን አገዛዝ /ግዛት<br>- በኀጢአት ኀይል (በአሮጌው ሰው)<br>- በሞት ኀይል<br>- በዓለም ኀይል | ጦር ሜዳ |
| 5. መታረቅ/ ልጅነት (ገላ 3፥26-27) (ሮሜ5፥1፡10-11) (2ቆሮ 5፥18-21) (ኤፌ 2፥13-18) (ቈላ 1፥20-22) | ከመለያየት ከጠላትነት<br>- ከእግዚአብሔር፣<br>- ከራስ፣<br>- ከሰው፣<br>- ከተፈጥሮ በረከት ጋር | ቤተ ሰብ፣ ማኅበረ ሰብ |
| 6. መክበር (ፍጽመተ ድነት) (ገላ 4፥4-7) (ሮሜ 8፥18-23) (ፊል 3፥20-21) (ቈላ 3፥3-4) (1ዮሐ 3፥2) (ፊል 3፥20-21) | አሮጌው ሥርዐት<br>የሚሞት አካል | ህላዌ /አኗኗር |

# የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል - የድነት መሠረት




*"የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው" (1ቆሮ 1፥18)፡፡*

*"ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ ይሁን"* (ገላ 6፥14)፡፡

*"መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናከል ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን አይሁድም ሆኑ ግሪኮች ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው"* (1ቆሮ1፥22-24)፡፡



በመስቀሉ ላይ የተከናወነልን ነገር የሚገልጡ የመግለጫ ቃሎች አሉ፡፡

አንደኛው *ሥርየት* ነው፡፡

ሥርየት ስንል ማስተሠረይ ከሚለው ቃል ጋር የተያያዘ የመጀመሪያ ትርጒምም መክደን፣ መሸፈን የሚል ፍቺ ያለው ነው፡፡ ይኸውም ኀጢአትን፣ በደልን ከእግዚአብሔር እይታ፣ ከእግዚአብሔር የቅድስና ዐይን ቍጣ መከለል ማራቅ፣ ማስወገድ የሚለውን ዐሳብ ይሰጠናል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በባሕርይው ኀጢአትን አይቶ ጽድቁ ዝም ስለማይል ነው፤ ቅድስናው ኀጢአትን የሚጸረር ባሕርይ አለው፡፡ ማስተሠረያ ስንል ከዚህ ቍጣ አስከታይ እይታ መሸፈን ማለት ነው፡፡

ይኽ ሥርየት የሚያርፈው ኀጢአት ወይም በደል ላይ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ጊዜ ይኽ በቤተ መቅደስ አካባቢ ሲከናወን እንመለከታለን፡፡ ለማስተሠረያ የሚሆን ነገር ምን እንደሚቀርብ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እናያለን፡፡ ነገር ግን ዋናው የዐሳቡ ትርጒም ከእግዚአብሔር እይታ መሸፈን ማስወገድ ነው፡፡ የሚሸፈነውም ኀጢአትና በደል ነው፡፡

ኀጢአት ስንል ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ለእግዚአብሔር አለመገዛት ነው፡፡ ምናልባት ለእግዚአብሔር አለመገዛት የሚለውን ብናስቀድመው ጥሩ ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ የምናየው አለመገዛት ወይስ አለመታዘዝ ነው የሚቀድመው? አለመታዘዝ የተሰጠን ትእዛዝ በተግባር አለመፈጸም፣ አድርግ የተባለውን አለማድረግ ወይም አታድርግ የተባለውን ማድረግ ነው፡፡ ሔዋን አትብዪ የተባለችውን የዛፍ ፍሬ ወስደችና በላች፡፡ ይሄ በተግባር የተፈጸመን ጒዳይ አለመታዘዝ እንለዋለን፡፡ አለመገዛትስ ከዚህ ቀደም ብሎ መጥቶአል ወይስ በኋላ ነው የመጣው? ቀድሞ ነው የመጣው፣ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ስትወስን፣

ከእግዚአብሔር ጋር ለመስተካከል ስትወስን፣ ለእግዚአብሔር ማደ ርን አሻፈረኝ ስትል፣ አለመገዛት ተከናውኗል።

ስለዚህ ኀጢአትን ባጭሩ አለመገዛትና አለመታዘዝ ብለን ብናስ ቀምጠው ምንነቱን ይገልጥልናል። በተለያዩ መንገዶች ሊብራራ ይችላል። አለመገዛት ራሱ ዐመፅ እንደ ሆነ እናውቃለን። ዐመ ፅም ኀጢአት ነው፤ ዮሐንስ በመልእክቱ ተናግሯል።

ሥርየት ኀጢአትና በደልን ይሸፍናል። በደል ስንል ከኀጢአት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው። በደል ኀጢአት ከማድረጋችን የተ ነሣ በኀጢአታችን ምክንያት ተጠያቂነታችንን የሚያውጅ ወይም ተጠያቂ የሚያደርገን ነው። የመጠየቅ ዕዳ እንዳለብን የሚገልጽ ነገር ነው።

ዘሌዋውያን 6፥4 ላይ «እርሱም ኀጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን» ይላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በደልን እንደዚያ አድርገው ይተረጕሙታል። በኀጢአት ምክንያት ተጠያቂ መሆናችንን ያሳያል።

«እርሱም ኀጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን በቅድሚያ የወሰደውን ወይም በግፍ የተቀበለውን ወይም የተሰጠውን ዐደራ ወይም ጠፍቶ ያገኘውን ወይም በሐሰት የሚለውን ...» እያለ ይቀጥላል።

ልብ እንድንል የምፈልገው «እርሱም ኀጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን» ስለዚህ አንድ ሰው ኀጢአትን ከሠራ በደለኛ ይሆናል። አንድ ሰው በደል ካለበት ኀጢአት አለበት ማለት ነው። በደል ስለ ኀጢአታችን ተጠያቂ መሆናችንን የሚያስረግጥ ነው።

ሥርየት በኀጢአትና በበደል ላይ የሚያርፍ ነው። በኀጢአትና በበደል ላይ ፈውስን የሚያመጣ ነው።

ሁለተኛው ***ጽድቅ*** ነው፤

ጽድቅ የሚለው ቃል ዐውደ ቃሉ ፍርድ ቤት ወይም የችሎት



ስፍራ ነው።

ጽድቅ ስንል የችሎት ወይም የፍርድ ቤት ቃል ነው። አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ተወንጅሎ፣ ተከሶ በፍርድ ወንበር ፊት ቀርቦ የጕዳዩ ዙሪያ ገብ ታይቶና ተመርምሮ ለዚያ ለተወነጀለበት ጕዳይ ተጠያቂ አይደለም፤ አይመለከተውም፤ ነጻ ነው ብሎ ሲታ ወጅለት ያ ሰው ጸደቀ (justified) እንላለን።

ጽድቅ የሚለውን በዚያ መልኩ ነው የምንጠቀምበት። እዚህ ጋ ጽድቅ ስንል ሕይወቱ ተቀድሶ ታየ፤ በጕዞው ጽድቅን አሳየ ማለ ታችን አይደለም። ነገር ግን ይኸ ሁል ጊዜ የሚታየው ከፍ ርድ ወንበር ጋር ተያይዞ ነው። በችሎት ፊት ቀርቦ ሳለ ይኸ ሰውዬ በዚህ ጕዳይ ላይ ተወንጃይ ተጠያቂ አይደለም ተብሎ ታወጀለትና ከቅጣቱ ነጻ ሆነ ማለትን ነው የሚያመለክተው።

ጽድቅን በሁለት መንገድ እንጠቀምበታለን። የጽድቅ ሕይወት መኖር ለብቻ ነው፤ ጻድቅ ሆነን ስንታወጅ ግን ከፍርድና ከኰ ነኔ ነጻ መሆናችንን የሚያሳይ ነው።

ሥርየት የቤተ መቅደስ ቋንቋ ሲሆን፣ ጽድቅ ግን የፍርድ ቤት ቋንቋ ነው። ጽድቅ የሚያርፈው በፍርድና በኵነኔ ላይ ነው። ጽድቅ ለዚህ ፈውስ ነው፤ ሥርየት ደግሞ ለኀጢአትና ለበደል ፈውስ ነው።

ሦስተኛው ቃል ***መዋጀት*** ነው።

መዋጀት ለባርነት ከመሸጥ ጋር ይያያዛል። ምርኮኛነትም ጥቂት ሊነካካው ይችላል። ይኸ ቃል የገበያ ቃል ነው። ብዙ ጊዜ አንድ ሰው በገንዘብ ባለዕዳ ቢሆን ያንን ዕዳ ሸጦም ተለቅቶም መክፈል ካልቻለ፣ ያ ሰው ራሱን ይሸጣል። ወይም ራሱ ይሸ ጥና ዕዳው ይከፈላል፤ እርሱ ነጻ መሆን የሚችለው ያንን ዕዳ ሲከፍል ብቻ ይሆናል።

በቈላስይስ ውስጥ የዕዳ ጽሕፈታችንን ደመሰሰ ይላል (ቈላ2፥14):: በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስንመለከት አንዳንዴ አንዳንዶች ሲቸገሩ ራሳቸውን ይሸጣሉ:: ወይም ተበድረው መክፈል ካቃታቸው ይሸጣሉ:: ዘመድ ቢሆን ወገን ቢኖር እነኝህ አሁን የተሸጡትን ሊዋጅ ይችላል:: የሚዋጀው ግን ያንን ዋጋ ሲያስቀምጥ ነው:: ዕዳቸውን ከፍሎ ያስመልሳቸዋል፣ ነጻ ያወጣቸዋል፣ የራሱም ገንዘብ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ወይም ነጻነታቸውን ያሳውጅላቸዋል::

ሌላው *ድል* የሚለው ቃል ነው::

*ማረፊያውም* ከውጊያ ጋር ይያያዛል:: ይኸ ደግሞ የጦር ሜዳ ቃል ነው:: ያሸነፈንን እርሱን በክርስቶስ አሸንፈናል ማለት ነው:: በሰይጣንና በሞት ላይ ድልን አግኝተናል (ዕብ2፥14-15) (ቈላ2፥14-15):: በኀጢአት ኀይልም ላይ ድልን አግኝተናል::

አምስተኛው *ዕርቅ* ነው::

*ዕርቅ የሚለው ቃል ጥል ወይም መለያየት ላይ የሚያርፍ ነው:: ይህ በቤተ ሰብ፣ በማኅበረ ሰብ ዙሪያ የሚነገር ቋንቋ ነው::* በእግዚአብሔርና በፍጡሩ ሰው መካከል የነበረው ጠላትነት ተደምስሶ ዕርቅ ሆነ:: በሰውና በሰው መካከልም ያለው ጠላትነት በክርስቶስ ተወግዶ ሰላም፣ ስምምነት እንደ ወረደ የሚያስረዳ ነው::

እዚህ ላይ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ዕርቅ ብቻ ሳይሆን፣ የተዘረጋው ከዕርቅም ሀልፎ የሄደ የልጅነትና የአባትነት ዝምድና መመሥረቱን የሚያስገነዝብ ነው:: ልጅነት ከተገኘ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽነት አለ:: ልጅነት በታተመበት በመንፈስ ቅዱስ የዘላለም ክብር ወራሽነት ወይም *ፍጽመተ ድኅነት* ይረጋገጣል:: የሚሞተው የማይሞተውን ለብሶ ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት በክብር መግባት ይሆናል::



የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ባሕርይ

1. የአዲሱ ኪዳን ኅበረተ ሰብ አኗኗር ዘይቤ የሞትና የትንሣኤ ዘይቤ ነው:-

   - በድካም ብርታት፣
   - በሞት ትንሣኤ፣
   - ስለ ክርስቶስ በመነቀፍ (በመሰደብ) የክብር መንፈስ መሞላት፣
   - በመስጠት ማግኘት፣
   - ራስን በማዋረድ ከፍ ከፍ ማለት
   - ኋለኛ በመሆን ፊተኛ መሆን፣
   - በማገልገል ጌትነት፣ ወዘተ... የሚታይበት ነው::

2. የአዲስ ኪዳን ኅበረተ ሰብ መጻተኛ ነው (1ጴጥ2፥11)

   ሀ. ከክፉ ሥራ ባርነት መውጣትና ለመልካም ሥራ የሚያበቃ ዐርነትን ማግኘት ነው(ኤፌ2፥1፤5፥8-11፤ 4፥28)::
   ለ. በእግዚአብሔር ምድራዊ ስጦታ ላይ ከመመሥረት ወይም ከመጣበቅ ይልቅ፣ በሰጪው ላይ የሚደገፍና የሚታመን ነው (ዘሌ 25፥23፤ ማቴ 6፥25፤ 1ጴጥ 1፥17፤ 2፥11፤ ሮሜ 12፥2፤ 1ጢሞ 6፥17-19)::

3. እንደ ቃሉ የአዲስ ኪዳን ኅበረተ ሰብ የእውነት ዐምድና መሠረት መግለጫ ነው::

የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ የነቢይነት አገልግሎት አለው (ማቴ 5፥13-14 *"እናንተ የምድር ጨው ... የዓለም ብርሃን ናችሁ"*)

   ሀ. ዓለም በግፍ እንዳትዋጥ ፍትሕ እንዳይጓደል ብዝበዛ እንዳይሰፍን በእውነትና በፍቅር የመጠበቅ ኀላፊነት አለበት (1ጢሞ3፥15፤ ኤፌ 5፥8-11፤ ማቴ 14፥4)::
   ለ. ስለ እውነት ስለ ፍትሕ መከራ የሚቀበል ነው

ሰዎች ፍላጐታቸው፣ ጥቅማቸው፣ ምድራዊ ክብራቸው፣ ሲነካባቸው አይወዱም፤ ያሳድዳሉ፤ ያጠቃሉ።

4. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ተልእኮኛነት

አሳት ያለ ሙቀት እንደማይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም ያለ ተልእኮ ልትሆን አትችልም፤ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም የማስታረቅ ተልእኮ ያላት መልእክተኛ ናት።

ሀ. ተልእኮው ሰውን ከእግዚአብሔር ማስታረቅ ነው፤ (2ቆሮ 5፥18-20፤ ማቴ 28፥18-20)።

ለ. የተልእኮውም ወቅት እስከ ዓለም ፍጻሜ ነው (ማቴ 28፥20)።

ሐ. ለተልእኮው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል የግድ አስፈላጊ ነው (ማቴ 16፥20፤ ሐሥ1፥6-8)።

መ. ስለተልእኮውም ማኅበርተኛ እንጂ ገለልተኛ አይደለችም (ማቴ10፥16-20፤ ዮሐ17፥14-15፤ ሐሥ1፥8)።

ስለ ሆነም ከመታዋቂያዋ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ከዓለመኛነት እንጂ፣ ከዓለም ገለልተኛ አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን ማንነቷን ጠብቃ በዓለም የምትገኝ ዓለምን ደራሽ ናት (Identification with identity)።

የቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄዋ:-

(I) ተልእኮ ያለ ማተበኛነት እንዳይሆን (Identification without identity) (መስቀልን ያስጥላልና) ወይም

(2) ማተበኛነት ያለ ተልእኮ እንዳይሆን (Identity without identification) (ተልእኮን ያስጥላልና) ነው።

ማተበኛነት ያለ ዓለምን ደራሽነት ተልእኮ ጣይነትን፣ ብሕትውናን ያመጣል። በማተበኛነት ዓለምን ደራሽነት ግን እውነተኛ <u>'ሐዋርያነት' ነው!</u>



የማስታረቅ አገልግሎት አለብን፤ ወደ ዓለም ሁሉ የመሄድ፣ የምሥራቹን ወንጌል የመስበክና ደቀ መዛሙርት የማድረግ (ማቴ 28፥18-20)።

5. የአዲስ ኪዳን ሕዝብ የሕያው እግዚአብሔርን ተስፋ ያበሥራል፤ በተስፋ ይኖራል የክርስቶስን መንግሥት ይናፍቃል ይጠብቃል ተስፋ ያበሥራል (ፊል 3፥3፤ 3፥20-21፤ ሮሜ 8፥19-23)።

በመገለጡ (በዳግም ምጣቱ) የመዳናችንን ፍጻሜና የልጅነት መገለጥ ለመቀበል እንጠባበቃለን።

6. ግራጫውን ግልጠት ነጭ ወይም ጥቍር አድርጐ ከመመደብ መቈጠብ ጥበቧ ነው (1ቆሮ 13፥12)።

መታወቂያዋም:- የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀልና ጌትነቱ ነው። የተሰቀለው ኢየሱስ ጌታም ክርስቶስም ነው ማለቷ።


## III. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ ተግባራት

የቤተ ክርስቲያን (የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ) ዐይነተኛ ተግባሯ እግዚአብሔርን ማምለክና መጸለይ፣ የወንጌልን ቃል ማወጅ/ማሠራጨት፣ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት፣ ኅብረትን መጠበቅና መተሳሰብን ማራመድ፣ ለተቸገሩትም ሁሉ የምግባረ ሠናይ የምኅረት አገልግሎት መስጠት፣ እንዲሁም የጽድቅና የፍትሕ ዐይነተኛ ምሳሌ /ሞዴል/ በመሆን በሕዝቦች መካከል ጽድቅንና ፍትሕን የማስረጽ ሚና መጫወት ነው።

# የቤተ ክርስቲያን ተግባር

ለእግዚአብሔር ፈቃድን ማስገዛት /እርሱን ማገልገል /ለእግዚ
አብሔር መስገድ
እግዚአብሔርን ማወደስ /ማመስገን
(ጸሎት፣ ዝማሬ፣ ስብከት፣ ቅዱሳት
ሥርዐት) ሐሥ 2፥32፡ 36-37፡
ዕብ 13፥15-16፤ 1ኛቆሮ 10፥14-18፤
ሐሥ 4፥23-24፤ ሮሜ 6፥3-4

የፍትሕ ዐይነተኛ ምሳሌነት
ፍትሕን ተናጋሪ
ሰላም አስፋኝ
ማቴ 5፥13-14፤ 14፥4፤
1ኛ ጢሞ3፥15፡ ኢሳ 1፥17
አሞ 5፥10-12፡ 21-24




የሌሎችን ማኅበራዊ/ መሠ
ረታዊ ፍላጎት ለማሟላት
ማገልገል
ሉቃ 10፥29-37፤ ኤፌ4፥28፤
ያዕ 2፥14-16፤ ኢሳ 58

ኢየሱስን መከተል
ቃሉን መመገብ፣ የእሁድ ትምህርት፣ የመጽሐፍ
ቅዱስ ጥናት /ውይይት፣ የጥሞና ጊዜ



# 1. አምልኮና ጸሎት

## ሀ. አምልኮ

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡ እስራኤልን ከግብፅ ምድር ለማ ውጣት በተነሣበት ጊዜ በሙሴ በኩል ለፈርዖን የተላከው መል እክት "... ያገለግሉኝ [ያመልኩኝ] ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" የሚል ነበር:: ዘፀ 9-1 በመጨረሻም ይህ ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማ ምለክ ታጭቶ በሙሴ መሪነት የግብፅን ምድር ለቆ እንደ ወጣ በዘፀአት ምዕራፍ 14 ላይ ተመልክቷል::

በርግጥ እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት በጸናችና በተዘረጋች የእ ግዚአብሔር ክንድ ነጻ ከመውጣታቸው በፊት እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ ቢነገራቸውም ተግባራቸው ግን ይህ ብቻ ነው ብሎ መደምደም ያስቸግራል:: ምክንያቱም በዘፀ 19÷5 ላይ እንደ ተጻፈው እግዚአብሔርን ቢታዘዙና ቃል ኪዳኑን ቢጠብቁ ለእርሱ የተለየ ቅዱስ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ካህናትም ያገለግሉ ዘንድ የተመረጡ መሆናቸው ተጠቅሷል:: እንግዲህ በፊቱ ተቀ ባይነት ማግኘት እንዲችሉ አስቀድሞ የኀጢአት ጉዳይ መፍት ሔ ማግኘት ነበረበት፣ በመጀመሪያ ለሥርዐተ ሥርየት የተለዩ መሥዋዕቶች መቅረብ ነበረባቸው:: እነርሱም የኀጢአት መሥ ዋዕት፣ የበደል መሥዋዕት፣ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእህል ቍር ባንና እንዲሁም የሕብረት መሥዋዕት ናቸው:: (ዘሌዋ 4÷1፤ 5÷3፤ 6÷23-24፤ ዘሌዋ 5÷14፤ 6÷7፤ 7÷1-10፤ ዘሌዋ 1÷3-1 7፤ ዘሌዋ 2, 6-14÷23, ዘሌዋ 3-7÷11-36) እነዚህ መሥዋዕቶች ለሥርዐተ ሥርየት ይቅረቡ እንጅ የአምልኮው ክፍል ነበሩ:: ሆኖም በአንድነት በሚቀርቡበት ጊዜ ግን ቅደም ተከተል ነበራ ቸው:: እነርሱንም ከዚህ በታች በሦስት ክፍለን እናያቸዋለን::

### ለ) የኀጢአትና የበደል መሥዋዕት

ይህ መሥዋዕት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የቆመውን ኀጢ

አት የሚያስወግድ (የሚያስተሠርይ) ሲሆን የሚቀርብበትም ምክንያት አንድ ሰው ኀጢአት ሠርቶ የበደለ ቢሆን ከእግዚአብሔር የቅድስና ባሕርይ የተነሣ በኀጢአተኝነቱና በበደለኛነቱ እንዳይጠፋ ለማድረግ ነው (ዘሌ 6÷14፤7÷1-7)።

እንግዲህ ይህን ኀጢአተኝነትና በደለኛነት ለማስተሠረይ የቀደመው የኪዳን ሕዝብ በመጀመሪያ የሚያቀርበው መሥዋዕት የኀጢአትና የበደል መሥዋዕት ነበር። ምክንያቱም ያለ እነዚህ ሁለት መሥዋዕቶች ማንም ሰው እግዚአብሔርን ማምለክና ማገልገል አይችልምና ነው። የሚቀርበውም መሥዋዕት ነውር የሌለበት በመሆኑም ኀጢአተኛውን ከኀጢአቱ በደለኛውን ከበደሉ ያነጻዋል። በዚህም መሥዋዕት ውስጥ የሚቀርበው ሥጋና የሚፈሰው ደም መካከለኛ ከመሆኑ የተነሣ ትልቅ ቦታ ነበረው። ቅዱስ ቅዱሳንም በመሆኑ ሥጋውን የነካው ወይም የበላው ሁሉ ይቀደስ ነበር።

### ሐ) የሚቃጠል መሥዋዕት

የኀጢአትና የበደል መሥዋዕት ከቀረበ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ይቀርብ የነበረው መሥዋዕት የሚቃጠል መሥዋዕት ነበር። ይህም መሥዋዕት ራስን ለእግዚአብሔር የማቅረብ፣ የመስጠት ምልክት ወይም መግለጫ ሲሆን በሚቀርብበትም ጊዜ የኀጢአትንና የበደልን መሥዋዕት አይቀድምም ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያትም መሰጠት ከመንጻት በኋላ ስለ ሆነ ነው። ሳይነጹ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት መነሣት ለፍርድ መዳረግ ይሆናል። ዛሬም የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ለዚህ የተጋለጠ እንዳይሆን ይኸ መዘንጋት የለበትም። ማንም ሰው እግዚአብሔርን ለማገልገል ከመነሣቱ በፊት ከበደልና ከኀጢአቱ በክርስቶስ ደም መንጻቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት።



### መ) የደኅንነት መሥዋዕት፣ የኅብረት መሥዋዕትና የእህል ቍርባን

በሦስተኛ ደረጃ የደኅንነትና የኅብረት መሥዋዕት እንዲሁም የእህል ቍርባን በአንድ ላይ ይቀርባል። ይህ ደግሞ ከላይ ወደ ታች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም በጐን ደግሞ ከካህናቱና ከአገልጋዮቹ እንዲሁም ከሕዝቡ ጋር ኅብረት እንዳለ የሚያሳይ ነው።

እንግዲህ ክፍሉን ለማጠቃለል ያህል ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ሀሳብ ላይ የቀደመው የኪዳን ሕዝቡ፣ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት፣ በጸናችና በተዘረጋች የእግዚአብሔር ክንድ የወጣው እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል እንደ ሆነ እና እንዲሁም ይህ አምልኮ በሚቀርቡ አምስት የመስዋዕት አይነት እንደሚከናወን ተመልክተናል።

ዛሬም የአዲስ ኪዳን ሕዝብ ጥሪ ከዚህ የተለየ አይደለም። የቀደመው ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማምለክ ከግብፅ እንደ ተጠራ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል በብሉይ ኪዳን የሚቀርቡትን የመሥዋዕት ዐይነቶች ይዞ መቅረብ አያስፈልግም፤ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዴ ለዘላለም ራሱን በማቅረቡና ነውር የሌለበት ደሙን በመስቀሉ ላይ በማፍሰስ ቀድሶናል። (ዕብ 10÷14፤ 1ጴጥ 1÷18-19) በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል የሚያስችል መንገድ ስለ ተዘጋጀ ወደ ጸጋው ዙፋን በደሙ በኩል ቀርበን በፊቱ ልንሰግድ ሁሉ ነገር ተመቻችቷል።

### ስናመልክ የምናደርገው ምንድን ነው?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በዘፍጥረት ሦስት ላይ የተገለጠውን ደግመን እናስታውስ። የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር ከመገዛት ይልቅ በእባቡ ቃል በመወረስና በመዋጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን እንደ ፈለጉና ያለ እግ

ዚአብሔር እንደ እግዚአብሔር መሆን እንደ መረጡ እንረዳ ለን:: ሰይጣን በዔድን ገነት እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ብሎ በእባቡ አማካይነት ለሔዋን የሰጠው ትምህርት ዛሬም በሰው ልጆች ጆሮ ላይ እንደ ገደል ማሚቶ ድምፅ እያስተጋባ ነው:: እኛ ግን እግዚአብሔርን ስናመልክና ለእርሱ ስንንበረከክ ያንን አሌ ማለታችን ነው:: ወይም በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ እኛ ደግሞ ፍጡር፣ እርሱ ብቻ ተመላኪ (ምሉክ) እኛ ደግሞ አምላኪዎች (ምልክ) መሆናችንን መግለጣችንና ማሳየታችን ነው:: ይህ ብቻ አይደለም እግዚአብሔርን ለማምለክ በተነሳንበት ጊዜ ሁሉ በፊቱ ስንሰግድና፣ ለሥልጣኑ ተገዥነታ ችንን በአምልኮ ውስጥ ስንገልጥ ለውጭው ዓለም አምላክ አለ መሆናችንን፣ ማሳየታችን ነው:: ሰይጣንም አምላክ አለመሆኑን አስረግጠን መግለጣችን ነው (መዝ95፥1-7)::

የሰው ልጆች ምን ጊዜም በመለኮት ሂደት ውስጥ ያሉ ሳይሆኑ ሁል ጊዜ ተፈጣሪ ሆነው የሚዘልቁ ናቸው:: ለምሳሌ አንዳንድ ጸሓፊዎች በምንም ደረጃ የበታችነት ስሜት ሳይሰማን ከእግዚ አብሔር ጋር እኩል ለእኩል እንሆናለን ነንም ብለው ይሰብካሉ:: ይኽ ግን ሙልጭ ውሸት ነው:: በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ሙላቱ ልክ ብንደርስ እንኳ በወይኑ ግንድ ላይ ያለን ጥገኞች፣ ቅርን ጫፎች እንጂ ራሳችንን ችለን የምንኖር አይደለንም:: ሌላው ቢቀር ዛሬ ብርሃን ፍለጋ በፀሓይና በመብራት ላይ ተደጋፊዎ ች እንደ ሆንን ሁሉ ከትንሣኤም በኋላ በሀዲሲቷ ኢየሩሳሌም ስንኖር በክርስቶስ ላይ ተደጋፊዎች ነን:: ራእይ 22፥5 ላይ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች "በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ ፡- ጌታ ችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና፤ ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ማኖራቸው እግዚአ



ብሔርን ማምለክ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ማቋረጫ የሌለው ቀጣይ ተግባር መሆኑን ያስገነዝበናል (ራእ 4፥9-11)::

እዚህ ላይ አንድ በብርቱ መታሰብ ያለበት ነገር አለ ይኸውም:- እግዚአብሔርን ለማምለክ በምንነሣበት ጊዜ ሁሉ ከእርሱ የሆነ ነገር ወደ እኛ እንዲፈስ፣ እንደ ገናም ከእኛ የሆነ ነገር በፍቃ ዳችን ወደ እርሱ እንዲደርስ በዚያም ደግሞ እኛ ተጠቃሚዎች እንድንሆን እንጂ እርሱን ለመጥቀም እንድናመልከው መፈለጉና የእኛን አምልኮ ጥማተኛ መሆኑ አይደለም:: እርሱ በፍጥረቱ ላይ ተደጋፊ ያልሆነ ፍጹም ሕያውና እውነተኛ አምላክ ነው:: ነገር ግን ፍጡርን ከፈጠረ ዘንድ መመለክና መወደስ ኪዳናዊ መብቱ ስለ ሆነ እናመልከዋለን:: ክፍ ከፍም እናደርገዋለን::

## የአምልኮአችን ይዘት

የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ ፍጹም ሕያውነት፣ ህላዌ ምጡቅነት፣ ዕጹብ ድንቅ ፈጣሪነት፣ እግዜ ኩሉ ነት፣ ጠባቂነት፣ መሓሪነት፣ እያየንና እያሰብን፣ ልንሰግድለት፣ ልንቀኝለት፣ በእንደበትም በመሣርያም ልናዜምለት፣ ልናወድሰውና ልናመሰግነው ይገባ ናል::

ዛሬ በጊዜ ውስጥ ሳለን እግዚአብሔር አምላክን አምላኪዎች ነን፤ በዮሐንስ ራእይ እንደምናየው ነገም፣ በሚመጣውም ዘላለማዊ መንግሥት አምላኪዎች ነን:: መቼም መች አምላክ አይደለንም፤ አምላኪዎች ብቻ እንጂ::

በአምልኮአችን የነቃና ሕያው የሆነ ፈቃዳችንን ለፈቃዱ አቅርበን ልንገዛለት፣ ለእርሱ ልናድር፣ ልናጥን ይገባናል:: ሥርዐት ያለው ሕያው አምልኮ ማካሄድ ይኖርብናል (በግልም በማኅበርም)::

አምልኮአችን ሕይወት የሞላበት፣ በነቃ ፈቃድና በነቃ ሰውነት የሚደረግ ሊሆን ያስፈልጋል:: በኑኖለለ ዐሳብ፣ በነፈዘ ስሜት እየ ፋሸክን የምናካሂደው ሙት ትርኢት መሆን የለበትም:: ዝጋት

እንዳይጋገርበት የመንፈስ ንቁነት እጅግ ያስፈልጋል:: በሕያው መንፈስ እንጂ በጀለ (በተጃጃለ) መንፈስ የሚካሄድ አይደለም::

የአምልኮ ሥርዐት፣ ያለ ሕይወት ምውት ነው፤ የአምልኮ ሕይወትም ያለ አምልኮ ሥርዐት ብክነት ነው፤ ስሜታዊ መረንነትንና ሁከትን ያስከትላል:: የአምልኮ ሥርዐት ያለው የአምልኮ ሕይወት የሚያውድ መልካም መዓዛ፣ ውብና የከበረ አምልኮ ነው::

ምን ጊዜም ቢሆን በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ፣ ሥርዐት የለሽ ሕይወት ወይም ቅርጽ አልባ ሕይወት መቼ ተበጅቷል?

ሕይወት በዕፀዋት
ሕይወት በእንስሳት } ውቅር አልባ የሆነ ፍሰት አይደለም::
ሕይወት በሰው

እግዚአብሔር ሰውን ከምድር ዐፈር *ዐበጀው* ሲል፣
ሥርዐተ ውቅር አመልካች ነው::
የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ሲል፣
የኀይለ ሕይወትን መሥረጽ የሚያሳይ ነው፤
ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ሲል፣
ሕይወት በሥርዐት ተገለጠ ማለት ነው፤ (ዘፍ2÷7)::

አምልኮአችን የግድ ሕይወትም ሥርዐትም ያስፈልጉታል::

*"... ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን"* (1ቆሮ14÷26)::

"የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይታዘዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም፤ <u>በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት</u> ሁሉ እንዲሁ ነው" (1ቆሮ 14÷32):: *"ነገር ግን ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን"* (1ቆሮ 14÷40):: ከዚህ ውጭ መሆን ለሌባው የሚመች ግርግር ነው::



ከአምልኮ ሕይወታችን ታካችነትን እንዲሁም አስመሳይነትንና ሽንጋይነትን ልናስወግድ ይገባል፤ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊዎች ናቸውና:: እግዚአብሔር በመንፈስና በእውነት የሚያመልኩትን ይወዳልና:: እውነትነት የሌለው አምልኮ ግብዝ ለታይታ የሚካሄድ ነው::

የውጫዊ የአደባባይ አምልኮ ስውነታችን፣ ዝማሬያችንና ጸሎታችን ለውስጥ የልብ ማንነታችን ባይተዋር እንዳይሆን ያስፈልጋል፤ ፈሪሳዊነት ነውና:: ዝማሬያችን ሲደምቅ፣ አንደበታችን በጩኸት ሲያስተጋባ፣ ነፍሳችን በውስጣችን ከጽድቅ ረሀብ የተነሣ እንዳታቃስት፣ አምልኮአችን ከሕይወት ንጽሕናችን ያልተነጠለ ሊሆን ይገባል፤ ይህ እግዚአብሔር የሚቀበልው አምልኮ ነውና፤ (ኢሳ 1÷10-17፤ አሞ 5÷21-24)::

**ሀ) እግዚአብሔርን ለማምለክ ከሃሊነቱን/ልዑልነቱን ማየት ቀዳሚ ነው::**

ርእሱን ለማብራራት ይጠቅመን ዘንድ ለአብነት ያህል ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2÷1-11 ላይ ስለ ጠቢባን ሰብአ ሰገል የተጻፈውን እንይ:: ክፍሉ እንዲህ ይላል፡- *"በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው .... ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው ወርቅ፣ ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት"*:: ጊዜው ቃል ሥጋ ሆኖ ጸጋንና እውነትን በመሞላት በሰው ልጆች መካከል ማደር የጀመረበት ነበር:: ይህ ጊዜ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በልዩ መንገድ ወደ ሰዎች የመጣበት ወቅት በመሆኑ፣ ሰዎችም ደግሞ ወደ እርሱ መቅረብ ነበረባቸው:: ስለዚህ ሰብአ ሰገል ሥጋ የሆነውን ቃል አይተው ሊሰግዱለት ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ::

እነዚህ ሰብአ ሰገል (ጠቢባን) ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመ ጡ የጉዞአቸውና የእንቅስቃሴአቸው ዓላማ፣ የእግዚአብሔርን ልጅ አይተው መስገድ ነበር። ስለዚህ ወደ ስፍራው በደረሱ ጊዜ "ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት..." ዛሬስ እኛ ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው ለምንድነው? እርሱን አይተን በፊቱ ቀርበንና ወድቀን ልንሰግድለት ወይስ መሻታች ንን እንዲያሟላልን? ብዙ ጊዜ ግን ቀዳሚ ፍላጎታችን የመሻታ ችን መሟላት ነው። እንዲደረግልን የምናመልክ ከሆነ በእን ዲህ ሀይነት የልብ ዕነት ወይም ዝመት የምናደርገው አምልኮ ከጣኦት አምልኮ ጋር የተመሳሰለ ይሆናል። በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች ጣኦትን የሚያመልኩት ኑሮአቸው እንዲሳካና እንዲከና ወን እንደ ሆነ እናውቃለን፡ እኛም ኑሮአችን እንዲሳካና እንዲ ከናወን በመጓጓት የምናመልክ ከሆነ አምልኮአችንን እግዚአብ ሔርን የማባበያ መንገድ ማድረጋችን ስለ ሆነ ልክ አይደለም። አንድ ጊዜ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንጀራ ስለ በሉ ፈለ ጉት፤ እርሱ ግን ለሚጠፋ እንጀራ አትስሩ አላቸው። ዮሐ 6፥26 -27 ዛሬም እግዚአብሔር አንድ ነገር ያደርግልኛል ብሎ ማም ለክ፣ እንጀራን ለመብላት ክርስቶስን ከፈለጉት ሰዎች ራዕይ የተ ለየ አይደለም።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡1-12 ባለው ታሪክ የተጠቀሱት ሰብአ ሰገል ግን አመጣጣቸው "የተወለደውን የአይሁድ ንጉስ አይተው ለመስገድ ብቻ ነበር።" ይህም መሻት እንደ እግዚአብ ሔር ፈቃድ ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር በኮከብ መራቸው። እኛም እንደ ፈቃዱ ብንሻ በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ ብርሃን ይመ ራናል። በብርሃኑም ብርሃንን እንድናይ ይረዳናል። በመጨረሻም የዚህ ውጤት ክርስቶስ ኢየሱስን ማየት ይሆናል።

እዚህ ላይ አብሮ መጤን ያለበት ሁለት መሠረታዊ ነጥብ አለ። ይኸውም ስናመልክ አምልኮአችንን ሕያው የሚያደርገው ነገር ቢኖር በአንደኛ ደረጃ እግዚአብሔርን ማወቃችን፣ ማመናችን



ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እርሱን ማየታችን ነው። እርሱን ማወቃችን እንድናምነው ሲያደርገን ከሃሊነቱና ልዑልነቱን ማየ ታችን ደግሞ በፊቱ እያመለክን፣ እየሰገድንለት እንድንመጣ ያደርገናል። ሰብአ ሰገልም ያደረጉት ይህንን ነው። "ወደ ቤትም ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር ባዩት ጊዜ ወድቀው ሰገዱለት ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው ወርቅ ዕጣንና ከርቤንም ሰጡት"። ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር ሆኖ ቢያዩትም የሰገ ዱት ግን ለእርሱ ብቻ ነው፤ ለሕፃኑ ብቻ ነው። ስጦታም ያቀ ረቡት ለእርሱ ብቻ ነው። ምንጊዜም ስግደት፣ አምልኮ ለአም ላክ ብቻ መሆኑን ልብ እንበል። ለሰውም ሆነ ለመላእክት ስግደት አልተፈቀደም፤ የተከለከለ ነው(ዘፀ 20፥3-6፤ ዘዳ 6፥13፤ ማቴ 4፥10፤ ራእ 22፥8-9፤ 19፥10)።

አሁን እኛ የምናየው ኢየሱስ በጨርቅ ተጠቅልሎ በከብቶች በረት በግርግም ያለን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር አብ በግርማው ቀኝ በክብር ያለውን ነው። እርሱን በእምነት ለማየት መንፈሳዊ ዓይን ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ በራሳችን ጥረት የሚከናወን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ አጋዥነት የልባችን ዐይኖች ሲከፈቱና ብርሃን ሲበራልን የሚሆን ነገር ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ ነገር ማየት የሚችለው ብርሃን ሲያገኝ ብቻ እንደ ሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ሀይን ያለው ሰው ሁሉ በጨለማ ውስጥ ዐይኑን አፍጦ ቢሄድ የዐይኑ መኖርና መፍጠጥ ነገሮችን እንዲያይ አያደርገውም። የግድ አንድን ነገር እንዲያይ ካስፈ ለገ ዐይኑ ብርሃን ማግኘት አለበት ልክ እንዲሁ እኛም እግዚአ ብሔርን ሀውቀንና አይተን ለማምለክ የልቦናችን ዐይኖች ሊከ ፈቱና ብርሃን ሊበራልን ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ቸርነት እነዚህ ሀይኖቻችን ተከፍተው እርሱን በትክክል ማየት ስንችል እንሰግድለታለን። በዚህ ጊዜ ከእርሱ ልንቀበል ይቅርና ያለንን ነገር እንኳ ከራሳችን ጭምር እንሰጣለን። ደግሞም የምንሰጠው ትርፍ ነገር ሳይሆን አለን የምንለውን ውድ ነገር ሕይወታችንንም

ነው። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይታያል ሕይወታችንም አማኑኤልን ያስተጋባል።

ለ) እግዚአብሔር ለማምለክ ፈቃዳችንን ማስገዛት ያስፈልገናል

እውነተኛው አምልኮ እግዚአብሔርን ሀውቆ ለእርሱ በመስገድ የሚያበቃ ሳይሆን፣ ራስንም ለርሱ መስጠት ያለበት ነው። በሮሜ 12÷1-2 ባለው ክፍል ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን። *"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው።*

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የብሉይ ኪዳን ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማምለክም ሆነ ለማገልገል የተለያዩ ዐይነት መሥዋዕቶችን ያቀርብ ነበር። መሥዋዕቱም ሲቀርብ እንስሳም ከሆነ ታርዶ ሲሆን እህል ከሆነ ደግሞ ተፈጭቶ፣ በሌላ ቋንቋና መንገድ "የለሁም በማለት" ለልዑል እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርብ ነበር። አሁን ግን በአዲስ ኪዳን ይህ ስለቀረ በእርሱ ምትክ ሰውነታችንን አርደን ወይም ገድለን ሳይሆን፣ በሕያውነት ለሕያው መሥዋዕትነት ራሳችንን ቀድሰን ለእግዚአብሔር እናቀርባለን። ወይም በሌላ አገላለጽ ንቁ ፈቃዳችንን በፈቃደኝነት ለእርሱ ፈቃድ እናስገዛለን።

እዚህ ላይ ከአምልኮ አኳያ ፈቃድን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ማስገዛት ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ አለ። ይኸውም፦ ማንኛችንም ወደ እግዚአብሔር መጥተን እርሱን የምናመልከው ፈቃዳችንን በፈቃደኝነት ለእርሱ ፈቃድ ለማስገዛት እንጂ የእኛን ፈቃድ በእርሱ ኀይል ለማስፈጸም መሆን የለበትም። አንዳንድ ጊዜ ግን እግዚአብሔርን የምናመልከው የእኛን ፈቃድ ለማሟላትና ለማስፈጸም ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ትክክል አይደለም።



ማናችንም የእኛ ፈቃድ እንዲደረግልን በአምልኮ እግዚአብሔርን ማባበል የለብንም። ከዚህ ይልቅ እርሱን ማምለክ ያለብን ፈቃዳችንን ለማስገዛት (ለመስጠት) መሆን አለበት። ምክንያቱም ፈቃድ ለእግዚአብሔር የማይገዛበት አምልኮ የተወደደ አይደለምና ነው። ስለዚህ ማንም ሰው ሕያው እግዚአብሔርን በሚያመልክበት ጊዜ፦ ፈቃዴን ለእርሱ ፈቃድ እያስገዛሁ ነወይ? ብሎ በመጠየቅ እሱነቱን (ፈቃዱን) ለእግዚአብሔር መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት። በእንዲህ ዐይነት መልኩ ሁላችንም በየቀኑ የክርስትና ሕይወት ጉዞአችንን ለራሳችን ሳንሰስት ለእግዚአብሔር እየተሰጠን ብንመጣ፣ በዚህ ውስጥ አምልኮአችን የተቃና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንም ኅብረት ጣፋጭና አርኪ ይሆናል።

የእግዚአብሔርንና የእኛን ፈቃድ አስመልክቶ ብዙ የሚባሉ ነገሮች አሉ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን ላይ በሉዓላዊነት ወሳኝ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች ስብከቱን ከመጨረሱ በፊት *"በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም"* አለ። እንደገናም ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች "*. . . የፈቃዱን ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላችሁ ዘንድ ስለ እናንተ መጸለይና መለመን አላቋረጥንም"* ይላል። ያዕቆብም በመልዕክቱ "*እናንተ ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህች ወይም ወደዚያች ከተማ እንሄዳለን በእርሷም አንድ ዓመት እንቈያለን፣ እንነግዳለን፣ እናተርፋለንም የምትሉ እንግዲህ ስሙ። ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም፤ ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ።"* ይላል (ማቴ 7÷21 ፣ ቈላ1÷9፣ ያዕ4÷13)። ስለዚህ አምልኮ ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የምናስገዛበትና ሉሌነታችን የሚገለጥበት

ቦታ እንጂ እርሱን እያመለክን የምንፈልገውን የሥጋችንን ነገር የምናገኝበት አይደለም።

በእምልኮ ውስጥ ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር እያስገዛን ስለ ታላቅነቱ እንዲሁም እርሱ ለእኛ በቸርነቱና በምህረቱ እንዲያው በጸጋው ስላደረገው ነገር ውዳሴና ምስጋናን ማቅረብ ነው። በዚህ ውስጥ ምስጋናችን እርሱ በቸርነቱና በታዳጊነቱ ለእኛ ካደረገው ነገር ጋር ሲያያዝ ውዳሴያችን ደግሞ ታላቅነቱ፣ እጹብነቱን፣ ንጽህናውንና ቅድስናውን እያሰብን ለማንነቱ አድናቆት ከማቅረብ ጋር ይያያዛል።

እግዚአብሔር ግን በባሕርይው ቸር ነው። ከቸርነቱም የተነሣ ለሰው ሁሉ የሰጠው ጸጋ አለ። እኛ ክርስቲያኖችም በክርስቶስ ስላመንን ለሰዎች ሁሉ ከሚሰጠው ጸጋ ውጭ የማዳኑን ልዩ ጸጋ ተቀብለናል። ይኸ ጸጋ በመጀመሪያ ወደ ጌታ ስንመጣ በዝቶልን እንደ ነበረ ዛሬም አገለገልን ካልንም በኋላ እንኳ ያው ነው። ነገር ግን ጸጋው በሕይወታችን መብዛቱና መትረፍረፉ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለማሳየት እንጂ ለምናደርገው ነገር እንደ ቅድሚያ ክፍያ ሆኖ አይደለም። ደግሞም ሁሌ ዐዲስ ከመሆኑ የተነሣ ምንም ብናደርግ የጸጋው ባለ ዕዳነታችን አይጐድልም። ነገር ግን ሰይጣን የጎደለ የሚመስለንን ነገር እያሳየ ይኸ ይኸ ጐድሎሃል ቢል ከእግዚአብሔር ጋር በመወዳደር ለምን ተበለጥሁኝ በሚል መንፈስ ካልሆነ በስተቀር እርሱን ንፉግ ልንልበት ምንም ምክንያት አይኖረንም። እርሱ ቸር እኛም ምን ጊዜም የጸጋው ባለ ዕዳዎች ነን። ስለዚህ እግዚአብሔር በጸጋው ባለጸጋ ከመሆኑ የተነሣ በቸርነቱ ለማንም ሰው የሚያስፈልገውን ነገር መጠኑን ተምኖ ሰጥቷል።

ሰው ግን ይኸ ጐድሎብኛል በማለት በእግዚአብሔር ላይ ቢያጉረመርም፣ ክስ ቢከፍት ክሱ ይከሽፋል። ለምሳሌ አንድ ዐይን ወይም አንድ እግር የሌለው ሰው፣ እግዚአብሔርን አንድ ዐይ



ኔን ወይም እግሬን ወሰደብኝ ቢል እግዚአብሔር ግን ማስረጃ ያመጣና ያኛው ዐይንና ያኛውም እግር የእኔ ነው የሚል ይሆናል። ስለዚህ እርሱን ስለ ቸርነቱ ከማመስገን ውጭ ማንም እግዚአብሔርን ሊከስ የሚችልበት ሕጋዊ መሠረት የለውም። ከዚህ ይልቅ በዙሪያችን ያለውን ለማየት ዐይናችን ቢከፈት እግዚአብሔርን ስለ ቸርነቱ የምናመሰግንበት ብዙ ነገር አለ። እኛ ግን እርሱን ለማመስገን በውድድር መንፈስ እንሄዳለን። ሥራውን ሠራ የምንለው እንኳ ታመን ስንፈወስና አጥተን ስናገኝ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ነገሮች ልክ እስከሆኑና እስካልታመምን ድረስ አናመሰግንም። ነገር ግን ዐይኖቻችን ተከፍተው ብርሃን ቢበራልን እግዚአብሔር ስለ ቸርነቱና በጎነቱ የምናመሰግንበት ብዙ ነገር አለ።

ሐ) የሚመለክ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ዕንጨትን እየጠረቡና ድንጋይን እየቀረጹ በወርቅና ብር በመለበጥ ልዩ ልዩ ጣኦታትን እንደሚያመልኩ እናውቃለን። ሆኖም በዘመናችን እንዲህ እየቀረጽን የምንሰግድላቸው ጣኦታት በቀጥታ ባይኖሩንም እንኳ እኛው ራሳችን እየፈጠርን የምንሰግድላቸው ጣኦታት እንዳሉ በመጽሐፍ ቅዱስ፡-

*"ከእስራኤል ሽማግሌዎች አንዳንዶቹ ወደ እኔ መጥተው በፊቴ ተቀመጡ። የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ የሰው ልጅ ሆይ እነዚህ ሰዎች ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል፤ ክፉታቸውን እንደ ማሰናከያ ድንጋይ በፊታቸው አስቀምጠዋል፤ ታዲያ ከእኔ አንዳች ነገር እንዲጠይቁ ልፍቀድላቸውን? ስለዚህ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ማንኛውም እስራኤላዊ ጣዖትን በልቡ አኑሮ ክፋቱንም የማሰናከያ ድንጋይ አድርጎ በፊቱ በማስቀመጥ ወደ ነቢይ ቢመጣ፣ እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖቱ ብዛት እመልስለታለሁ። በጣዖቶቻቸው ምክንያት ከእኔ የተለዩትን የእስራኤ*

ልን በት ሁሉ ልብ ወደ ራሴ ለመመለስ ይሆን አደርጋለሁ::" በሕዝ 14፥1-5 ያለው ክፍል ያስተምረናል::

እንደ ጥንት ሰዎች እንጨት እየጠረብን ጣዖታትን እናምልክ እንጂ ዛሬም ቢሆን ከጣዖታት አምላኪነት አልወጣንም ከዚህ በተ ጨማሪም ራሳችንን እንደ አምላክ በመቍጠር እኛነታችንን እንደ ጣዖት ለማምለክም ሆነ ለመመለክ ልባችንን የምንሰጥበት ጊዜ አለ:: ለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ ብናደርግ ሄሮድስ ጥሩ ምሳሌ ነው:: በሐሥ 12፥20-23 እንደ ተጻፈው በአንድ ወቅት ሄሮድስ የጢሮስና የሲዶና አገር ሰዎች ተጣልቷቸው ነበር:: እነ ዚህ ሰዎች እህል የሚያመጡት ሄሮድስ ከሚገዛበት አገር ስለነ በር በመጣላታቸው ምክንያት የሚያስመጡትን እህል እንዳያግ ድባቸው ፈሩ:: ስለዚህም የተሰባሰበው ወደ ቂሳርያ መጥተው የንጉሥን ባለሟል ብላስጦስን፣ ከንጉሥ ጋር እንዲያስታርቃቸው እሽ አሰኝተው ዕርቅ ለመኑ በመጨረሻም ከንጉሡ ፊት ቀርበው ይቅርታ እንዲጠይቁ ተፈቀደላቸውና ቀጠሮ ተያዘላቸው:: በቀ ጠሮም ዕለት ሕዝቡ ተሰብስበው ሳሉ ሄሮድስ ልብሰ መንግሥ ቱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጠ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ህዝቡ "የእግዚአብሔር /የእምላክ/ ድምዕ ነው የሰውም አይ ደለም ብለው ጮኹ ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ::"

ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ እንደምናየው ሕዝቡ ሄሮድስን አምላክ ነው ብለው ሲጮኹ እርሱ ግን ተዉ ብሎ አልከለከላቸውም ነበር:: በመጨረሻ ላይ የዚህ ነገር ውጤት በመልአክ መመታትና በትል ተበልቶ መሞት ሆነ:: ዛሬም እግ ዚአብሔር አምላክ ሆኖ ሳለ ራሳችንን እንደ አምላክ ቈጥረን ልንመለክ ብንፈልግ እግዚአብሔር በፍርዱ ይገለጣል:: እን ዲህ ዐይነት የልብ ጽነትም ሰዎችን ለመለኮታዊ ፍርዱ ያመቻ ቻል:: ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ አዳምና ሔዋንን እንደ እግዚአ ብሔር ትሆናላችሁ ብሎ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተካ



ከል ተቈርቋሪ መስሎ በመቅረብ ያሳተው እባብ በዘመኑ መጨ ረሻም በዚህ መልኩ ሰፍቶና ደርቶ ስለሚመጣ ራሳችንን እንደ አምላክ ቈጥረን ለጥፋት እንዳንመለክ ትልቅ ጥንቃቄና ሽሽት ልናደርግ ይገባል::

ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 14፥8-18 ባለው ክፍል ላይ ስናነብ፡- አንድ ጊዜ በልስጥራ ጳውሎስና በርናባስ ወንጌልን እየሰበኩ ጳው ሎስ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነውን ሰው እምነቱን አይቶ በእግሩ እንዲቆም አዞት በተፈወሰ ጊዜ፣ በዚያ የነበሩ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል ብለው እንደ ሄሮድስ ችግር ውስጥ ሊከቷ ቸው ነበር:: ነገር ግን ልባቸው በእውነት መንፈስ ተጠብቆ ስለ ነበር ለነገሩ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳቸው እንዳይወስዱ የሚቻላቸውን አደረጉ:: በመጨረሻም ልብሳቸውን ቀደው እየጮኹ ሮጡ:: ሌላው ቢቀር የድያ ቤተ መቅደስ ካህን ኮርማዎችና የአበባ አክሊሎችን አምጥቶ ሊሰዋላ ቸው በተዘጋጀ ጊዜ እንኳን ስሜታቸው በውስጣቸው ብድግ ብድግ ብሎ እኛ አማልክቶች ነን ቢሆንም አምልኮ አይገባንም አላሉም:: ከዚህ ይልቅ "እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን" ከዚህ ከንቱ ነገር ሰው ለሰው እየሰዋ ሰውን ከማም ለክ አካሄድ) ሰማይንና ምድርን ባህሩንም በእርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን አሉ:: በመጨረሻም ይህን ብለው እንዳይ ሰውላቸው በጭንቅ አስተዋቸው::

ራስን እንደ አምላክ የመቍጠሩና የእግዚአብሔርን ክብር የራስ የማድረጉ ጕዳይ በሐዋርያት ሥራ 12፥20-23 ተገልጾ እንዳየን እንዲሁ በሕዝቅኤል 28፥1-10 ባለው ክፍልም ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን:: ከክፍሉ እንደምንረዳው ጢሮስ የምትባል አንድ የምትታወቅ ደሴት ነበረች:: በዚህች አገር ውስጥ የነገሠው ንጉሥ ልቡ ከፍ ከፍ ብሎበት "እኔ አምላክ ነኝ በአምላክ ወንበር በባ

ሕር መ ከል ተቀምጫለሁ አለ:: በመጨረሻ ላይ ግን በእግዚአብሔር ተፈረደበት" ከታሪክ እንደምንረዳውም ያቺ ከተማ እንዳልነበረ ሆናለች::

የዚህን ክፍል ምዕራፍ እየጨመርን ስናነብ "እኔ አምላክ ነኝ" ከሚለው የትዕቢት አሳብ በስተ ጀርባ ያለው የቀደመው እባብ (ዲያብሎስ) እንደ ሆነ እናያለን:: ነገር ግን በዚህ ክፍል በምዕራፍ 34፥30-31 (ነባሩ ትርጉም) ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ ይላል "እኔ እግዚአብሔር አምላካቸሁ ከእነርሱ ጋር እንዳለሁ፣ እነርሱም የእስራኤል ቤት ሕዝቤ እንደ ሆኑ ያውቃሉ ይላል ጌታ እግዚአብሔር:: እናንተም በጎቼ የማሰማርያዬ በጎች፣ ሰዎች ናችሁ እኔም አምላካችሁ ነኝ፣ ይላቸዋል::" አምላካችን እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰዎችና አማልክቶች አይደሉም:: ከዚያ አኳያ ልናመልክ የሚገባን እግዚአብሔርን ብቻ ነው:: በሰማይ ሰው እንደማይመለክ ሁሉ በምድርም መሆን ያለበት ይኸው ሥርሀት ነው:: እንግዲህ እውነታው ይኸ ከሆነ ቀደም ብለን እንዳየነው እግዚአብሔርን እንደ ጣዖት እንዳንቈጥረው እንዲሁም ለምድራዊ ሕይወታችን ክንውን ብቻ የምንፈልገው እንዳይሆን እንጠንቀቅ፣ ከዚህ ይልቅ እርሱን አክብረን ትእዛዙን ለመጠበቅ በሚያስችል ልቦና ለመኖር ተጠርተናል:: በዚህ መጠራት እንደሚገባ እንመላለስ!

## ለ. ጸሎት

ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል

*"ይህንም የምጽፍልህ ብዘገይ እንኳ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንድታውቅ ነው፤ ቤቱም የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ይኸውም የእውነት ዐምድና መሠረት ነው::"* (1ጢሞ 3፥15)



*"ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሻጮችን ከዚያ አስወጣ ደግሞም 'ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል' ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት" አላቸው* (ሉቃ 19፥45-46)

*"ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የዘራፊዎች ዋሻ አደረጋችሁት" አላቸው* (ማቴ 21፥13)

የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው:: በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ዐይነተኛ እንቅስቃሴ ጸሎት ነው:: እግዚአብሔርን ማወደስ ለእግዚአብሔር መስገድ ነው:: ምንጊዜም የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤትነት ባሕርይውን ሊለቅ አይገባም:: ከጸሎት ቤትነት ይልቅ ለሌላ ጉዳይ እንዳይውል ለሌላ ጕዳይ መዋያ እንዳናደርገው በሌላ ነገር እንዳንተካው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር ቤቱ በጸሎት እንዲሞላ ይሻል፤ በቤቱ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ ይወዳል::

ስለዚህ ሰው በደመ ነፍስ ዕውቀቱ ተደጋፊነቱን ይገልጻል:: በአኗኗሩም በተለያየ መልኩ አሜን ማለቱን ያሳያል:: ከዚህ ሁኔታ በወግድልኝ ባይነት ተደጋፊነቱን ከላዩ ላይ አውልቆ ለመጣል ቢታገልም አይሆንለትም:: ፍጥረቱ፣ የፍጥረቱ እይይዝ አይፈቅድለትም:: ተቃውሞና ተቃርኖ መቆሚያውንና መቋሚያውን እንደማፈራረስ ወይም መስባበር ነው:: መቆሚያውና መቋሚያውን አስወግዳለሁ ሲል ራሱ ተወግዶ ይገኛል:: ዓሣ ከባሕር ውጭ እንደማይኖር ሁሉ በባህር አልሆንም ብሎ በራሱ ሆኖ መገኘት እንደማይችል ሁሉ ሰውም ያለ እግዚአብሔር ምንም መሆን አይችልም::

### (1) ጸሎት ምንድን ነው?

ጸሎት ማለት በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለውን የህልውና እይ

ይዝ (connectedness) የሚገልጽ ህይነተኛ ተራክቦ ነው:: የሰው ልጅ ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በፈጣሪው ላይ ሲደገፍ ማየት በጣም የተለመደ ነው:: እንዲያውም ሰው ከእግዚአብሔር ውጭ ህልውናም ሆነ ዘላቂ ተስፋ የሌለው ፍጡር ነው:: እንግዲህ ሰው በፈጣሪው ላይ ሲመካና ከፈጣሪውም እንዳች ነገርን ለማ ግኘት በጸሎት ሲማጠን ይታያል:: ይህንንም ሁኔታ ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከት ይቻላል::

ጸሎት ዓለም ዐቀፍ ነው:: ሆኖም ጸሎት ለሚሰማና ለሚመለስ የሚጣራ መሆን አለበት:: ኤር 33፥3 አለበለዚያ ጸሎት በግ ዋው (vacuum) ውስጥ ድምፅ ለማሰማት እንደመሞከር ነው፤ ወይም ራስ ለራስ መናገር ይሆናል:: ጸሎት ወደ እንድዬ፣ የፍጥረት ሁሉ ባለቤት ወደ ሆነው፣ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እንጂ "እሰማለሁ እመልሳለሁ ለሚል ሁሉ ሊጸልይ አይገ ባም" (ኢሳ 16፥12፤ 45፥17፤ 1ነገ 18፥26)

ጸሎት ወደ አበጀን ወደ ሠራን የሚደረግ የማያቋርጥ ግሥገሣ ነው:: ይኸውም ከእርሱ ጋር ለመራከብ ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ ሁልጊዜ ወደ እርሱ የምንገሠግሥበት መንገድ ነው:: ሰው ሁሉ ለምን የሠራውን፣ ያበጀውን ፍለጋ አይነሳም? ሰው የሥጋ ወላጆቹን ካላወቀ ለማወቅ፣ ካላገኘም ለፍለጋ እንደሚነሣ ለምን የሠራውን እግዚአብሔርን አይፈልግም?

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የምናደርግበት እንጂ አንድ የምንፈልገውን ነገር ጠይቀን፣ ተቀብለን የምንመለስበት መስተጋብር አይደለም:: ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገር ነው:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው፤ ጸሎት ወደ እግዚ አብሔር መቅረብ፣ ፊትን፣ ልብን፣ ዐይንን፣ ወደ እግዚአብ ሔር ማቅናት ማንሳት ነው:: ጸሎት ወደ ፈጣሪአችን ወደ ሠራን ወደ ተቤዠን ወደ ሕይወታችን ባለቤት ወደ እግዚአብ



ሔር አምላክ መቅረብ ከእርሱም ጋር ኅብረት ለማድረግ በመ ንፈስ ለመረካከብ መገሥገሥ ነው:: ከኅብረት ወደ ጠለቀ ኅብ ረት መጓዝ ነው::

ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ የጸጋ ዙፋን መቅረብ፣ ጸጋንና ምሕረ ትን ለመቀበል መምጣት ነው::

ጸሎት በአንደበት በቃላት የሚገለጥም ቢሆን በመሠረቱ የል ባችን በእግዚአብሔር ዙፋን ሥር መገኘት በእግዚአብሔር ፊት የልባችን መዘርጋት የነፍሳችን መፍሰስ ነው::

ጸሎት ከድርጊትነት ይልቅ "መሆንን" አመልካች ነው:: አንደ በታችን ከሚያወጣው የቃላት ቅንብር ከማዳመጥ ይልቅ እግዚ አብሔር የልባችንን ቃል ነው የሚያደምጠው:: ብዙ ጊዜ አንደ በት በሚለውና ልብ በሆነው መካከል ብዙ ርቀት አለ:: አንደ በታችን የሚናገረው ነገር ብዙ ጊዜ ለልብ ባይተዋር ይሆናል:: አንደበትና ልብ አብረው ሲተሙ እምብዛም አይታይም::

*"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀ ርባል በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ የሚ ያመልከኝም ሰው ባስተማረው ሰው ሠራሽ ሥርሀት ብቻ ነው"* (ኢሳ 29፥13)

ስለሆነም ጸሎት የልብ ቋንቋ ነው:: ጸሎት የውስጥ ቋንቋ ነው:: የጸሎት መነሻ የልብ፣ የነፍስ፣ የውስጥ ሰውነት ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ድግምት ነው:: ትክክለኛ ጸሎት አድራሻው እግዚ አብሔር ነው::

ጸሎት ጸሎት የሚሆነው፣ ከአንደበታችን በወጣ ቃል ወይም ድምፅ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የልባችን አቋም፣ መለኮትን አክ

ባሪና አፍቃሪ እንዲሁም "በጸጋው ዙፋን ሥር ዋይ" ሲሆን ነው።

በአንደበትም በሕሊናም መጸለይ መቻል አለብን። መደበኛ የጸሎት ጊዜ ከጠፋ ግን፣ የጸሎት ሕይወት ይሞታል።

ጸሎታችን በእኛም ዘንድ የተደመጠ ሊሆን ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ ጸሎታችን ልብ የሌለበት ድግምት ብቻ ይሆናል፤ ጌታችንም ስትጸልዩ እንደ አሕዛብ በከንቱ አትድገሙ ብሎናል።

ሰው ከአንደበት የሚነገረውን ያደምጣል፤ እግዚአብሔር ግን የልብን ያደምጣል።

ሰው የሰውነታችንን እንቅስቃሴ ያያል፤ እግዚአብሔር ግን የልብ ሁኔታችንን ይመለከታል (ኢሱ 7÷7፤ 1ሳሙ 16÷7)።

የጸሎት አድራሻ እግዚአብሔር አምላክ ነው። የአደባባይ ጸሎታችን እግዚአብሔርን ረስቶ ወደ ጉባኤተኛው ወደ ዐላፊ አግዳሚው እንዳይሆን ልብ ልንል ያስፈልጋል። አለበለዚያ ጸሎታችን:-

- ለታይታ
- ለመመጻደቂያ
- ሌላውን ማሚያ/ መወንጀያ
- አሽሙር መናገሪያ . . . ይሆናል።

በጸሎት ጊዜአችን ልባችን ቀድሞ የአካላችን እንቅስቃሴ ቢከተል ጸሎታችን ቅን ነው። ልብ በሌለበት የአካል መወራጨት ጠቃሚነቱ አካልን የሚያፍታታ ጅምናስቲክ መሆኑ ላይ ብቻ ነው።

በአደባባይ ስናመልክ፣ ስንጸልይ እውነተኞች በማንሆንበት ጊዜ ሁሉ ግብዞች ነን፤ ተዋንያን ነን፤ መንፈሳውያን አይደለንም።

1. እግዚአብሔር እንድንጸልይ ይፈልጋል

እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ይወዳል፤ እግዚአብሔር ሰውን ፈላጊ ወደ ራሱ ጠሪ ነው።



*"እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ"* (ማቴ 11÷28)።

*"መንፈስና ሙሽራዪቱ ና ይላሉ፤ የሚሰማም ና ይበል የተጠማም ሁሉ ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ በነጻ ይውሰድ"* (ራእ 22÷17)።

የእግዚአብሔር መንፈስ እና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ ይጣራሉ።

2. እግዚአብሔር የኪዳኑ ሕዝብ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ እንዲጸልዩ ያዛል

*"ለምኑ ይሰጣችኋል*
*ፈልጉ ታገኛላችሁ*
*አንኳኩ በሩም ይከፈትላችኋል"* (ማቴ 7÷7)።

*"ሳታቋርጡ ጸልዩ"* (1ተሰ 5÷17)

*"በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ ይህንም በማሰብ ንቁ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ"* (ኤፌ 6÷18)።

ጸሎት የእግዚአብሔር ኀይል የፈቃዱ ዕውቀት ወደ ልጆቹ የሚወርድበት፣ የሚፈስበት መስመር ነው።

3. መንፈስ ቅዱስ የጸሎት አጋር ለጸሎታችን ፍልቀት ነው

*"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል፤ ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ዐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና።"* (ሮሜ 8÷26-27)

ዳገት የሚመስለው ጸሎት፣ ጉምዛዛ የሚመስለው ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ ዕገዛ የሜዳ ግልቢያ፣ ጣፋጭ የሕይወት ዘይት፣ የሚያውድ መልካም ሽቱ ይሆናል::

*"አባ አባ ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ላከ"* (ገላ 4፥6)

*" ... አባ አባት ብለን የምንጣራበትን የልጅነት መንፈስ ተቀብላችኋልና"* ሮሜ 8፥15)

## 4. እግዚአብሔር ጸሎታችንን ለሥራው መንገዱ ያደርገዋል

እግዚአብሔር በግል ሕይወታችን፣ በሌሎች ሕይወት ወይም በታሪክ ውስጥ አንድን ነገር ለማከናወን ወይም ለውጥ ለማምጣት ጸሎታችንን መንገዱ ያደርገዋል:: ለምን ቢባል መልስ መስጠት አይቻልም፤ ብቻ እግዚአብሔር የባሮቹን፣ የልጆቹን ጸሎት ያሰበውን፣ ያቀደውን ወደ ተግባር ለመለወጥ መንገዱ ያደርገዋል::

እግዚአብሔር የሕዝቡን፣ የባሪያዎቹን ጸሎት ያቀደውንና የሚሻውን ለመፈጸም መንገዱ ሲያደርገው እናያለን::

በአክዓብ ዘመነ መንግሥት በኤልዛቤል መሪነት እስራኤል ወደ በኣል፣ የዝናብና የልምላሜ ምንጭ እንደ ሆነ ወደ ተቈጠረው ጣዖት አምልኮ በነጐደ ጊዜ ነቢዩን ኤልያስን አስነሣው:: ወደ አክዓብም ልኮት ኤልያስም "በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር በሚቀጥሉት ዓመታት ዝናብ ወይም ጠል አይኖርም" ብሎት ሰማያት ተዘጉ:: እግዚአብሔርም ኤልያስን እንዲሸሸግ አዘዘው፤ ከዚያም በሦስተኛው ዓመት "ሄደህ ለአክዓብ ተገለጥ እኔም በምድሪቱ ላይ ዝናብ አዘንባለሁ" አለው::



በኤልያስና በበኣል ነቢያት መካከል እውነተኛ አምላክ በእሳት የሚመልሰው እርሱ መሆኑ እንደሚታወቅ ባደረጉት ድርድር ኤልያስ ከጸለየ በኋላ እሳት ከሰማይ ወርዶ መሥዋዕቱን በመብላቱ ሕዝቡ እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው ብለው በማረጋገጥ ሰገዱ:: አሁን ዝናብ ቢዘንብ አዝናቢው በኣል ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንደሚሆን የሚያምን ልብ ተዘጋጀ:: ይሁንና እግዚአብሔር ዝናብ አዘንባለሁ ብሎ ተስፋ የሰጠ ቢሆንም ዝናቡ እንዲዘንብ ኤልያስ ሰባት ጊዜ እየደጋገመ መጸለይ ነበረበት:: እዚህ ላይ እግዚአብሔር ዝናብ ለማዝነብ`የኤልያስን ጸሎት መንገዱ ሲያደርገው እናያለን (1ነገ 17-18)::

ይሁዳ በባቢሎን መንግሥት ሥር በምርኮ ለሰባ ዓመታት እንደሚቈይ፣ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ከምርኮ ምድር እንደሚመልሳቸው በነቢዩ ኤርምያስ አስቀድሞ ትንቢት ተናገረ:: ዘመኑም በተፈጸመ ጊዜ ከምርኮ የመመለሳቸው ርምጃ የተወሰደው የነቢዩ ዳንኤልን ጸሎት ተከትሎ ነበር:: ምንም እንኳ ከሰባ ዓመት በኋላ ከምርኮ እንደሚመልሳቸው እግዚአብሔር ፕሮግራም የያዘ ቢሆንም፣ የመመለሻቸው በር እንዲከፈት የዳንኤል ሃያ አንድ ቀን በመጾም የምልጃ ጸሎት ማድረግ ነበረበት:: የምርኮኞቹ መመለስ የዳንኤል ጸሎት መልስነት ተግባራዊ ሆነ:: እግዚአብሔር ታሪክን ለመለወጥ የዳንኤልን ጸሎት ፈለገው::

እግዚአብሔር ኢዮብን ለማጽናናት በመጡ በእነኤልፋዝ በተቆጣ ጊዜ እንደ አሳፋሪ ተግባራቸው እንዳያደርግባቸው ኢዮብ ስለ እነርሱ እንዲጸልይላቸው እግዚአብሔርም የኢዮብን ጸሎት እንደሚቀበል ተናገራቸው:: በኢዮብ ወዳጆች ላይ ቍጣው እንዳይወርድ እግዚአብሔር የኢዮብን ጸሎት መንገዱ ሲያደርግ እናያለን (ኢዮ 42፥8-10)::

እግዚአብሔር የሕዝቡን፣ የልጆቹን ጸሎት በእነርሱ ወይም በሌ

ሎች ወይም በታሪክ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት መንገዱ ያደርገዋል። እግዚአብሔር አንድን ነገር ለማድረግ የእኛን በጉዳዩ ላይ መጸለይ ይፈልጋል። በዚህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ትልቅ ሚና አለው።

ሀ) ጸሎት የተደጋፊነት ቋንቋ ነው

ጸሎት የተደጋፊነት ቋንቋ ነው። የሚጸልይ ሁሉ ተደጋፊ ነው፤ አልሞላሁም የሚል ሰው ቋንቋ ነው፤ ከዚህ ጋር ልሞላ፣ ሙሉ ልሁን ባይ ሰው፣ የናፍቆቱ ቋንቋ ነው።

እኛ ፍጡራን በራሳችን ዐቅመ ቢሶች ነን። ከዚህ የተነሣ በራሳችን ምንም ማድረግ አንችልም፡ ስለዚህ በሕይወት ለመኖርም ሆነ ከክፉ ለመጠበቅ እንዲሁም በኑሮ ለመከናወንና ዋስትና ለማግኘት በእግዚአብሔር ላይ ሙጥኝ እንላለን። ሁላችንም በዚህ ምድር ስንኖር በፍጥረቱ ላይ ሙጥኝታ አለብን። ለምሳሌ በቀን ብርሃን እንድናገኝ ፀሓይን ሰጥቶናል። ነገር ግን ፀሓይ ለሰው ልጆች ብርሃን አሻፈረኝ ብላ ብርሃን ብትከላከል ማናችንም አንኖርም። ምክንያቱም ለመኖር መብላት አለብን። ያ የምንበላው ነገር ደግሞ የሚገኘው በምድር ላይ ካሉ ዕፀዋትና እንስሳት ነው። ዕፀዋት ደግሞ የሚበቅሉት የፀሓይ ሙቀት ሲኖር ነው። እንዲሁ ለመተንፈስ ደግሞ አየር ያስፈልገናል። ነገር ግን አየሩ ከዚህ ከምንኖርበት ምድር ወደ ሌላ ፕላኔት ቢሄድ ሁላችን በአንድ ጊዜ እርግፍ እንላለን።

ከዚህ ተነሥተን ስለ ፍጥረት ስናስብ ይህ የምናየው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እኛ ብዙ ጊዜ ይህንን እንረሳና ትምክህተኞች እንሆናለን። ያለ እግዚአብሔርና ያለ በረከቱ በራሳችን እንደምንኖር እናስባለን። ከዚህ ይልቅ ተደጋፊ መሆናችንን መቀበል፣ በየጊዜው ልብም ማለት ትክክለኛ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በያዕቆብ መልእክት ላይ እንዲህ ይላል *"የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ አትሳቱ፤ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው። መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ"* (ያዕ 1፥16-17)።



ወደ ከዋክብት ዓለም፣ ወደ ሰማይ አካላት ብንሄድ አንዱ በአንዱ ላይ ያጠላል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ የሚያጠላ የሰማይ አካል የለም። እርሱ ከሰማያት ሁሉ በላይ ነው። ሰማየ ሰማያት ምድርንም ሁሉ የሞላው ፍጥረት ሁሉ የእርሱ ነው፤ በእርሱም ተደግፎ ይኖራል። እኛ በራሳችን ምንም መሆን አንችልም፤ ስለዚህ ጸሎታችን ሙጥኝ ባይነታችንንና ተደጋፊነታችንን የሚገልጥና የሚያመለክት ነው።

የዳዊት የተደጋፊነት ጸሎት (መዝ 57፥1፤ 61፥4፤ 62፥1-5፤ 42፥1-11)

ማንነታችን የሚቀነባበረው የምንቀናጀው ከእግዚአብሔር ጋር ስንሆን ነው፤ ከእግዚአብሔር ስንርቅ እሾህና አሜካላ በሕይወታችን ያቈጠቍጣል፤ ለጤናማነታችን ለልምላሜአችን ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ያሻናል። እርሱ የልምላሜአችን ሰበብ ነው። እኛ በሕይወታችን ተደጋፊዎች ነንና ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ልንሆን ግድ ነው።

በእኛ ዘንድ ያለ እግዚአብሔር የሰጠን ብዙ ነገር አለ፤ ለምሳሌ ዐይኔ ሊጠፋ ነው ብለን ዐስበን ተስፋ ቈርጠን ደምድመን ሳለ፣ እግዚአብሔር ለዐይናችን ሙሉ ጤና ቢሰጠን ኋላ በዐይናችን እግዚአብሔርን እንበድል ይሆን? አእምሮአችንን ልናጣ ብለን እግዚአብሔር ሲመልስልን በዚያ አእምሮአችን እግዚአብሔርን ብንበድልበት በጣም አሳዛኝ ይሆናል።

በክርስትና ማደግ፣ መብሰል ማለት በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ

በሙሉ መደገፍ ማለት ነው:: በእግዚአብሔር አለመደገፍ በራስ መመካት አለማደጋችንን የሚያሳይ ነው:: በእያንዳንዱ ነገር ላይ በእግዚአብሔር ከተደገፍንና ነገራችን ከተሳካልን በኋላ፣ እንደ ብዙዎቹ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት፣ በእግዚአብሔር ላይ ዐመፅ የምናነሳበት እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል:: ተደጋፊነታችንን ካወቅንና ሁሌ ካሰብነው ግን እንዳንታበይ ይረዳናል:: በራስ ከመፎከርም ያድነናል::

ጸሎት የተደጋፊነት ቋንቋ ነው ስንል፣

የመደገፋችን ሰበቡ:-

- ሕይወት እንዲዘራብን
- በሕይወት ለመኖር ( በራሳችን ሕይወታችንን ልንይዝ ስለማንችል (ኤር 10፥23))
- ከክፉ ለመጠበቅ

| | |
|---|---|
| የምንጠበቀውም | ከራስ/ከሥጋችን |
| | ከሰይጣን/ከክፉው |
| | ከሰዎች ክፋት |

ከራስ/ከሥጋችን፤ ስንል አንዳንዴ የምንጸልየው አልተመለሰም ብለን ከማጉረምረም፣ ጸሎት እኛን እየቀረጸን ስለ ሚሄድ፣ ራእያችን ይህ ነው ብለን ለታዋቂነት ዝናን ለማትረፍ ከምንጸልየው ከምንመኘው ምኞት ጸሎት ያድነናል::

ከሰዎች፤ በዳዊት መዝሙርና ከኤርምያስ ውስጥ ባብዛኛው የምናገኘው ከሰዎች አድነኝ የሚልን ጸሎት ነው:: እኛም በዚህ ምድር ስንኖር አብዛኛው ችግራችን ጭንቀታችን ሰው ነው፤ ብዙም የምንጸልየው ከሰዎች ለመዳን ነው (መዝ 38፥19-20፤ 39፥7-8፤ 41፥1-13)::



የጳውሎስ መከራዎች ከሞላ ጐደል በሰዎች የተሰነዘሩ ናቸው:: አንዳንዴ ደግሞ ጭንቀታችን ችግራችን ብቻ ሳይሆን ከዚህ በላይ ከሚደርስብን ችግር ባሻገር ሰው ምን ይለኛል የሚለው ነው::

ለ) ጸሎት የእንጻኝ ባይነት ቋንቋ ነው

የይቅር በለኝና ሌሎችን ይቅር የምንልበት ቋንቋ ነው (መዝ 35፥1-28፤ 56፥1-13፤ 51፥1-19):: እውነተኛ የሆነ ጸሎት አንፃኝ ባይ ነው:: በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአታችንን ክፉ ምኞታችንን ሁሉ በፊቱ ዝርግፍ አድርገን ስናቀርብ እግዚአብሔር ያነጻናል:: የእኛ ማንነት ምንጊዜም የጐደፈ ነው፤ ይህ ካልነፃ አእምሮአችንን/ህሊናችንን ያውካል፣ ሰላም ይነሣናል፣ የሕይወት እርካታን የሚቀንስ ይሆንብናል:: ስለዚህ ሁል ጊዜ በጌታ መንጻት አለብን::

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሥራት የሚጀምረው ራሳችንን በፊቃዳችን ለእርሱ ስናቀርብ ነው:: እኛ ብዙ ምስጢር ወይም ድብቅ ነገር አለን፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግልጥና ቅልጥጥ ያለ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ዐውቆም ሰብእናችንን አክብሮ ነው የሚይዘን::

ሐ) ጸሎት የታደገኝ ቋንቋ ነው

2ዜና 20፥1-3 ኢዮሣፍጥ ጠላት እንደ መጣበት ሰማ፤ እጅግም ፈራ ፍርሃቱም ወደ እግዚአብሔር አቀረበው:: ፍርሃት አሉታዊ ስሜት ነው፤ ይሁንና ፍርሃት ሲመጣብን ወደ እግዚአብሔር ከገፋተረን ወይም ካቀረብን መልካም ነው::

ሕይወታችን በበደለኝነት ሲሞላ ዐቅመ ቢስ፣ ሁሉም የሚያስደነግጠን/የሚያሸብረን እንሆናለን:: ምንም እንኳ ውጪያችን ሞገስ ያሰጠን ቢመስልም ውስጣችን ግን ባዶነት፣ አይገባኝም ባይነት

ይሰማዋል::

ጸሎታችንን የሚቀናቀኑ/ጸሎት ሥርዐትና ወግ ብቻ የሚያደርጉ/ ጸሎትን እንደ ነቀዝ የሚበሉ ባዶ የሚያደርጉ ነገሮች:-

1. የጸሎት አድራሻ እግዚአብሔር መሆኑ ይቀርና ሰው ሲሆን፣
2. ለጸሎታችን ልባችን ባይተዋር ሲሆን ወይም ጸሎታችን የአንደበት ብቻ፣ የቃላት ድግግሞሽ ሲሆን::

ሰይጣን እንዳንጸልይ በጣም ይፈልጋል/ይተጋልም:: እምቢ አሻፈረኝ ብለን ከጸለይን የጸሎታችን አድራሻው ሰው እንዲሆን አለበለዚያም ልብ ያላወቀው የአንደበት ዓለም ጸሎት እንድንጸልይ ይተጋል::

ማቴ 6፥5 ስትጸልዩ እንደ ግብዞች (እንደ ተዋንያን) አትሁኑ:: በሰው ፊት ለመታየት ስትሉ አትድገሙ ይላል:: ለፈሪሳውያን የጸሎት ታይታ ስፍራ፣ የመንገድ ማዕዘን ወይም ምኩራብ ነበር:: ለእኛ ዛሬ የመንገድ ማእዘን በጉባኤ ውስጥ መጸለይ ይሆን? በግል ግን የጸሎት ፍላጐት የሌለን ሆነን ሳለን በአደባባይ ጸሎተኛ መስሎ መታየት የጸሎት መድረክ መናፈቅ መሻማት ከንቱ ነው:: ጸሎት አድራሻው እግዚአብሔር ካልሆነ አሽሙር፣ ሽንገላ፣ ፌዝ ወይም እንደፈሪሳውያን መመጻደቂያ ይሆናል::

በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን መሆን አለብን:: ራስን አለመሆን ማስመስል ራስን እንደ መሸጥ ማለት ነው:: ጸሎት አስተውሎትን ይጠይቃል፤ ዝም ብለን ሥርዐታዊና ሃይማኖታዊ እንዳይሆንብን ዕለት ዕለት ጸሎታችንን ከድግምትነት መዋጀት አለብን፤ በከንቱ በመድገም ድካምን እንዳናተርፍ::

መ) ጸሎት የምስጋና፣ የውዳሴ ቋንቋ ነው

ምስጋና ስለ ተደረገልን ነገር፣ ስለ ቸርነቱና ምኅረቱ የምናቀር



በው ነው:: ውዳሴ ግን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ኀያልነት ከማየት የተነሣ በማድነቅ ላይ የሚሽከረከር ነው:: እርሱ የሠራውን ሥራ ታምራቱን፣ ድንቁን ማየት፣ ማሰብና ማስተዋል ስንጀምር ጸሎታችን እግዚአብሔርን የሚያወድስ ይሆናል::

ሠ) ጸሎት በሰይጣን መንግሥት ላይ የማመጽ፣ የጠበኝነት/የፍልሚያ ቋንቋ ነው

ጌታ ባስተማረው ጸሎት ውስጥ *መንግሥትህ ትምጣ፣ ከክፉው አድነን እንጂ* ብለን ስንጸልይ በጨለማው መንግሥት ላይ ማመጻችን፣ ከእርሱ ጋራ በምናደርገው ፍልሚያ አኳያ ምሽግ ማብጀታችን ነው (ይኸው ሐሳብ ጌታ ባስተማረው ጸሎት ማብራሪያ ሥር የበለጠ ተገልጦአል)::

ረ) ጸሎት የፍቅር፣ የምልጃ ቋንቋ ነው

- ጸሎት ከራስ ባሻገር የምልጃ ቋንቋ ነው
    - ◊ ሕይወት ሰጥ/ሕይወት አለምልም
    - ◊ ከክፉ ጠብቅ
    - ◊ ታደግ/ፈውስ
    - ◊ አንጻ/መልስ ብሎ ስለ ሌሎች መማጠን ነው::

እኛ ሰዎች ያለ እግዚአብሔር በራሳችን ህልውና የሌለን መሆናችንን ከዚህም የተነሳ በሕይወት ለመኖርም ሆነ ከክፉ ለመጠበቅ እንዲሁም በኑሮ ለመከናወንና ዋስትና ለማግኘት ስንል በእግዚአብሔር ላይ ሙጥኝ እንደምንል ቀደም ብለን ጠቅሰናል:: ይሁን እንጂ ከዚህ ተነስተን እያንዳንዳችን ጸሎታችንን ብንገመግም ብዙ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የምንጸልየው የምንፈልገው ነገር እንዲሞላልንና እንዲከናወንልን ስንል እንጂ እርሱን ናፍቀነው አይደለም:: ምክንያቱም ብዙዎቻችን ያ የምንፈልገውን ነገር መልስ ካገኘንበት በኋላ ጸሎታችንም እንደ

ቀድሞው አይሆንም ፈጥኖም ይቀዘቅዛል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ነገር ሲጎድልብንና ልንወጣው የማንችለው ችግር ውስጥ ስንዘፈቅ እንደገና የእግዚአብሔርን ፊት እንፈልጋለን፡፡ ጸሎታችንም በዚያን ሰሞን ይሞቃል፡፡ እዚህ ላይ ይህ ሀሳብ የተነሣው ስለሚያስፈልጉን ነገሮችና ስለሚደርስብን ችግር መማጠን እንደሌለብን ለማሳየት አይደለም፡፡ ጸሎት አጽንኦት እንዲሰጠው መለስ ቀለስ ካለ የጸሎት ሕይወት ወጥተን ፍቅር፣ ናፍቆት ግድ የሚለው የጸሎት ሕይወት ማምጣት እንዳለብን ለማስገንዘብ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር አንድ ነገር ፈልገን ሳይሆን፣ ወደነው መጸለይ ስንጀምር የጸሎታችን ይዘቱ ክብሩም እየተቀየረ መምጣት ይጀምራል፡፡

ከዚህ ቀደም በግል የሕይወታችን ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኩር የነበረው የጸሎት ይዘት ወደ ምልጃ ጸሎት እየተቀየረ ይመጣል፡፡ የምልጃ ጸሎት እየጸለይን መምጣት ስንጀምር ጸሎታችን "የፍቅር ቋንቋ" መሆን ይጀምራል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ "በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን የፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር" በውስጣችን ሲገለጥ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ፡-

- አብርሃም ለሎጥ (ዘፍ 18፥22-23)፣
- ሙሴ ለእስራኤል (ዘፀ 32፥11-34፤ ዘኁ 11፥2፤ 21፥3፤ ዘዳ 9፥23)፣
- ሳሙኤል ለሕዝቡና ለሳኦል (1ሳሙ 7፥5፤ 12፥19-23)፣
- ዳዊት ለሕዝቡ፣ የእግዚአብሔር ሰው ለኢዮርብአም (1ነገ 13፥6)፣
- ኤልሳዕ ለሞተው ሕጻን (2ነገ 4፥33)፣
- ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብና ለሕዝቅያስ (2ነገ 19፥4፤ 2ዜና 32፥20)፣
- ኢዮብ ለጓደኞቹ (ኢዮ 4፥2-10)፣



- ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱና ለኢየሩሳሌም (ዮሐ 17፤ ሉቃ 31፤ 19፥22)፣
- ጳውሎስ ለእስራኤል (ሮሜ 9፥1-33) እንደ ጸለዩ እኛም ስለ ሌሎች እንማልዳለን፡፡

ጸሎት ለውጥ የሚያመጣ መንፈስ ቅዱስ ሲሳተፍበት ነው፡፡ ጸሎት በክርስቶስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ አብ የሚደረግ የማያቋርጥ ግሥጋሣ ነው፡፡ ዕዝ 9፣ ዳን 9፣ ነህ 9 ላይ ያሉት በሙሉ የጸሎት ምዕራፎች ናቸው፡፡

ዕዝራ ተሐድሶ እንዲመጣ፣ እስራኤል ከአሕዛብ ጋር ስለተጋቡ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ገሰገሰ ቀኑን ሙሉ ራሱንም ጨምሮ ለምሕረት አለቀሰ፡፡ ዕዝራ ዝም ብሎ ወደ እግዚአብሔር ብቻ ስለ ጮኸ ሌሎችን ወደ ንስሓ ጠራ፡፡ አፋችን ብቻ ሳይሆን፣ ልባችን በእግዚአብሔር ፊት ሲጮኽ መልስ እናገኛለን፤ ሌሎች ወደ እግዚአብሔር ይሳባሉ፤ ማግኔት ብረትን እንደሚስብ ሁሉ፡፡

### ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ስለ ጸሎት አስተምሮአል

ጌታችን ባስተማረን ጸሎት ውስጥ ስምህ፣ መንግሥትህ፣ ፈቃድህ (የእግዚአብሔር) ዋነኛ ነገር ሲሆን ይህ ጸሎት የመንግሥት ጸሎት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ እውነተኛ ጸሎተኞች ከሆንን ተራ ሰው ከመሆን እንወጣለን፡፡ የተለየ ሰው እንሆናለን፡፡

ጸሎት እንዲለወጥ የሚፈለገውን ነገር ይለውጣል ወይም የሚጸልየውን ሰው ይለውጣል፡፡ ሰው የሚጸልየው ተአምራትን ለማየት ከሆነ ተአምሩ ሳይመጣ ገና የጠያቂው ሕይወት ይለወጥና በጸሎቱ እግዚአብሔር እንዲሠራ የሚጠይቀው ቀርቶ አንተ ራስህ እግዚአብሔር ሆይ ተአምር ነህ ወደማለት ያደርሳል፡፡ የውስጥ መለወጥ ታላቅ ነገር ነው፤ የብዙ ውጫዊ ለው

ጦች ምትክ ነው፡፡

**(2) ጌታ ያስተማረው ጸሎት**

*"አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ሥፍራ ይጸልይ ነበር፡፡ ጸሎቱንም እንደ ጨረሰ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ "ጌታ ሆይ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ጸሎት እንዳስተማራቸው አንተም መጸለይን አስተምረን አለው"* (ሉቃ 11፥1)

በዓለማችን ላይ ለጸሎት የተሰጠ ሕይወት ያላቸው ቅዱሳን ስለ ጸሎት ከእግዚአብሔር ቃልና ከልምድ ያገኙትን ብዙ መልካም ነገር አስተምረውም ሆነ በመጻሕፍታቸው ጽፈው ተባርከንባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ስለ ጸሎት ስናስብ እውነተኛ የጸሎት አስተማሪ ጌታችን ኢየሱስ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ በሉቃስ 11፥1 የተጠቀሰው ደቀ መዝሙር በጌታ ኢየሱስ የጸሎት ሕይወት ተነክቷል፡፡ ስለ ጸሎት ሊያስተምር የሚችል የጸሎት ሰው መሆኑን ስለ እርሱ ተገንዝቦአል፤ ስለዚህም ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን ሲል ከታላቁ የጸሎት መምህር እግር ሥር ለመቀመጥ ያለውን ጉጉት ገለጠ፡፡ በመጀመሪያ ይህ የሁላችንም ፍላጎት መሆን አለበት፡፡

ጌታም አላቸው "ስትጸልዩ እንዲህ በሉ" ሉቃ 11፥2 "እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ" (ማቴ 6፥9) በማለት ዛሬ "አባታችን ሆይ!" የምንለውን ጸሎት አስተማረ (ማቴ6፥9-13) ይህ ጸሎት በግልም ሆነ በኅብረት ባለን ስብሰባዎች መደምደሚያ ላይ መጸለዩ ስህተት ባይሆንም፣ ሁልጊዜ የፕሮግራም መዝጊያ ጸሎት አድርጎ መመልከቱ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ይልቁኑ ስለ ጸሎት መሠረታዊ እውነቶችን የምናይበት መሆኑን ልንረዳና ምን ጊዜም ልንጸልየው ይገባናል፡፡ ቀጥለን ይህን ጸሎት



እንመለከታለን፤ ጸሎቱም አድራሻን ልመናን፣ ውዳሴንና ምሥጋናን ያየዘ ነው፡፡

**ጌታ ያስተማረን ጸሎት ይዘቱ**

- በሰማያት የምትኖር
- አባታችን
- ስምህ
- መንግሥትህ
- ፈቃድህ

→ ስለ እግዚአብሔር

- የዕለት እንጀራችንን ስጠን
- በደላችንን ይቅር በለን
- ወደ ፈተና አታግባን
- ከክፉው አድነን

→ ስለ ራሳችን

- መንግሥት
- ኀይል
- ክብር

→ ወደ እግዚአብሔር

**የጸሎት አድራሻ**

"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ"

ሀ) "በሰማያት የምትኖር"

ይህ አባባል እግዚአብሔርን ከእኛ ከፍ ያለና ምጡቅ (transcendent) እንደ ሆነ ያሳየናል፡፡ ይሁን እንጂ እርሱ ምጡቅ ሆኖ ከእኛ ጋር ያልተገናኘ ወይም በእኛና በእርሱ መካከል ያለው ግንኙነት ማንም ተጉዞ ሊጨርሰው የማይችል ነው እንዳንል ደግሞ "አባታችን ሆይ" ይላል፡፡ ይህ እጅግ ቅርብ ያደረገውና ዝምድና እንዳለን ያስረግጣል፡፡

## ለ) "አባታችን ሆይ"

በመሠረቱ ይህንን ጸሎት መጸለይ የሚችሉ ልጆች የሆኑ ብቻ ናቸው:: ልጅ ለመሆን ደግሞ የሚጠየቀው በኢየሱስ አምኖ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ማግኘት ብቻ ነው:: ዮሐ 3፥16 በመስቀሉ ላይ በተከናወነው ነገር የኀጢአትንና የበደልን ሥርየት ያገኙ ወይም ከክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት የተነሣ ጽድቅ የታወጀላቸው ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ የመሠረቱ በመለኮታዊ ድንጋጌ (ሕግ) መሠረት "አባታችን ሆይ" ብሎ ለመጸለይ መብት አላቸው:: አባታችን ሆይ ብሎ ለመጸለይ ልጅነት ያስፈልጋል:: አንድ ሰው ልጅ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ስም እንዲቀድስ መንግሥቱ በበላይነት ሁሉን እንድትገዛና ፈቃዱ በምድር እንዲፈጸም እንዴት ሊጸልይ ይችላል? የልጅነትስ መንፈስ ሳይኖረው እንዴት "አባ" የሚለው አጠራር ከልቡ ይወጣል? ማንም ልጅ ሳይሆን ይህንን ጸሎት ከልብ መጸለይ አይችልም:: ለመጸለይ ቢሞክር እንኳ የሕይወት ዝምድና የሌለበት ውስጣዊ ይዘት የለሽ ግንኙነት ይሆናል::

እንግዲህ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጸሎታችን ሊሰማና ሊመለስ ወደሚችለው አባታችን እግዚአብሔር በእምነት መቅረብ አለበት:: ከዚህ ውጭ እሰማለሁ እመልሳለሁ ወደሚል ወይም ወደሚባልለት ሁሉ ጸሎት ሊደረግ አይገባም:: በተጨማሪ በአእምሮአችን ወደ ሳልናቸው የምናብ ውጤቶች መጸለይ ለተለያዩ የመናፍስት አሠራር ያጋልጣል::

## ሐ) ስምህ ይቀደስ

"ስምህ ይቀደስ" የሚለው ንዑስ ሐረግ ስምህ በሰው ልጆች መካከል ከፍ ይበል፣ ይከበር፣ ይፈራ፣ ተራ ሆኖ አይቈጠር/አይታይ፣ አይደፈር የሚል ሀሳብ ያሳያል:: በሁሉ ረገድ ስምህ የላቀ ይሁን ማለት ነው::



በመጽሐፍ ቅዱስ ስም የተግባር፣ የማንነት መግለጫ ነው:: ለእኛ እንዲህ አይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ግን ስሙ ከባሕርይው (ከማንነቱ) የተለየ አይደለም:: የእግዚአብሔር ስሞች ከእርሱነቱ የሚነሱ በመሆናቸው ራሱን ለእኛ የገለጠበት አንድ መንገድ ነው:: እግዚአብሔር ራሱን ካልገለጠ አይታወቅም ምክንያቱም እግዚአብሔር ጥልቅ ነውና (ዮሐ 17፥6)::

እግዚአብሔር ራሱን በተግባር ለባሪያዎቹ ሲገልጥ ማንነቱን በስሙ አስታወቀ፤ ስሙን መረዳት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው ወይም እግዚአብሔርን ማወቅ የማንነቱ መግለጫ የሆነውን ስሙን ማወቅ ነው::

የስሙ እውነት ይዘቱ በውስጥ ሰውነታችን ሲሰርጽ፣ ሲያድር ስሙን ዐወቅነው እንላለን:: አለበለዚያ የአእምሮ ብቻ እንጂ፣ የውስጥ ሰውነት የተራከበ ዕውቀት አይሆንም:: ስሙን ማወቅ በስሙ ይዘት መሞላትና የስሙን እውነት ማመን ነው:: እውነትን በዚህ መልክ ማወቅ ነው በሕይወታችን ለውጥ የሚያመጣው (*"እውነትን ታውቃላችሁ፤ እውነትም ዐርነት ያወጣችኋል"* (ዮሐ 8፥32)::

የእግዚአብሔር ስም በውስጣችን ሲልቅ ከወረድንበት፣ ከዘቀጠንበት ሥጋዊነት፣ ዓለማዊነት፣ እንወጣለን፤ ከጊዜያዊ ማንነት ወደ ላይ፣ ወደ ሰማይ፣ ወደ ክቡራማነት እንሳባለን፤ ከደካማነት ወደ ብርቷማነት ከፍ ከፍ እንላለን፣ እንገባለን:: በክርስቶስ ውስጥ አብዝተን እንሰወራለን::

*"የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል"* (ምሳ 18፥10)::

*"በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ"* (መዝ 19፥14)::

እግዚአብሔር ለአብርሃም የመሥዋዕቱን በግ ሲያቀርብለት እግዚአብሔርን 'በስጭነት ስሙ' ተረዳው:: እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለ (ዘፍ 22፥13-14):: ከእግዚአብሔር ጋር እየተጓዝን ስንሄድ ስሞቹን በሕይወታችን እየተረዳን፣ በውስጣችን የስሙ ምንነት ፍቺ እያደረ ይሄዳል:: እግዚአብሔር ውሃውን ሲፈውስ የቀደመው የኪዳን ሕዝብ እግዚአብሔርን በፈዋሽነት ስሙ ዐወቁት (ዘፀ 15፥22-26)::

ይሁን እንጂ ማናችንም እነዚህን ስሞች በሙላት አላወቅናቸውም፤ ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔርን አለማወቃችን ነው:: እርሱን እያወቅነው ስንመጣ በዚያው ልክ የስሞቹ ምንነትና ትርጕሞች እየገቡን (እያወቅናቸው) እንመጣለን:: ይህ ደግሞ የሚሆነው እንደየአቅማችን ራሱን በገለጠልን መጠን ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያት ዕውቀታችን የተመጠነ ስለ ሆነ ነው (1ቆሮ 13፥11-12):: ይሁንና የእግዚአብሔር ስሞች የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጡ ናቸው:: ለምሳሌ ያህል 'ኤሎሂም' ስንል ኀያልነቱንና ብርቱነቱን ያሳየናል:: እንዲሁም 'ያህዌ' የሚለው ደግሞ እርሱ በራሱ የሚኖር ፈጣሪ የለሽ (ሰበብ የሌለው ሰበብ፣ ምክንያት የሌለው ምክንያት) መሆኑን ያሳስበናል:: ለሙሴም ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ነው ያለው (ዘፀ 3፥14):: እርሱ በራሱ ህልውና አለው:: ለዘለአለም ነዋሪ መነሻም መድረሻም የሌለው ነው::

እኛ ለነገሮች ሁሉ መነሻ ሊኖራቸው ይገባል ስለምንል ይህ ዘላለም ለፍጥረታዊ ማንነታችን አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም አስተሳሰባችን በጊዜ የተዋቀረ ወይም በጊዜ ጽንስ ዐሳብ ውስጥ የታነጸ ነው:: ከዚህም የተነሣ ከዚህ በፊት ምን ነበረ የምንል ነን:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለአለም ኀይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና" ይላል (ሮሜ 1፥20-21)::



ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ለማወቅ ፍጥረቱን ማወቅ ግድ ነው::

ሁላችንም የምንኖርበት ቤት መሠረት ግድግዳና ጣራ አለው:: ከቤታችን የወጣን እንደ ሆነ ደግሞ ምናልባት የቤታችን አጥር ግቢ አለ:: ከግቢው የወጣን እንደ ሆነ የቀበሌው ክልል አለ፤ ከቀበሌው ክልል የወጣን እንደ ሆነ ደግሞ የወረዳው ክልል አለ፤ ከወረዳው የወጣን እንደ ሆነ ዞን አለ፤ ከዞን የወጣን እንደ ሆነ ክልል አለ፤ ከዚያ ስንወጣ የአገር ክልል አለ፤ ከአገር ክልል ስንወጣ የአህጉር ክልል አለ፤ ከአህጉር ክልል ስንወጣ ደግሞ የመሬት ክልል አለ፤ ከመሬት ክልል ስንወጣ የአየር ክልል፣ የመሬት ስበት ክልል አለ፤ እንዲህ እያልን ስንሄድ ብዙ ያልታወቁ የዳርቻ ክልሎች አሉ:: እንዲህ እያልን ብንቀጥል ከመጨረሻው በኋላ ምን አለ? ከዚያስ ... እያልን ብንቀጥል ማቆሚያ የለንም:: ሆኖም እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረት መጨረሻ (መደምደሚያ) ማድረግ አይቻልም:: ከመጨረሻው በኋላ ምን አለ? ለሚለው አንድ ነገር መልስ ሲሆን ከዚያስ በኋላ ምን አለ? አንድ ሌላ ነገር አለ እያለ ያለማቋረጥ ልንቀጥል ነው፤ መሄድም ከፈለግን 'መጨረሻ የለው' የሚለው ዐሳብ መደምደሚያ ይሆንልናል (ዛሬ አስትሮፊዚስት፣ አስትሮነመርስ ዩኒቨርስ ወይም ሕዋ ድንብር የለሽ ነው ይላሉ)::

አንድን ነገር ለመሸከም ሌላ አንድ ነገር ያስፈልገዋል:: ታዲያ እውነቱ እንዲህ ከሆነ ይህን ሁሉ ፍጥረት ደግሞ የያዘ፣ የተሸከመ ምንድን ነው? ምድርን በመሠረቷ፣ ፀሓይንም በሥፍራዋ ማን ያዛት? የሚለው ጥያቄ መነሣት አለበት:: በመሠረቱ ወደ ሥነ ፍጥረት ስንሄድ መሬት በፀሓይ ስበት ተይዛ በዙሪያዋ እንደ መሽከርከሯ ፀሓይም ምድርም ያሉት በሰማይ ላይ ነው:: እግዚአብሔር ግን ተፈጥሮንና የተፈጥሮን ሕግጋት በሥልጣኑ ቃል ደግፎ ይዟል (ዕብ1፥3፤ ቈላ1፥17):: በፍጥረቱ ታላቅነቱን

እንኳ ማየት የእርሱን ታላቅነት እያሰብን እንድንዋጥ ያደርገናል። ይህን ስናይ ጸሎታችን በስግደት ይሆናል። ስንደነቅ ከመንበርከክ ወደ ኋላ አንልም። እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ስም ብንመለከት ምስጢሩ ብዙ ነው። ስሙ ማንነቱንና ባሕርይውን ያሳያል።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 8፥32 ላይ ያለውን ክፍል ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥፍራው ከነበሩ የአመኑ አይሁዶች ጋር ይወያይ የነበረው የስምን ምንነት በማሳየት ጉዳይ ላይ ነበር። እነርሱ የአብርሃም ልጆች ነን ሲሉ እርሱ ግን የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ትሠሩ ነበር አላቸው። በዚህ ክፍል የልጅነት ምልክት የተተረጎመው በግብር (በሥራ) ነው። ምክንያቱም ለአይሁድ ብዙ ጊዜ ስም ግብርን የሚያሳይ መግለጫ ነው።

ከሰው ስሞች በላይ የእግዚአብሔር ስሞች ትክክለኛ ባሕርይውን ገላጮች ናቸው። እርሱ ለስሙ ያለው ነገር እኛ ከምንገምተው በላይ በጥንቃቄ የተሞላ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖር ሁሉ የስሙን ምንነት ማወቅ፣ መገንዘብ እጅግ የሚረዳን ነው። ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ከባርነት ቤት አውጥቶ በሲና ተራራ ላይ በሚያስፈራ ግርማና በክብር ተገልጦ ካስጠነቀቃቸው ነገር አንዱ ስሙን በምን መልክ እንደሚጠቀሙበት ነው። "የእግዚአብሔር አምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውም" (ዘፀ 20፥7)። ይህ ከአንደበታችን ጋር የተያያዘ ነው። ሰይጣን እግዚአብሔር ለስሙ ያለውን አክብሮት ያውቃል፤ በላይ በሰማይ ባሉት ዘንድ ምንም ማድረግ ባይችልም በምድር በሰዎች አንደበት ስሙ እንዲቀል እያደረገ ነው። በፍጻሜው ዘመን በአመጽ ሰው አማካኝነት ከሚደረገው ነገር አንዱ ይህ ነው።



"እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውን በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ" (ራእ 13፥6)።

ሕዝበ እስራኤል በዘመናቸው ይህን ስም በማርከስ የእግዚአብሔርን ልብ ያሳዘኑበት ጊዜ ነበር (ሕዝ 36፥20)። ዛሬ እግዚአብሔር በምድር አሕዛብ ሁሉ ፊት ስሙን ለማክበር የሚጠብቀው የእኛን የልጆቹን ጸሎት እንደ ሆነ እናውቃለን። ስለዚህ ጌታ ሆይ! ስምህን በከንቱ ከመጥራት የተነሣ በሕዝብህ መካከል ያለውን በደል ይቅር እንድትል እንድታነሣ ስምህንም እንድታከብር እለምንሃለሁ ብለን ልንጸልይ ይገባል። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ስም በመባረክ ከፍ ከፍ በማድረግ ልንቀድሰው ይገባል። ይህ መባረክ የሚለው ሀሳብ ከሞላበት ወደ ጎደለበት ይፍሰስ ማለት ነው። ይሁን እንጂ እኛ እግዚአብሔርን ከእኛ ዘንድ ሞልቶ ወደ እርሱ ይፍሰስ ማለታችን ግን አይደለም።

## መ) መንግሥትህ ትምጣ

በዚህ ዓለም የተለያዩ መንግሥታት አሉ። ሆኖም የአንዱ አገር ሕዝብ የሌላው አገር መንግሥት ይምጣ ቢል፣ ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነስቶ የአሜሪካ መንግሥት ስለሚሻለን ይምጣልን ብሎ ቢለምን፤ በሌላ ቋንቋ የኢትዮጵያ መንግሥት ይፍረስ (ይውደቅ) እንደ ማለት ነው። በመንፈሳዊ እይታ በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ዐለም ሁለት መንግሥታት አሉ። እነርሱም በአንደኛ ደረጃ የሰይጣን (የዚህ ዓለም ገዥ) ሲሆን በሁለተኛ ደግሞ መንግሥተ እኔ ነው። መንግሥተ እኔ ማለት፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ፣ በእኔ መንገድ ካልሄደ፣ የእኔ ጥቅም፣ የእኔ ክብር፣ የእኔ ምቾት፣ የእኔ ተድላ ማለት ነው። ሰይጣን በሚገዛው ዓለም ውስጥ ከእግዚአብሔር ጎን ሆነን መንግሥትህ ትምጣ እያሉ መጸለይ የሰይጣንም ሆነ የእኔነት መንግሥት ይፍረስ

(ይውደቅ) ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከሰይጣን ጋር ጠብ መጫርና ለራሳችን ማለትም ለአሮጌው ሰዋችን ስፍራ መንሳት ነው።

ሰይጣን መንግሥቱ የሚጸናለት እያንዳንዱ ሰው ሆኖ የማይሆንለትን የራሱን መንግሥት ሊያውጅ፣ ሊያቆም ሲነሣ ነው። አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት የራሳቸውን መንግሥት አወጁ፣ ከእግዚአብሔር ጥላ ከለላ ወጡ፤ በመጨረሻ በሰይጣን መንግሥት ሥር ወደቁ። የሰው መንግሥት በቀላሉ በሰይጣን የሚገረሰስ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ በሰይጣን ፊት አቅም አይኖረውም፤ ሰይጣን ከሰው ይልቅ ኀይለኛ፣ አዋቂ፣ ዘዴኛ ነው። ሰው በሰይጣን ላይ ሊሰለጥን የሚችለው በክርስቶስ ውስጥ ሲሰወር ብቻ ነው። ዛሬም የሰይጣን መንግሥት የሚሰፋው ሰው የራሱን መንግሥት ባቈመ (ባወጀ) ቁጥር ነው። በሰው ዘንድ 'እኔ' ባለበት ነገር ሁሉ፣ የሰይጣን ነገር አለ።

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6፥33 ላይ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል አለ። ይህ የሚጨመረው ነገር፣ የሚመጣው 'መንግሥተ እኔ' ን አፍርሰን የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ስንፈልግ ነው። ሆኖም 'መንግሥተ እኔ' የሚፈርሰው ጌታ ኢየሱስ እንዳለ ራስን በመካድና ዕለት ዕለት መስቀልን በመሸከም ነው (ሉቃ 9፥23-24)። ሥጋ ከክፉ መሻቱ ጋር ሲሰቀል ነው።

ብዙዎቻችን ብዙ ችግር የሚደርስብን የራሳችንን መንግሥት ለማቋቋም ስንነሣ ነው። በቤተ ክርስቲያን ባሉ የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ ሁሉ የራሳችንን መንግሥት እያቋቋምን አትንኩብን፣ አትድረሱብን ስንል ብዙ ትርምስ ይሆናል። ነገር ግን ሁላችን መንግሥታችንን ጥለን ለአንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ስንሆን፣ ሰናድር ሰላም ይሆንልናል።



አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የጸሎታችን ይዘቱ የአንተም መንግሥት ይሁን የእኔም አይነካ ዐይነት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥምር መንግሥት  አያቋቁምም። ራሱንም ለጥምር መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት አይስማማም። ታዲያ እነኝህ ከእግዚአብሔር መንግሥት በመለየት የተቋቋሙ ሁለት መንግሥታት እንዴት ይፈርሳሉ? ይኸውም፡- 'መንግሥተ እኔ' የሚፈርሰው ፈቃድን በፈቃደኝነት ለእግዚአብሔር በማስገዛት ሲሆን የሰይጣን መንግሥት ግን የሚፈርሰው በመንፈሳዊ ውጊያ ነው። የሰይጣን መንግሥት እንዲፈርስ የሰይጣን ፈቃደኝነት አይጠየቅም ምክንያቱም በመስቀሉ ላይ ተሸንፏልና ነው። ወደ ሰው ሲመጣ ግን የሰው ፈቃድ ይጠይቃል።

ሁላችንም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ተስማምተን የራሳችንን መንግሥት በራሳችን ፈቃድ ማፍረስ አለብን። ያለነው በጸጋ ዘመን ነው። እምቢ ብንል ግን መንግሥት የእግዚአብሔር ናት የሚባልበት ጊዜ ይመጣል። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በኀይሉ ሁሉን ያንበረክካል። መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች። ጊዜው ሲደርስ ዛሬ ፈቃድ የተጠየቀውንም ያንበረክካል ከዚያ በፊት ግን ሰው በፈቃዱ መንግሥተ እኔን እያፈረሰ መንግሥተ ሰማይ እንድትመጣ አጥብቆ መሻት አለበት።

መንግሥትህ ትምጣ ብሎ መጸለይ የሰይጣን መንግሥት ይፍረስ፣ ይንኮታኮት፣ ይዞታውን ይልቀቅ ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ በማቴ 12፥28 እና በሉቃ11፥20 ላይ እንዲህ አለ፡-

*"ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች"* (ማቴ 12፥28)።

*"እኔ ግን አጋንንትን የማወጣው በእግዚአብሔር ጣት ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደመጣች ዕወቁ"*

(ሉቃ 11፥20)።

የእግዚአብሔር መንግሥት ወደዚህ ዓለም መጣ ማለት አጋንንት ከሰዎች ሕይወት ተባርረው ይዞታቸውን አጡ ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ሲሰፍን ሰዎች ከአጋንንት ተላቀቁ ማለት ነው።

የአጋንንትን ይዞታ የማያፈርስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት መገኘት (ህልዎት) በሚገባ ገና አልተከሰተም ማለት ነው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት የልጁ መንግሥት ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠው ደግሞ የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው (1ዮሐ 3፥8)። የዲያብሎስን ሥራ ማፍረስ የጌታ ኢየሱስ የመገኘቱ ኢላማ ነው።

ጌታ ያስተማረው እውነተኛ ጸሎት ነው። ይህ ጸሎት ፈጽሞ ሕጸጽ (እንከን) የሌለበትም ጸሎት በመሆኑ እግዚአብሔር ሰምቶ ምላሽ ይሰጥበታል።

ሠ) ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን

የጸሎት ህላማው የሰው ፈቃድ በሰማይ እንዲከናወን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲፈጸም ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲከናወን እኛ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖር አለብን። የጸሎት ምስጢር የተመሠረተው በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ነው። በሰማይ የእግዚአብሔር ፈቃድ የተከበረ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገዛበት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲመጣ የሰይጣንን ፈቃድ ይገጫል፣ ያፈልሳል። ይህ ብቻ አይደለም፣ የእኛንም ፈቃድ ይገዛል። በመጨረሻም በፈቃዳችን ላይ የእርሱን ፈቃድ እናነግሣለን።



እግዚአብሔር ሰውን ከምድር ዐፈር ሲሠራው የራስ ሕልውና ግንዛቤ ያለው አድርጎ ነው። ስለዚህ እርሱ ወደ ሰው ሕይወት ሲመጣ የሰውን ፈቃድ ገፍቶ አንድ ነገር ማድረግ ሲችል ለሰው ሰብዕና ካለው አክብሮት የተነሣ የሰውን ፈቃድ እያከበረ ነው የሚመጣው። ይህንንም የሚያደርግበት ምክንያት ሰው በፈቃደኝነት ፈቃዱን ለእርሱ እንዲያስገዛ ነው።


እግዚአብሔር በፈቃዱ ሰውን ፈቃድ ያለው ፍጡር አድርጐ ሠራው። እግዚአብሔር ሰውን ሲሠራው ባለ ልዩ ልዩ ፍላጐት አደረገው ወይም ልዩ ልዩ ፍላጐት ያደረበት አድርጐ አበጀው። የመብላት፣ የመጠጣት፣ የወሲብ፣ የመውደድ-መወደድ፣ የመኖር፣ በሕይወት የመጠበቅ፣ የማወቅ፣ የክብር፣ የተራክቦ ... ወዘተ ፍላጐቶች ባለቤት ሆነ። እግዚአብሔር ፍላጐቶች ሲያሳድርብን ፍላጐቶቻችንም የሚረኩበትን ምንጮች አብሮ አዘጋጅቶአል፤ ለረሓብ ምግብን፣ ለጥማት ውሃን፣ ለወሲብ ተቃራኒ ፆታን ... ወዘተ አመቻችቶአል። ይሁንና ለዚሁ አጠቃቀም አግባብና ሥርዐት ደንግጎልናል፤ ይህንኑ በኅሊናችን አሳድሮአል። ለምሳሌ የሚበላ ፍሬ ያላቸው ዛፎች ያብቅልልን እንጂ ከዚህኛው ዛፍ ደግሞ አትብላ ብሏል፤ ወሲብም በጋብቻ ኪዳን ውስጥ ብቻ ታቅቧል።

የሥጋ፣ የነፍስ፣ የመንፈስ ፍላጐቶች አሉን፤ ምድራዊና ሰማያዊ ወይም ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ሊያድሩብን ይችላሉ፤ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ስንመጣ ሰማያዊ ፍላጐቶች፡- የእግዚአብሔር መንግሥትን መሻት፣ ጽድቅን መራብ፣ መፈለግ፣ ማስታረቅ ያድሩብናል።

ፈቃድ ከመስመር የወጣ ፍላጐትን የመግቻ ልጓም ነው ወይም የመልካም ፍላጐት መኮልኮያ (መቈስቈሻ) ሊሆን ይችላል። ፈቃድ ከንጹሕ ኅሊና ጋር ተጐዳኝቶ ሲሠራ መልካምና ሕያው

ነት ነው:: ፈቃዳችን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሕያው ሆኖና ነቅቶ ሊያድር፣ የሰይጣንን ፈቃድ ደግሞ ሊቃወምና ሊቋቋም ያሻዋል::

በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ የሰይጣን ፈቃድና የሰዎች ፈቃድ እንዳለ ከመጽሐፍ ቅዱስ እናስተውላለን::




የሰው ፈቃድ ከውድቀት የተነሣ ኀይለ ቢስ ወይም አቅመ ቢስ የሥጋ ፍላጐትን ለመቋቋም የማይችል ሆኖአል:: የሥጋን ፍላ ጐት ለማሸነፍና የሰይጣንን ፈቃድ ለመቋቋም የሰው ፈቃድ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ሊሞላ፣ ሊታደ ስና ሊታነጽ ይገባዋል::

ሰው ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት አለበት ስንል ነፈዝ (የማይላወስ/passive) መሆን አለበት ማለታችን አይደለም:: ይህ ፈጽሞ አግባብ አይደለም:: ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት ማለት የተኮላሸ ፈቃዳችንን ሕያውና ንቁ አድርገን የእርሱን ፈቃድ እንዲያገለግል ማድረግ ነው:: ማና ችንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማገልገል የምንችለው በነቃ እንጂ በጠወለገ ፈቃዳችን አይደለም:: ይህን ልብ ማለት ከብዙ መታለል ይጠብቀናል::



ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አገልጋይ እናደርገዋለን እንጂ እግዚአብሔርን ለፈቃዳችን አገልጋይ አናደርገውም:: ይህን ማድረጋችን ደግሞ ሞኝነት ሳይሆን ጥበበኛነት ነው:: ምክንያቱም በሮሜ 12፥2 ላይ እንደተጻፈው *"መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ"*:: መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነው ነገር ለእኛ ክቡር ነው:: የውስጥ ማንነታችን፣ እውን ሰብዕናችን የሚሻውም ይህንኑ ነው:: እነዚህ ነገሮችን የምናገኛቸው ከሌላ ስፍራ፣ በሌላ መንገድ እየመሰለን እንታለላለን እንጂ የምናገኛቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ነው:: ደግሞም ፍጹም ነው ሲል ጸጸት፣ ጉድ ለት የሌለበት ነው የሚለውን ያሳያል:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግን ስንመጣ አንጸጸትም::

ጌታ ኢየሱስ ለሞት አልፎ ሊሰጥ ባለበት ጊዜ ሲጸልይ "አባት ሆይ ብትወድ ይቺን ጽዋ ከእኔ ውሰድ" በሌላ አገላለጽ በዚች ሰዓት ውስጥ የታመቀው ክፉ ነገር እኔን ዘሎ ይለፍ፤ ይሁን እንጂ "የአንተ ፈቃድ ይሁን" አለ (ሉቃ 22፥39):: መቼም ስለ ጊዜ ስናስብ በራሱ ምንም አይደለም:: ጊዜ ትርጕም የሚኖ ረው በውስጡ በታቀፈው ነገር ነው:: በዚያ በተገኘው ጊዜ ውስጥ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ጥበበኛነት ነው:: እኛ ስንጸልይ በጸሎታችን ውስጥ አንዱና ትልቁ ነገር የእግዚ አብሔር ፈቃድ ነው:: በጸሎታችን ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ መኖሩ ጸሎታችንን ውብ (ልዩ) ያደርገዋል:: ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችን እግዚአብሔር የእኛን ፈቃድ እንዲፈጽም የሚ ባበልበት ይሆናል:: ይህ ልክ አይደለም:: በጸሎታችን ፈቃዱ እንጂ ፈቃዳችን መፈጸም የለበትም:: በእኛ ጸሎት የእግዚአ ብሔር ፈቃድ በሕይወታችን ቢፈጸም ለስሙ ክብር ለእኛም ደግሞ መልካም ነው:: ለእግዚአብሔር ፈቃድ እጅ ብንሰጥ

ወይም ሁሉም ነገር እንደ ጌታ ፈቃድ ብንል እኛ ምንም አይ ጎድልብንም:: ከዚህ ይልቅ ሁሉም ነገር ለእኔ ፈቃድ ስንል ሁሉም ይጎድልብናል:: ለራስም አዋቂ መሆንና አለመታመንም ነው::

የእኛ ፈቃድ አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እሺ የሚል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እሺ ከማለት የሚያፈገፍግ ነው:: ስለዚህ ጌታ ችን ያስተማረውን ጸሎት ከልብ ሆነን በደንብ ልንጸልየው ይገባናል::

ረ) የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን

ይህ ጸሎት በሌላ አገላለጽ እኛ ምድራዊ ነን፣ በየዕለቱ እንጀራ የሚያስፈልገው ሰውነት ውስጥ አለን ስለዚህ የዕለት እንጀራ ችንን ስጠን የሚለውን ያሳያል፤ እንጀራ ምድራዊ ፍላጎታችንን ይወክላል:: ይሁን እንጂ ይህንን ፍላጎት ሊያሟላ (ሊሰጥ) የሚ ችል እግዚአብሔር ነው:: ይህንንም የሚያደርግልን እርሱ በባሕ ሪው ለሰው ልጆች በጎና አሳቢ ስለሆነ ነው:: በዘፍጥረት ምዕ ራፍ 1 እና 2 ውስጥ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት በስድስቱ ቀን የፈጠራ ጊዜያት ውስጥ አየ ሩን፣ ጸሓይን፣ ጨረቃን፣ ውሃን፣ መሬትን፣ ዕፀዋትን፣ እንስ ሳትን ... ወዘተ አዘጋጀለት፤ ከዚያም በኋላ ሰውን ፈጠረና በአ ዘጋጀለት ስፍራ በኤደን ገነት አስቀመጠው:: ይህ እግዚአብ ሔር በባሕሪው ለሰው ቸር መሆኑን ያሳያል:: እርሱ ለሰው ያውቅለታል:: በዚህ መነጽር ይህን እውነታ ስንመለከት እኛ እግ ዚአብሔርን ለምንነ ከቸርነቱ እንቀበላለን እንጂ ቸር አናደር ገውም:: ስለዚህ እርሱ ቸር ሰጪ ስለ ሆነ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ብለን እንለምናለን:: እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ ሲጓዙ በየዕለቱ መናን ከሰማይ አወረደላቸው (ዘፀ 16፥4-21) ልክ እንዲሁ ዛሬም ቢሆን ለየዕለቱ የሚያስፈል



ግንን ነገር የሚሰጠን (የሚያዘጋጅልን) እግዚአብሔር ነው:: ይሁን እንጂ በሰጠን ነገር ላይ እንድንታመንና እንድንደገፍ ግን አይ ፈልግም:: በሰጭው ላይ ሳይሆን በስጦታው ላይ መደገፍ መን ፈሳዊ ችግር ውስጥ ይከታል:: ብዙ ጊዜ ግን ስንታይ ትግላች ንና ጥረታችን የእኛ መንግሥት እንዲሰፋና እንጀራችን እን ዲሰባሰብ ነው:: ይህ ነገር የእስራኤልንም ነገሥታት አስቸግሯ ቸዋል:: እግዚአብሔር የእስራኤልን ነገሥታት ከታች አንስቶ በዙፋን ላይ ካስቀመጣቸው በኋላ፣ መንግሥታቸው ሲደላደል ሁሉን ሲያገኙ እግዚአብሔርን ይተዋሉ ከዚህም የተነሣ ፍጻ ሜያቸው የተበላሸ ይሆናል:: እግዚአብሔር ሁሉን ከምርልኝ የሚል ልመናና ጸሎት እንዲኖረን አይፈልግም:: ይህ ነፍስን የሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ነው (1ጴጥ 2፥11)::

በተጨማሪም ይህ "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" የሚለው ጸሎት ለግል የሚጸለይ ብቻ ሆኖ አይደለም የተቀመጠው፤ ምክ ንያቱም እንዲህ ቢሆን ኖሮ "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" የሚለው ሀረፍተ ነገር በብዙ ቍጥር ባልተቀመጠ ነበር:: ስለ ዚህ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን ብለን ስንጸልይ ለእኔም ስጥ፣ ለእርሱም ስጠው፣ ለእርሷም ስጣት እንደማለት ነው:: በአጠቃላይ ለጋራ የሚጸለይ ጸሎት ነው:: ሌሎች አጥተው እኛ እንድናገኝ አይደለም:: ስናገኝም አቤት! እግዚአብሔር እኔን ብቻ ነው የሚወደኝ እንዳንል በዚህ ውስጥ ለሌሎችም መለ መንን ያስተምረናል:: ነገር ግን ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን የቤታችን ጣዖት፣ የግል ጣዖት ልናደርገው እንፈልጋለን:: እርሱ ግን የሁላችን አባት ነው::

ስለ ዕለት እንጀራ ስናስብ ከዚህ ጋር አብረን መገንዘብ ያለብን ነገር አለ:: ይኸውም ስለ እንጀራ ጉዳይ ሲነሳ፡- ሰይጣን እኔም ሰጭ ነኝ ማለቱ ነው:: ይሁን እንጂ ከጨለማ ልጆች ሕይወት በተግባር እንደታየው የእርሱ ሰጭነት ወድቀው እስከሰገዱለት

ድረስ ነው:: እኛም እግዚአብሔር ሰጫችን መሆኑን ረስተን ለእንጀራ ስንል ለሌላው (ለጣዖት) እየሰገድን ካለ ያን ስግደት በተዘዋዋሪ ተቀባዩ የዚህ ዓለም ገዥ ይሆናል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው:: አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ በዚያን ጊዜ ፈታኝ ቀርቦ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው::"

ይህ ፈተና "በመኖር ጥያቄ" ላይ የተመሠረተ ነበር:: በመጨረሻም "እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ በመውሰድ የያለምን መንግሥታት ሁሉ ክብር አሳየና ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ" አለው:: የሰይጣን ዓለም ብቸኛ የክብር ምንጭ ሆኖ እንድትታይለት ይፈልጋል:: የዚህ ዓለም ገዥ በመሆኑና ከእግዚአብሔር ተለይተው ያሉትን የዓለምን መንግሥታት ክብር በራሱ አገዛዝ ሥር በማድረጉም:- አሳይቶት ወድቀህ ብትሰግድልኝ "ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ" ለማለት ችሎአል:: የሚሰጠው እርሱ አምላክ የሚያደርገው ካገኘ ብቻ ነው:: በተረፈ ሰይጣን ቸርነት አያውቅም:: የእርሱ የበላይነት በማይረጋገጥበት ቦታ ፈጽሞ ከእርሱ ስጦታ ማግኘት አይቻልም፤ እግዚአብሔር ግን ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል:: በሰይጣን መመሪያ አምልኮና ስግደት ከማግኘት ጋር የተያያዘ ነው:: ሰይጣን፣ እግዚአብሔር የሚመለከው ጉቦ እየሰጠ ነው ባይ ነው:: ኢየሱስም "ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል" ብሎ እግዚአብሔር ስላልሰጠ የማይመለክ፣ ስለሰጠ ደግሞ የሚመለክ አይደለም በማለት አምልኮት ከእግዚአብሔር የማግኘትን ነገር በማገናዘብ ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ ገለጠ::



ዛሬም ሰይጣን አንዳንድ ነገሮችን ያሳየናል፤ በመጨረሻም በውስጣችን ለነገሩ ጕጕት፣ መሻት ሲነሳሳብን ወድቀህ ብትሰግድልኝ እሰጥሃለሁ ይላል:: ከዚህም የተነሣ ብዙ ወንድሞችና እህቶች ከእውነት መንገድ እየወጡ እንጀራ ለማግኘት ሲሉ ለክፉው 'ይሰግዳሉ':: ጌታ፣ በውኑ በድንገት ወደ መቅደሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ቢገባ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ያገኛት ይሆን? እንጀራን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው ብሎ ከመጠበቅ እጅ ነስቶና 'ሰግዶ' ከሰይጣን ከመቀበል እንጠንቀቅ! ሥጋ ብዙ በልቶ ነፍስ ከምትከሳ ከንጽህና ጋር ጾም ማደር ይሻላልና ቈራጥነቱን ይስጠን::

## ሰ) እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6፥9-15 ባለው ክፍል ውስጥ ጸሓፊው ስለ ይቅርታ ሁለት ጊዜ ይናገራል:: ጸሓፊው በዚህ ክፍል ውስጥ የሚያወራው (የሚያካትተው) እርስ በርሱ የተያያዘና አንዱም በሌላው ላይ የሚደገፍ ነው:: ሰዎች ሲበድሉን ይቅር ማለት ያለብን (6፥12) እኛ ራሳችን እግዚአብሔርን በድለን ሳለ ይቅርታን ስለተቀበልን ነው:: (6፥14-15) ስለዚህ ይቅርታ እንደ ተቀበሉ ሰዎች መኖር እንዳለብን ይህ ክፍል ያስተምረናል:: ይቅርታ የሚያደርጉ ይቅር የተባሉ ናቸው ስለ ይቅርታም የሚያውቁ ይቅር መባልን ያወቁ ናቸው:: በሌላ ቦታ ሌላው የአዲስ ኪዳን ጸሓፊ ስለ ይቅርታ ሲናገር እንዲህ ይላል "እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ሩኅሩሆች ሁኑ እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ" ኤፌ 4፥32 እንደ ገናም በቈላስይስ ላይ "ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፍበት ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ" ይላል:: አሁንም ሐዋርያው የሚያስተምረን እርስ

በርሳችን ስንኖር ይቅር እንደተባሉ ሰዎች መኖር እንዳለብን ነው።

ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የምንማረው ሁለት መሠረታዊ ነገሮች አሉ። አንደኛው በቀጥታ የተጠቀሰ ሲሆን ሁለተኛው ግን ንባቦቹን በሚገባ በማጤን የምናገኘው ነው። እነዚህ ክፍሎች በቀጥታ የሚያስተምሩን ስለ ይቅርታ ነው። ሌላው ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የምንማረው በሁለት ወንድሞች መካከል መበዳደል ሊኖር ወይም አንዱ ወንድም ሌላውን ወንድም ሊበድለው የሚችል መሆኑን ነው።

ሸ) ከክፉው አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን

ይህ ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልልህም ሲል በዮሐ 17፥15 የጸለየውን ጸሎት ያስታውሰናል። ይህ ዓለም ክፉው ያለበትና የሚሠራበት ነው። በዚህ ዓለም የመንግሥተ ሰማይ ሰው ሆነን የመንግሥቱን ጸሎት ለመጸለይና የመንግሥቱን ሥራ ለመሥራት የምንችለው በሰማዩ መንግሥት ጥበቃ ሥር ሆነን ነው። አለበለዚያ በእኛ ላይ የሚነሳ ክፉ አለ። እርሱ ደግሞ በእኛ ላይ ቢነሣ ብርቱ ነው። ፈተናውንም በራሳችን አቅም መቋቋምና ማምለጥ አንችልም። ስለዚህ "ከክፉው አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን" ብለን እንጸልያለን። እኛ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጣ ፈተና አለብን። ይህ ጸሎት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ትድግና እንድናገኝ የሚረዳ ጸሎት ነው።

ስለ ፈተና ሲነሣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ልንፈተን እንችላለን። 1ጴጥ 1፥5 ፈተናዎቻችንም በየጊዜው ልዩ ልዩ ቀለም ሊኖራቸው ይችላል። ይሁን እንጂ ሐዋርያው እንዳለ ለጥቂት ጊዜ ነው። ጌታ መውጫውን ያዘጋጃል። ከዚህ ውጭ ግን ፈታኙ ሊፈትነን ወደ ፈተናም ሊያስገባን በአጠገባችን አለ። እኛም



ጌታችን ባለው መሠረት ወደ ፈተና እንዳንገባ ተግተን መጸለይ አለብን (ማቴ 26፥41)። ሰይጣን የሚፈትነን እምነታችንን ለማጥፋትና ከእግዚአብሔር ጋር እንድንቈራረጥ ነው።

*"ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ"* (ሉቃ 22፥31-32)።

ምስጋና - ለመንግሥቱ

ቀ) "መንግሥት የአንተ ናትና ኀይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን"

የእግዚአብሔር ስም እንዲቀደስ መንግሥቱም ወደ ምድር እንድትመጣና ፈቃዱ በምድር እንድትከናወን የሚጸልይ ማንኛውም አማኝ እነኚህን ጸሎቶች ተግቶ ሲጸልይ ሰይጣን ችግር ሊያስነሣበት ይችላል። ሆኖም መንግሥት የእግዚአብሔር እንጂ የእርሱ ስላልሆነ፣ ኀይል የእግዚአብሔር እንጂ የእርሱ ስላልሆነ አንዳች ሊያደርግበት ሥልጣኑም ሆነ ችሎታው የለውም። በእግዚአብሔር መንግሥታዊ ሥልጣንና ኀይል ተጠብቀን በዚህ በጨለማ ዓለም ይህን ጸሎት እንጸልያለን፤ ለስሙ መቀደስና ለፈቃዱ መከናወን እንጋደላለን። ክብርም ለዘለዓለም መንግሥትና ኀይል የእርሱ ብቻ ለሆነው ለአባታችንና ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው "አሜን"።

(3) ለጸሎት መልስ እንቅፋቶች

ሀ) በክፉ መለመን

መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች መለመን እንዳለባቸው ሲናገር በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 7፥7-8 ባለው ክፍል ውስጥ እንዲህ ይላል። "ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያውን

እንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል:: የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልገውም ያገኛል መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል ሲል እንዲሁም በያዕቆብ ምዕራፍ 4፥3 ላይ ደግሞ "በምቾቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም" በማለት ሁለተኛውን ነጥብ ይናገራል:: ክርስቲያኖች የሚያስፈልጋቸውን ነገር እግዚአብሔርን መለመን ይችላሉ:: ነገር ግን ከሚያስፈልጋቸው (ከመጠን) በላይ የሥጋቸውን ምኞት ለመፈጸም መለመን የለባቸውም:: ማንኛውም አማኝ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የጸሎት ሰው ሆኖ ለመጸለይ ጥቂት ዐመታት ስለ ጸሎት መማር አለበት::

'በክፉ' መለመን ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት በሥጋዊ ምኞት ላይ ተመርኩዘን የሥጋዊ ደስታ የሚሰጠንን መለመን ወይም ከመጠንና ከሚያስፈልገን ነገር በላይ በራስ ወዳድነት መጠየቅ ማለት ነው:: ለምሳሌ አንድ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖርና ከዚያ ከሚያስፈልገን ነገር በላይ ተስገብግበን በምኞታችን ላይ ተመርኩዘን ሌላው ጉድሎበት፣ አጥቶና ገርጥቶም እንኳ ቢሆን፣ ለእኛ ሥጋዊ ደስታ ለማግኘት ስንል ብንለምን ይህ በክፉ መለመን ነው:: የሚያስፈልገን ብዙ ከሆነ እግዚአብሔር በሚያስፈልገን ልክ እንዲሰጠን መለመን እንችላለን:: ነገር ግን ከሚያስፈልገን በላይ መለመን የለብንም እንዲህ ዐይነት ጸሎት እግዚአብሔር ደስ አያሰኘውም ልመናችን በሚያስፈልገን ነገር ወይም መጠን መለካት አለበት:: ያለ ጥንቃቄ መቅረብ የለብንም:: አላግባብ መለመን እንደ አራት ዓመት ህጻን ልጅ በሰማይ ያለችውን ጨረቃ አውርደህ ስጠኝ ወይም በሰማይ ያሉ ከዋክብትን ሸምጥጠህ አስታቅፈኝ ብሎ እንደመለመን ነው::

ለ) በደልን ከልብ አለማራቅ

ክርስቲያኖች ስህተት የሌለበት ልመና ልንለምን እንችላለን::



ነገር ግን ጸሎታችን ሳይሰማ ይችላል፤ የዚህ ምክንያቱ የጸሎታችን መልስ የሚከለክል ኀጢአት በልባችን ኖሮ ሊሆን ይችላል:: አንድ ሰው በልቡ የሚያውቀውን ኀጢአት ቢኖርና ልቡ ከዚያ ኃጢአት ጋር ከተባበቀ አይሰማም:: ዳዊት በመዝሙር 66፥18 ላይ "በልቤስ በደልን ዐይቼ ቢሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር" ይላል:: በደልን በልብ ማየት ማለት ያልተናዘዙትን፣ ሊተዉትም የማይፈልጉትን ኀጢአት በልብ ሰውሮ መያዝ ማለት ነው:: አንድ ሰው ትልቅ ድካም ቢኖርበት እስከተናዘዘ ድረስ እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል፤ ኀጢአቱን እንዲያሸንፍም ያስችለዋል:: ነገር ግን በልቡ የሚያውቀው ኀጢአት ቢኖርና ያንንም ገና እየተወዳጀው ቢሆን በውጫዊ ባሕርይው ከሚታየው ድካም በላይ ነው:: በልቡ ውስጥ ያለው ኀጢአትን መውደድ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፥15 ላይ የሚናገረው ከዚህ የተለየ ነው:: ይህ ሰው የሚያደርገው ነገር የሚጠላውን እንደ ሆነ ይናገራል:: ወድቋል ነገር ግን ይህንን ውድቀት ይጠላዋል:: በልቡ ያለውን ኀጢአት (በደል) የሚወድ ሰው፣ ኀጢአቱን ያልተወ ሰው ነው:: ጌታ የእንደዚህ ዐይነቱን ሰው ጸሎት አይሰማም ምክንያቱም ኀጢአቱ ጸሎቱ እንዳይመለስ ከልክሎበታል:: አጓጉል ፈቃዱ በጸሎቱ ፊት ተጋርጦበታልና ነው::

ስለዚህ በልባችን ውስጥ ያለን በደል ማስወገድ አስፈላጊ ነገር ነው:: ማንኛውም ዐይነት በደል ይኑርብን በመናዘዝ ኀጢአታችን ከክርስቶስ ኢየሱስ ደም በታች መሸፈን አለበት:: አንድ ሰው ኀጢአትን ድል የመንሳቱ ምስጢር ቀላል ባይሆንም በደልን ግን ከልቡ መውደድ የለበትም:: እግዚአብሔር ድካማችንን ይቅር ይላል ነገር ግን በልባችን በደልን እንድንወደ አይፈቅድም:: ልባችን ንጹሕ እስኪሆን ድረስ ማንኛውንም ኀጢአት እንዲጠላና አንድ የሚወደው በደል እስከማይኖር ድረስ

መስተካከል አለበት። ኀጢአትን በልባችን እየወደድን መጸለይ ከንቱ ነው። ምክንያቱም ጌታ አይሰማንምና።

በመጽሐፈ ምሳሌ 28፥13 ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን "ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል" ኀጢአትን መናዘዝና መተው ያስፈልጋል። ከተናዘዝን በኋላ ግን ጌታ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። 1ዮሐ 1-9 አንድ ሰው ወደ ጌታ በመምጣት "ልቤ የወደደውን ለመተው ያቃተኝ ኀጢአት ይኸውና አሁን ግን ለመተው ፈቃደኛ ነኝና ይቅር ብለህ ነጻ እንድታወጣኝ እለምንሃለሁ" ማለት አለበት። በፊቱ በእውነት ከተናዘዝን ጌታ ኀጢአታችንን ያስወግደዋል፤ ከዚያም ጸሎታችን ይሰማል። ይህን ቸል ልንለው የሚገባ አይደለም።

ሐ) መታከት

ጸሎት እስከ አሁን ከተነጋገርነው ነገር ጋር የሚቃረን የሚመስል ሌላ ገጽታ አለው። ይሁን እንጂ እውነት የሆነ ነገር ነው። በሉቃስ 18፥1-8 ባለው ክፍል ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ መጸለይ እንዲችሉ በምሳሌ ሲያስተምራቸው እንመለከታለን። ዛሬም ጌታ ከዚህ ክፍል የሚያስተምረን በአንዳንድ የጸሎት ርእሶች ላይ መልስ እስኪያገኝባቸው ድረስ ሳይቋረጥ መጸለይ እንዳለበት ነው። ይህ የእምነት ማነስ ምልክት አይደለም ይልቁንም ሌላኛው የእምነት ገጽታ ነው እንጂ። እንዲህ ህይነት ጸሎት ፈጽሞ ከማርቆስ 11 ጋር አይቃረንም። ማርቆስ 11 የሚለው የለመንነውን እንዳገኘን እስከምናምን ድረስ መጸለይ አለብን ሲሆን፣ ሉቃስ 18 ደግሞ ሁል ጊዜ ሳንታክት መጸለይ እንዳለብን ይነግረናል። ብዙ ጸሎቶቻችን ከልብ ያልሆኑ ስለሆኑም ወዲያውኑ



ይረሳሉ። እንደዚህ ያሉትን ከልብ ያልሆኑትን ጸሎቶችን እግዚአብሔር ይሰማናል ብለን እንዴት መጠበቅ እንችላለን? እኛ ራሳችን ረስተን እግዚአብሔር እንዲያስታውሳቸው እንፈልጋለን።

ደግሞም ጸሎት ልመና ብቻም አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ የመንፈስ ተራክቦ ነው። በዚህም ውስጥ ኀይልና ብርሃን ወደ እኛ ይወርዳል። ወዳጅነትና ተወዳጅነትም እየታነጸ ይሄዳል።

መ) ይቅር አለማለት

ይቅር አለማለት ጸሎታችን እንዲከለከል የሚያደርግ የመንፈሳዊ ሕይወት ልምላሜ ጠር ነው፤ ስለዚህም ነው ይቅር ተባባሉ የሚለውን ትዕዛዝ በአዲስ ኪዳን ተደጋግሞ የምናገኘው። (ስለ ይቅርታ በሚቀጥለው ክፍል ሰፋ ባለ መልኩ ቀርቧል)።

## 2. ኅብረት ... አንድነትን መጠበቅና ማራመድ

የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ አንዱ ተግባሩ የመንፈስን አንድነት መጠበቅና ማራመድ ነው።

### 1) ኅብረት

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር ሰውን "በመልኩና በአምሳሉ" ፈጥሮአል (ዘፍ 1፥26-27)። በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠር ማለት ምን ማለት ነው ለሚለው ጥያቄ ዝርዝር መልስ መስጠት አሁን ቦታው ባይሆንም፣ ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጥሮአል ሲባል አንዱ ገጽታ እግዚአብሔር "ኅብረ ህላዌ" (ኅብረ አምላክ) እንደ ሆነ ሁሉ ሰውም "ኅብረ ህላዌ" ነው (ኅብረ ሰብ) ማለት ነው። "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" (ዘፍ 2፥18) ያለው እርሱ

ነውና:: ግለኝነት ኑሮ ለሰው አልተፈቀደም:: መልክ መለኮት
በመሆናችን ማኅበራዊያን ነን:: "ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉአት
ግዙአትም" (ዘፍ 1÷28) የሚለው ትእዛዝ ከአፈጣጠራችን ጋር
የሚስማማ እንጂ የሚቃረን አይደለም:: ትእዛዙ ኅብረትንና አን
ድነትን ይሻል:: ሰው ብቻውን ሊባዛ፣ ምድርንም ሊሞላና ሊገዛ
አይችልም:: ከመሰል ፍጡሩ ጋር ካልተባበረ ኀላፊነቱንም ሊወጣ
አይችልም:: ይሁን እንጂ ኀጢአት ወደ ዓለም በገባ ጊዜ ይህ
ታላቅ ኅብረት ተበላሸ:: በዚህም ምክንያት በሰዎች መካከል
አገርጋሪነት፣ ጠላትነት ሰፈነ:: ሰው የተፈጠረበትም ዐላማ ተለ
ውጦ ባላጋራነት ነገሠ:: የሰው ልጅ እርስ በርሱ ጠላት ሆኖ
ዝንተ ዓለሙን እንዲኖር ግን ጌታ አልወደደም:: ይህን የጠላት
ነት ግድግዳ ያፈርስና በምትኩም ሰላምን ያቆም ዘንድ አንድ
ልጁን ላከ:: ልጁም "የሰላም አለቃ" ነበረ (ኢሳ9÷6):: ይህ አጭር
ጽሑፍ የሚያተኩረው በኅብረት አስፈላጊነት ላይ ሲሆን ለዚ
ህም ምክንያቶች ቀርበዋል::

ኅብረት የእግዚአብሔር ሀሳቤ ነጸብራቅ ነው:: የክርስቲያኖች
ኅብረት ምሳሌው ኅብረተ ሥላሴ ነው:: የኅብረትን ጽንሰ ሀሳብ
የፈጠሩት ሰዎች አይደሉም:: እግዚአብሔር ኅቡረ አምላክ በመ
ሆኑ የኅብረትን ምስጢርና አስፈላጊነት አስተማረን:: የኅብረታ
ችን መሠረቱ፦ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: በሥላሴ
አካልነት መካከል ያለው ኅብረት ምሳሌያችን ብቻ ሳይሆን
መመሪያችን ነው:: በመሆኑም በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ
ግለኝነት ስፍራ የለውም:: ግለኝነትን ለመናኘት መነሣት የእግ
ዚአብሔርን ሀሳማ መቃረን ይሆናል:: ይህ ደግሞ ትልቅ ጥፋት
ነው:: የእግዚአብሔር ሀሳቤ ብቻ ሳይሆን የፍጥረትና ታሪክም
የሚያስረዳን በጌታ ዘንድ ኅብረት ጽኑ ቦታ ያለው መሆኑን
ነው:: በፍጥረትና በድነት ሥራ ውስጥ ሦስቱም አካላት በአ
ንድ ዐሳብ፣ በአንድ ዐላማና በአንድ ፈቃድ ተባብረው በአንድ



ነት ይሠሩ ነበር:: እንግዲህ ኅብረትና አንድነት የሥላሴ
አካላት መለያ ከሆነ እኛ ከዚህ ምን እንማራለን የሚለውን
ጥያቄ ዘወትር እንድናነሣ እንገደዳለን:: ሰውን ከሰው፣ ወገንን
ከወገን፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለያይቶ የነበረው የጥል ግድግዳ በክ
ርስቶስ ተወግዷል (ኤፌ 2÷14) አሁን ጥል ተሽሮ ሰላም ወር
ዷል (ኤፌ 2÷15):: በክርስቶስ የሆንን ሁሉ የአንድ አገር ዜጐች
ሆነናል(ኤፌ 2÷19):: ከዚህ በኋላ የሚቀረው የጌታ ቅዱስ ቤተ
መቅደስ ለመሆን በአንድነት እየተሠራ ወደ ክርስቶስ ፍጹም
ሙላት ማደግ ነው (ኤፌ 2÷21)::

ኅብረት ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት አስፈላጊ ነው:: በመጽ
ሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ከተመሰለችባቸው ተምሳሌ
ቶች ውስጥ አንዱ "አካል" ነው:: አካል በባሕሪው አንድ ሆኖ
ሳለ፣ በአሠራሩ ግን ልዩ ልዩ ክፍሎች ወይም ብልቶች አሉት
(1ቆሮ 12÷12):: የአንዱ አካል ክፍል ወይም ብልት ህልውና
በሌለው ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ የአንዱ አካል ክፍል
(ብልት) መኖር ለሌላው ዋስትና ነው:: ስለዚህ አንዱ ብልት
ወይም የአካል ክፍል ሌላውን አታስፈልገኝም ሊለው ከቶ አይ
ችልም (1ቆሮ12÷21):: ምክንያቱም በአካል ክፍሎች (ብልቶች)
መካከል የእርስ በርስ ኅብረትና አንድነት እንዲኖር እግዚአብ
ሔር ወስኖአል (1ቆሮ 12÷18):: ሥጋዊ አካል በሕይወት ሊኖር
የሚችለው የአካሉ ክፍሎች በሙሉ ተባብረውና ተስማምተው
የተሰጣቸውን ሥራ በአንድነት ሲያከናውኑ ብቻ ነው:: ልክ እን
ዲሁም መንፈሳዊም አካል በሕይወት ሊኖር የሚችለው የአካሉ
ክፍሎች በሙሉ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች
አማካይነት አካሉን በኅብረት ሲያገለግሉ ብቻ ነው:: እንደ
እውነቱ ከሆነ ለግል ጥቅም የተሰጠ አንድም የጸጋ ስጦታ
የለም:: ስጦታዎች በሙሉ የተሰጡት "ለጋራ ጥቅም" (1ቆሮ
12÷7) ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር "መንፈሳዊ ስጦታዎ

ችን ለማግኘት የምትሹ በመሆናችሁ፣ ቤተ ክርስቲያን የምት ታነጽበትን ስጦታዎች ለመግኘት ይበልጥ ፈልጉ" (1ቆሮ14÷12) ይላል:: ይህ የአካልና የጸጋ ስጦታዎች ምሳሌ የሚያሳየን መን ፈሳዊ ዕድገት ሊኖር የሚችለው ኅብረት ሲኖር ብቻ መሆኑን ነው:: መንፈሳዊ ኅብረት ከሌለ መንፈሳዊ ዕደገትም የለም:: እንዲያውም ከኅብረት ውጭ ዕድገት ሊታሰብ አይችልም:: ለሌላው ሳልኖር ራሴን በራሴ እኖራለሁ የሚል የአካል ክፍል (ብልት) የሌላውን ዕድሜ ብቻ ሳይሆን የኋላ ኋላ የራሱ ንም ዕድሜ ያሳጥራል:: ጌታ በወሰነው የአካልና የብልቶች ግን ኙነት ውስጥ "ግለኝነት" (ለራስ መኖር) ስፍራ የለውም::

ኅብረት የተሻለ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ነው:: ቀደም ባለው ሥርዐተ ማኅበር ውስጥ "ኅብረት ኀይል ነው" የሚል መፈክር እንደ ነበር ትዝ ይለኛል:: ይህ አባባል እውነትነት አለው:: መንፈሳዊ አገልግሎታችን የምንፈልገውን ዐይነት ውጤት ሊያመጣ የሚችለው ሁላችንም የተሰጠንን ነገር ሁሉ ይዘን በኅ ብረት ስንወጣና እንደ አንድ ሰው ሆነን ስንሰለፍ ነው:: ታዲያ እንዲህ ዐይነቱ ኅብረት የሰይጣንን ዕድሜ ስለሚያሳጥር ሰይ ጣን በብርቱ ይቃወመናል:: በመሠረቱ ሰይጣን "መተባበርንና አንድ መሆንን" ከቶ አይፈቅድም:: ለምሳሌ ቃሉ በግልጥ ሊሰ በክና ሰዎችም ድነው የጨለማ ግዛት ሊፈርስ የሚችለው ሰባ ኪዎች ሲኖሩ ነው:: ሰባኪዎች የጌታን ቃል በግልጥና በኀይል ሊሰብኩ የሚችሉት እነርሱን በጸሎትም ሆነ በገንዘብ የሚደ ግፉ ሰዎች ሲኖሩ ነው:: እነዚህ ሁሉ ሊኖሩ የሚችሉት በጌታ ነው:: ይህ እንግዲህ የኅብረት ሰንሰለት ነው:: ሰንሰለቱ መገ ናኛ (ተቆላልፎና ተያይዞ ማሰሪያ) ከሌለው የተፈለገውን ሥራ ሊያከናውን አይችልም:: አንዱ ያስተምር እንደ ሆነ ሌላው ይሰጣል፤ አንዱ ይጸልይ እንደ ሆነ ሌላው ይዘምራል፤ አንዱ ያስተምር እንደ ሆነ ሌላው ያገለግላል፤ አንዱ ይመራ እንደሆነ



ሌላው ይመክራል (ሮሜ 12÷4-8):: በዚህ ዐይነት የተባበሩ መንፈሳውያን የላቀና የተሻለ ሥራ ያከናውናሉ:: ኅብረት ካለ ኀይል አለና::

*"ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግ ሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአ ብሔር ነው"* (1ቆሮ 12÷4-6)::

ኅብረት የተጠራንበትን ዐላማ እውን ለማድረግ አስፈላጊ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ረገድ ሲናገር "በሰላም ማሰሪያ የመ ንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ:: በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ" (ኤፌ4÷3-4) ይለናል:: በዚህ ምድር የክርስቶስ ወኪሎች እንድንሆን እግዚአብሔር መርጦናል:: ይህ ውክልና ታላቅ ኀላ ፊነት በመሆኑ ታላቅ ኅብረትን ይፈልጋል:: ጳውሎስ እንደሚ ለው ከሆነ እንዲህ ዐይነት ኅብረት እንዲያው ዝም ብሎ የሚከሰት ነገር አይደለም:: ብርቱ ትጋትን ይሻል:: የኅብረት ፀር የሆኑ ነገሮች ሁሉ መወገድ ይኖርባቸዋል:: በክርስቶስ ሞት የተገኘውን አንድነት (ኤፌ 2÷14-22) በትጋት መጠበቅ አለ ብን:: ቋንቋ፣ ዘር፣ ቤተ ሰብ ወይም ደግሞ ዕድሜ፣ ሀብት፣ ትምህርት ሊለያዩንና ሊከፋፍሉን አይገባም:: እኛ የተጠራነው አንድ አካል ሆነን የክርስቶስ ሰላም በልባችን እንዲነግሥ ነው (ቄላ 3÷15):: የአንድነትን መንፈስ መጠበቅ (ሮሜ 15÷5) የክ ርስቲያኖች ሁሉ ኀላፊነት ነው:: ቤተ ክርስቲያን የሰላም እንጂ የሁከት መናኸሪያ መሆን የለባትም:: ሰላም ሲባል ከግጭትና ከጦርነት የጸዳ ቀጣና ማለት ብቻ አይደለም:: እንዲህ የሚመ ስለን ግን ጥቂቶች አይደለንም:: "ሻሎም" የሚለው የዕብራይ ስጡ ቃል ከውጊያና ከፍልሚያ ማረፍን ብቻ ሳይሆን ብልጥግ ናን፣ ጤንነትን፣ ልምላሜን፣ ደኅንነትን፣ ፍትሐዊነትንና ስሙ

ምንትን ሁሉ ያካትታል። የተጠራነው የሰላም ልኡካን እንድን
ሆን ነው። ጳውሎስ እንደሚለው እግዚአብሔር "የማስታረቅን አገ
ልግሎት ሰጥቶናል" (2ቆሮ5÷18-19)። ማለትም ሰላም አውራጆች
አድርጎናል። "ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የም
ንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ" (ሮሜ 14÷19)።

በመጨረሻም፣ ኅብረት የመጻኢው ዘመን ሕይወት ነጸብራቅ
ነው። ባለ ራእዩ ዮሐንስ፣ በጉ በሰባት ማኅተም የታሸገውን ጥቅ
ልል መጽሐፍ ሊፈታ የቻለበትን ምክንያት ሲናገር "ምክንያ
ቱም ታርደሃል፣ በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን
ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል" (5÷9)
ይላል። በወዲያኛው ዓለም በቋንቋ፣ በዘርና በጎሳ ላይ የተመሠ
ረተ ልዩነት የለም። የሰላሙ አለቃ በፍጹም ሰላሙ በሚገዛበት
አጽናፈ ዓለም ልዩነትና ጠርነት የለም። መቧደንም ሆነ ጎራ
ለይቶ መፋለም የሥጋና የሰይጣን ሥራዎች ናቸው (1ቆሮ 3÷
3-4)። ልባችን በላይ በሰማይ ተተክሎ ከሆነ የሰማዩን ሕይወት
እንኑር። የሰማዩ ሰላም፣ ኅብረትና አንድነት ይግዛን።

እንግዲህ ኅብረት አስፈላጊ የሆነው ከላይ በተጠቀሱት ሀበይት
ምክንያቶች ከሆነ፣ እኛ ሕዝበ እግዚአብሔር ለዚህ እውነት
መተግበር ምን ያህል ቀናኢያን ነን? የሚለው ጥያቄ ከዚህ ላይ
ይነሣል። ኅብረት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መለያና መታወ
ቂያ መሆን አለበት። ያለ ኅብረት ጌታ የሰጠንን ተልእኮ
በሚገባ መፈጸም አንችልም። ጌታ ኅብረተ ሰላሙን ያልብሰን፣
ያጐናጽፈን።

ሀ) በክርስቶስ የተገኘ አንድነት

ቤተ ክርስቲያን አምልኮ እንዳላት ሁሉ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከዘ
ርና ከቀለም ያለፈም ሕብረትና አንድነት አላት። ይህም አንድ
ነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለያየ ቦታ፣ በልዩ ልዩ መንገድ



ተገልጧል። ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል በ1ቆሮ 12:12-13
እና በሮሜ 12:4 ላይ ጳውሎስ በአንድ አካል ላይ እንዳሉ የሰው
ብልቶች አድርጎ ሲናገር ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ የአንድ
ሕንጻ ጡቦች ወይንም ሕንጻውን ለመገንባት የተሰበሰቡ ሕያዋን
ድንጋዮች አድርጎ ተምሳሊታዊ በሆነ አነጋገር ያቀርባል (1ጴጥ
2፥4-5)።

ሁላችንም በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ
ከሚከናወኑ ነገሮች አንዱ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ
አካሉ መጨመር ነው (1ቆሮ 12፥13)። ይህም መጨመር ወደ
አጠቃላዩ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን (universal chrch) እንጂ
ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አይደለም። ከዚህም መጨመር የተ
ነሣ ሁላችን በክርስቶስ አንድ ሆነናል። ይኸ ደግሞ ሰው በድ
ምጽ ብልጫ ያመጣው ሳይሆን የጌታ ኢየሱስ የጸሎት ውጤት
ነው። እረሱ በዮሐ 17፥20 ላይ "አንድ ይሆኑ ዘንድ" ብሎ ጸለየ
በመጨረሻም ይህ ጸሎት መልስ አግኝቶ በመንፈስ ቅዱስ ተከ
ናወነ።

በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ የመሆናችን ጉዳይ ያመኑት ከማመና
ቸው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ያገኙት ሳይሆን የእግዚአብሔር
ሥራ ነው። ለምሳሌ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ወንድማማቾችና
እህትማማች ወይም ወንድምና እህት ይኖራሉ እንበል። በዚህ
ቤተሰብ ውስጥ አንዱ ለአንዱ ወንድም እንዲሆን ወይም እህት
እንድትሆን የውሳኔ ድምጽ የሰጠ ማንም የለም። በዚህ ነገር
ውስጥ ማንም ምንም አስተዋጽኦ አያደርግም የግድ ወንድማማ
ቾችና እህትማማቾች የሚያደርጋቸው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ
ከአንድ አባትና እናት መወለዳቸው ነው። ልክ እንዲሁ በክርስ
ቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መጥተን የእግዚአበሔር
ቤተሰብ ስንሆን የማናችንም የውሳኔ ድምጽ በዚያ ውስጥ የለም።
ግን በመስቀሉ ላይ ከተከናወነው ሥራና ከፈሰሰው ደም የተነሣ
የአንድ ቤተሰብ አባል በጌታም ወንድምና እህት (ወንድማማቾች)

ሆነናል። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ወንድሙን መርጦ ወንድሙ ያደረገ ማነው? በዚህ ነገር ውስጥ ወሳኞቹ አባትና እናት ናቸው እንጂ ልጆች አይደሉም። እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር ስለ ተቀበለን ወንድማማቾች፣ የአንድ ቤተሰብ አባል ነን። (ኤፌ 2፡19) ይህ ልንክደው የማንችል ሃቅ ነው።

ወንድሞቻችንን የምንወደው መቼ ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቤተሰቦቻችንን ስንወድ የሚል ይሆናል። እግዚአብሔርን ስንወድ የእግዚአብሔር የሆኑትን ሁሉ እንወዳለን። ነገር ግን ወንድሞቻችንን ካልወደድን የዚህ መንስኤ የሆነውን እግዚአብሔርን አለ መውደዳችን ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ወደ እግዚአብሔር ስንጠጋ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ እንወዳለን። በእግዚአብሔር ፍቅር እየበረታንና በፍቅሩ እየተሸነፍን ስንመጣ ወንድሞቻችንን ሳናውቅ ወደናቸው ራሳችንን እናገኛለን። ልባችንም ይስባቸዋል፤ በውስጣችንም ከፍተኛ ስፍራ ያገኛሉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረትና ግንኙነት እየራቀ ሲሄድ ማለትም ለአባታችን ያለን ፍቅር ሲቀንስ የወንድማችን ወንድምነትም በዚያው ልክ እየመነመነ ይመጣል። እኛ አማኞች አንድ መመዘኛ አድርገን ልንወስደው የሚገባ ነገር ወንድሞቻችንን የማንወድ ከሆነ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ከእኛ ርቋል ማለት ነው። *"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን። ማንም፣ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ፣ እርሱ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ አይችልምና"* (1ዮሐ 4፥19-20)። ነገር ግን እያንዳንዳችን ከያለንበት ቦታ እግዚአብሔር ወደ አለንበት ብርሃን ብንሮጥና ብንጠጋ ከመራራቅ ይልቅ ወደ መቀራረብ እንመጣለን።

ጳውሎስ በቆላ 3፥10-11 ባለው ክፍል ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ ስንሆን አዲሱን ሰው እንደምንለብስ ከተናገረ በኋላ በዚያም "ግሪክ ሰው፣ አይሁዳዊም፣ የተገረዘም፣ ያልተገረዘም፣ አረማዊ፣



እስኩቲክም፣ ባሪያም፣ ጨዋሰውም መሆን አልተቻለም ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው በሁሉም ነው" ይላል።

እንደ ገናም በገላ 3፡28 ላይ "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" ብሎ ይናገራል።

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ወደ ክርስቶስ መጥተን አዲስ ሰው ስንሆን እርሱን እንደምንለብስ ያስተምሩናል። ከዚህም የተነሳ አይሁዳዊ የለም የግሪክ ሰው የለም፣ ወንድ የለም፣ ሴት የለም፣ ሃብታምና ደሃ የለም። በምድር አዋቂ ይሁን ጥበበኛ እንዲሁም ማይም ሁሉም እኩል ነው። እነዚህ ነገሮች ብቅ የሚሉት ከክርስቶስ ስንርቅ ነው እንጂ በእርሱ ከሆንን ፈጽሞ አይታዩም። እነዚህ ልዩነቶች በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ እስካለን ድረስ የልዩነት መስፈሪያ አይሆኑም። የልዩነት መስፈሪያዎቻችን በክርስቶስ ኢየሱስ በተገኘ ማንነት ውስጥ ስንገባ ይሟሟሉ።

በኤፌ 4፥3 ላይ "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን። ይህን ክፍል ልብ ብለን በምናነብበት ጊዜ የምናየው እውነት የመንፈስ አንድነት ለመፍጠር ትጉ የሚለውን ሳይሆን "ለመጠበቅ ትጉ" የሚለውን ነው። ይህ አንድነት አማኞች ተሰብስበው የሚፈጥሩት ሳይሆን በክርስቶስ ሞት ተመሥርቶ በመንፈስ ቅዱስ የተከናወነ ነው። ከዚህም የተነሣ አማኞች አንድነትን ለመመስረት ትጋት አያስፈልጋቸውም፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን አንድነት በተመለከተ ለሁላችነም አንድ ትእዛዝ ተሰጥቷል። ይኸውም "የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" ተብለናል። የጥበቃ ትጋቱ ለአማኞች የተተወ ነው።

በክርስቶስ በተገኘው በዚህ አንድነት ውስጥ መቀባበል እንዱና ትለቁ ነገር ነው (ሮሜ 15፥7)። ይህም መቀባበል ከዘርና ከቀለም ልዩነት ከጾታ ልዩነት፣ ከሥነ-ልቡና ልዩነት፣ ከኑሮ ደረጃ

ልዩነት ያለፈ መሆን አለበት። ሁል ጊዜም አንድነቱ ከልዩነቶች ሁሉ በላይ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ወደ ክርስቶስ ከመጣን በኋላ የእያንዳንዳችን ዋጋ በክርስቶስ ውስጥ የሚለካ ነው (2ቆሮ 5፥15-16)። ከዚህም የተነሣ የማንም ሰው ዋጋ በዓለም እንዳለው ዐይነት በዘርና በኢኮኖሚው ደረጃ እንዲሁም በሕብረተ ሰቡ ውስጥ በሚኖረው ቦታ የሚለካ አይ ደለም። ነገር ግን የሰዎች ሁሉ ዋጋ በክርስቶስ ሆኖ ሳለ መለኪ ያችንን የዓለም ሚዛን አድርገን ለራሳችን ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጥ ከሆነ፣ በሽተኞች ነን። እንደ ገናም ሰዎች ወደ እኛ ቀረብ ሲሉ ለራሳችን ዋጋ የምንሰጥ፣ ከእኛ ሸሽት ሲሉ ደግሞ የምንቀንስ ከሆነ አሁንም ፈውስ የሚያስፈልገን ሕመምተኞች ነን። መቆ ሚያችን የተደላደለ አይደለም። ይህን አንድ ነገር ጠንቅቀን እን ወቅ የሁላችን ዋጋ ያለው በክርስቶስ ውስጥ ነው። እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል ሁላችን ም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል (1ቆሮ 12፥13)። መለኪያችን ሊሆን የሚገባው ይኸ ሆኖ ሳለ ሌላ መለኪያ ብናስቀምጥ ከቅ ዱስ ቃሉ እውነት ስተናል። በክርስቶስ ውስጥ ያለን ከሆንን በሁ ላችን ውስጥ የሚሠራው የተለያየ መንፈስ ሳይሆን አንድ መን ፈስ ነው። ይህም መንፈስ በክርስቶስ ሞት የተገኘውን ሕበረትና አንድነት /ቤተሰባዊነት/ ይጠብቃል።

እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተን በንስሓ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነትና ጌትነትን በማመን በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ስናገኝ ወደ ልዩ ኅብረት ወይም አንድነት እን ገባለን። ይህም ኅብረት ወይም አንድነት በልዩ ልዩ መልክ በሚከተለው ሁኔታ በአዲስ ኪዳን ተገልጿል።

### ለ) የአንድነት መግለጫዎች

አዲሱ የኪዳን ሕዝብ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እርስ በርሱ ያለውን አንድነት ለማሳየት የተለያዩ መግለጫዎች ተመ



ልክተዋል:-

1. ለርስቱ እንደተለየ ወገን እንደ ካህናት መንግሥት
   1ጴጥ 1፥9፤ ራእ5፥9-10፤ ኤፌ2፥13-22
2. እንደ ሕያው ድንጋይ ጡብ (በመቅደሱ/በቤቱ)
   1ጴጥ 2፥4-5፤ 1ቆሮ 3፥16-17፤
3. እንደ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ (ተክል)
   ዮሐ 15፥1-7
4. እንደ ልጅ በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ
   ዮሐ 1፥12-13፤ ገላ3፥26-27

እኛ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ነን፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ግን የእግዚአብሔር የባሕርይ አንድያ ልጅ ነው።

5. እንደ ብልት በክርስቶስ አካል ውስጥ
   1ቆሮ 12፥12-27፤ ሮሜ 12፥3-8፤ ኤፌ 4፥25

አዲሱ የኪዳን ሕዝብ አንድነቱን የሚመሠርት ሳይሆን የኪዳን ሕዝብ ከመሆኑ የተነሣ አንድነቱ ተመሥርቷል።
ሰባቱ የአንድነት መሠረቶች ወይም እውታሮች እንደሚከተ ለው ተዘርዝረዋል

1. አንድ አካል
2. አንድ መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ
3. አንድ ተስፋ፣ የክርስቶስ መገለጥ (የልጅነታችን መገለጥ)
   ቲቶ 2፥13፤ ሮሜ8፥18-25
4. አንድ እምነት (ሃይማኖት)
   ኤፌ 2፥8፤ ገላ 2፥20
5. አንድ ጥምቀት (ወደ ግልጧ ቤተ ክርስቲያን መደባ ለቂያ የዳግም ልደት የአዲሱ ሕይወት መግለጫ)

6. አንድ ጌታ
7. አንድ አባት (ቤተ ሰብ) አንድ አምላክ

ሐ) አንድነት እንደግብ/ እንደ መድረሻ

የአዲስ ኪዳን ሕዝብ አንድነት የተመሠረተም ቢሆን ግቡም አንድነት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአንድነታችን መሠረትና ራስ፣ አልፋና ኦሜጋ ነው። *"ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው"* (ኤፌ 4፥13)።

ጌታ ኢየሱስ ስጦታን ሰጠ

ጌታ ኢየሱስ 1. ለእያንዳንዳችን ጸጋ ሰጥቶናል
2. ሰዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል

ለምን ሰጠ?

1. ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማብቃት
2. አካሉን በማነጽ (በማጥራት መገንባት)
3. የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን
4. የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ ሳቢያ ወደሚገኝ አንድነት ማድረስ/ማምጣት

<u>ፍሬውም</u>

1. በትምህርት ነፋስ አለመፍገምገም
ገላ 1፥6
2. እውነትን በፍቅር መያዝ
3. ወደ ክርስቶስ (ራስ ክርስቶስ) ማደግ (መብሰል)



ማጠቃለያ

"የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" ኤፌ 4፥3

ለመጠበቅ ትጉ፡- - አትኩሮ ማየትን
- ከፊት የሚመጣንም አጥቂን አፍራሽ ኀይልን መክተን መገኘት
- መከላከልን፣ አልበገር ባይነትን ያካትታል

ሰላም ሁከትን ተከላካይ ነው፣ ፀረ ሁከት ነው፣ በረብሻ ትኩሳት እሳት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ከላሽ ነው።

መ) ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን

(ሮሜ 12፥3-12፤ 1ቆሮ 12፥14-27፤ ገላ 6፥1-5)

በልዩነት መካከል አንድነት የሚገኘው በክርስቶስ ነው። የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ አንድነትን ለመግለጥ የአካል ምሳሌነት ሀይነተኛ መግለጫ ነው።

1. አካል
1) አካል አንድ ብልት ወይም አንድ ብልትም አካል አይደለም
2) አካል የብዙ ብልቶች የተቀናጀ ስብስብ ነው።

2. ብልቶች
1) እያንዳንዱ ብልት በአካል ነው (1ቆሮ 12፥18)

አንድ ብልት ከአካል ውጭ እውንነት ወይም ትርጉም የለውም፤ አንድ ብልት ከሌሎች ብልቶች ተለይቶ መኖርም፣ መጥቀምም አይችልም (ሮሜ12፥5)። የአንድ ብልት ማንነት ወይም ትርጉም ከሌሎች ብልቶች ጋር ተያይዞ የሚታይ የሚከሰት ነው።

6. አንድ ጌታ
7. አንድ አባት (ቤተ ሰብ) አንድ አምላክ

ሐ) አንድነት እንደግብ/ እንደ መድረሻ

የአዲስ ኪዳን ሕዝብ አንድነት የተመሠረተም ቢሆን ግቡም አንድነት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአንድነታችን መሠረትና ራስ፣ አልፋና ኦሜጋ ነው:: *"ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው"* (ኤፌ 4፥13)::

ጌታ ኢየሱስ ስጦታን ሰጠ

ጌታ ኢየሱስ 1. ለእያንዳንዳችን ጸጋ ሰጥቶናል
2. ሰዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል

ለምን ሰጠ?

1. ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማብቃት
2. አካሉን በማነጽ (በማጥራት መገንባት)
3. የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን
4. የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ ሳቢያ ወደሚገኝ አንድነት ማድረስ/ማምጣት

<u>ፍሬውም</u>

1. በትምህርት ነፋስ አለመፍገምገም
ገላ 1፥6
2. እውነትን በፍቅር መያዝ
3. ወደ ክርስቶስ (ራስ ክርስቶስ) ማደግ (መብሰል)



ማጠቃለያ

"የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" ኤፌ 4፥3

ለመጠበቅ ትጉ:- - አትኩሮ ማየትን
- ከፊት የሚመጣንም አጥቂን አፍራሽ ኀይልን መክተን መገኘት
- መከላከልን፣ አልበገር ባይነትን ያካትታል

ሰላም ሁከትን ተከላካይ ነው፣ ፀረ ሁከት ነው፣ በረብሻ ትኩሳት እሳት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ከላሽ ነው::

መ) ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን

(ሮሜ 12፥3-12፤ 1ቆሮ 12፥14-27፤ ገላ 6፥1-5)

በልዩነት መካከል አንድነት የሚገኘው በክርስቶስ ነው:: የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ አንድነትን ለመግለጥ የአካል ምሳሌነት ዐይነተኛ መግለጫ ነው::

1. አካል
1) አካል አንድ ብልት ወይም አንድ ብልትም አካል አይደለም
2) አካል የብዙ ብልቶች የተቀናጀ ስብስብ ነው::

2. ብልቶች
1) እያንዳንዱ ብልት በአካል ነው (1ቆሮ 12፥18)

አንድ ብልት ከአካል ውጭ እውንነት ወይም ትርጉም የለውም፤ አንድ ብልት ከሌሎች ብልቶች ተለይቶ መኖርም፣ መጥቀምም አይችልም (ሮሜ12፥5):: የአንድ ብልት ማንነት ወይም ትርጉም ከሌሎች ብልቶች ጋር ተያይዞ የሚታይ የሚከሰት ነው::

2) እያንዳንዱ ብልት የራሱ የሆነ
   (1) ማንነት (ኤፌ 3÷7)
   (2) ሥፍራ ( ሮሜ 12÷4-6)
   (3) ራእይ(ጥሪ) ተግባር
   (4) ፀጋ አለው።

3) አንድ ብልት ከራሱ ማንነት፣ ራእይ/ተግባር፣ ፀጋ ተሻግሮ የሌላውን ማንነት ራእይ፣ ተግባር ፀጋ በቀጡ መረዳት መገንዘብ ያጸግተዋል፤ አይሆንለትም፤ ለሠሪው ከበሬታ ከመስጠቱ የተነሣ ሌላውን ብልት ይቀበላል፤ ያከብራል እንጂ፤

4) እያንዳንዱ ብልት የሆነውን የሆነው በራሱ ምርጫ ወይም ውሳኔ አይደለም፤ ከተሰጠው ድንጋጌ የተነሣ ነው። (DNA በተገኘ መመሪያ)

ማንኛውም የአካል ሕዋስ (ሴል) ወደ ሙሉ አካል የመዳበር (የማደግ) በተፈጥሮው እምቅ ኀይል ያለው ወይም የነበረው ነው።

3. የውድድር መንፈስ በብልቶች መስረጽ የማይጠበቅ ተውሳክ ነው
   1) መነሻው ሥፍራና ዋጋ መሻት
   2) የሚያስከትለው ውጤት
      ሀ) የበታችነት ስሜት ምሳሌ፣ ጆሮ ከዐይን፣ እግር ከእጅ ጋር ሲወዳደሩ (1ቆሮ12)
      ለ) የበላይነት ስሜት ምሳሌ፣ ዐይን/እጅ፣ ጭን ቅላት/እግር ጋር ራሳቸውን ሲያወዳድሩ

4. የትብብር መንፈስ በብልቶች ዘንድ የማደር አስፈላጊነት (1ኛ ቆሮ 12÷25)
   1) እያንዳንዱ ብልት ለሌላው ብልት አስፈላጊ ነው



   2) አንድ ብልት ሌላውን ሲያገለግል ራሱ ተገልግሎ ይገኛል፤ ምሳሌ ምላስ ለጥርስ፣ ለሆድ
   3) እያንዳንዱ ብልት ለአካል (ለክርስቶስ) ይኖራል።
   4) ብልቶች እንደ ኮንሰርት የመዘምራን ቡድን በኅብረት ነው ማዜም ያለባቸው።

5. አንድ ብልት ሲሰቃይ ብልቶች ሁሉ አብረው ይሰቃያሉ
   1) አንድ ብልት ሲጐዳ ሌሎችም ይጐዳሉ
   2) የአንዱ ብልት ስቃይ በሌሎች ብልት ዘንድ እንዳይሰማ ማድረግ የሚቻለው ማደንዘዣ በመውሰድ ብቻ ነው። ወይም ነርቭ በድን ሲሆን ነው።
   3) ሕመም ለርዳታ ብልቶችን የሚያስተባብር ጥሪ ነው

6. አንድ ብልት ቢከበር ብልቶች ሁሉ አብረው ይከብራሉ (ደስ ይላቸዋል)
   1) አንድ ብልት ሲሰቃይ አብሮ ማዘንና ማጽናናት አንድ ብልት ሲከብር አብሮ ከመክበር ይልቅ ይቀላል።
   2) አንድ ብልት ሲከብር አብሮ ከመደሰት፣ ከመክበር ይልቅ ተበለጥሁ፣ ተጣልሁ ብሎ ማሰብ በሥጋ ይቀናናል (ይቀላል)

7. የአንድ ብልት ዋጋ በማንነቱ፣ በስፍራው፣ በራእዩ ወይም በተግባሩ፣ እንዲሁም በተሰጠው ጸጋ አይተመንም (ማቴ 20÷9-14፤ 1ኛ ሳሙ 30፡22-25)።
   - ማንነቱ
   - በስፍራው
   - ራእዩ/ጥሪው ወይም ተግባሩ
   - ጸጋው

ዋጋው የተተመነው ስለ ብልቶች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስማ

ያዊ ክብሩን ትቶ በመምጣቱ፣ በመሞቱና በመነሳቱ ነው::

8. ግጭት/ ፍልሚያ በብልቶች መካከል

1) ቅንነት ጎደል፣ ያልሆነ ግጭት
ምሳሌ: - የእግርና እግር መጋጨት
- የጥርስ ምላስን /ጣትን መቀርጠፍ
- እጅ እጅን ሲቆርጥ/ሲቀጠቅጥ

2) ብልት በሌላ ብልት መሳደድ
- አለመበረታታት
- ቦታ አለመስጠት
- አለመከበር
- መወንጀል
- መኮነን

ምሳሌ:- የነርቭ መውረጃው የጀርባ አጥንት ሲጠብ

3) ብልት በራሱ መሳደድ (ራሱ ለራሱ ሲያለቅስ፣ ለራሱ እዝን ሲቀመጥ)
- ተስፋ ማጣት
- በራስ መከሰስ (መወንጀል)
- በራስ መኮነን

ምሳሌ: ዐይን ከመሬት ተነሥቶ ሲያለቅስ
እግር በራሱ ፍርግጥ ፍርግጥ ሲል

9. የብልት መታወክ

1) የአንድ ብልት ጠንቅ የብልቶች ጠንቅ ነው (ምሳሌ - አካን እና እነ ኢያሱ)
የሰንሰለት ጥንካሬ የሚለካው በደካማዋ ቀለበት ነው::

2) ለፈውሱ የብልቱ መተባበር ዝግጁነት እንዲሁም የሌሎች ብልቶች ተሳትፎና መተዛዘን ያሻል::



10. የብልት መታቀብ
- የተሰበረ እጅ ወይም እግር በጀሶ ይታጀላል
- ሕክምና ይሰጠዋል

11. የብልት መቈረጥ/መወገድ
- አካለ ጐዶሎነትን ያመጣል ሆኖም የጤነኛ ብልቶችን ጤንነት ያረጋግጣል (የሆነው ሆኖ ኩስ የነካውን እጅ ያጥቡታል እንጂ አይቈርጡትም)
- በሰው ሰራሽ ብልት መተካት

12. የብልት ትጋት እና ዕረፍት (ዘፀ 31፥17)

- ብልቶች እንደተሰጣቸው ፀጋ መትጋትም ማረፍም ይኖርባቸዋል::
- የአንዱ ብልት ዕረፍት ለሌላው ብልት ዕረፍት ሊሆን ይችላል::

ሠ) የብልቶች ሥራ በአካል ውስጥ

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በሥጋ የተወለዱ ልጆች አንድ ዐይነት እንዳልሆኑ ሁሉ እኛም ወደ ክርስቶስ አካል ስንመጣ በክርስቶስ አካል ላይ የምንገኝ የተለያዩ ብልቶች እንጂ አንድ ዐይነት አን ሆንም:: የእግዚአብሔርም ዐሳብ አንድ ዐይነትነትን ለማስገኘት ሳይሆን አንድነትን ለመፍጠር ነው:: ፍጥረት ሁሉ ልዩ ልዩ ሆኖ ሳለ አንድ ፈጣሪ አለው፤ ብልቶችም የተለያዩ ቢሆኑም በአንድ አካል ላይ ይገኛሉ፤ ለአንድ አካል ይሠራሉ:: ብልቶች የተለያዩና የየራሳቸው ባህሪይ ቢኖራቸውም እርስ በርስ የተያያዙና በኅብረት ተቀናጅተው የሚሠሩ ናቸው::

የእግዚአብሔር መንፈስ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን ኅብረትና አንድነት በሐዋርያው በኩል ሲገልጥ የአካል ብልቶችን እንደ ማስተማሪያ አድርጎ በ1ቆሮ 12: ባለው ክፍል ላይ ያቀርባል:: ቍጥር 14 "አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለ

ምና" ይላል በክርስቶስ አምነን መንፈስ ቅዱስ ወደ አካሉ ሲጨ ምረን ሁላችን የአካሉ ብልቶች እንሆናለን:: ነገር ግን አንዱ ምን ዐይነት ብልት ሌላው ደግሞ ምን ዐይነት እንደሚሆን ይህ ለእግዚአብሔር እውቀት እና ውሣኔ የሚተው ነው:: ሆኖም ሁላችንም የአካሉ ብልቶች እንሆናለን:: የማናችንም አካል የብ ልቶች ቅንብር እንጂ የአንድ ብልት ውቅር እንዳልሆነ፣ ወይም አንድ አካል ብዙ ብልት እንጂ አንድ ብልት እንዳይደለ እናው ቃለን:: በአካል ብዙ ብልቶች አሉ:: እነዚህ ብልቶች የየራሳቸው ማንነት አላቸው:: ሁሉም ያሉት ግን በአካል ውስጥ ነው::

በአካላችን ላይ ዐይን አንድ ብልት ሲሆን ጆሮ ደግሞ ሌላ ብልት ነው:: እንዲህ እያልን አፍንጫ፣ እጅ፣ እግር፣ ጣፊያ፣ ጉበት ብለን ልንዘረዝር እንችላለን:: እያንዳንዱም ብልት በስፍራው የራ ሱን ማንነትና ተግባር አለው:: ብልቶች ልዩ ልዩ ናቸው ነገር ግን በአንድ አካል ውስጥ ካሉ እርስ በእርስ መተባበርና መቀባ በል አለባቸው እንጂ መሽቀዳደም፣ መፎካከር፣ መገፋፋት የለ ባቸውም::

እዚህ ላይ መጤን ያለበት መሠረታዊ ነጥብ አለ:: ይኸውም እያንዳንዱ ብልት በአካል ላይ ሲኖር የራሱ ማንነት፣ የራሱ ስፍራ የራሱ ራእይ ወይም ተግባርና እንዲሁም ጸጋ አለው:: በዚህ መሠረት የዐይን ራእይ ወይም ተግባር ማየት ሲሆን የጆሮ ደግሞ መስማት ነው:: ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ብልት የሌላው ብልት ራእይ ላይገባው ይችላል:: ሆኖም ጠቃሚነቱና አስፈላጊ ነቱን ግን ማመን፣ መገንዘብ አለበት:: ለምሳሌ ለዐይን ስለ መ ስማት የጠለቀ ገለጻ ቢደረግለት ስለ ጆሮ ተግባር ምንም ግንዛቤ የለውምና መስማት ማለት ቀይ ወይም ቢጫ ብርሃን ነው እያለ ያስብ ይሆናል፤ ከዚህ ውጭ ያለ እውነታም፣ ቋንቋም ያስቸግ ረዋል:: እንዲሁም ለጆሮ ስለ ማየት ቢነግረው ማየት ማለት ልዩ ድምጽ ወይም ዜማ ነው ከማለት ውጭ ምንም ሊያስብ፣ ሊል አይችልም::



እንዲህ እያልን የሌሎችን ብልቶች ሥራ ብንመለከት የእግር ተግባር መሄድ ሲሆን የእጅም ደግሞ አገልግሎቱ ብዙ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ግን እጅ የእግር ተግባር ሊገባው ይችል ይሆናል:: ምክንያቱም እግር በሌለበት ጊዜ ማለትም በሕመም ወይም በአደጋ ሲወገድ ምርኩዝ በመጠቀም በእጅ መሄድ (በምር ኩዝ፣ በውሂልቸር) በየመንገዱ ላይ ስለሚታይ እጅ ትንሽ ትንሽ የእግርን ራዕይና ተግባር ሊካፈል ይችላል:: ብልቶች በአ ካል ላይ በመዋደድ ሲኖሩ አንዱ የአንዱ ራእይና ተግባር በደ ንብ ባይገባውም በእምነት ተቀባብለው ይሠራሉ:: ነገር ግን እያ ንዳንዱ ብልት የራሱን ራእይና ተግባር እንደሚገባ ይወጣል:: እዚህ ላይ አብረን በማያያዝ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር በአካል ውስጥ "ዐይን" የማየትን "ጆሮም" የመስማትን ሥራ እንዲሠራ የወሰነ የበላይ ፈጣሪ ነው::

ስለ ሰውነት ሴሎች የሚያጠኑ ጠበብት እያንዳንዱ ሴል የትኛ ውንም ሀይነት ሆኖ ለመሥራት የሚያስችል እምቅ ኀይልና ችሎታ እንዳለው ይናገራሉ:: በመሠረቱ የዐይን ህዋስ የጆሮም ህዋስ ለመሆኑ እምቅ ችሎታ ነበረው ወይም አለው:: ነገር ግን ከበላይ በመጣው ትእዛዝ መሠረት የዐይን ህዋስ ዐይን ሆኖአል:: ዐይን "ዐይን" የሆነው በራሱ ምርጫና ውሳኔ ሳይሆን ከተሰጠው ትእዛዝ የተነሣ ነው:: እኛም በክርስቶስ አካል ውስጥ ስንገባ እግ ዚአብሔር እንደ ፈለገ የሚሻውን ዐይነት ብልት ያደርገናል እንጂ በእኛ ፈቃድ የሚሆን ምንም ነገር የለም:: ይሁን እንጂ ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ነን::

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ብልት በአካል ውስጥ ቦታ ወይም ስፍራ መድቦለታል:: ቅርጽን ሲሰጥ፣ እግዚአብሔር ለብልቶች ስፍራ ሲመድብ ጥበብ የተሞላ ምክንያት አለው:: አንዳንዱን በውጭ በኩል ሲያደርግ ሌሎችን ደግሞ በውስጥ ሰውሮ አስቀ ምጦአቸዋል:: እነ ዐይን፣ አፍንጫ፣ ጆሮ ወዘተ ከውጭ ሲሆኑ፣

እነ ልብ፣ ሳምባ፣ ጉበት፣ ኩላሊት ወዘተ ከውስጥ በኩል
ናቸው:: ሀይንን ከውስጥ እግር ሥር ወይም ቊርጭምጭሚት
አጠገብ ሳይሆን ወይም ከፍ አድርጎ ወደ ጭንቅላት አስጠግቶ
ከማጅራት ላይ ሳይሆን፣ ፊት ላይ ነው ያስቀመጠው:: እነ ሳን
ባን ከውጭ አድርጓቸው ቢሆን ኖሮ በቀላሉ በተበረጣጠቁ
ነበር:: አፍንጫን ከወደ ውጭ አድርጎ በዙሪያው ያለውን እን
ዲያሽት አስቀመጠ እንጂ በውስጥ አድርጎ እነ ጣፊያን፣ ኩላ
ሊትን፣ ጅማትንና የመሳሰሉትን እንዲያሽት አይደለም::

ለሁሉም በማስተዋልና ጥበብ ባለው አሠራሩ ቅርጽ አውጥቶ
ቦታ ቦታ ሰጥቶ አስቀምጧቸዋል::

ረ) ከብልቶች የሚጠበቀው ትብብር ወይስ ውድድር?

ብልቶች ቅኝታቸው ትብብር እንጂ ውድድር አይደለም:: ለው
ድድር ተጠርተው ቢሆን ኖሮ በጣም አስቸጋሪ ነገር ይሆን ነበር::
ለምሳሌ በሆዳችን ውስጥ አንዳንድ ክፍሎች አሲድ ያፈልቃሉ
ይህን አይተው ብልቶች በውድድር መንፈስ ቢገቡ እና ይህ
ክፍል በውድድር ብዙ አሲድ ቢያፈልቅ አንጀት ይሞሸለቃል፣
ይቀቀላልም:: ከዚህ የተነሳ ውድድር ለብዙ ችግርና ፍልሚያ
በር ከፋች ይሆናል:: ምክንያቱም በውድድሩ አሸነፍኩ የሚለው
የበላይነት ሲሰማው ተበለጥኩ የሚለው ደግሞ በአንጻሩ የበታች
ነት ስሜት ያድርበታል::

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 12:12-13 ባለው ክፍል ላይ የተለ
ያዩ ዜግነትና የኑሮ ደረጃ ያላቸውን አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ
አንድ እንደሆኑ ካሳየ በኋላ በመካከላቸው መለያየት እንዳይኖር
በብልቶች መካከል ያለውን ትብብር (ህብረትና አንድነት) ለማ
ሳየት በሰው አካል ላይ ያሉ ብልቶችን ለማስተማሪያነት ሲጠቀም
እንመለከታለን:: ስለዚህ በቊ 15 "እግር እኔ እጅ አይደለሁ
ምና የአካል ክፍል አይደለሁም ብትል ይህን በማለትዋ የአካል



ክፍል መሆንዋ ይቀራል? ጆሮም እኔ ሀይን አይደለሁምና የአካ
ል ክፍል አይደለሁም ቢል ይህን በማለት የአካል ክፍል መሆኑ
ይቀራልን?" ይላል::

እዚህ ክፍል ላይ ጆሮና እግር የተሰማቸው ምንድነው? "እግር
እኔ እጅ አይደለሁም ጆሮም እኔ ዐይን አይደለሁም" ሲል ጆሮና
እግር ምን ለመሆን የፈለጉ ይመስላል? ጆሮ እኔ ዐይን አይደለ
ሁም እግርም እጅ አይደለሁም ሲሉ ጆሮ ሀይን፣ እግር ደግሞ
እጅ ለመሆን የናፈቁ አይመስልም? ይህን ከመናፈቃቸው በፊት
ግን ጆሮ ጆሮነቱን ተቀብሎት ይኖር ነበር:: ሀይንም እንዲሁ::
ጆሮና እግር፣ ሀይንና እጅ መሆን ሲፈልጉ የውድድር መንፈስ
ሰርጸባቸው ችግር ውስጥ የገቡ ይመስላል:: የውድድሩ መንፈስ
ብልቶችን ሲጠናወታቸው አንዱ የበላይ አንዱ የበታች ይሆ
ናል:: በክፍሉ ጆሮና እግር የበታችነት ስሜት የተሰማቸው ዐይ
ነት ሆነዋል:: ጥያቄው ለምን የበታችነት ስሜት ተሰማቸው አይ
ደለም ለምን የውድድር ስሜት ውስጥ ገቡ ነው::

ምናልባት እኛ የየራሳችንን አስተያየት ልንሰጥ እንችል ይሆ
ናል:: ጥያቄው አሁንም ጆሮ ለምን ሀይን መሆን ፈለገ? የሚል
ነው:: ምናልባት ጆሮ ዐይንን ሲመለከት የበለጠ ክብር ስለተሰ
ጠው ይሆን? እንደምናውቀው ብዙ ሽር ጉድ ለዐይን ነው::
በአኗኗራችን ለጆሮ ግን ብዙ ትኩረት አይሰጠውም:: ዐይን
ውስጥ ትንሽ ብናኝ ቆሻሻ ገብቶ ከሆነ ጥድፊያው ሌላ ነው::
ንጹህ መሀረብ ይፈለጋል፣ ወደላይ ወደታች ወደ ጎን ተመልከት
ይባላል ጆሮ ውስጥ ግን ስንቱ ቆሻሻ ሲንጋጋ በእስክሪብቶ ክዳን
ወይም በለስላሳ ሥንጥር ቢጤ የገጠመው ችግር ይቃለልለታል::
ጆሮ ለዐይን የሚደረገውን ጥንቃቄ የሞላበት እንክብካቤ ሲመለ
ከት ይህ ነገር እንዴት ነው? ሳይል አልቀረም (በአንደኛው
ዓለም የተለየ መልክና እንክብካቤ ሊኖረው ይችላል)::

እንደየ ባህሉም ቢሆን ሰው ፊቱን ሲታጠብ ለመታጠብ ሰፊ

እድል ያለው ከጆሮ ይልቅ ዐይን ናት። ተባራሪ አውራ ጣት መጥታ ጆሮን ትነካዋለች እንጂ ለእርሱ ነገሮች የጠበቡ ናቸው። ቢኳሉ ዐይንን፣ መነጽር ቢደረግለት ለዐይን፣ ዐይን ሲንቆጠቆጥ /ሲዋብ/ ጆሮ ግን መነጽር ተሸካሚ ነው። ይህንን ሁሉ አይቶ በእነዚህ ሁኔታዎች ጆሮ ከፍተኛ የዝቅተኝነት ስሜት የተሰማው ይመስላል። ከተሆነ ከተሆነ፣ ብዙዎቻችን መሆን የምንፈልገው ዐይንን ነው ብሏል። ብዙ ጊዜ ደግሞ የሚወዳደሩት የሚቀራረቡ ብልቶች ናቸው። ትንሽ መመሳሰል ያላቸው ወደ ውድድር ይገባሉ። ሩቅ ለሩቅ ያሉ ብዙም አይወዳደሩም ሀይንና ጆሮ ሳያውቁት ውድድር መንፈስ ውስጥ ገቡ። በዚህም ምክንያት ጆሮም ዝቅተኝነት ስሜት ውስጥ የገባ ይመስላል።

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት ማለት፣ ማሰብ ከሚገባው በላይ ማሰብ የመንፈስን አንድነት ማደፍረስ ነው። ብልቶች ለውድድር አልተጠሩም። ቅኝታቸው የውድድር ሳይሆን የመተባበር ነው። በውድድር መንፈስ የተመረዘ ብልት ምንም መልካምነት አይታየውም። ለምሳሌ ጆሮን ከተሰማው ስሜት ለማውጣት ላጽናናህ ብለው ሎቲው እንጥልጥሉ የከበረው ነገር ሁሉ ለአንተ አይደለም እንዴ! ቢባል ስንት መከራዬን አይቼ፣ ደሜን አንጠፍጥፌ፣ ተበስቼ፣ ይብዛብኝ እንዴ ይሄ! በማለት ዋጋ አይሰጠውም።

የውድደር መንፈስ በክርስቶስ ባለን አንድነት ህብረት ውስጥ ሲሰርጽ የሆነውን እንዳንቀበል ከመስመራችን ገፍትሮ ሊያስወጣን እንደ ሆነ ሊስተዋል ይገባል። ይህም መንፈስ ሲጸናብን የሌላው የከበረ መስሎ ይታየናል። እግዚአብሔር ግን የሰጠንን ጸጋ እርሱ በሰጠን አገልግሎት እንድንጸና ነው።

እግርም እንዲሁ ጆሮ የተሰማውን ዐይነት ስሜት የተሰማው ይመስላል። በእግርና በእጅ መካከል ብንመለከት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ከእግር ይልቅ እጅ ነው። በወንዶችና በሴቶች መካ



ከል ልዩነት ቢኖርም ብዙ ጊዜ የሚነቀስ ቶሎ ቶሎ የሚታጠብ፣ ቀለበትና ሰዓት እንዲሁም አንባር ብዙ ጊዜ የሚደረግለት እጅ ነው። ይሄ ነገር ለእግር አልተስማማውም። ከተሆነ አይቀር እጅ መሆን ነው እያለ ያሰበ ይመስላል። እጅ ሲፈልግ እየተወዛወዘ ነፋስ ይቀበላል፤ ሲፈልግ ኪስ ውስጥ ውሽቅ ይላል፤ እግር ግን በጫማ ውስጥ ታጅሎ ይውላል። አለበለዚያ እንቅፋት ያጎነዋል። የእጅ ጥፍር በየጊዜው ሲነቀስ፣ የእግር ጥፍር ግን የሚታሰበው ምናልባት ካልሲ ሊቀድ ሲል ይሆናል።

በቍጥር 21 ላይ "ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም ይላል ማንም አማኝ በክርስቶስ ያለውን ወንድሙን እንደ ማያስፈልገው ማሰብ የለበትም። ያለ አንተ እኔ ብቁ ነኝ ቢል ስቷል። ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ማለቷ በትዕቢት መወጠሯን ያሳያል። ምናልባት ይህንን ትዕቢት በዐይን ውስጥ ያመጣው እነ ጆሮ ተነስተው ዐይነ ካልሆንን ብለው የጮሁት መጮህ እኔ ልዩ ነኝ እንድትል አድርጓት ይሆን? ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ወደሚል ድምዳሜ ያመጣት ምን ይሆን? መቼም ትዕቢት ሲመጣ መታወር ነው። ዐይንን የመሰለ የሚያይ እጅን አታስፈልገኝም ሲል በትዕቢት መጥፋቱ ነው። በራሱ ላይ እልቂት ማወጁ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ዐይን ለአደጋ ሲጋለጥ ከመቅጽበት ያለ ብዙ መውጣትና መውረድ፣ ማቅማማት ተሯሩጦ ለማዳን፣ መሥዋዕትነት ለመክፈል የሚመጣ ማነው? እጅ አይደለምን? ዐይን ለደህንነቷ የሚኖረውን እጅን አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም።

ጌታ ለምን ሞተ? በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሳው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ (2ቆሮ 5፥15) እያንዳንዱ ብልት ለአካል ሲኖር ለክርስቶስ ይኖራል። ለክርስቶስ ደግሞ ሲኖር ለሌላው ብልት ይኖራል። ብልቶች በቅድሚያ ስለራሳቸው መኖር የለባቸውም። ነገር ግን ለሌ

ላው በሚያደርጉት መኖር ለራሳቸው ኖረው ይገኛሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምረን ትምህርት ይህ ነው።

ብዙ ጊዜ ለባብሰን ልንወጣ ስንል እንከን ካለብን ለማስወገድና አለባበሳችንን ለማየት መስታወት እንመለከታለን። ነገር ግን ይህን ለማድረግ ከብልቶቻችን የምንጠቀመው ዐይንን ነው። ሆኖም መስታወትን በማየት ሂደት ውስጥ የምንቆየው የዐይናችንን ብሌን በማየት ሳይሆን ሌላውን የሰውነት ክፍል በማየት እንደ ሆነ ሁላችንም እናውቃለን። እስኪ በሕይወታችን ዘመን የዐይን ብሌናችንን ያየንበትን ጊዜ እናስታውስ፤ እጅግ በጣም ጥቂት ጊዜ ቢሆን ነው። ወደ መስታወት በሄድንበት ጊዜ ሁሉ ዐይን በማየት ሌላውን ሲያገለግል ነው የቆየው። የዐይን ብሌን ሌላውን የሰውነት ክፍል ለማየት ነው የምትሰማራው፤ እንግዲያስ አንዱ ብልት ለሌላው ነው የሚኖረው።

ተርበን ሳለን ምግብ ሲመጣ ከብልቶቻችን ምግቡን ቶሎ የሚያገኘው ብልት አፍ ነው። አፋችን የቀረበውን ምግብ ከእጅ ተቀብሎ በምላስ አጋዥነት ወዲያ ወዲህ ወዲህ እያዘዋወረ ጥርስ አድቅቆና ፈጭቶ አንዱ ከአንዱ በመቀበልና በማስተላለፍ ወደ ሆድ፣ ወደ አንጀት ይልከዋል። በዚህም ተግባር በብልቶች መካከል መስገብገብ የለም። ነገር ግን ከመስግብግብ የተነሣ ምላስና ጥርስ የያዙትን ምግብ እዚሁ እናስቀራለን አናስተላልፍም ቢሉ ዕድል ፈንታቸው መበብበስ ይሆናል። ጥርስ ውስጥ የሚተራረፍ ምግብ ውሎ ሲያድር ጥርስን እንደሚያበሰብስ እናውቃለን። ለመነቀልም ይዳርጋል፤ ለዚህ ነው በየጊዜው አፋችንን የምንጉመጠመጠውና የምንፍቀው ወይም የምንበርሸው።

ጥርስና ምላስ ምግቡን አድቅቀው ወደ ሆድ፣ ወደ አንጀት ሲልኩት ቢያስቀሩትም ያስቀሩት ብለው በእምነት ነው። እነዚህ ሁለት ብልቶች እኝከውም ወዲያና ወዲህ ብለውም በእምነት ልከው መጨረሻ ላይ ግን ባዶአቸውን የሚቀሩ አይደሉም። ለመ



ጽናናት እንኳን በአፍ ውስጥ ምንም አያስቀሩም። ነገር ግን በእምነት ጠብቀው ሲኖሩ ሰዓታት ይቆጠርና በተመቻቸው መንገድ ለጥርስ የሚያስፈልገው ለጥርስ፣ ለምላስ የሚያስፈልገው ለምላስ በደም ስር ውስጥ በሚደረግ ዝውውር እየተሯሯጠ ይመጣና ይጠግባሉ።

ብልቶችን ስንመለከት አንዱ ለሌላው ነው የሚኖረው፤ አንዳቸውም ለራሳቸው አይኖሩም። ለሌላው መኖር መጥፋት (ማጣት) አይደለም። አፍ ወይም አንደበት ባዜመው ጥዑም ዜማ ጆሮ ሰምቶ ይደሰታል፤ ደስታውም በመላ አካል ይሠራጫል። አፍንጫ መልካም ምግብ ባሸተተ፣ ምራቅ በምላስ ሜዳ ላይ ይፈነጫል።

የተጠራነው ለሞተልን ጌታ ልንኖር ነው። ለእርሱ ስንኖር ለሌሎች ወንድሞቻችን እንኖራለን። ይህ ደግሞ ክስረት የለበትም። ለሌላው መኖር የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርሀት እንጂ የዓለም አይደለም። ለሌሎች መኖራችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። መለኪያችንን የዓለም ሚዛን ስናደርግ ግን ይህንን እንጥላለን።

በመስጠት ማግኘት አለ። እያንዳንዱ ለክርስቶስ ሲኖር በተዘዋዋሪ ለራሱ ይኖራል። በአካላችን ላይ ካሉ ብልቶች ትብብር ይህንን እንማራለን። ጌታ "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ነፍሱንም ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል" አለ (ሉቃ9፥23-24) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምረው እውነት ዓለም ከሚያስተምረው በጣም የተለየ ነው። የዓለም ሥርዓትና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዐት ፈጽሞ አይገናኝም። ሁላችንም በዚህ ብዙ ውጥረት አለብን። ፍቱኑ ሥርዐት ጌታ ኢየሱስ ያስተማረው የሰላም ሥርዐት ነው። በእኛ መንገድ በእኛ ብልሃት በእኛ ጥበብና እስ

ተሳሰብ ሕይወትን ለመምራት ብንሞክርና ነፍሳችንን ለማዳን ብንፈልግ እርሱ ጌታችን እንዳለው እናጠፋታለን:: በክርስቶስ ያለን ማናችንም እስከ ዛሬ የኖርነው ኑሮ ወደ ኋላ ቃኝተን ሕይ ወታችንን እንፈትን ከዚያም ውጤቱን እናየዋለን:: ለክርስቶስ የሆነው ነገር ሁሉ ትርፍ አለው:: ግን በራሳችን መንገድ ያደረ ግነው ሁሉ መልሶ እኛኑ ይጎዳናል:: እኛ አማኞች ይህንን በቅ ድሚያ ማየት ያስቸግረናል:: ስለዚህ ነው "የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱ በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነውን ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ" የተባልነው (ሮሜ 12÷2) በዚህ ዓለም መለኪያ አንለካ፣ ይህ ዓለም የሚያደንቀውን አናድንቅ ይህ ዓለም የሚያንኳስሰውን አብረን አናንኳስ እኛ በክርስቶስ በኩል የተወ ደድን የእግዚአብሔር ልጆች መለኪያችን የእግዚአብሔር መለ ኪያ ይሁን እንጂ የዓለም አይሁን::

የተጠራነው ለትብብር ነው፤ በመስጠት ማግኘት ደግሞ የሕይ ወት ዘይቤአችን ነው:: ወንድሞቻችንን በገፋንበት ነገር አብረን የእግዚአብሔርን ልጅ ስለ ገፌተርን በጎደልንበት ነገር ሁሉ ንስሐ ልንገባ ይገባል:: አማኞችን ስንገፌትር አብረን እግዚአብሔርን ነው የምንገፌትረው (የምንገፋው)::

በመሠረቱ ሰው ሁሉ የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ነው:: (ዘፍ 1÷26) ከዚያም አልፎ ደግሞ ክርስቶስ ኢየ ሱስ ለሰው በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ሞቷል:: ለምሳሌ የአ ንድን ሰው ዕቃ ተውሰን ብንሸራርፈው ሰውየው ደስ እንደማይ ለው ሁሉ እንደዚሁ እግዚአብሔር ብዙ ዋጋ የከፈለበትን ሰው ብንገፋ ደስ አይሰኝም፤ ልጁ ታላቅ መስዋዕት በመክፈል ለፍቶ በታልና::

የልዩነት መለኪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ጭራሽ ዋጋ የለሽ ነው:: ስሙን ብቻ ይዘን ከእግዚአብሔር እየራቅን ስንመጣ ከምድር የሆነ መለኪያ በቅዱሳን ዘንድ እየገነነ ይመጣል:: አንዱን ተቀ



ብለን አንዱን እየገፋን ከመኖር እንራቅ፤ ከዚህ ይልቅ አንዱ ብልት ሌላውን እንደሚያገለግለው ልንተሳሰብ ተጠርተናል:: በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ባለቤት ስለ ሆነ ስጋት እንኳን የለም:: አንዳንድ ጊዜ ያለ እምነት እንሆናለን:: ከዚህ ቀደም ያለውን ምሳሌ ላንሳና እንመልከት ምላስና ጥርስ አላምጠው ስል ቀው ወደ ሆድ የላኩት ምግብ ወዲያው እየሮጠ ተመልሶ አይ መጣም:: እንደ ምግቡ ዐይነት ለመፍጨት ከ4-6 ሰዓት ይፈጃል:: ጥርስና ምላስ በዚህ ውስጥ በእምነት ይጠባበቃሉ፤ እምነት አንዱ ለሌላው ለመኖር የሚያስችል መንፈሳዊ መሳሪያ ነው:: ለምሳሌ:- ሁለት ብር ኖሮን አንዱን ብንሰጥ ከሰጠንም በኋላ ምን ይውጠ ኛል የሚለው ስጋት አለማመን (አለመታመን) ነው:: ምንም እንኳ ለነገ ያስቀመጥነው ባይኖረንም የማያቋርጠውና የማይደ ርቀው ምንጭ ጌታ ኢየሱስ መታመኛችን ከሆነ ለነገ የሚ ሆን አለን::

እያየን ባለነው በዚህ በ1ቆሮ 12÷26 ላይ እንደምናነበው" አን ዱም ብልት ሲሰቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ አንድ ብልትም ሲከብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል" ይላል::

በአካላችን ላይ ካሉ ብልቶች አንዱ ቆስሎ በህመም ምክንያት ሲሰቃይ አብረውት ሌሎችም ብልቶች ተካፋይ በመሆን ይሰቃ ያሉ:: አፍንጫ ሲመታ ሀይን ያለቅሳል፤ እንዲሁም የአንድ አካል ብልቶች እስከሆንን ድረስ አንድ ብልት ሲሰቃይ ሊሰማን ይገ ባል:: ማንም ሰው እጁ ወይም እግሩ ቢቆስል ሕመሙ በዚያው ቦታ ላይ ብቻ ተከልሎ አይቀርም፤ ትኩሳቱ በሰውነቱ ውስጥ ያል ፋል፣ ይሰራጫል:: በዚህ ምክንያት ስቃዩ ለብልቶች ሁሉ ደርሶ አካልን ሁሉ ያሳምማል፣ ያስተኛል:: አንዳንድ ጊዜ እንዲህ እን ላለን ሕመሙ ያለው እግሬ ላይ ነው፤ ለምን ስሜቱ እዚያው ላይ አያበቃም? ሕመም ለፈውስ የሚጣራ ጥሪ ነው:: ብዙ ጊዜ ወደ ህክምና የምንሄደው ሲያመን ነው በአንጻሩ ሕመሙ ከመ

ላው ሰውነታችን ላይ ቀነስ ሲያደርግ ሕክምናውንም ቸል እን
ለዋለን።

አንድ ብልት ሲሰቃይ ሌላው ብልት አብሮ የሚሰቃይ ከሆነ
ታማሚው ብልት ፈውስ እንዲያገኝ ሌሎች ብልቶች ይሯሯጣሉ።
ብዙ ጊዜ ከሰውነታችን አንዱ ሲታመም የህመሙን ስሜት
ለማደንዘዝ የማደንዘዣ መጽሐኒቶችን እንወስዳለን። ማደንዘዣ
መውሰድ ምናልባት በሽታችን መፍትሔ እስኪያገኝ ይረዳ ይሆ
ናል። ይሁን እንጂ ሕክምና ማግኘት አለበት። ማደንዘዣ ወሰ
ደን በሽታው ተወገደ ማለት አይደለም። ማደንዘዣ እየወሰድን
በሽታውን ዝም ብንለው ቀስ እያለ ሁሉንም የአካል ክፍሎች
ያጠቃል።

አንዳንድ ጊዜ የሌላውን ብልት ስቃይ እንዳይሰማን የምንውጣ
ቸው ማደንዘዣዎች አሉ። ምናልባት እነዚህ ማደንዘዣዎች የተ
ለያዩ ይሆናሉ። ለምሳሌ አንድ በጌታ የሆነ ወንድማችን ጉዳት
ሲደርስበት ከመርዳትና ከማጽናናት ፈንታ ይበለው ጌታ ሊያስ
ተምረው እየቀጣው ነው እንላለን። ሰውየውን ላለመርዳት "እግ
ዚአብሔር እየቀጣው ነው" 'እያስተማረው ነው' ተወው ማለት
ይህ ራሱ አንድ ማደንዘዣ የምንወስደው የፈራጅነት፣ የግድ
የለሽነት ችግራችን ነው። ነገር ግን ክፍሉ "አንድ ብልት ሲሰ
ቃይ ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው ይሰቃያሉ አንድም ብልት ሲከ
ብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል" ነው የሚለው።

ብዙ ጊዜ እንደሚታየው አንድ ብልት ሲሰቃይ ያንን ብልት ከስ
ቃይ ማውጣት ይቀላል? ወይስ አንዱ ብልት ሲከብር አብሮ
መደሰት? አብሮ መደሰት ከባድ ነው። ለራሳችን ክብር ስለምን
ፈልግ ሌላው ከእኛ ይልቅ የከበረ ሲመስለን ጥሩ ያልሆነ ስሜት
ይረጭብናል። አንዱ ከእኛ ቀድሞ በረከት ካገኘ "ወይኔ" እንላ
ለን። "ጌታ ሆይ ምነው እኔን ረሳኸኝ?" የሚል ሙግት ውስጥ
እንገባለን። ርግጥ ሌላው ሲሰቃይ እኛ የደረስንበት ደረጃ ገና
ስላልደረሰ እርሱን ማውጣቱ ለእኛ ቀላል ይሆናል። የከበረ እንደ



ሆነ ግን እኛን ትቶ ወደ ላይ መውጣቱ ነው ብለን ያመናል።
እኛ ዝቅ ለማለታችን ሰበብ እንደ ሆነ በኃሉታዊ መልኩ ሁኔ
ታውን እንመለከታለን።

ለምሳሌ ዐሥር ሥራ አጦች፣ ሥራ እንዲያገኙ አብረው መጸለይ
ቢጀምሩና ጌታም መልስ በመስጠት በቅድሚያ ሰባቱ ሥራ
ቢያገኙ ያገኙት ወንድሞች ለቀሩት ለሦስቱ ጌታ ሥራ ስጠን
ቢሏቸው ሥራ ያላገኙት ቶሎ የሚያስቡት ስለ ራሳቸው ነው።
ከዚያም የሚሉት "ጌታ ሆይ ምነው እኔን ረሳኸኝ?" ነው ወይስ
"የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን ወንድሞቻችን ሥራ አገኙ
ልን!" ይላሉ? የቱ ፈጥኖ ይታሰባል? ምነው እረሳኸኝ የሚለው
አባባል ጥያቄ ሆኖ አእምሮአቸውን ይይዛል። አንዱ ሥራ ሲያጣ
ማስተዛዘን የተለመደ ነው። ነገር ግን አንዱ ሥራ አጥቶ ኖሮ
ከእኛ ደመወዝ ይልቅ ዳጎስ ያለ ደሞዝ ያለበት ደህና ሥራ
ድንገት ያገኘ እንደ ሆነ አንዳንዶቻችን ዐይናችን ድፍርስ ይልና
ፊታችን ይቀላል። አሁን እኮ ሊኮራ ነው እያልን መጥፎ መጥፎ
ነገር እናስባለን። እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም። አንዱ ብልት
ለሁሉም ነው እንጂ ለሌላው የሚኖር ከሆነ ጭንቀት የለውም።
ጭንቀትና ችግር ያለው በውድድርና በሽቅድድም ውስጥ ነው።
የውድድር ነገር ቀርቶ ትብብር ከሆነ ሥጋት ይቀራል። በአካላ
ችን ላይ ያሉ ብልቶች ልንኖረው የሚገባውን እውነት ያስተም
ሩናል።

በዓለማችን ላይ ብዙ ጥሩ የእግር ኳስ ተጨዋች ቡድኖች አሉ።
እነዚህ ተጫዋቾች ወደ ሜዳው ገብተው ኳስ ሲጫወቱ ከብል
ቶቻቸው ውስጥ አቀንቃኝ ብልቶች አንደኛው እግር ሲሆን
በሁለተኛ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ደረትና ጭንቅላት ናቸው።
በእዚህ የእግር ኳስ ጨዋታ ውስጥ ሁሉም የየራሳቸው እንቅስቃሴ
ቢያደርጉም ከብልቶች መካከል አላስፈላጊ ያልሆነና እንደ ከይሲ
የሚቈጠረው እጅ ነው። እጅ በእግር ኳስ ጨዋታ ውስጥ ለግብ
ጠባቂው ካልሆነ በስተቀር ኳስ እንዲነካ አይፈቀድም። የብልቶ

ችን ሩጫና ድካም ከንቱ ያደርጋል፡፡ በጨዋታ ውስጥ ተጨዋቾች ለፍተው ለፍተው ወደ ግቡ ሲሄዱ እጅ ሮጦ ኳሱን ተንቀኅ ቅገ የነካ እንደ ሆነ ነገር ሁሉ ይበላሻል፡፡ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ነገሮች ተሳክተው ድል ተገኝቶ በጨዋታ ውስጥ በአሸናፊነት ከተወጣ በመጨረሻ የክብር እንግዳውን ለመጨበጥና ዋንጫውን ለመውሰድ የሚመጣው እጅ ነው፡፡ እጅ ዋንጫውን ለመቀበል ወደ ክብር መቀመጫው (ትሪቡን) ሲመጣ እግር ድካሙ የእኔ ነው አልሄድም አይልም፡፡ ምክንያቱም አንዱ ብልት ሲከብር ብልቶች ሁሉ ይከብራሉ፤ አብረው ደስ ይላቸዋል፡፡

ሌላው ከብልቶች የምንማረው በደልን አለመቍጠር፣ ቂም አለመያዝን ነው፡፡ ጥርስ ምላስን በሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ቢነክስ ወይም በጕዞ ላይ እግርና እግር ቢጋጩ አንዱ በሌላው ላይ በደል ቈጥሮ በኵርፊያ አይለያይም፡፡ ህመሙ እስካለ ድረስ ጥንቃቄ አድርገው ከዚያም ሁሉንም ረስተው የጋራ ተግባራቸውን ተስማምተው መፈጸምን ይቀጥላሉ፤ ይቅር ይባባላሉ፡፡

የእግሮችንም አረማመድ ስንመለከት አንዱ ሌላውን በማስቀደም እንጅ ሁለቱም በእሽቅድምድም መንፈስ በአንድ ጊዜ ተነሥተው ወደ ፊት ለመራመድ፣ ለመቅደም የሚሞክሩ አይደሉም፡፡ አንዱ ሌላውን ሲያስቀድም የቀደመው እግር ደግሞ ቆሞ ሌላኛውን እግር ቅደም ይለዋል፡፡ በዚህ ረገድ እግሮች አካልን ይዘው ይጓዛሉ፡፡ ተግባራቸውን በመከበባርና ግራ እግር ቀኝን አንተ ትቀድም፣ ቀኝ እግር ግራን አንተ ትቀድም በመባባል ሳይጋጩ ይቀጥላሉ፤ የአካልን ዐላማ ያራምዳሉ፡፡

እጅም በከፍታ ቦታ በትከሻ ላይ የተንጠለጠለ ቢሆንም ዝቅ ብሎ የእግርን ቈሻሻ ለማስወገድ፣ ያለመጠየፍ የሚያጥብ እርሱ ነው፡፡



ከታች ያለው እላይ ላለው ምክንያት ቢሆንም እላይ ያለው ደግሞ ዝቅ ብሎ የታቹን ጕድለት ለማስወገድ ትህትናንና ትጋትን ያሳያል፡፡

በዕድገት አኳያም ስንመለከት በብልቶች መካከል የተመጣጠነ ዕድገት ነው የምናየው፡፡ አንድ ብልት ሌሎችን ጥሎ ብቻውን አያድግም፡፡ በዚህም በሽቅድምድም የአስተዳደግ አካሄድ ጤንነት አይኖርም፡፡ እጅ ብቻውን ልደግ ብሎ ቢመዘዝ የቁም መጥረጊያ ሆኖ ጣቶች መሬትን እያሰሱ የሚሄዱ ነው የሚሆኑት፡፡ አሊያም እጅ እግር ሆኖ ይገኛል፤ ካንሠርም እኮ ዕድገት ነው፤ የሴሎች የተፋጠነ መባዛት ነው፤ ችግሩ ገዳይነቱ የተመጣጠነ ዕድገት አለመሆኑ ነው፡፡

በብልቶች መካከል የሚታየው መተባበርና መተሳሰብ በዐዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብ መካከል ቢታይ ምን ዐይነት መተናነጽ፣ ምን ዐይነት ውጤት በተገለጠ ነበር፡፡
የተጠራንበት መጠራት ከፍ ያለ ነው፡፡ እኛ ግን ያለንበት ስፍራ ታች ነው፡፡ ወደ ተጠራንበት ደረጃ ማናችንም በተፈጥሮ አስተሳሰባችንና በግል ኀይላችን ልንወጣና ልንደርስበት አንችልም፡፡ ይህንን ሊያደርግ የሚችለው በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው፡፡ ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ተቈጣጣሪነትና ምሪት ካላስገዛን በስተቀር ሊሆን የማይችል ነው፡፡

የሚያረካ ሕይወት ለክርስቶስ የተኖረ ሕይወት ነው፡፡ እኔ ለራሴ የኖርኩትን ኑሮ ወደኋላ ዘወር ብዬ ስቃኘውና ሳየው ከእግዚአብሔር ሀሳብ ይልቅ የራሴንና ራሴን ያስቀደምሁባቸው ጊዜያቶች አያስደስቱኝም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋና ቸርነት ለሌላው የሆንኩትን ሳስብ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ ብዙ ትርምስምስ ያለው በሸለቆው ስፍራ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃዱና ሀሳቡ ባለበት በከፍታው ስፍራ ስንሆን ግን ይኸ ችግር አይኖርም፡፡ ለምሳሌ በአውሮፕላን ስንጓዝ የነገሮች ትልቅነት ምድርን ለቀን

በአየር ላይ እስክንንሳፈፍ ድረስ ነው:: ከዚያ በኋላ ግን ትልቅ ሆኖ ይታየን የነበረው ነገር ሁሉ እያነሰ፣ እያነሰ ይመጣል:: በመንፈሳዊው ሕይወት ዓለምም እንዲሁ ነው:: እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ፈቃዱ፣ ምግባሩና ሐሳቡ ባለበት ከፍታ ላይ ሲያስቀምጠን የሥጋዊ ነገር አላፊ የሆነው ኢምንት ይሆንብናል::


ብዙ ግዜ የምንጣላውና ቂም የምንያያዘው በመንፈሳዊ ሕይወታችን ታች ስንወርድ፣ ዝቅጥ ስንል ነው:: ወደ ላይ ስንወጣ ግን ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር እንዳለ የበደሉንን ይቅር እንላለን:: በዚህ መንፈሳዊ የከፍታ ስፍራ ላይ ጥዳያችን ሰዎች ሳይሆኑ እግዚአብሔር ይሆናል:: ከሰዎች ጋር ብርቱና መራራ ፍልሚያ ውስጥ የምንገባው ጥዳያችን ሰዎች ሲሆኑና ተራ ኑሮ ስንኖር ነው:: ሰይጣን ሰዎች በተለያየ ነገር ሲወጋጉን ጥዳያችን እንድናደርጋቸው ይፈልጋል:: ነገር ግን እነርሱ የሚያደርጉብንን ክፋት ትተን ጥዳያችን እግዚአብሔር ሊሆን ይገባል:: እርሱ ጥዳያችን ሲሆን ለሰዎች እንኖራለን:: ወደዚህ ዐይነት ሕይወት ስንመጣ የሰዎችን በደል አንቈጥርም፤ ሌላው ወንድምም ስለ ተቀበለው መልካም ነገር እግዚአብሔርን እናመሰግናለን::

እስቲ አንድ ጊዜ የሰውን መለኪያ ወስደን አንዳንድ ሰዎች በተባረኩበት ነገር እግዚአብሔርን ከልብ ሆነን እናመስግን በረከቱ ይመጣል:: ሕይወታችን ለሌሎች በጎ በማሰብ ሲሞላ እግዚአብሔር በሰማያዊ በረከት ይባርከናል:: ሰይጣን ክርስቲያኖችን የሚንቀን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልኖርን ልክ ነው:: ነገር ግን ለእርሱ በኖርን ቍጥርና ጥዳያችንም እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን የጽድቅ ሕይወታችን እያስፈራው ይመጣል::

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን ክርስቲያኖች በመካከላቸው በነበረው መከፋፈልና መለያየት ምክንያት ሲነቅፋቸው እናንተ ገና ሥጋውያን እንጂ መንፈሳውያን አይደላችሁም ብሏቸው ነበር:: (1ቆሮ 3፥1-4) መለያየትና መከፋፈል የሥጋዊነት ምልክት ነው የመንፈሳዊነት መለኪያው ግን በኅብረት መሥራትን በአንድነት መሆን ነው:: ስለዚህ በሰላም ማሠሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ ይለናል (ኤፌ 4፥3)::



ከጠባብ አመለካከት እግዚአብሔር ይጠብቀን!






በአካል ብልቶች መካከል ያለው ግንኙነት መቀባበልን፣ መተባበርና መተሳሰብ ነው:: ይህንኑ ዐይነት ግንኙነት በክርስቶስ ቤተሰብ ውስጥ ይጠበቃል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ማኅበረ ምእመናንን አስመልክቶ "እርስ በርሳችሁ ..." በማለት የተሰጡት ትእዛዞች አዎንታዊ የተግባር ምላሽ ቢያገኙ የክርስቶስ አካልነትን ቤተ ክርስቲያን በጎ አድርጋ በገለጠች ነበር:: ፍቅሯም፣ ኀይሏም፣ ክብሯም፣ ባለ ሥልጣንነቷም በላቀ ነበር::

እርስ በርሳችሁ በሚል ቀዳሚ ሐረግ ከተገለጡት እሴቶች መካከል ዐብይ የሆኑትን እንጠቃቅስ:

በአዎንታዊ:-

1. እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ (ሮሜ12፥10፤1ተሰ4፥9፤1ጴጥ1፥22፤ዕብ13፥1)
2. " ተከባበሩ (ሮሜ 12፥10)
3. " ተቀባበሉ (ሮሜ15፥7)
4. " ይቅር ተባባሉ (ቈላ3፥13)
5. " ቸሮች/ሩኅሩሖች ሁኑ (ኤፌ 4፥32)
6. " ተስማምታችሁ ኑሩ (መዝ 133፥1፤1ዮሐ1፥7)
7. " ተቻቻሉ/ታገሡ (ኤፌ 4፥21፤ ቈላ3፥13)
8. " ተሳሰቡ/ተደጋገፉ (1ጴጥ3፥8፤ ዕብ10፥24)
9. " ተማማሩ/ተገሳሰጹ (ቈላ 3፥16)
10. " ተመካከሩ/ተበረታቱ (ዕብ 10፥25)
11. " ሰላምታ ተሰጣጡ (1ጴጥ 5፥14)

በአሉታዊ:-

1. እርስ በርሳችሁ አትወነጃጀሉ/አትፈራረዱ (ሮሜ 14፥13፤ ያዕ4፥11)
2. " ውሸትን አትነጋገሩ (ኤፌ4፥25)
3. " አታጕረምርሙ
4. " አትበላሉ /አትነካከሱ (ገላ 5፥15)

5. " አትጐነታተሉ /አትቀናኑ (ገላ5፥26)

6. " ክፉ አትመላለሱ (1ተሰ5፥15)



## እርስ በርሳችሁ:-

ሮሜ 12፥4-5፣ 9-16፣ 15፥7፣ ኤፌ 4፥2:32፣ ቆላ 3፥9-17

**እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ**
- ለሌላው ክፉ አለመመኘት
- ሌላው ክፉ እንዳይደርስበት መፈለግ
- ለሌላው መልካም (ከእኛም የሚበልጥ) ሲሆንለት መደሰት (የሌፍና ወንድሞቹ)

**» ተከባበሩ**
- የራስን ክብር አለመፈለግ አለመሽቀዳደም ( X አለመውደድ ማቴ 23)
- (አጋር፣ ዮሐንስ መጥምቁና ጌታ ኢየሱስ፣ የዘብዴዎስ ልጆች)
- ክብር ያስፈልገናል ሆኖም የራስን ክብር መፈለግ የለብንም ክብር እንዳንሻ
- ክብር እንቀበላለን እንጂ አንነጥቀውም፣ ነጥቀን ለራስ አናደርገውም
- ሌላውን ለማክበር «መጐንበስ»

**» ተቀባበሉ**
- የሌላውን ማንነት መቀጠር
- ለሌላው ተስጥኦ ሥፍራ መስጠት
- ለሌላው ዋጋ መስጠት

**» ተስማሙ (ኑሩ)**
- ለሌላው ቦታ አመቻቹ
- እልፍ እልፍ /ፈቀቅ ፈቀቅ በማለት ተደላደሉ
- ለኅብረት የሚጠበቅባችሁን የዘመትር ድርሻ መሥዋዕት ስጡ

**» ትዕግሥተኞች ሁኑ**
- መከራን /ችግርን ቻሉ
- ልባችሁን አስፉ፣ ችግርን ለመፍታት ጊዜን እንደ አማራጭ ተቀበሉ

**» ይቅር ተባባሉ**
- የበደልን መዝገብ (የስሜት) መሠረዝ
- በደልን ከበዳዩ መለየት
- በደል ለርዳታ የሚጣራ ጩኸት መሆኑን መገንዘብ ነው

**» ቸሮች /ሩኅሩሖች ሁኑ**
- የተቸሩትንና የቸርነት መዝገብ አለመያዝ
- ማበደር አይደለም ምላሽ አይጠበቅበትም
- የቸርነት ምክንያት

**» እውሸት አትነጋገሩ**
- ውሸትን ጥበብ ነው አትበሉ
- ውሸትን ማምለጫ መንገድ አታድርጉ

**» አትወነጃጀሉ/አትፈራረዱ**
- ከሳሽም ዳኛም አትሁኑ፤ ከሳሽና ደኛ ልዩ ልዩ ሲሆኑ ግድ ነው
- ሕግ አውጪም ሕግ አስፈጻሚም አትሁኑ

**» ተማማሩ/ተገሳሰጹ (በጥበብ)**
- እንዱ ሌላውን ያቅናው፣ ያንጸው
- መገሰጽ ተገቢ ጊዜን፣ ጠንቃቃ ቃላትን የፍቅር መንፈስን ይጠይቃል

**» ተመካከሩ/ተበረታቱ**
- በግል ሀሳባችሁ ብቻ አትያዙ፣ ለራሳችሁ ሀሳብ ዘብ አትቁሙ
- በሌላው ዘንድ ያለውን በጎ ነገር እንዲፋፋ አድርጉ፤ መልካምነቱን
- ግለጹ፤ ጠቀሜታውን መስክሩ

**» አትናጩ**
- ውድድር፣ ፉክክር፣ መሽቀዳደም፣ ራስን ከሌላው ጋር ማስተያየት
- ለሁከት፣ ለአድመኝነት፣ ለጥላቻ፣ ለቅናት፣ ለመለያየት ይጋብዛል

## 2) ይቅር መባባል

*እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ሩኅሩሆች ሁኑ፣ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ::* (ኤፌ. 4፥32)

*«በዚህ ጊዜ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ ጌታ ሆይ፤ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን? አለው:: ኢየሱስም "እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም" አለው:: ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣ በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች:: ሂሳቡን ማጣራት እንደጀመረም ዐሥር ሺህ ታላንት ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ አቀረቡለት:: አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ መክፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ:: በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ላይ ወድቆ፣ 'ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ' ሲል ለመነው:: ጌታውም አዘነለትና ማረው፤ ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው:: ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ አንድ መቶ ዲናር የእርሱ ዕዳ ያለበትን አገልጋይ ባልንጀራውን አግኝቶ አንቅ አድርጎ በመያዝ፣ 'ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ' አለው:: ባልንጀራው አገልጋይም ከፊቱ ወድቆ፣ ታገሠኝ እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው:: ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነበረ፣ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ ወህኒ ቤት አስገባው:: የሆነውን ነገር ያዩ ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤ ሄደውም ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው ነገሩት:: በዚህ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ፤ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልትምረው አይገባህም ነበርን?' በቍጣም ያለበትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ ለአሳሪዎች አሳልፎ ሰጠው:: ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኋል::"* (ማቴ 18፥21-35)

ሌሎችን ይቅር የማለታችን መነሻ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ እኛን ይቅር ማለቱ ነው:: እናንተ እግዚአብሔርን በድላችሁ ፍርድ የሚገባችሁ ሆኖ ሳለ ፍርዳችሁን እርሱ ተሸክሞ እናንተን እንዲቀበል ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጥቶ ይቅር ካላችሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ ይለናል ቃሉ:: «መባሕን በመሰዊያ ላይ ብታቀርብ በዚያም በወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ መባህን ትተህ ሂድ ከወንድምህ ጋር ታረቅ» ነው የሚለን ጌታ::

ከወንድሞች ጋር ቅሬታ ኖሮን ይቅር ሳንል ወደ ጸሎት ብንሄድ ጸሎታችን ይያዛል:: ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ አንችልም:: 'አባታችን ሆይ' የሚለውን ጸሎት ስንጸልይ «በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል» እንላለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ይቅርታ በጣም ወሳኝ ነገር እንደ ሆነ ያስተምረናል:: ይቅር ማለት የሕይወት ልምዳችን ሊሆን እንደሚገባ ያስተምረናል::

መቼም ይቅርታን ለመለማመድ ከይቅርታ በፊት መኖር ያለባቸው ነገሮች አሉ:: በደል መኖር አለበት፤ በደል ካለ በዳይም ተበዳይም አለ:: አንድ ሰው በሌላው ሰው የሚያደርሰው ማንኛውም ጥቃት በደል ይሆናል:: ይቅር ማለት ደግሞ የበደልን መዝገብ መሰረዝ ማለት ነው::

ይቅር ማለት በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው:: ይቅር ማለት የሚከብደን ለራሳችን የከበረ ዋጋ መስጠት ስለምንፈልግ ማንነታችን እንዲነካ ስለማንወድ ይቅር ማለት ይከብደናል::

ጴጥሮስ ጌታን፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው ይልና ራሱ መልሱን ይሰጣል:: ሰባት ጊዜን? ይላል::

ጌታ ግን ኀባ ጊዜ ሰባት ይለዋል:: ይሄ ደግሞ 490 ይሆናል:: መቼም እግርና እግርም ይጋጫልና ሰው መጋጨቱ አይቀ ርም:: እርሱ በበደል ደረጃ የሚቆጠር አይደለም::

ነገር ግን አንድ ሰው በሕይወታችን ምንም ያህል ጊዜ ቢበድ ለን ይቅር ለማለት ወሰን እያስፈልገውም:: ጌታ ኢየሱስ መን ግሥተ ሰማይን ባሮቹን ሊቆጣጠር በወደደ ንጉስ ይመስላታል:: መቆጣጠርም በጀመረ ጊዜ እልፍ ወይም አስር ሺህ መክሊት ዕዳ ያለበት አንድ ሰው ተገኘ:: ስለዚህም ይህን ዕዳ መክፈል ነበረ በት:: ዋጋው ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ያንን ዋጋ ወደ መሸፈን ለመጠጋት ያለው ንብረት ሁሉ እንዲሸጥ ተወሰን:: ያ ብቻ አልበቃም:: ልጆቹ፣ ሚስቱ፣ እርሱም እንዲሸጡ ተወሰነ::

ይኸ በሚሆንበት ጊዜ ዕዳው ከባድ ነው ልከፍል አልቻልኩም:: ብሎ በጌታው እግር ሥር ወደቀና ታገሰኝ፣ ጊዜ ስጠኝ አለው:: ተስፋ ይሆንለት እንደ ሆነ እንጂ ያንን ሀብት ሁሉ ሊከፍል የሚችል ሆኖ አይደለም:: ምክንያቱም ንብረቱን ሚስቱንና እር ሱን የሚያሸጥ አስር ሺህ መክሊት መክፈል የሚችል አይመስ ልም:: ጌታው አዘነለትና ይቅር አለው፣ ዕዳውን ተወለት፣ ነፃ አወጣው:: ንብረቱን፣ ልጆቹን ሚስቱን ራሱን ነፃ አወጣቸው::

ግን ይኸ ሰው አንድ ባለ ዕዳው የሆነ ሰው ያውቅ ነበር:: ያ ሰው ዕዳው 100 ዲናር ነበር:: ተበዳሪውን ወይም ባለ ዕዳውን ባገኘ ጊዜ ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው:: ይሄ ሰው ዕዳው ሲማር ለት ፈንጠዝያ ማድረግ ነበረበት:: ይኸ እልፍ መክሊት ወደ ዲናር ሲለውጥ ባልሳሳት ስልሳ ሚሊዮን ዲናር ያህል ነው:: ያኛው መማር ያለበት መቶ ዲናር ነው:: ስናካፍለው 600 ሺህ ጊዜ ነው የተማረው:: አሁን ባንክ 600 ሺህ ዶላር ይቅር ቢለን 1 ዶላር ይቅር ማለት ሲከብደን ያሳዝናል:: ይሁንና የእርሱን ባለ ዕዳ ሄደና አነቀው:: ስለዚህም ባልንጀራው ባሪያው ወድቆ ታገሰኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው:: እርሱም አልወ



ደደም:: እዳውንም እስኪከፍል ድረስ በወህኒ አኖረው:: ይህን የሰሙ ባልንጀሮቹ ባሮች ለጌታው ተናገሩ:: ጌታው በዚህ ነገር ተናደደ፤ አንተ ክፉ አገልጋይ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተው ሁልህ፤ እኔ እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልትምረው አይገባህም ነበርን? በማለት ዕዳውን ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ ላይወጣ ለአሳሪዎች አሳልፎ ሰጠው::

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ:: ልጅ የአባቱን ተግባር መከተል አለበት:: የእግ ዚአብሔርም ልጆች የአባታቸውን ተግባር ሊከተሉ ይገባል::

አይሁዶች አንድ ጊዜ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሲከራከሩ እኛ ለማንም ባሪያ አልሆንም የአብርሃም ልጆች ነን ይሉ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ደግሞ እናንተ የአብርሃም ልጆች አይደላችሁም:: የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ ኖሮ የአብርሃምን ሥራ ትሠሩ ነበር:: የሥራ መመሳሰል ስለ ሌለ ልጆች አይደላችሁም:: እነርሱ የዘር ነገር ሲቈጥሩ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ የጠባይ፣ የግብር ነገር ነበር የሚቈጥረው:: 'እናንተ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፤ ዲያብሎስ ከጥንት ነፍስ ገዳይ፣ ሐሰተኛ ነው' አላቸው::

ሀ) ይቅር ማለት የበደልን መዝገብ መሰረዝ ነው

በውስጣችን ስለ ሰዎች የምንመዘግበው ብዙ መዝገብ አለን:: ሰዎች እኛን የበደሉበትን በደል እንመዘግብበታለን:: መዝግበን ካስቀመጥን ደግሞ በቀልንም እናስባለን:: ምላሹን እንሰጣለን::

ይቅር ስንል በደልን ከበዳዩ ለይተን ጠቀሜታ ባለው መንገድ መመልከት መቻል መጀመራችን ነው:: መንገድ ላይ ድንጋይ አደናቅፎ ሲመታን ልንወድቅ፣ ልንላላጥ እንችላለን:: ከተነሣን በኋላ ግን ያን ያደናቀፈንን ድንጋይ ትተን ወይም ከመንገድ ዞር አድርገን እንሄዳለን:: እኛንም ሌሎችንም መልሶ እንዳያደ

ናቅፍ ጤቀቅ እናደርገው ይሆናል እንጂ ቤት ከገባን በኋላ ማታ ስንተኛ ያ አድራሻ ቢስ፣ ሽረፍራፋ፣ ጉርበጥባጣ ድንጋይ እያልን ብዙ በስሜታችን ውስጥ የምናብሰለስለው፣ የምናሳድ ረው ክፉ ነገር የለም:: በድንጋዩ ላይ ቂም አንይዝም:: በደሉን ከበዳዩ ለይተን አየነው ማለት ነው:: እንደእስፈላጊነቱ ድንጋዩ ሌላ በደል እንዳያመጣ ከመንገድ አስወግደነዋል:: ይቅር ስንል በደሉን ከበዳዩ እንለያለን፤ በደሉን ለብቻ በመመልከት በዳዩን ነፃ እናወጣዋለን::

ለ) ይቅር ስንል በደልን እኛን የሚቀርጽና የሚገነባ መሣሪያ አድርገን እንመለከታለን:-

ሰዎች ሲበድሉን በቀና ከተመለከትነው ያ በደል አንድ ከኛ ዘንድ የሚታረም፣ የሚቃና ወይም መሻሻል የሚገባው ነገር እንዳለ ሊያመላክተን ይችላል:: ጥፋተኛ ሌላውም ወገን ቢሆንም እንኳ አንድ የሚሻሻል ወይም የሚታረም ነገር ይኖራል::

አንድ ጊዜ ዳዊትን ሳሚ ሰደበው «ተውት እግዚአብሔር ልኮት ይሆናል» አለ:: እና የሚነቀፍ ነገር እኔ ውስጥ ይኖር ይሆናል:: ተመልከቼ የማጠራው ነገር ሊኖር ይችላል:: አንዳንድ ሰዎች ሲበድሉን ምላሽ ከመስጠት ፈንታ ይቅር የምንላቸው ከሆነ እነርሱን ነፃ እናወጣና ምናልባት በኔ ዘንድ የሚታረም የሚ ስተካከል ነገር አለን? ብለን መመልከት እንችላለን::

ሐ) ይቅር የሚል ልብ ሲኖረን በደል ለርዳታ የሚጣራ ጩኸት መሆኑን እንገነዘባለን

*አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ ስንሄድ፣ በጥንቆላ መንፈስ ትንቢት የምትናገር አንዲት የቤት አገልጋይ አገኘችን፤ እር ሷም በዚህ የጥንቆላ ሥራዋ ለአሳዳሪዎችዋ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው ነበር:: ይህችው አገልጋይ ጳውሎስንና እኛን*



*እየተከተለች፣ "እነዚህ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚነግሯ ችሁ፣ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!" በማለት ትጮኽ ነበር፤ ይህንም ብዙ ቀን ደጋገመችው፤ ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ በመታወኩ ዞወር ብሎ ያን መንፈስ፣ "ከእርሷ እንድ ትወጣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃ ለሁ!" አለው፤ መንፈሱም በዚያው ቅጽበት ወጣላት::*

አጋንንት ያደረባት ሴት እነ ጳውሎስን አስመልክታ «የመዳ ንን መንገድ የሚነግሯችሁ ሰዎች ናቸው» እያለች ትጮህ ነበር:: መቼም ከአፏ የወጣው ቃሉ ምንም ክፋት የለውም፤ እንዲያውም ውብ ነው:: ነገር ግን የነጳውሎስን ተልዕኮ ታደናቅፍ ነበር:: ኣንዳንድ ጊዜ መልካም መስሎ የሚመጣ ነገር ጥቃት መሆኑን ቶሎ አንገነዘብም:: ጳውሎስም ዘግይቶ ነው ልብ ያለው፤ ሆኖም ጩኸቷ ጳውሎስን ወደ ችግሯ ጠራው:: ያም መሠረ ታዊ ችግሯ የሟርት መንፈስ ነበር:: ስለዚህ ዞረና አንተ መን ፈስ ውጣ ብሎ አዘዘው፤ ክፉውም መንፈስ ለቋት ሄደ::

ሰዎች ብዙ ጊዜ ሰውን የሚበድሉት ሲቸገሩ ነው:: ጊዜ ወስደን ብንመረምር ሰዎች እኛን ሲበድሉ ታውከዋል፤ ተቸግረዋል:: ስለዚህ ሰዎች ሲበድሉን ወደ ችግራቸው ሊያመላክተን ይገባል:: ባብዛኛው በደል ወደ በዳዩ ችግር የሚጣራ ጩኸት ነው:: ይህ ነገር ብዙ ጊዜ ለማወቅ ፈልጌ የመረመርኩት ነገር ነው:: እን ዲያውም ለበደል ምላሽ ልሰጥ ከተንደረደርኩ በኋላ እውነታው ሲበራልኝ ተመልሼ ለበዳዩ የራራሁባቸው ጊዜያት ብዙ አሉ::

አንድ ጊዜ አንድ ቢሮ ውስጥ የሚሠሩ ሁለት ጓደኛሞች ነበሩ:: ዘወትር ደህና ተጣጥመው ነበር የሚሠሩት:: አንድ ቀን ጥዋት አንደኛው በጣም መነጫነጭ አበዛ:: ሁለተኛው በሥራ እንዲረ ዳው አንዳንድ ወረቀት ይዞ ርዳኝ ሲለው ተጠያቂው 'ተወኝ ባክህ' አለውና ተመለሰ:: አሁንም ቆይቶ ርዳኝ ብሎ መጣ:: በዚ

ህም ጊዜ ሰውየው 'ተወኝ ነው የምልህ፤ ተወኝ አንተ ሰውዬ'
ብሎ በቍጣ መለሰለት። በዚህ ጊዜ ያኛው ጓደኛው ግራ ገባው።
እያዋዛ፣ በአነጋገሩ እያለሳለሰው «ዛሬ ምን ሆነሃል?» አለው።
«አቦ ተወኝ» ብሎ እያጉተመተመ 'ማግባት መቃጠል አይደ
ለም እንዴ?' አለው።

ለካስ ከባለቤቱ ጋር ተጣልቶ "ብትፈልጊ ገደል ግቢ" ብሏት፣
እርሷም ሻንጣዋን ይዛ ለመሄድ እየተዘጋጀች ነበር። ብዙ ጊዜ
ንዴትና እልህ የማንወጣውን ዳገት እንድንያያዘው ያደርገ
ናል፤ ዕዳ ውስጥ ይጨምረናል። ከዚያ በኋላ ችግሩን ይነግረ
ዋል። «ባክህ ተጣልተናል እርሷም አሁን ልትሄድ እየተዘጋጀች
ነው» ይለዋል። የዚህን ጊዜ ስልክ ወደ እርሷ በመደወል፣ ሥራ
ውን ትቶ ወደ ቤቱ ይሄድና ይመክራል፤ ኋላም ሁለቱንም
ያስማማል።

የዚያኛው ማመናጨቅ ወደ ችግሩ የሚጣራ ቋንቋ ነበር። ብዙ
ጊዜ ሰዎች ሲቸገሩ ነው ሌላውን የሚያስቸግሩት። እኛ ካልተቸ
ገርን እኮ ሌላውን አናስቸግርም። ሰዎች ሲበድሉን ማሰብ የሚ
ኛለው ይሄ በደል ወደ ችግር የሚጣራ ጩኸት መሆኑን መፈ
ተሽ ነው። እኛ ግን ለበደል ምላሹን መስጠት ነው የሚቀናንና
የምናስቀድመው፤ እና ነገሩ ይሰፋል። ብዙ ጊዜ የዝቅተኛነት
መንፈስ የሚሰማቸው ሰዎች አገርጋሪና ናጩርት የሚሆኑት
ከዚሁ የተነሣ ነው።

በመበደል ወይም በመበዳደል ሰዓት እኛው ከሳሽ እኛው ዳኛ
የሆንን እንደ ሆነ ይበላሻል። እግዚአብሔር ግን ሲዳኝ ሁሉን
በትክክል ያየዋል። እኛ ሰው በድሎን ለበቀል ስንነሳ ስለ ሰው
የው የሚኖረን ስሜት ጥላቻ ነው። ጥላቻ ደግሞ ክፉ መነጽር
ነው። ፍቅር እውር ነው ይባላል፣ ምናልባት ይሆን ይሆናል።
ጥላቻ ግን የሌለውን ጨምሮ ያያል። አንድን ሰው ስንጠላው



ትንሽ ጉድለት ቢኖርበት ጉድለቱን እናሰፋዋለን፤ መነጽራችን
ያጉላዋል፤ መጠኑንም ያባዛዋል። በጥላቻ ውስጥ የሌለ፣ ከነገሩ
ፈንጠር ያለ ሰው ቢመለከተው ጥፋቶቹ ትንሽ፣ ጥቃቅን ሊሆኑ
ይችላሉ። በጥላቻ ውስጥ ስንሆን ግን እናሳድገዋለን። ትንሽዋን
የቴኒስ ኳስ እንደፖሎኒ ኳስ እናስተልቃታለን።

ስለዚህ ይሄ ችግር በቀላሉ ስለሚጠናወተን በቀል ለእግዚአብሔር
ቢሆን ይሻለናል። እርሱ «በቀል የእኔ ነው ይላል» ሮሜ
12፥19)።

እግዚአብሔር በቀል የኔ ነው ሲል እኛ ከዳኝነትና ከመቅጣት
ኀላፊነት ነፃ ነን ማለት ነው። እርሱ ይቀጣል ሲቀጣም ያቅበ
ታል። ቃሉ ክፉን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አትሸነፍ
ይላል። አለበለዚያ በቀል የእኛ ነው ካልን የእግዚአብሔርን
ስፍራ፣ የፍርዱን ወንበር ተጋፋን ማለት ነው። ለእግዚአብሔር
ስንተወው ግን እንረሳዋለን። አንድ ሰው የተቀጣው በኛ ምክ
ንያት እንኳ ቢሆን ተመልሰን ከተውነው ተመልሰን እንራራ
ለን።

ይቅር ስንል በቀል የእግዚአብሔር መሆኑን እንገነዘባለን። አለበ
ለዚያ ለበቀል የምንዘጋጅ ከሆነ ጥላቻ ውስጥ ነው ያለነው።
ደግሞ ሰውን ከጠላነው «ጠላትህ የሚጠላህ ሳይሆን የምትጠ
ላው ነው» ይባላል። አንድን ሰው ከጠላነው እርሱ ጠላን አልጠ
ላን ጠላታችን ነው። እርሱን ሳይጎድልበት፣ ሳይጠቁር፣ ሳይ
ከሳ፣ ሳይሻር፣ ሳያመው፣ ሳይጎዳ፣ ቅስስ ሳይል ወዘተ ... ባየን
ቍጥር በተለያየ የመከፋት ሁኔታ እንበግናለን። እርሱ ትንሽ
የተመሠገነ እንደ ሆነ እንንጨረጨራለን። ሰው ስለሱ መልካም
ያወራ እንደ ሆነ እንበሳጫለን።

እኛ የጠላነውን ሁሉ ዓለም እንዲጠላው ነው የምንፈልገው።
ለእኛ ወዳጆችን የጠላታችን ጠላት ይሆናል። እና ብዙ ጊዜ በጥ

ላቻ እንተባበራለን:: ሰዎችን በጋራ ፍቅር ማስተባበር በጣም
ከባድ ነው:: በጋራ ፍቅር የሚያስተባብር ጌታ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ብቻ ነው:: ሌላው በጋራ ጥላቻ ነው:: የፖለቲካ መሪዎች
ሰውን የሚያስተባብሩት በጋራ ጥላቻ ነው::

በቀን እርስ በርሳቸው የሚናከሱ ውሾች ማታ ጅብ የመጣ እን
ደሆነ ይተባበራሉ:: አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ለማ
ስተባበር ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ካሉት ጋር ማቃረን ለአንዳን
ዶቹ ይቀላቸዋል:: ግን ጥላቻው ሲጠፋ ትብብሩ ይቀራል::

ይቅር ማለት ሸክምን የሚያቃልል ነገር ነው:: ይቅር አለማለት
ወጪው ብዙ ነው:: በመንፈስ በነፍስ በአካላችን እንጐዳለን::
አንድ ጊዜ ክርስቲያን የሆነ ሰው ሌላውን ስለበደለው ተቀይሞ
ታል:: ስለዚህ እሱንም ማየትም ጠልቷል:: እርሱ በሄደበትም
መሄድ አይፈልግም:: እና አንዴ ቸኩሎ ካለበት ከተማ ወደ ሌላ
ከተማ በአውቶቡስ ሊሄድ አውቶቡሱ ውስጥ ሲገባ ያ የሚጠላው
ሰው ቁጭ ብሏል:: ስለዚህም ወረደ፤ ያ አውቶብስ ሞልቶ ከሄደ
በኋላ ሌላ መጠበቅ ነበረበት:: ድምጹንም ላለመስማት የምንጠላ
ከሆነ የሱን መልካም ሰውነት አንወድም:: ብዙ ኪሳራ ከሠረ::
ለቀጠሮውም በሰዓቱ ሊደርስ አልቻለም:: ይቅር በማንልበት ጊዜ
በጣም ብዙ ችግር በራሳችን ላይ እንጨምራለን:: ወደ ባርነት
እንገባለን፤ ነፃነታችን ይገፈፋል:: ከሰይጣንም ጋር ማኅበርተኛ
መሆን እንጀምራለን ምክንያቱም ቶሎ ይቅር ተብሎ ያልተወ
ገደ ቊጣ ውሎ አድሮ መራርነትን ይዞ ወደ መንፈሳችን ሰርጾ
ይገባል:: ፀሐይ በገባበት የቍጣ ዕድሜ ሰይጣን እግሩን ማስገ
ቢያ ስፍራ ያገኛል፤ ያደቆነ ሰይጣን ደግሞ ማቅለሱ አይቀርም::
ቀላሉ ይቅር መባባል ነው::

የክብር ነገር ሲያስቸግር ነው እንጂ ይቅር መባባል ቀላል ነው::
ዛሬ ይቅር ያልኩት እንደ ሆነ ነገ አናቴ ላይ ይወጣል የሚል
የሥጋ አስተሳሰብ ነው:: እግዚአብሔር ካወጣው ይውጣ፣



እግዚአብሔር ያላወጣው ግን ማንም ሊወጣ አይችልም:: እና
ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ጋር ቢያያዝ ይሻላል::

ብትወዱኝ ትእዛዜን ፈጽሙ ነው የሚለን ጌታ ኢየሱስ:: እኛ
ወደነው ትእዛዙን ስንፈጽም የኛን ጉዳይ ስለኛ መብት ተከራካሪ
እርሱ ይሆናል:: ፍሬውን ግን በጊዜው እናየዋለን:: እኛ በነገሩ
ስንገባ ይበለሻሻል::

ባልና ሚስት አንዴ ተኳርፈው ማታ ባል ሲተኛ በዐሥር ሰዓት
ላይ ቀስቅሽኝ ብሎ ለማነጋገር ስላልፈለገ ትራሱ ላይ ጽፎ አስቀ
ምጧል፤ እሷ ደግሞ እንደጠየቃት ዐሥር ሰዓት ላይ ትነቃና ዐሥር
ሰዓት ሞልቷል ብላ ጻፈችለትና በትራሱ አጠገብ አስቀመጠች
ለት ይባላል:: በይቅርታ ቢስነት መኖር ፍዳ ነው:: እና የሚቀ
ለው መንገድ ስንጣላ አእምሮአችን በማያስፈልገው ሥፍራ ላይ
ጉልበቱን ይጨርሳል:: ስንት ሥራ የሚሠራው አእምሮ በዚያ
ይያዛል:: መንገድ ላይ ነጠላ ለብሰን አምሮብን ስንሄድ ትንሽ
ቆንጥር ብጤ ነጠላውን የያዘችው እንደ ሆነ እሷን ማላቀቅ ጊዜ
የሚወስድ ነው::

ጥላቻም ትንሽም ብትሆን ብዙ ሥራ ልንሠራ የምንችልበትን
ጊዜ ያጠፋብናል:: የእንቅልፍን ጊዜም ይጋፋል:: አእምሮ ጥላ
ቻን ምግቡ ሲያደርግ ራሱ ይበላል:: ከዚያም ዐልፎ ሰውነት
ውስጥ መርዝ ሆኖ ይገባል፤ ስለዚህ የሚሻለው መንገድ ይቅር
ማለት ነው::

ይቅር ማለትን አስቸጋሪ የሚያደርገው እኔነት በዙፋኑ ላይ
ሲሆን ነው:: እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ምንም በደል ቢኖር
ከመቶ ዲናር አይበልጥም:: እኛ ግን ምሕረት የተደረገልን እልፍ
መክሊት ሳይሆን ህልቆመሳፍርት የሌለው የትየለሌ ዕዳ ነው::
የይቅርታ መንገድ ሸክማችን የሚቀልበት መንገድ ነው:: አለ
በለዚያ ደግሞ የአእምሮ፣ የነፍስ፣ የስጋ ችግር ብቻ ሳይሆን የመ

ንፈስም ችግር ነው:: ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ
በደላችንን ይቅር በል እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል እን
ላለን:: አለበለዚያ ያ ካልሆነ ተወው ማለት ነው:: መንፈሳች
ንም ይታሠራል:: በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ነገር
ይዘጋል:: እያደርን እየታሰርን እንሄዳለን:: መንፈሳችን እየፈ
ዘዘ፣ እየተራቈተ ይሄዳል::

## 3. ወንጌል ስርጭት - - - የንስሐና የእምነ ጥሪ

"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ"
የሚለው ትእዛዝ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ከጌታዋ የተቀበለ
ችው ተልእኮ ነው:: "የተሰጠውን ተስፋ እስክትቀበሉ ከኢየሩሳ
ሌም አትውጡ፤ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ግን ኀይልን ትቀበ
ላላችሁ .... እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሚለው
መሪ ቃል ዛሬም ለቤተ ክርስቲያን ሕያው መመሪያ ነው::

የእግዚአብሔርን ታላቅነትና በጎነት መናገር የዐዲስ ኪዳን ሕዝብ
ዓላማና ተግባር ነው:: ዛሬም ወንጌልን መስበክ፣ የጌታ ኢየሱ
ስን ጌትነትንና መድኀኒትነትን ማወጅ፣ እግዚአብሔር ሰውን
መውደዱን ማብሰር፣ ሰዎች ንስሓ ገብተው በኢየሱስ ክርስቶስ
አምነው የእ፣ ዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ያለመማቋረጥ መጣ
ራት የቤተ ፣ ስቲያን ኀላፊነት ነው::

የክብሩን ወ፣ ፣ል ምንነት ለማየትና ለማሳየት፣ የትንሣኤውን
ኀይል ለመስበክ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ኀይል
መሞላት ያሻታል:: በሰማያዊው ኀይል ካልተሞላች ከሌላው ዓለ
ማዊ ማሕበር የሚለያት፣ ከተራነት የሚያወጣት ሕይወት አይኖ
ራትም:: ወንጌልን የማሰራጨት ተልእኮ የተወሰኑ ወንጌላውያን
ግዳጅ ብቻ ሳይሆን፣ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ሙሉውን ወንጌል
ለመላው ዓለም የማዳረስ ኀላፊነት አለባት:: የሐዋርያት ተል
እኮ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ነው::



*"በንስሓ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ
እንዲያምኑ፣ ለአይሁድም ለግሪክ ሰዎችም አጥብቄ መስክሬላ
ቸዋለሁ:: ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬ
ንና የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን
ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቈጠር እንደ ከንቱ
ነገር ናት"* (ሐሥ 20፥21:24)::

የንስሓ ጥሪ

የአዲስ ኪዳን መክፈቻ ስብከት በመጥምቁ ዮሐንስ የተሰበከው
"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" ነበር:: ጌታ ኢየ
ሱስም አገልግሎቱን ሲጀምር በዚሁ ስብከት "ንስሓ ግቡ መን
ግሥተ ሰማያት ቀርባላችና" ነው:: በዮሐንስም ራእይ ጌታ ኢየ
ሱስ አብያተ ክርስቲያናትን ለንስሓ ሲጣራ ነው የምናየው::
በእግዚአብሔር መንግሥት አንፃር "የንስሓ ግቡ" ስብከት የማያ
ቋርጥ የእውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ ነው:: ምን
ነው ቢባል ከአመንም በኋላ የግልም ሆነ የማኅበረ ምእመናን
ሕይወት ጕዞ የሚበዛውን ጊዜ ወደ መቆሸሽ ሕይወት ስለሚንሸ
ራተት ነው:: የምንመላለሰው፣ የምንኖረውም በክፉው በተያ
ዘች ዓለም ውስጥ በመሆኑና ከአሮጌውም ሰው ገና ያልተላቀ
ቅን ከመሆኑ የተነሣ ነው፤ የሥጋም ስበት፣ የዓለምም ስበት
ስላለብን ነው::

ማናችንም በሌላችን ላይ የምንነቅፈው ነገር ቢኖረንም፣ እንደየ
ሁኔታውና እንደየመልኩ አንዳችን ለንስሓ ጠሪ፣ ሌላችን ተጠሪ
መልክ ብናሳይም እንደ እውነቱ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት
ንስሓ የሚያሻን ነን፤ የምንነቀፍበትም ነገር አለ:: እያንዳንዳችን
የምናስተካክለው ንስሓ የምንገባበት ጕዳይ አለን:: ለራሳችን ብቻ
ሳይሆን ለሌላውም ስለ ምድራችንም የምንናዘዛቸው ልንማልድ
ባቸው የሚገቡ አያሌ ጕዳዮች አሉ:: አንዱ ለንስሓ ጠሪ ሌላው

ተጠሪ ሁኖ በቋሚነት የምናካልለው ነገር ሳይሆን እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን ፊት በመሻት ከጊዜ ወደ ጊዜ በንስሓ መንገድ የምንጓዝ ነን::

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ ጌታ ኢየሱስ ሰባቱን የእ ስያ አብያተ ክርስቲያናት በገመገመበት ጊዜ ከሰባቱ በአምስቱ በታላላቅ ጉዳዮች ላይ ንስሓ እንዲገቡ አለበለዚያ መቅረዛቸው ከስፍራው እንደሚወሰድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸው ነበር::

የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚ ሉትን መርምራ ሐሰተኛ ሆነው ስላገኘች፣ ስለ ስሙም ስለ ታገ ሡች፣ ጸንታም ስለቆመች ስትመሰገን፣ የቀደመውን ፍቅርዋን ስለ ተወች ግን ተነቅፋ ንስሓ እንድትገባ ተጠርታለች::

የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ በምድራዊ ነገር ድሀ ብትሆንም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ መሆኗ ተረጋግጦላት በተቃውሞ መካከል እስከ ሞት ድረስ በመታመን እንድትጸና ተበረታትታለች::

የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ በታላቅ ስደት ጊዜ በመጽ ናትዋ ብትመሰገንም ኋላ ግን የበለዓምን እንዲሁም የኒቆላውያ ንን ትምህርት (የስህተት ትምህርት) የሚጠብቁትን በማስተናገ ድዋ ተነቅፋ ንስሓ እንድትገባ ተጠይቃለች::

የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን በፍቅርዋ፣ በእምነትዋና በአገልግሎ ትዋ ስትመሰገን፣ ዳሩ ግን እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እን ዲበሉ የምታስተምረውን፣ የምታስተውን፣ ነቢይ ነኝ የምትለው ንም ኤልዛቤልን ስለ ተወቻት (ስላልተቃወመቻት) ንስሓ እንድ ትገባ ታዛለች::

የሰርዴስም ቤተ ክርስቲያን በማንቀላፋት በሕይወትና በሥራዋ ደክማ ስለ ነበረች ንስሓ እንድትገባ ተገሥጻለች::

ፊልደልፍያ ኀይሏ ምንም ታናሽ ቢሆን፣ ቃሉን ስለ ጠበቀች፣ ስሙንም ስላልካደች ተመስግና ያላትን አጽንታ እንድትይዝ ተበ ረታታለች::

የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊው፣ በሰማያዊው ነገር ደሀ ይታ ተጎሳቁላና ዕውር ሆና ሳለች፣ በምድራዊው ነገር ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኛለሁ አንድም አያስፈልገኝም በሚል ቅዠት ውስጥ ስለ ገባች ንስሓ እንድትገባ ታዝዛለች::

የወደቅን እንድንነሣ፣ የሳትን እንድንመለስ ምናሴን ይቅር ያለ አምላክ፣ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው::

እንግዲህ እኛም ቤተ ክርስቲያን እንደ መሆናችን መጠን እነዚ ህንና እነዚህን በመሳሰሉና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ በጋራም በተ ናጠልም ንስሓ የምንገባባቸው ጕዳዮች አሁንም አሉ::

በሕዝቡ፣ በነቢያቱ፣ በካህናቱና በነገሥታቱ ዓመፅ ሰበብ በይሁዳ ምድርና በሕዝቡ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ሊወርድ ባንዣበበ በት ሰዓት እግዚአብሔር በኤርምያስ አፍ ለንስሓ ሲጣራ ጥሪ ውን ተቀብለው ባይመለሱ ረሓብ፣ ሰይፍ፣ ቸነፈር እንደሚጠ ብቃቸው አስጠነቀቀ፤ በተቃራኒው አያሌ ነቢያት በሐሰት በእ ግዚአብሔር ስም የተገላቢጦሹን መልእክት ለፈፉ:: "በእውነት ሰላምን በዚህ ስፍራ እሰጣችኋለሁ እንጂ ሰይፍን አታዩም፣ ራብም አያገኛችሁም" ይላል እግዚአብሔር (ኤር 14፥13-18) እያሉ የንስሓ አስፈላጊነት አሟሸሹ፤ የሕዝቡን ንስሓ የመግባትን ሐሞት እንዲፈስ አደረጉ፤ የመመለሱን አጣዳፊነት አከሸፉ፤ ለጥ ፋት የሚዳርግ አጕል መረጋጋት ናኙ::

## 4. ደቀ መዛሙርት ማፍራት

ወንጌልን ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ከማድረስ አገልግሎት በኋላ ተከ ትሎ የሚመጣው ያመኑትን ምዕመናን በጌታ ቃል እንደሚገባ **ማስተማርና ማሳደግ ነው**:: በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ወንጌልን ለዓለም ሕዝቦች ማዳ

ረስና፣ ምእመናንን የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተግባሮች ነበሩ:: ሐዋርያው ጳውሎስም ለጌታ ሥራ ከስፍራ ወደ ስፍራ በሚዘዋወርባቸው ቦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር መመለክ የሚገባው አምላክ እንደ ሆነ ሲያሳውቅ በአንጻሩም ደግሞ ምዕመናንን በእግዚአብሔር ቃል ሲያሳድግና ወንጌል ላልዳኑት ሁሉ መሰበክ እንዳለበት ሲያሳስብ ነበር:: (ቈላ 1፥12-13፤ ሐዋ 18፥11፤ 2ጢሞ 4፥2):: ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ጌታ ያስተማረውን ሁሉ ማስተማር ግዴታ ነው::

ደቀ መዝሙርነት የተሰጠ ሕይወትን ይጠይቃል

የነገር ሁሉ ማዕከል ክርስቶስ ነው:: የጌታ ኢየሱስ ጥሪ ይሄ ነው:: ሥር ነቀል የሆነው ጥሪ "ከኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ:: ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለኔ ግን የሚያጠፋት ያገኛታል" የሚለው ነው::

በአንድ ወቅት ትልቅ የመሆን፣ ታዋቂ የመሆን፣ የተመቸው ሰው መሆን ፍላጎት በውስጤ ተነሣሣ:: ከእንግዲህስ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ለእኔ መንቀሳቀስ እንዳለበት አሰብኩኝ:: ልክ ይሄን በማስብበት ጊዜ «ከኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ:: መስቀሉንም ተሸክሞ ዕለት ዕለት ይከተለኝ::» የሚለው ጥቅስ አፍጥጦ መጣብኝ፤ መምጣቱም አበሳጨኝ፤ ጎምዛዛና ምኞቴን የሚያስጥል ጥሪ ሆነብኝ፤ ሆኖም ላመልጠው አልቻልኩም::

ግን ሳስበው ለካ ይሄ ጥሪ ጐምዛዛ ይመስላል እንጂ የፍቅር ጥሪ ነው:: ለምን? ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና ብሎ ነው የሚያስረግጠው::

እኔ ነፍሴን ለማዳን፣ ለማስደሰት ነው ራሴን መካድ የማልፈልገው፤ ማለትም ራሴን ለመሙላት፣ ለማጉልበት:: ነገር ግን መጀ



መሪያ ነገር ሕይወታችንን ለመምራት እኛ ችሎታው የለንም:: ልምምዱ የለንም:: ገና ለማጅ ነዋሪዎች ነን:: ተለማምደን አይደለም ለመኖር የምንመጣው ገና ኑሮ ሞካሪዎች ነን:: ስለዚህ እናበላሻለን::

መኪና መንዳት የማይችል ሰው መኪና ቢሰጠውና ለመንዳት ቢሞክር፣ ቢያንቀሳቅስ ፍጻሜው መኪናዋን ማጋጨት ነው:: ምክንያቱም አልተማረም፤ አልተለማመደም:: እኛም የሕይወታችንን መሪ ብንይዝ ፍጻሜያችን ተመሳሳይ ነው:: እርሱ ፈጣሪያችን የሕይወታችን ባለቤት፣ የሥሪታችን ንድፍ (manual) ደራሲው ነው:: የመምራት ብቃት አለው::

ሁለተኛ ደግሞ ጥቃትን የሚቋቋም ኀይል የለንም:: እኛን የሚቃወሙ ብዙ ኀይላት አሉ፤ ሕይወት በባዶ ሜዳ የሚደረግ ምቹ ጕዞ አይደለም:: ብዙ ተቃውሞ፣ ብዙ ሰልፍ አለበት:: "የሰው ሕይወት በምድር ላይ ብርቱ ተጋድሎ አይደለምን?" (ኢዮ 7፥1):: ሕይወታችንን በእጃችን ብንይዛት ክፉው በቀላሉ ያስረግፈናል:: በጌታ እጅ ብትሆን ግን የሚደፍራት አይኖርም:: ሕይወታችንን የሚጠናወተውን የሚቋቋም ኀይል በእርሱ ዘንድ ተትረፍርፎ አለ:: እርሱ የመጠበቃችን ዋስትና አለው::

ሌላው ደግሞ የእርሱ መሆን ጽድቅ ነው:: ምክንያቱም ካሁን በፊት እንዳነሳነው ሰውን ከምድር አፈር አበጀው የሕይወትንም እስትንፋስ እፍ አለበት:: ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ የሚል የእግዚአብሔር የፈጣሪና የባለቤትነት ማረጋገጫ ቃል አለ:: የምድር አፈር የማነው? የሕይወቱ እስትንፋስ የማነው? የእግዚአብሔር አይደለም እንዴ? በኛ ዘንድ ያለው ሁሉ የማን ነው? መሠረቱ ባለ ንብረቱ እርሱ ነው:: እኛ ራሳችንን ለርሱ ብናስረክብ ለባለቤቱ ንብረቱን መመለሳችን ነውና ጽድቅን ማድረጋችን ነው:: የተስፋዬን ለተስፋዬ የአበበን ለአበበ የአልማዝን

ለአልማዝ ብንሰጥ፣ የየራሳቸውን ብንመልስ ጽድቅ ነው። የእኔ ያልሆነውን ከሌሎች ባልወሰድ በጽድቅ መገኘት ነው።

አንድ ጊዜ ሽማቂዎች ወደ ጌታ ኢየሱስ መጡ። ሊፈትኑት ከቄሳር ጋር ከፖለቲካው ጋር ሊያጋጩት። «ለቄሳር ግብር እንድንሰጥ ተፈቅዷልን?» ብለው ጠየቁት። መጀመሪያ ይህን ከማለታቸው በፊት አቆላመጡት፣ ካቡት።

ጌታ ኢየሱስ ግን አንድ ዲናር አምጡልኝ አለ። ይሄ ዲናሩ መልኩ ጽሕፈቱ የማነው አላቸው። የቄሳር ነው አሉት። እንግዲያው የቄሳርን ለቄሳር ስጡ። ይህ ጽድቅ ነው። የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ አለ። እኛ ደግሞ በማን መልክና ምሳሌ የተሠራን ነን? የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ያለን ነን። ስለ ዚህ ሕይወታችን ለማን ነው? ለእግዚአብሔር ነው። እንደዚያ ስናደርግ ጽድቅ ነው። ደግሞ ባለቤቱ ሲይዘው በጣም ጥሩ ነው። ነፍሱን የሚያድን ያጠፋታልና ነፍሱን ግን ስለኔ የሚያጠፋ ያድናታል። ይህ ጣይ አንሺ (paradoxical) ንግግር ነው፤ አይ አዎ ነው። ጥሎ የሚያነሣ የለሁኝም ስንል በሕያውነት የምንኖርበት ነገር ነው።

ይኽ ጥሪ ክርስቶስን ማእከል የማድረግ ጥሪ የሕይወት ጥሪ፣ ነው። ስለዚህ ያንን መንገድ ብንሄድ የሞኝ መንገድ አይደለም። የአዋቂዎች፣ የጥበበኞች መንገድ ነው። በሰው ዐይን ሳይሆን በዓለም መለኪያ ሳይሆን፣ በሕይወት ዓለም፣ በዘላለማዊ አምላክ፣ በመለኮት ዘንድ የአዋቂዎች መንገድ ነው። የጠቢባን መንገድ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ለሚገኙ ክርስቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ ውስጥ *"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው"* (ሮሜ 12፥1) ይላል።



ሰውነታችንን ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር ማቅረባችን ሙሉ በሙሉ ሕይወታችንን ለእርሱ መስጠታችንን ያመለክታል። ካላቀረብን ግን የእግዚአብሔርን ንብረት ነጥቀን የራሳችን ማድረጋችንን መገንዘብ ይኖርብናል። መሰጠት የሌለበት ሕይወት መለወጥ የለውም። ከተሰጠን ግን ሕይወታችን ይለወጣል። በመቀጠልም ዓለምን መምሰል እንተዋለን። በተጨማሪም ዋጋ አሰጣጣችንና ዝንባሌአችን እንዲሁም ምርጫችን ጭምር ይለወጣል።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በቃሉም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ለእርሱ ሰጥተን እንድንመላለስ ሲጠይቀን፣ እርሱን ለልጆቹ እንደማይራራ አባት እያየነው እንፈራለን። የእግዚአብሔርን ሩኅሩኅነት እንጠራጠራለን፤ በአዕምሮአችንም ራሴን ከሰጠሁት በኋላ የማልፈልገውን ቢያደርገኝስ፣ ቢያስደርገኝስ የሚል ፍርሃት ይመጣብናል። ከዚህም የተነሳ ራሳችንን እንሰስታለን። ይሁን እንጂ እርሱ ቸር እንደ ሆነ ዐውቀን፣ የእግዚአብሔር የሆነውን ማንነታችንን ለእርሱ በእምነት ብንሰጥ እኛ ለእኛነታችን ከምናደርገው ጥንቃቄ በላይ እርሱ ለንብረቱ ይጠነቀቃል። ከዚህ ይልቅ ነፍሳችንን የራሳችን ለማድረግ ብንሮጥ "ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፉታልና" ስለተባለ ነፍሳችንን እናጠፋለን (ሉቃ 9፥23-24)።

ሁላችን ክርስቶስ ኢየሱስን አምነን ስንኖር፣ ወደ ደቀ መዝሙር የሕይወት ደረጃ በመምጣት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ከምንወዳቸው አላፊ ነገሮች መለየት ይኖርብናል።

ጌታ ኢየሱስ ባደረገው ድንቅና ተአምራት ተገርመው ወደ እርሱ ይጎርፉ ለነበሩት ሰዎች፣ ስለ ደቀ መዝሙርነት ትምህርት ሲሰጥ፣ ሊከተሉት ለሚፈልጉ ሁሉ ውሳኔያቸው በሕይወታቸው ሊያስከ

ትለው የሚችለው ነገርም እንዳለ በጥብቅ እንዲያጤኑት ነበር። ከዚህ ጉዳይ ጋር በማያያዝ የነገራቸውም የመጀመሪያ ምሳሌ፣ ሕንጻ በመሥራት ላይ ስለ ነበረው ሰው ነው። ሕንጻ ለመገንባት የሚፈልግ ሰው ሕንጻውን ለመሥራት መፈለጉ ብቻ በቂ መነሻ አይደለም። ከፍላጎቱም ጋር ሥራውን ማስፈጸሚያ በቂ ገንዘብ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። የሕንጻው ሥራ ከዕቅዱ አወ ጣጥና ከዝግጅት ጉድለት የተነሣ ቢቋረጥ፤ ቤቱ በጅምር መቅ ረቱን የሚመለከቱ ሰዎች ሁሉ ይስቁበታል።

ማናችንም ደቀ መዝሙር ለመሆን መፈለጋችን ወይም ለመባል መጓጓታችን በራሱ በቂ አይደለም። ከዚያ በፊት አስቀድመን ጥሪው የሚጠይቀውን ዋጋ ማወቅና ራሳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት፣ መወሰን ይጠበቅብናል። ያለዚያ እውነተኛ ደቀ መዝሙር መሆን አንችልም። ክርስቶስ ለደቀ መዝሙርነት የሚ ፈልገው፣ የራሳቸውን ፈቃድ የሚያደርጉ ሰዎችን ሳይሆን፣ የእ ርሱን ፈቃድ ለመፈጸም የሚፈልጉትን ነው።

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ፈተና ጠባቡን መንገድ ሰፊ የማድረግ ጥረት ነው፤ መንግሥተ ሰማያትን ከመስበክ መንግሥተ ምድ ርን መስበክ፣ እግዚአብሔርን ከማሳየትና ከመስበክ ይልቅ በስመ እግዚአብሔር ራስን መስበክ ነው። ከጨውነት ወደ አልጫነት የመሄጃውና ዓለም በቤተ ክርስቲያን እንድትስተናገድ የማድረ ጊያን መንገድ መምረጥ ነው።

ቃሉ «በዓለም ያለውን አትውደዱ በዓለም ያለው የዐይን አምሮት የሥጋ ምኞት ስለ ገንዘብ መመካት (የእንግሊዝኛው ትርጉም ስላደረግነው ነገር መመካት ይላል) ነው» ይለናል። ቤተ ክርስ ቲያን ጠባቡን መንገድ ሰፋ ብታደርግ ስለ ዐይን አምሮት፣ ስለሥጋ ምኞት ስለ ገንዘብ ብትሰብክ ዓለም «ቤተ ክርስቲያን ወይም ሞት» ብላ ሰተት ብላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ትገባለች። ዓለም በቤተ ክርስቲያን በገባች ጊዜ ስለንስሐ መናገር አይወደ



ድም፤ መስቀልን ማንሳት ያንገሽግሻል። «ኑ ወደ ጌታ» የሚለው መልዕክት የክርስቶስን ተከታዮች ከማፍራት ይልቅ የምዕመናንን ክበብ ዐይነት ማቋቋም ይሆናል።

ጌታ ኢየሱስ «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁ ንም ፈልጉ ይህ ሁሉ ይጨመርላችኋል» ይላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን ከመፍጠሩ በፊትም ለሰው የሚያስብ ቸር አምላክ ነው። እግዚአብሔርን እኛ በጸሎታችን ቸር አናደር ገውም። እርሱ በባህርይው ቸርነት ገንዘቡ የሆነ አምላክ ነው። አዳምና ሔዋን ከመፈጠራቸው በፊት ነው ቸርነቱ። ምድርን ያዘጋጀ የሰማይ አካላትን ያስቀመጠ እግዚአብሔር ቸር ነው። ግን የእኛ አጀንዳ መንግሥተ ሰማይ እንዲሆን ይፈልጋል።

ቤተ ክርስቲያን የተጠራችው የእግዚአብሔርን መንግሥት ወን ጌል ልትናገር ነው። ይህን ስታደርግ ሌላው ይጨመርላታል። በእግዚአብሔር ነገር ካልበለጠግን ምድራዊ ነገር ምንም ቢከ ማች አንበለጥግም። በእግዚአብሔር ዘንድ ባለው ነገር ካልረካን የትኛውም ምድራዊው ነገር ቢከማች፣ ቢግበሰበስ አያረካንም። ጥሪው ምንድን ነው? ጥሪው ብዙሃኑ በሚሄዱበት መንገድ መሄድ አትችሉም ነው። በጠባቡ መንገድ የእያንዳንዳችን ሕይ ወት 'ከአልጫነት' ወደ 'ጨውነት' በሚለውጠው መንገድ እን ድንጓዝ ተጠርተናል።

የግል ሕይወታችን፣ የቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ዙሪያ የሚሽከረከር፣ በዚያ ዙሪያ የሚያጠነጥን በዚያ ዙሪያ የሚጠመጠም እንጂ በግላችን ዙሪያ መሆን የለበትም። መንግሥተ እኔ ሳይሆን መንግሥተ እግዚአብሔር ሊገዛን ያስፈ ልጋል። መንግሥተ እኔነትን ሽረን የእግዚአብሔርን መንግሥት ማእከላዊ ማድረግ አለብን። የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቁ ንም እሹ ማለት እኮ መንግሥተ እኔን ማሟሸሽ፣ የራሳችንን መን ግሥት ማቋቋም ትተን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ መግባት

መስወር ማለት ነው። ለክርስቶስ ኢየሱስ መማረክ ጌታ ኢየሱስን ንጉሣችን ማድረግ ማለት ነው። በራስ ላይ ያጠነጠነ ሕይወት ትተን የራስን ፍላጐት ማስቀደም ትተን፣ የራስን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በፊት ማምጣት ትተን ለእግዚአብሔር መኖር ማለት ነው።

ዛሬ ግን ብዙዎቻችን አጀማመራችን መልካም ሆኖ አፈጻጸማችን ክፉ እየሆነብን ነው። አጀማመራችን መንፈሳዊ ይሆንና አፈፃጸማችን ሥጋዊ ይሆናል። ቁም ነገሩ «የትኛው ይመቻል?» ሳይሆን "የትኛው ትክክል ነው?" «እግዚአብሔር እንዴት ነው የሚያየን» እንደ ሆነ እናስታውስ። እግዚአብሔር የሚያየን፣ የሚለካን በቃሉ አኳያ ነው፤ እግዚአብሔር መለኪያውን አይቀይርም። የእግዚአብሔር መለኪያ አይላሽቅም።

ጳውሎስ *"እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ! ለመሆኑ ማን መተት አደረገባችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ ነበር። .... በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ፍጻም ለመሆን ትጥራላችሁ?* ብሎ ይጠይቃቸዋል (ገላ 3፥1-3)። የስንቶቻችን ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ስትጠነሰስ በመስቀሉ ዙሪያ ጀምራ በኋላ ግን ሌላ ነገር ኮተት ሁሉ ገብቶ የመስቀሉ ነገር የቅድስና ነገር የእውነት ነገር ሸሽቶ የራሳችን ነገር ሆኗል?

መንገዱ የመስቀል መንገድ ነው። አንተ ግን በመስቀሉ መንገድ ተጓዝ ነው የሚለን። የመስቀሉ ማእከልነት ከተዘነጋ የመስቀሉ ዐሳብ ብርታትም ከእኛ ይሸሻል። «የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» የሚለው ዐሳብ ከእኛ ይሸሻል። በመካከላችን መለያየት መናቆር ብቻ ይሆናል። በሰይጣን ላይ የሚሰለጥን ኀይል በመካከላችን አይኖርም። እርስ በርስ በመበላላት እርስ በርስ መጠፋፋት ይመጣል።



ለማያምኑ የመስቀሉ ቃል ሞኝነት ነው። ለእኛ ግን የመዳን ኀይል ነው። እርሱ ከጨለማ ስልጣን አዳነን። ጳውሎስ «አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ» ይላል። ድንቅና ታምራትን ለማየት ይጓጓሉ። አይተው አይጠግቡም፤ ሌላ ምልክትን ይፈልጋሉ የግሪክ ሰዎች ጥበብን ይሻሉ። እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን። በዚህ በተሰቀለው ክርስቶስ ውስጥ ኀይሉ አለ፣ ጥበቡም አለ። *"የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት ሀብት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ ዘንድ ነው"* (ቈላ 2፥3)።

ዛሬ ግን የመስቀሉ ቃል ከቤተ ክርስቲያን ምስባክ ገሸሽ እየተደረገ ነው። በአንድ ወቅት አንድ ሰው ባለቤቱን ተሰናብቶ ፈረሱን ጭኖ ዝናሩን ታጥቆ ጠመንጃውን አንግቦ፣ ሽጉጡን፣ ሰይፉን፣ ጐራዴውን ሙሉ ትጥቅ አድርጎ ሄደ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሲመለስ በእግሩ መጣ። ፈረሱም የለም። ሚስት ጮኸች። ውሻው ጮኸ። ባሏ ነው የመጣው ደስ አላት ግን ስታየው በእግሩ ነው። «ፈረሱስ?» አለችው፤ «አይ ወሰዱት» «እነማን?» «ሽፍቶች» «ጠመንጃውስ?» «ወሰዱት» «ሽጉጡንስ?» «ወሰዱት» «ጐራዴውንስ?» «ወሰዱት» «ታዲያ እንዴት ሰገባውን ተውት?» ስትለው «ሞቻለሁ እንዴ ሰገባውን የማስወስደው?» አለ ይባላል። ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ስላለው የመስቀሉ ሰገባ አይገደውም የመስቀሉ ቃል፣ የመስቀሉ እውነት እስከተጓደለ ድረስ።

## ደቀ መዝሙር ማድረጋችን ለማን?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርትን ጠርቶ ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ካስተማረ በኋላ፣ እነርሱ ደግሞ አምነው የሚጠመቁትን እያስተማሩ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጓቸው በማቴ 28:19-20 ባለው ክፍል ላይ ትዕዛዝ ሲሰጣቸው እንመለከታለን። በዚህ መሠረት በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ውስጥ የነበረች የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን እያስተማረች የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ታደርግ ነበር (ሐዋ

11፥26)። ሐዋርያው ጳውሎስም በበኩሉ ሰዎችን ሁሉ በጥበብ እያስተማረና ወደ ሙሉ ሰውነት እንዲመጡ የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ያደርግ ነበር (ቈላ 1፥28)። ልክ እንዲሁ የአሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያንም ሰዎችን እያስተማረችና እየገሰጸች የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ልታደርጋቸው ይህ አደራ አለባት።

ጥያቄው ግን ዛሬ በአገልግሎት ላይ የተሰማራን አማኞችን የማን ደቀ መዝሙር እያደረግናቸው ነው? የሚል ነው። የእኛ ወይስ የክርስቶስ? ብዙ ጊዜ ግን እንደሚታየው ጸጋና አገልግሎት ሲበዛልን ሰዎችን የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ከማድረግ ይልቅ የራሳችን ለማድረግ እንተጋለን። ምዕመኑንም በእኛ ዙሪያ ሰብስበን ለራሳችን ጽኑና እስተማማኝ ድጋፍ ለመፍጠር እንጥራለን። ይኸ ጌታ ከሰጠን ተግባር ጋር አብሮ የማይሄድ እኩይ ተግባር ነው። ጌታ ኢየሱስ አማኞችን አስተምረን የእርሱ ደቀ መዝሙር እንድናደርጋቸው እንጂ በእኛ ዙሪያ እንድንሰበስባቸው ትእዛዝ አልሰጠም።

የሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት የሚያስገርም ነው። በየትኛውም በታ ላይ ሰዎችን የራሱ ደቀ መዝሙር ለማድረግ አንድም ምዕራፍ ስንኳ ሲሄድ አንመለከትም። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞች በመካከላቸው መከፋፈልን ፈጥረው፣ የአገልጋዮቻቸው ተከታዮች ለመሆን ሲነሱ የሰጣቸው ምላሽ "*አሁንም ሥጋውያን ናችሁ፤ በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር አለ፤ ታዲያ፣ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን? ተግባራችሁስ እንደ ማንኛውም ሰው ተግባር መሆኑ አይደለምን? ምክንያቱም አንዱ፣ "እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ ሌላው ደግሞ፣ "እኔ የአጵሎስ ነኝ" ቢል፣ ሰብአዊ ፍጡር ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?*" (1ቆሮ 3፥3-4) የሚል ነበር።

የቆሮንቶስ ሰዎች ራሳቸውን እንደ መንፈሳዊ የሚቈጥሩ አማኞች



ናቸው። ሐዋርያው ግን፣ በማስረገጥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የማትመላለሱ ሥጋውያን ናችሁ ይላቸዋል።እንዲህ ያለበትም ምክንያት አንዳንዶች እኛ የጳውሎስ ነን፣ ሌሎች የአጵሎስ ነን፣ እንዲሁም ሌሎች የኬፋ ነን፣ በአራተኛ ደረጃ ደግሞ በመለያየት መንፈስ ነጠል ብለው፣ እኛ የክርስቶስ ነን የሚሉ ቡድኖች ስለ ነበሩ ነው። እነዚህን ሁሉ በአንድ ላይ ይወቅሳቸዋል። "እኔ የጳውሎስ ነኝ" ላሉት እንኳ የተለየ እንክብካቤ አላደረገላቸውም። ወይም እናንተ እወነቱ የገባችሁ፣ ተስፋ ያላችሁ ናችሁ ብሎ ልዩ ስፍራ አልሰጣቸውም። እንዲያውም ተቆጥቶ ዘወር በሉልኝ ያላቸው ይመስላል። ይህ ሐዋርያ የሚፈልገው ሁላቸው የክርስቶስ ኢየሱስ እንዲሆኑ እንጂ ማናቸውም እንዲጣበቁበትና እንዲንጠለጠሉበት የእርሱ ተከታዮች እንዲሆኑ ፍላጎቱ አልነበረም። እንዲያውም በ2ቆሮ 11፥2 ላይ "*በእግዚአብሔር ቅናት እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻችኋለሁና*" ይላቸዋል። ከዚህ ውጭ የራሱ ተከታይ ደቀ መዝሙር ሊያደርጋቸው አይፈልግም።

ዛሬስ እኛ አገልጋዮች ነን የምንል እንዴት ነን? ምዕመኑ በእኛ ዙሪያ ሲሰባሰብ ምን የሰማናል? ጳውሎስ ሁሉን እንደ ንጽህት ድንግል ለክርስቶስ አጨ፤ እኛስ ለማን እናጫለን? የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእኛ መጠቀሚያ፣ ክብር ማግኛችንና አድናቂያችን ሊሆንልን አይገባም። ከእኛ ይልቅ ሁል ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሊከብር ይገባል። በዚህ ውስጥ እኛ የእግዚአብሔርን ክብር ለመሻት ልንቀድም ብንሞክር ከፍተኛ ትርምስ ነው የሚሆነው።

እንደ ገና በመቀጠል በዚሁ በ1ቆሮ 3፥5 ላይ "አጵሎስ እንግዲህ ምንድነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ" ይላቸዋል።

እነዚህ አገልጋዮች በራስ በሆነ ነገርና በተፈጥሮ ችሎታ ሳይሆን
ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግሉ ነበር:: እንደዚህ ሆኖ እንኳ የሚ
ተክሉና የሚያጠጡ ነበሩ እንጂ የሚያሳድጉ አልነበሩም:: ይህ
ሐዋርያ አሳማኝ ምክንያቶች እየደረደረ በሚያገለግለው ሕዝብ
መካከል ለራሱና ለሌሎች ብጤ አገልጋዮቹ የክበሬታ ስፍራ
ይነሣል:: ጥያቄው ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን የክርስ
ቶስ ሳይሆን የራስ ደቀ መዝሙር የማድረግ ደባል ነገር ከየት
መጣ? የሚል ነው፤ እኛ ምክንያቶች ነን እንጂ ምንም አይደለ
ንም::

ዛሬ በአንዳንድ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ የሚታየው አማኞ
ችን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በማድረግ ፈንታ ግለሰቦችን የሚ
ያደምቅ በእነርሱም ዙሪያ ደቀ መዛሙርት ወይም ጭፍራን
የሚያከማች ነው:: በአንዳንድ ስፍራ የሚታየው፣ እየተነገረለት
ያለው "መንፈሳዊ መነቃቃት" እውን መንፈሳዊ መነቃቃት ነው?
ወይስ የሕይወትን ንቃቃት የሚያስከትል አደጋ?(church re-
vival or church removal) በእግዚአብሔር ስም ሐሰትን፣ ሽንገላን
ማስተናገድ በእነ አሞጽ፣ በእነ ኤርምያስ፣ በእነ ሕዝቅኤል፣
በእነ ሚኪያስ ወዘተ ጊዜ ብቻ የታየ ክሥተት ሳይሆን ዛሬም
በመንፈስ ቅዱስ ስም እየታየ ያለ ነው:: ከሥላሴ አንዱ የሆነው
የከበረው ንጹሑ መንፈስ ቅዱስ ለቅድስና ባይተዋር፣ ለእውነት
እንግዳና ባዕድ ይመስል ንጽሕና፣ ቅድስና፣ እውነትና ሐቅ የማ
ይስተናገድበት፣ በሽንገላ የተዘፈቀውን እንቅስቃሴ ከከበረው
መንፈስ ከመንፈስ ቅዱስ ስም ጋር ማያያዝ፣ በእግዚአብሔር
ስም ላይ የሚደረግ ታላቅ ንቀትና ዐመፅ ነው:: ለግለሰቦች የመ
ድረክ ታይታ እንደ ማረግረጊያ ሙዚቃ (background music) እየ
ዋለ ነው:: ይህንኑ ዐይነት እንቅስቃሴ ሰማያዊና መለኮታዊ የእ
ውነት መንፈስ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለማስመሰል ከልብ ባል
ሆነ ሃሌ ሉያን እና አሜን አሜንን እንደ ቅባ ገጽታ (cosmotic)
መጠቀም እየተለመደ መጥቷል:: ግን በቅባ ገጽታው ሰዎች



እንጂ ፈጣሪ አይሸነገልም:: "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ
ዘላለም ያው ነው" ስንል፣ በኀይል መገለጥ ላይ ብቻ የሚያተኩር
ሳይሆን በአኀዜ ኵሉነቱ (ሁሉን የያዘ) በታማኝነቱና የቅድስና
ውም የንጽሕናውም የእውነትና የእውነት መለኪያነቱ፣ አይለወ
ጥም በሚለው ሐቅም ላይ የሚያርፍ ነው::

ይህ ዐይነቱ የተዛባ ወይም ፈር የለቀቀ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ
በብቸኛው ጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት ላይ የሚያተኩር ሳይ
ሆን "ተቀብተናል" ወይም "ተቀብተዋል" በሚባሉ ግለሰቦች
ዙሪያ የሚያጠነጥን ጌታ ኢየሱስ ላይ ግርዶሽ የሚጥል ነው::
ተላላ አጃቢዎችም ለእነዚህ ግለሰቦች "ማጠንን" ይጎተጉታሉ::
"የተቀባ" ብለው ለቈጠሩት ሌሎች ሁሉ እንዲያጥኑለት እንዲ
ያውጁለት ይማጠናሉ፤ ይርዋርዋጣሉም:: ይህም የዘማዊቷ ቤተ
ክርስቲያን አንዱ ችግር ነው::

በእነዚህ ዘንድ የሚገኙ ልዩ መንፈሳዊ መገለጥ ወይም ልምምድ
ውስጥ የገቡ እየመሰላቸው ከትክክለኛ መስመር የሚወጡ አማ
ኞች፣ "በዐይናችሁ ፊት ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ
ተስሎ ነበር ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን
ነው?" ተብለው የገላትያ ክርስቲያኖች በተነቀፉበት ዐይነት የመ
ታወር አዚም ውስጥ ይሠርጋሉ:: በእነርሱ ዘንድ ክርስቶስ ዳግ
መኛ እስኪሳል ሐዋርያው ጳውሎስ በምጥ መያዙን እንደ ገለ
ጠው ዛሬም እውነተኛ አገልጋዮች በተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ
ለወደቁት ምጥ ቢይዛቸው ለእውነተኛ እረኝነታቸውም ምስክር
ነው::

የጊዜያዊውን፣ በእግዚአብሔር ስም በሽንገላ የሚገኘውን የዝናና
የጥቅም፣ የደራ ገበያ እየተመለከቱ ከእውነት መንገድ ወጥተው
ራሳቸውን ለሽንገላ የሚሸጡ አገልጋዮች ቍጥራቸው እየጨመረ
ነው::

"ተቀብቻለሁና አትንኩኝ" "ተቀብቷልና አትንኩት" የሚለው

ፊሊጥ፣ አለአግባብ ተለጥጦ፣ ሾልከውና የማይሆነውን ትምህርት
አሾልከው የሚያስገቡት ማንነታቸው እንዳይፈተሽ ትምህርታቸ
ውና የአገልግሎታቸው ፍሬ እንዳይመዘን በተገንነት ያገለግላል።
ይህን መከላከያ ማግኘት ደግሞ የሚሹትን ሊሉ፣ በሚፈልጉት
መንገድ ሊሄዱና ሊያደርጉ እንዲችሉ፣ የይለፍ ወረቀት እንደ
ማግኘት ሆኖላቸዋል።

"የቀባኋቸውን አትንኩ" የተባለውኮ፣ ከአምላኩ ጋር አካሄዱን
አስተካክሎ በአሕዛብ መካከል ለተንቀሳቀሰውና ለኖረው ለቀደ
መውም ሕዝብ ነበር። ይሁንና ይሄው ሕዝብ ጀርባውን ለአም
ላኩ በስጠ ጊዜ÷ ለመሣለቂያ ለመሰደቢያና ለመራገሚያ ሆኖ
አል። እግዚአብሔር ራሱ ይህ እንዲሆንባቸው አድርጓል። የአ
ዲስ ኪዳን አገልጋዮች ሲታጠንላቸው "ነጋሪት" ሲጎሸምላቸው
የነበሩ ሳይሆን÷ ይልቁኑ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስምና ስለ ጽድቅ
እንደ ተሰደዱ ነው የምንመለከተው፤ "በእውነትም በክርሰቶስ
ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደ
ዳሉ" (2ጢሞ 3÷12)። በብሉይ ኪዳን ሐሰተኛ ነቢያት እንጂ
እውነተኛ ነቢያት በሕይወት ዘመናቸው የሚወደሱ ሳይሆኑ የሚ
ሰደዱ ነበሩ፤ መቃብራቸው ተጌጠላቸው እንጂ። ይህንኑ አስመ
ልክቶ ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ 6÷26 "ሰዎች ሁሉ መልካም ሲና
ገሩላችሁ ወዮላችሁ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ
ያደርጉላቸው ነበርና" ብሎአል። የሕዝቡ ሕይወት ከእግዚአብ
ሔር ጋር በተስተካከለበት ወቅት ብቻ ነበር ነቢያት የተወደዱ
ትና የተከበሩት።

አልፋቸውም ኦሜጋቸውም ይህች ዓለም የሆነች ምድራውያን
ለገንዘብ፣ ለጉልበትና ለሥልጣን ይሮጣሉ፣ ይሞታሉ። የቤተክር
ስቲያንም መሪዎችና አገልጋዮች እንዲሁ ገንዘብንና የገዢነትን
ሥልጣን ለማግኘት ቢሽቀዳደሙ፣ ቢሻረኩ ወይም ቢሻኮቱ አደ
ገኛ ነው። በሎሌ መሪነት ዘይቤ ዝቅ ብሎ ለማገልገል ወገብን
በመታጠቅና በመነሳት ፈንታ ለከበሬታ ስምና ለከበሬታ ወንበር



"ስውር ጥሪ አለኝ" እያሉ ቢራወጡ፣ ወንበሩን ለእኔ ለተቀባሁት
ልቀቁልኝ አመቻቹልኝ ቢሆን ራእያቸው፣ ትጋታቸው፣ ትግላ
ቸው ቤተ ክርስቲያን ትበታተናለች። ጌታ ኢየሱስ ግን በሉቃስ
22÷26 እንዲህ አለ፦ *"እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፣ ነገር ግን ከእ
ናንተ ታላቅ የሆነ እንደ ታናሽ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን"*

ማገልገል እኮ፦ ከተቀመጡበት መነሳትን
- ማበሻ ጨርቅ መታጠቅን
- እግር ማጠቢያ ማዘጋጀትን
- ጎንበስ ብሎ፣ በርከክ ብሎ የሌሎችን እግር ማጠብን
- የረጠበውን እግር አብሶ ማድረቅንና
- እጣቢ መድፋትን ይጠይቃል /ዮሐ 13÷4-5/

ደግሞም ዓመፅ የሌለበት እውነተኛ አገልጋይ የላከውን ክብር
እንጂ የራሱን ክብር አይፈልግም (ዮሐ 7÷18)። ለእግዚአብ
ሔር አምላክ ክብር ስላልሰጠ በመላእክት ተመትቶ፣ በትል ተበ
ልቶ የሞተውን ሄሮድስን እናስታውስ (የሐዋ 12÷20-23)።

የእግዚአብሔር ልጅ በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ አስራ ሁለት ሰዎ
ችን ጠርቶ ካስተማረ በኋላ የራሱ ደቀ መዝሙር አረጋቸው(ማቴ
4÷18-22)። ነገር ግን በመጨረሻ ስለ በደላችን ሀልፎ ሊሰጥ ባለ
በት ጊዜ፣ ክደውት ሄዱ። እኛ የራሳችንን ደቀ መዝሙር ብና
ፈራ ልክ እንዲሁ ክፉ ነገር ሲመጣብንና ሲደርስብን ትተውን
ይሄዳሉ። በርግጥ ጌታችን የካዱትን መልሶ የሚያነሣ አምላክ
በመሆኑ በማለደላቸው መሠረት መልሶ አነሣቸው። (ሉቃ22÷31፤
ዮሐ 21÷15-17) እኛ ግን ከካዱን በኋላ "መልሰን እንዴት የራሳ
ችን ልናደርጋቸው እንችላለን?" የወደቁትን የሚያነሣ፣ የካዱትን
ይቅር የሚል ጌታ መድኀኒታችን ብቻ ነው። ሰሞነኛ ደቀ መዝ
ሙር ልንሰበስብ እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን የዘለቄታ አይሆኑ
ንም። በክፉ ቀን ተትውን ይሄዳሉ ። እኛም ደግሞ የእግዚአብ
ሔር የሆነውን ለራሳችን አድርገናልና ልንተው ይገባናል! ጥሪ

ያችን የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሆነን፣ ሌሎችን ደቀ መዛሙ
ርት የእርሱ ተከታዮች እንድናደርግ ነው።

## 5. ምግባረ ሠናይ - የምኅረት አገልግሎት

እግዚአብሔር በኅብረተ ሰብ ውስጥ የተለያየ ጉዳት ለደረሰባ
ቸው ሁሉ ይገደዋል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ተጨንቆ
እንዲኖር ሳይሆን ተመቻችቶ እንዲኖር እንደ ነበረ የመጀመ
ሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች በግልጥ ያሳዩናል።

እግዚአብሔር፣ ሰው ተፈጥሮን ይንከባከብና ይጠብቃት ዘንድ
የሥራ ባለ አደራ አደረገው። ይልቁንም ሰው ለሌላው ሰው በጎነት
የበለጠ ኀላፊነት እንዳለው ከዚሁ እንረዳለን። የተፈጥሮን በረ
ከት፣ የምድርን በረከት እያንዳንዱ ሰው የራሱ ድርሻ እንዲኖ
ረው እግዚአብሔር በፍጥረት አባትነቱ ፈቅዶአል። ለቀደመው
የኪዳኑ ሕዝብ የደነገገው የኢዮቤልዩ ሥርሀት (ዘሌ 25) ይህ
ንኑ እውነት ያረጋግጣል።

በአንድ ቤት ውስጥ እንዳሉ በወላጆችና ልጆች ዘንድ እንደሚ
ታይ ወይም መገኘት እንደሚኖርበት ሀይነት መተሳሰብ፤ አንዱ
ለሌላው መጠንቀቅ፣ የአንዱን ደስታ ወይም ሐዘን ሌላው እን
ደራሱ አድርጎ ደስታውን መደሰት ሐዘኑንም መካፈል፣ ሸክ
ሙን መሸከም ማለት ነው።

እግዚአብሔር የኪዳኑን ሕዝብ እንደ አንድ አባት ልጆች፣ እንደ
ወንድማማቾች አድርጎ እንደሚቈጥራቸው መጽሐፍ ቅዱስ
ያስገነዝበናል። ይህም ቤተሰባዊ መተሳሰብ በዚሁ እውነት ላይ
የሚመሠረት ነው።

በኪዳኑ ኅብረተሰብ መካከል በዝቅተኛ ደረጃ ለሚቈጠሩ ክፍ
ሎች ኅብረተሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ እግዚአብሔር
አበክሮ ያስገነዝባቸዋል። ጥንቃቄ ሊደረግላቸው የሚገቡ የኅብ



ረተ ሰቡ ክፍሎች:-

1. ስደተኞች
2. ድሃ አደጎች /ወላጅ አጦች/
3. መበለቶች እንዲሁም ለድሆች በአጠቃላይ
4. ሙያተኞች

በዚህ ረገድ ትምህርት ከሚሰጡን ብዙ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶ
ችን ልንመለከት እንችላለን። የሚከተሉት ዐሳቦች የጥንቃቄውን
ዐይነት ይፈነጥቃሉ የመተሳሰብን አስፈላጊነት ያስረግጣሉ።

1. «ከአንተ ጋር ለተቀመጠው በወገኔ ለድሃው ገንዘብ ብታበድ
ረው፣ እንደ ባለ አራጣ አትሁን ....» ዘፀ 22፥25
2. «የምድራችሁን መከር በሰበሰባችሁ ጊዜ የእርሻችሁን ድን
በር ፈጽማችሁ አትጨዱ፣ የመከሩንም ቃርሚያ አትልቀሙ።
የወይንህን ቃርሚያ አትቃርም፤ የወደቀውን የወይንህን ፍሬ
አትሰብስብ፤ ለድሆችና ለእንግዶች ተወው። እኔ እግዚአ
ብሔር አምላክህ ነኝ።» ዘሌ 19፥9-10
3. « .... የሞያተኛው ዋጋ እስከ ነገ ድረስ በአንተ ዘንድ አይ
ደርብህ።» ዘሌ 19፥13
4. «አምሳኛውን ዓመት ትቀድሳላችሁ በምድሪቱም ለሚኖሩባት
ሁሉ ነፃነትን ታውጃላችሁ፣ እርሱ ለእናንተ ኢዮቤልዩ ነው፣
ሰው ሁሉ ወደ ርስቱና ወደ ወገኑ ይመለስ።» ዘሌ 25፥10
5. «ወንድምህም ቢደኸይ ራሱንም ለአንተ ቢሸጥ እንደ ባሪያ
አድርገህ አትግዛው።» ዘሌ 25፥39
6. «በየሰባቱ ዓመት መጨረሻ የዕዳ ምሕረት ታደርጋለህ። ....
ከወንድሞችህ አንድ ቢደኸይ፣ ልብህን አታጽና፣ በድኻው
ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ። .... ሰባተኛው ዓመት
የዕዳ ምሕረት ዓመት ቀርቧል ብለህ ክፉ አሳብ በልብህ
እንዳታስብ፣ ለድሃውም ወንድምህ አንዳች የማትሰጥ እንዳ
ትሆን ... በሰጠኸውም ጊዜ በልብህ አትፀፀት። ... ለተቸገ

ረው ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አዝዝሃለሁ።»
ዘዳ 15፥1-11

7. «አምላክህ እግዚአብሔር በረከት እንደ ሰጠህ መጠን እያን ዳንዱ ሰው እንደ ችሎታው ይስጥ።» ዘዳ 16፥17

« .... ያም ሰው ድኻ ቢሆን መያዣውን በአንተ ዘንድ አታሳ ድር ... ድኻና ችግረኛ የሆነውን ምንደኛ .... አታስጨን ቀው፤ .... ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በየቀኑ ስጠው። .... የእር ሻህን መከር ባጨድህ ጊዜ ነዶም ረስተህ በእርሻ ብታስቀር፣ ትወስደው ዘንድ አትመለስ፤ አምላክህ እግዚአብሔር በእጅህ ሥራ ሁሉ እንዲባርክህ ለመጻተኛና ለድኻ አደግ ለመበለትም ተወው። የወይራህን ፍሬ ባራገፍህ ጊዜ ከቅርንጫፎቹ ላይ ማር ገፍን ለማጣራት አትመለስ ለመጻተኛ፣ ለድኻ አደግ፣ ለመ በለትም ይሁን። የወይንህን ፍሬ በቈረጥህ ጊዜ ቃርሚያውን አትልቀመው ለመጻተኛና ለድኻ ዐስብ፣ ስለዚ ' ይህን ታደርግ ዘንድ አዝዝሃለሁ።» ዘዳ 24፥10-22

ይህ መተሳሰብ ማዕከሉ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ» የሚለው መሠረታዊ እውነት ነው። /ዘሌ 19፥10:31:34:37/

መታዘዝም ተግባራዊ የሚሆነው በዚሁ እውነት ላይ በሚመሠ ረት እምነት ነው። የነገም ዋስትናችን በእኛ ዘንድ የተካ በተ ዕውቀት፣ ሃብትና ጥሪት ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን ስንገነዘብ ነው። ይህም እምነትን ግድ ይላል።

እግዚአብሔር ልጆቹ ሁሉ ደስ እንዲላቸው ይሻል። አንዱ ተር ፎት ሌላው ጉድሎበት ሲቸገር፣ ሲሰቃይ የእግዚአብሔር ደስታ አይደለም። የዚህም ጥያቄ መልሱ ያለው ለጉደለው ማካፈሉ ላይ ነው። ይህም ለእግዚአብሔር የምስጋና መስዋዕት ያበዛል።

2ኛ ቆሮ 8፥13-15፤ 9፥6-13፤ ዘዳ 16፥17



የእግዚአብሔር እጅ ሥራ ማለትም (ተፈጥሮ) ይህን እውነት ያስተምረናል።

ውሃ:- ከከፍታ ወደ ዝቅታ ይፈሣል።
ሙቀት:- ከበለጠ የሙቀት አካል ወደ ዝቅተኛ ሙቀት አካል ይፈሣል።
አየር:- ከበለጠ የአየር ግፊት ወደ ዝቅተኛ አየር ግፊት ይነፍሳል።
ዐፈር:- ከተራራማ ስፍራ ወደ ጐድጓዳማ /ረባዳ/ ስፍራ ይወ ርዳል።

እንዲሁም ሀብትና ጥሪት፣ ዕውቀትም ካለው ሰው ወደ ጐደለው ሊጨመር ወይም ሊተላለፍ ይገባል። ሆኖም በፈቃደኝነትና በደስታ መሆን ይኖርበታል። ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ዐይነቱ ምግባረ ሠናይ ህይነተኛ ምሳሌ ልትሆን ያስፈልጋታል።

በኑሮው የተደላደለ ሰው ለተቸገረው፣ ጕዳት ለደረሰበት እንክ ብካቤ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ያዛል። የእግዚአብሔር ወገ ንነት የሚገለጠው በዚሁ ምግባረ ሠናይ የተሞላ አኗኗር ነው። በኢሳ 58 ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነት የጾምም ይዘት:

የጭቈናን ሰንሰለት መበጠስ - የተጨቈኑትን ነፃ ማውጣት፣
የቀንበርን ገመድ መፍታት - ቀንበርን መስበር፣
ምግብን ለተራብ ማካፈል፣ ለተንከራታቹ ድኻ መጠለያ መስ ጠት፣
የተራቈተውን ማልበስ፣
ችግረኛውን የሥጋ ዘመድን ፊት አለመንሣት የመሳሰሉት ትሩፋት መሆናቸውን አበክሮ ያስረዳናል።

ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለሰው ልጆች የሚያቀ ርበው ጥያቄ፣ እንዴት የምድርን ኑሮ ተጓዛችሁ በሚል ረገድ

የሚታዩ የግምገማ ጥያቄዎች:

| | | |
|---|---|---|
| ተርቤ | - | አበላችሁኝ? |
| ተጠምቼ | - | አጠጣችሁኝ? |
| እንግዳ ሆኜ | - | ተቀበላችሁኝ? |
| ታርዤ | - | አለበሳችሁኝ? |
| ታምሜ | - | ጠየቃችሁኝ? |
| ታስሬ | - | ጠየቃችሁኝ? |

በሌላ አነጋገር በነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች እንጻር ምን ምግባረ ሠናይ አከናወናችሁ? ምን የምኅረት አገልግሎት ፈጸማችሁ? የሚል ነው:: ይህም በጎ አድራጎት በጌታ ዘንድ ታላቅ ቦታ እንዳለው ያስገነዝባል::

በተራራው ስብከት እንደተጠቀሰው:

"ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ" የሚለው የጌታችን ትዕዛዝ የሚያተኩረው ተከታዮቹ በኅብረተ ሰብ ውስጥ በሚያሳዩት ቀና አመለካከትና ምግባረ ሠናይ ላይ ነው::

## 6. የጽድቅና የፍትሕ አገልግሎት

በብሉይ ኪዳን ስንመለከት ጽድቅና ፍትሕ ብዙውን ጊዜ ተያይዘው በጥንድ ይቀርባሉ፤ ጽድቅ የውስጥን ሁኔታ ሲያመላክት፣ ፍትሕ ደግሞ ጽድቅን በተግባር የመገለጽ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ሆኖ ይታያል:: ጽድቅና ፍትሕ ተወራራሽነት አላቸው:: ሁለቱም እግዚአብሔር ከሰጠው ሞራላዊ መለኪያ ጋር በልብ በተግባርም ተጣጥሞ መገኘት ነው:: ጽድቅ የልብ (የውስጥ) ሁኔታን ሲያመለክት፣ ፍትሕ ድርጊትን ያሳያል::



ፍትሕ በምድር ላይ የሚሰፍነው በሰዎች መካከል ኀይልና ሥልጣን በአግባቡ ማለትም የእግዚአብሔርን መመሪያ በጠበቀ መልኩ ሥራ ላይ ሲውል ነው:: ምንጊዜም ኀይልና ሥልጣን በኅብረተ ሰብ መካከል በእያንዳንዱ ግለ ሰብ ላይ ተሠራጭተው ይገኛሉ:: የሥርጭት መጠናቸውም ከሰው ወደ ሰው ይለያያል:: በሰዎች መካከል ልዩ ልዩ ኀይሎች አሉ፤ ለምሳሌ ያህል የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ግብረ ገባዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ቤተ ሰባዊ፣ የጉልበትና የአእምሮ ብሎ መጠቃቀስ ይቻላል::

እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ነው ካልን እነዚህ ኀይሎች በትክክል ተግባር ላይ ሳይውሉ ቢቀር ይገደዋል ማለታችን ነው:: ፍትሕ ተዛባ ስንል የሌሎችን ሕይወት፣ ክብር፣ ጸታዊ ፈቃድ፣ ነጻነት፣ ጒልበት፣ ሥራ፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ጥቅም ለመንፈግ ወይም ለመንጠቅ ኀይል ወይም ሥልጣን በአሉታዊ መልኩ ሥራ ላይ ውሎአል ማለት ነው::

እግዚአብሔር የጽድቅና የፍትሕ አምላክ ነው:: ጽድቅና ፍትሕ ከእርሱ ባህርይ የሚመነጩ ናቸው:: ቤቱም የጽድቅና የፍትሕ ቤት እንዲሆን ይሻል:: ሕዝቡ በጽድቅና በፍትሕ የሚኖር ከዚያም አልፎ ለጽድቅና ለፍትሕ መስረጽ የሚሠራ፣ የሚቆም፣ የሚሟገት እንዲሆን ይወዳል::

*"ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶችናቸው፤*
*ምሕረትና ታማኝነት በፊትህ ይሄዳሉ"* (መዝ 89፥14)::

*"ፍትሕን የምትወድ፣ ኀያል ንጉሥ ሆይ፤*
*አንተ ትክክለኛነትን መሠረትህ፤*
*ፍትሕንና ቅንነትንም፣*
*ለያዕቆብ አደረግህ"* (መዝ99፥4)::

*"ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤*
*እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው?*

*ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣*
*በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ*
*አይደለምን?"* (ሚኪ 6፥8)

እግዚአብሔር ሕዝቡ በገዛ ጥበቡ፣ ኀይሉ፣ ወይም ብልጥግናው እንዲመካ አይሻም:: እንዲያውም ይከላከላል:: የሚመካ ግን እግዚአብሔርን በማወቁ በተለይም በምድር ላይ ምኅረትን፣ ፍትሕንና ጽድቅን የሚያደርግ እርሱ መሆኑን በመረዳቱ እንዲመካ ይፈልጋል:: እግዚአብሔር በእነዚህ ነገሮች ደስ ይሰኛል (ኤር 9፥24)::

በሃይማኖታዊ ሥርሀት፣ በዳኝነት፣ በንግዱ እንቅስቃሴ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት፣ በማኅበራዊ ግንኙነት፣ በሕዝብ አስተዳደር፣ በአገሮች መካከልም ፍትሕ እንዲሰፍን እግዚአብሔር ይሻል::

እግዚአብሔር በኅብረተ ሰቡ መካከል ፍትሕ ሲጓደል መንግሥታትም ግፍ ሲፈጽሙ፣ ኢፍትሐዊ ሕግን ሲያወጡ ነቢያቱን እያስነሣ ይገሥጽ፣ መንገዳቸውንም እንዲያስተካክሉ ይጣራ፣ አሻፈረኝም ሲሉ ይቀባ ነበር:: የመቅጫውም መንገዶች ረሓብ፣ ሰይፍ፣ ቸነፈር እና ክፉ አውሬዎች ነበሩ::

ለአብነት ያህል በዚህ አቅጣጫ የተጻፉትን በመቶ ከሚቈጠሩት መካከል ጥቂቶቹን ለግንዛቤያችን ያህል እንጥቀስ፡

*"በመስፈሪያ ወይም በሚዛን አታጭበርብሩ:: እውነተኛ መለኪያ፣ እውነተኛ መመዘኛ፣ እውነተኛ የኢፍ መመ ዘኛ፣ እውነተኛ የኢን መስፈሪያ ይኑራችሁ:: ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ:: ሥርዐቴንና ሕጌን ሁሉ ጠብቁ፤ ተከተሏቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ"* (ዘሌ 19፥35-37)::

*"እግዚአብሔር የተጭበረበረ ሚዛንን ይጸየፋል፤*
*ትክክለኛ መለኪያ ግን ደስ ያሰኘዋል"* (ምሳ11፥1)::



*"ነጋዴው በሐሰተኛ ሚዛን ይሸጣል፤*
*ማጭበርበርንም ይወዳል"* (ሆሴ 12፥7)::

*"እናንት ችግረኞችን የምትረግጡ፣*
*የምድሪቱንም ድኾች የምታጠፉ ይህን ስሙ፤*

*እንዲህም ትላላችሁ፤*
*መስፈሪያውን በማሳነስ፣*
*ዋጋውን ከፍ በማድረግ፣*
*በሐሰተኛ ሚዛን በማጭበርበር፣*
*እህል እንድንሸጥ፣*
*የወር መባቻ መቼ ያበቃል?*
*ሰንዴም ለገበያ እንድናቀርብ፣*
*ሰንበት መቼ ያልፋል?"* (አሞ8፥4-5)

*"የክፉት ቤት ሆይ፤*
*በግፍ የተገኘ ሀብታችሁን፣*
*በሐሰተኛ መስፈሪያ የሰበሰባችሁትን*
*አስጸያፊ ነገር እረሳዋለሁን?*
*አባይ ሚዛን የያዘውን ሰው፣*
*ሐሰተኛ መመዘኛ በከረጢት*
*የቋጠረውን ንጹሕ ላድርገውን?*
*ባለጠጎቿ ግፈኞች፣*
*ሰዎችዋ ሐሰተኞች ናቸው፤*
*ምላሳቸውም አታላይ ናት "* (ሚክ 6፥10-12)::

*"በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን ለሚገነባ፣*
*ከጠላት እጅ ለማምለጥ*
*ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሠራ ወዮለት!"* (ዕን 2፥9)::

*"ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣*
*ጭቈና የሞላበትን ሥርዐት ለሚደነግጉ ወዮላቸው!*

*የደ ኾችን መብት ለሚገፉ፣*
*የተጨቈነውን ሕዝቤን ፍትሕ ለሚያዛቡ፣*
*መበለቶችን ለሚበዘብዙ፣*
*ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለሚመዘብሩ ወዮላቸው!"*
(ኢሳ 10፥1-2)።

*"ከትንሹ እስከ ትልቁ ሰው፣*
*ሁሉም ለጥቅም የሚስገበገቡ ናቸው፤*
*ነቢያቱም ካህናቱም ሳይቀሩ፣*
*ሁሉም ያጭበረብራሉ"* (ኤር 6፥13)።

ነቢያት ፍትሕ ሲጓደል ለፍትሕ የተሟገቱት ሥልጣንን በምንም መልኩ በመጓጓት አልነበረም። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ይህ ጥሪና አገልግሎት አለባትና ቤተ ክርስቲያን ፍትሕንና ሰላምን በኅብረተ ሰብ ውስጥ ለማስረጽ አስቀድማ በጽድቅና በፍትሕ፣ በእርቅና ሰላም ረገድ ራሷ ሕያው ምሳሌ መሆን ይኖርባታል፤ አለበለዚያ ጥረቷ ሁሉ በተራበሸው ዓለም ዘንድ እንኳ ዋጋና ከበሬታ አይኖረውም። በዚህ አኳያ ቤተ ክርስቲያን የት ነው ያለችው?

እግዚአብሔር ሕዝቡ ጽድቅንና ፍትሕን ረግጦ የአምልኮ ሥርዐቱን ቢያደምቅ፣ የመሥዋዕት ጋጋታ ቢያቀርብ ጸሎትና ዝማሬ ቢያበዛ ምንም ስፍራ እንደማይሰጠው ደጋግሞ በነቢያቱ ተናግሮአል።

*"እናንተ የሰዶም ገዦች፤*
*የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤*
*እናንተ የገሞራ ሰዎች፤*
*የእግዚአብሔርን ሕግ አድምጡ።*

*ታጠቡ፤ ራሳችሁንም አንጹ፤*
*ክፉ ሥራችሁን ከፊቴ አርቁ፤*
*ክፉ ማድረጋችሁን ተዉ፤*



*መልካም ማድረግን ተማሩ፤*
*ፍትሕን እሹ፣*
*የተገፉትን አጽናኑ፤*
*አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው፤*
*ለመበለቶችም ተሟገቱኝ* (ኢሳ 1፥10:16-17)።


*"እኔ ግን፣*
*ለያዕቆብ በደሉን፣*
*ለእስራኤልም ኀጢአቱን እነግር ዘንድ፣*
*ኀይልን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ፣*
*ፍትሕና ብርታት ተሞልቻለሁ፤*
*እናንተ የያዕቆብ ቤት መሪዎች፣*
*እናንት የእስራኤል ቤት ገዦች፣*
*ፍትሕን የምትንቁ፣*
*ትክክለኛ የሆነውንም ነገር ሁሉ የምታጣምሙ፣ ስሙ፤*
*ጽዮንን ደም በማፍሰስ፣*
*ኢየሩሳሌምን በክፋት የምትገነቡ፤ ስሙ።*
*መሪዎቿ በጉቦ ይፈርዳሉ፤*
*ካህናቷ ለዋጋ ሲሉ ያስተምራሉ፤*
*ነቢያቷም ለገንዘብ ሲሉ ይናገራሉ።*
*ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ተደግፈውም፣*
*እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን?*
*ምንም ዐይነት ክፉ ነገር አይደርስብንም ይላሉ"*
(ሚክ 3፥8-11)።

*"ዓመት በዓላችሁን ተጸይፌአለሁ፤*
*ጠልቼውማለሁ፤*
*ጉባኤዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም።*
*የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል*
*ቍርባን ብታቀርቡልኝም፣*

*እኔ አልቀበለውም፤*
*ከሰቡ እንስሶቻችሁ የኅብረት መሥዋዕት ብታቀርቡልኝም፣*
*እኔ አልመለከተውም።*
*የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤*
*የበገናህንም ዜማ አልሰማም።*
*ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣*
*ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍሰስ* (አሞ5፥21-24)።



# IV. የአዲስ ኪዳን ኅብረተ ሰብን የሚገዳደሩ ተቃውሞዎች




1 ሳሙ 8፥19-20

## 1. አሮጌው ሰው እና የዓለም ሥርዐት

እግዚአብሔር ሲፈጥረን የራስ ሕልውና ግንዛቤ ሰጥቶናል። እኔ ማለት እንድንችል አድርጐናል። ከዚያም በላይ ፈቃድ ያለን ፍጡሮች አድርጐናል። ያ ብቻ አይደለም ልዩ ልዩ ፍላጐት በውስጣችን አኑሮአል። የመብላት ፍላጐት፣ የመጠጣት ፍላጐት፣ የወሲብ ፍላጐት፣ የክብር ፍላጐት፣ የማወቅ ፍላጐት፣ የመውደድ የመወደድ ፍላጐት፣ ሌሎችም ፍላጐቶች አስቀምጦብናል።

ነገር ግን እግዚአብሔር እነኝህን ፍላጐቶች በእኛ ሲያሳድር እነኚህ ፍላጐቶች ደግሞ የሚረኩበትን ምንጮች አንጥፎ ወይም አምክኖ አይደለም። እግዚአብሔር ረሓብን ፈጥሮ የሚበላ ባይሰጠን ኖሮ ያሳዝን ነበር። ግን እንዲርበን ሲያደርግ የሚበላም አዘጋጅቶአል።

ሆኖም የሚበላ ሲያዘጋጅ አንዳንድ መልአክ መድቦ እየቈረጠ እንዲያበላን አላደረገም። ሰውነታችን እንዲንቀሳቀስ አድርጓል። እግራችን ይሄዳል። ይሁንና እነዚህ ፍላጐቶቻችን መርካታቸው አስፈላጊ ቢሆንም በሥርዐቱ በአግባቡ እንዲረኩ እግዚአብሔር ወዶአልና ለዚህ ጕዳይ ተጠሪ እንዲሆን በውስጣችን ፈቃዳችንን አሳድሯል።

«በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ እግዚአብሔር አለ፤ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም» የመብላት ፍላጐት መርካት ነው የሚሻው፤ በምንም ዐይነት መንገድ መርካት ነው። ከየትኛውም በልቶ ሊረካ ነው የሚፈልገው። ግን ከተከለከለው በልቶ መርካትን ሊከላከል የሚገባው ፈቃድ አለ። በዚህ ረገድ ፈቃድ የፍላጐት ልጓም ሆኖ እንዲያገለግል እግዚአብሔር ሰጥቶናል።

ፍላጐቶቻችን «እምጣ» ነው የሚሉት። በልቶ የመርካት ፍላጎታችን:-



- "ሂጂ እግሬ" (ወደ ዛፉ)፣
- "ቅጠፊ እጄ" (ፍሬውን)፣
- "ግመጥ አፌ" (የተቀጠፈውን) ... ነው የሚለው፤ ነገር ግን እነዚህን ፍላጐቶች በፈለግነው እንድናረካቸው አይወድም። መመሪያ ሰጥቶናል። ከፈቃድ ጋር አብሮ የሚሠራ ኅሊና፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየጠበቀ የሚሠራ ኅሊና አድርጓል። ፈቃድ የኅሊናን ሀሳብ አስከባሪ ነው። የወሲብ ፍላጐት ያድርብናል። በወንድና በሴት መካከል መሳሳብን እግዚአብሔር አስቀምጧል። ይሁንና የእግዚአብሔር ሀሳብ ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ነው።

የሥጋ ፍላጐት ግን ያጓጓውን ሁሉ መያዝ ይሻል። ፈቃድ በዚህ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ቃል መመሪያ "ይህ አይሆንም!" ማለት ያስፈልገዋል። መቼም በውድቀት ጊዜ ፈቃዳችን ጉልበት አጥቷል። ይሁንና ወደ ክርስቶስ ስንመጣ ፈቃዳችን በመንፈስ ቅዱስ ብርታት አግኝቷል። ፈቃዳችን ሕያው ሆኗል። የመንፈስ ቅዱስን ሀሳብ እንዲያገለግል በፈቃዳችን ውስጥ የእግዚአብሔር ኀይል ሆኖልናል። የማይሆነውን አይ ለማለት መንፈስ በሥጋ ላይ ይነሣል። ሥጋ በመንፈስ ላይ ይነሣል። ወደ ክርስቶስ ስንመጣ አዲሱ ሰው በእኛ ውስጥ ማደር ጀምሯል።

ዐዲሱ ሰው የራሱ መሻትና ፍላጐት አለው። የቀደመው ሰው የራሱ መሻትና ፍላጐት አለው። በመካከላቸው ፈቃድ ይገባል። ፈቃድ አላግባቡ ሊረካ በሚፈልገው የተፈጥሮ ፍላጐት ላይ ልጓም እያስገባ ይገታል፡፡ መረን ወጥቶ ለመርካት የሚፈልገው ላይ ልጓም ይይዛል።

አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የሆኑትም ጭምር «ይህን ፍላጐት ያሳደረብን እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ይህን ፍላጐቴን ባረካ ተጠያቂው እኔ ብቻ ሳልሆን እርሱ የፈጠረኝ ጭምር ነው» የሚሉ አሉ።

ፈጣሪ ፍላጐት ብቻ ሰጥቶን ያለፈቃድ አልተወንም፤ ያለ ኀሊና
አልተወንም፤ ፈቃዳችን ፍላጐታችንን በአግባቡ እንዲቈጣጠር፣
እንዲሄድ፣ ልጓም እንዲሆን ነው የተሰጠን። እነኝህ ራሳቸውን
የማይገዙ የተባሉት ፍላጐቶቻቸውን በእግዚአብሔር ቃል ሥር
ዐት የማያስኬዱ ናቸው። እግዚአብሔር ደግሞ የማይሆኑ ፍላ
ጐቶቻችንን ለመቆጣጠር ለፈቃዳችን የመንፈስ ቅዱስን ኀይል
በውስጣችን አድርጐአል። ስለዚህ ልናመልጥ አንችልም።

ሮሜ 7 ላይ ጳውሎስ ምን ያህል የውስጥ ትግል እንደ ነበረው
እናያለን። በሮሜ 7 ላይ በጥቂቱ በጳውሎስ ትግል ውስጥ መጀ
መሪያ ላይ ሕግን ሲኮንን እናያለን። ሕግን ይኮንናል፤ ሕግ ባይ
ኖር ኖሮ ኀጢአትን ባላወቅሁም፣ ኀጢአት ባልተቈጠረብኝና
ኀጢአተኛ ባልሆንሁ ኀጢአተኝነቴ ባልተረጋገጠ ነበር ይላል።

መጀመሪያ ሕግን ሲኮንን ይቆይና ከዚያ ሕግን ተወት ያደር
ግና የራሱን ሕይወት ይቃኛል፤ ይመለከታል። በራሱ ሕይወት
ውስጥ ለማድረግ የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ። መልካም ናቸው።
ሆኖም እነኛን፣ መልካም የሚላቸውን ነገሮች ለማድረግ ሳይ
ችል ያገኘዋል። እርሱ ሆኖ ወይም ፈጽሞ ለመገኘት የሚሻው
ንና ሕጉ የሚያዘውን ሲያስተያይ ተመሳሳይ ናቸው። እንግዲያ
ውስ ብሎ የሕግን መልካምነት ይመሰክራል። እንዲህም ይላል፣
«ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለን። እኔ ግን ከኀጢአት
በታች ለመሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። የማደርገውን አላውቅ
ምና፣ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፣ ጻሩ ግን የምወደውን እር
ሱን አላደርገውም፤ የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንኩ ሕግ
መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ» ይላል።

በሕግ ላይ የሚያሰማውን ሮሮ ተወት ያደርግና ወደ መሻቱ
ይመለሳል። እርሱ የሚሻው መልካም ነገር ማድረግ ነው። ግን
ያንን ለማድረግ የሚፈልገውን መልካም ነገር ለማድረግ አቅቶት
ያገኘዋል። ያ የሚጓጓውን፣ ሆኖ መገኘት የሚሻውንና ሕጉ የሚ



ለውን፣ ሲያስተያያቸው ተመሳሳይ ናቸው። እንግዳው ሕጉ መን
ፈሳዊ ነው፤ ግሩም ነው። መልካምን ለማድረግ እየፈለግሁ
የማላደርግ ከሆነ ችግሩ እኔውጋ ነው ይላል። የማልወደውን
ግን የማደርግ ከሆንሁ እኔ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራ
ለሁ። የምሻውን የማላደርግ ከሆነ ያን የማደርገው እኔ አይደለ
ሁም፤ በእኔ የሚያድር ኀጢአት ነው እንጂ» ይላል። ይኸ ሀሳብ
ትንሽ የተሳከረ ይመስላል፤ አልሸሹም ዞር አሉ እንደሚባል።

አባባሉ ግን እኔ ዐውቄ /consciously/ በፈቃዴ የማደርገው አይ
ደለም። ምናልባትም እኔ መናደድ ሳልፈልግ፣ ሳልናደድ መመ
ላለስ ስፈልግ፣ ነገር ግን ራሴን ተናድጄ አገኘዋለሁ። እኔ ለመ
ሳደብ አልፈልግም፣ ግን ተሳድቤ አገኘዋለሁ፤ እንደ ማለት
ይሆናል።

እንግዳው ያን የማደርግ ከሆነ ያን የማደርገው እኔ አይደለሁም፤
በእኔ ያደረ ኀጢአት ነው እንጂ። ምናልባት በኅቡዕ አእም
ሮው (Subconscious mind) የሚያድረውን የአሮጌውን ሰው
ባሕርይ የሚያመለክት ነው።

ሌባ ማነው? የሰረቀው ነው ወይስ የሚሰርቅ ነው? ሌባ የሰረቀ
ነው ወይም ሰው ሌባ የሚሆነው ሲሰርቅ ነው። ግን ሌባ ካል
ሆነ ደግሞ እንዴት ይሰርቃል? ኀጢአተኝነታችን በሁለት ሊከፈል
ይችላል። አንዱ ሀውቀን በገሃድ በድርጊት የምንገልጠው ሌላው
ግን ኀጢአት ለመፈጸም ያለን እምቅ አቅም ወይም ዝንባሌ
ነው። መቼም እኛ ኀጢአተኞች ነን ስንል አንዳንድ ጊዜ ምን
ሠራሁኝ እንላለን። እኛ አልሰረቅን ይሆናል፤ ለምሳሌ ምግብ
እንደልብ የምናገኝ ከሆነ ለመስረቅ ምክንያት የለንም። ነገር
ግን ምግብ የማናገኝ ከሆነ ቢርበን እንሰርቃለን። በመሠረቱ
የመስረቅ ነገር ውስጣችን አለ፤ ሁኔታዎች አላጋለጡትም እንጂ።
በመካከላችን ጠባያችንን የሚለያየው፣ ያለንበት ሁኔታ የሚያ

ጋልጥ ወይም የማያጋልጥ በመሆኑ ነው። ስለዚህም አንዳንድ ኀጢአቶችን ሽሹ የሚለው ቃሉ፣ በመሸሽ በተግባር ከመፈጸም የሚመለጡ ኀጢአቶች እንዳሉ የሚያስገነዝብ ነው።

ሰው ሁሉ ቢያሞግሰኝ ለእኔ ደስታ ነው። የማሳየውም ትህትና፣ እጅ መንሳቴ ሁሉ፣ ለተሰጠኝ ሙገሳ ምላሽ ነው። ግን ያበሻ ቀጠኝ እንደ ሆነ አውሬ ልሆን እችላለሁ። በጉባኤ ፊት አዳማ ጮቼን ባፋጭ ሰላምታ ሳቀርብ ፈገግ ይላሉ፣ ትንሽ ግን መብታ ቸውን የሚነካ ቋንቋ ብናገር ወዲያው ይበሳጫሉ፣ 'ይሄ ሁሉ ደነዝ ተሰብስቦ' ሀይነት ቋንቋ ብናገር ስሜታቸው ይደፈርሳል፣ ይለወጣል።

የመጀመሪያው ፈገግታ፣ የሁልጊዜ ፈገግታ፣ የዘለቄታ ፈገግታ አይደለም። የሁኔታዎች ነጸብራቅ ነው። አንዳንድ ሊቃውንት ለዚህ ነው ሰዎች ሌላ ምንም አይደሉም፣ መንኩራኩር ናቸው፣ ለሚደረግባቸው ተፅዕኖ ምላሽ ሰጪ ናቸው። ሲሞገሱ ደስ ይላ ቸዋል፣ ፈገግ ይላሉ። ሲሰደቡ ይቆጣሉ። እና ሰው መንኩራ ኩር ብቻ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን ሰው ከዚያ የከበረ ነው።

በሁለት መንገድ ኀጢአተኞች ነን። በተለይ ይሄንን ከውስጥ እየመጣ፣ እየገፈተረ፣ የማይፈልገውን የሚያስደርገውን፣ ያይና ጳውሎስ በጣም ይማረራል። "እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ። ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" ይላል፣ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ተስፋ ማጣት ውስጥ ይገባል።

ደግነቱ አልቻልንም እቃተን፣ ማን ያድነናል ስንል በእኛ ተስፋ ማጣት ውስጥ በዚያ ጨለማ ውስጥ ፏ ብሎ የሚመጣ፣ እኔ አዳኝ ነኝ የሚል፣ ብርሃን አለ። ማን ያድነኛል ብለን ስንል ሁል ጊዜ እኔኮ ላድናችሁ አለሁኝ የሚል ድምፅ እንሰማለን፣ ብርሃ ንም እናያለን። እርሱም መድኀኒታችን ጌታ ኢየሱስ ነው።



አዳኙ ጌታ ኢየሱስ እኮ በሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ አለ። እርሱ በአ ዳኝነት የታወቀ ፍቱን መድኀኒት ነው። በዘላለም ታሪክ ውስጥ የታወቀ ነው። እርሱ ብቻ አዳኝ ነው። የዚህን ጊዜ ማን ያድነ ኛል ባለበት በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለጳውሎስ ፏ ብሎ መጣ ጌታ ኢየሱስ። ወዲያው ከመቅጽበት ከዚህ ተስፋ ከማጣት ሁኔታ ውስጥ አወጣው፣ በመንፈሱም ብድግ ብሎ ምስጋና ውስጥ ይገባል። «በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» ይላል። እንግዲህስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ በሥጋዬ ለኀጢአት ሕግ እገዛለሁ። ወይም በሌላ ቋንቋ ይህ የአ ሮጌው ሰው ሥርዐት በኔ ውስጥ ይኖራል። እኔ ግን በንቁው ማንነቴ፣ በፈቃዴ ለእግዚአብሔር ሕግ እገዛለሁ ይላል።

ያ አሮጌው ሰው፣ በእኛ ውስጥ ያለው ከእኛ አይወገድም። በአፀደ ሥጋ እስካለን አሮጌው ሰው ቊጥጥር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል እንጂ አይደመሰስም ወይም ጨርሶ አይጠፋም። ግዞት እናወርደው ይሆናል እንጂ ግባተ መሬቱን እንፈጽምም። በየጊዜው ፍተሻ ማድረግ ያለብን ከእስር ቤት ተቆልፎበት ያለ መሆኑን ነው። በኀጢአት ላይ ስልጣን አለን (ከመስቀሉ ሥራ የተነሣ) እንጂ ይህ ሥጋ ብለን የምንጠራው አሮጌው ሰው ምንም ሀይነት መን ፈሳዊ ዐውድ ልምምድ ውስጥ ቢያልፍ ባሕርዩን አይለውጥም። ከእሁድ ጀምረን ሰኞ ዕለትንም ጨምረን ቤተ መቅደስ ብናው ለው ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሐሙስ፣ አርብም ቢውል አይ አሁን ተገ ርቷል፣ ዛሬ ምንም አይደለም እንልቀቀው ብንል ያንን የድሮ ውን ጠባይ ሙሉ በሙሉ ይዞ ከተፍ ይላል።

የክርስቶስ የሆኑቱ ሁሉ ሥጋን ከክፉ መሻቱ ጋር ሰቀሉ ይላል። ሌላ ቦታ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ የሚል አለ። ዶክተር ጆን ስቶት እንደሚሉት "አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን" የሚለው የሮሜ 6፥6 ሀሳብ ከገላትያ 5፥24ቱ ሀሳብ የተለየ ነው።

ስቅለት በዚያን ዘመን እንደምናውቀው የአፍታ ጉዳይ አይደለም:: መድኀኒታችን ተሰቅሎ ከመስቀል ላይ እንዳይወርድ ወይም ሌሎች መጥተው እንዲያወርዱት ጥበቃ ተካሂዷል:: ሥጋን ከክፉ መሻቱ ጋር የመስቀሉ ተግባር የእያንዳንዳችን ኀላፊነት ነው:: ይኸ መስቀል፣ አንገት በገመድ ውስጥ ገብቶ እንደመንጠልጠ ልና ሲጥ ብሎ እንደ መሞት ያለ አይደለም:: ማቅቆ ማቅቆ፣ ቃትቶ ቃትቶ የሚሞትበት ዐይነት ነው:: አሮጌውን ሰው ስቀ ሉት ሲል ሰቃዩ ማን ነው? አሁን ከባድ የሚያደርገው ሰቃዩ እኛው ራሳችን መሆናችን ነው:: ጠባቂዎችስ እነማን ናቸው? ጠባቂ ዘበኞችም እኛው ራሳችን መሆናችን ነው:: ሌላው ሰው ይዞ አንዴ ጥርቅም አድርጎ ቢሰቅለን ልባችን እንኳ ለመውረድ ቢፈልግ መውረድ አንችልም በዚያው እንቀራለን እንጂ::

ይኸኛው ግን እኛው ራሳችን ከሰቀልነው ሲያሰኘን፣ ሲዳዳን እን ወርዳለን:: ችግሩ ይሄ ነው:: ላከ ይሄ እስር ቤት ማስገባቱ እንደ ዚያ ነው:: ከክፉ መሻቱ ጋር ስቀሉት ጠባቂም የለም:: ጠባቂ ዎቹ የሮማ ወታደሮች የሉም:: ሰቃይም ጠባቂም እኛው ነን::

አሮጌው ሰው ጠባዩ ይጠፋል ማለት አይደለም:: አሮጌው ሰው ሥፍራው ድርሻው ተሰቅሎ መቆየት በሌላ አባባል እስር ቤት ውስጥ መታጀል ነው:: የእኛ አሸናፊነት አሮጌውን ሰው ሰቅለን ወይም በግዞት አሳድረን ማኖራችን ነው::

ታንቆ መሞት፣ ሲጥ ማለት ያንድ አፍታ ጉዳይ ያልሆነ፣ የስቅ ለት ልምምድ ቀናት ይፈጃል:: እና ክፋቱ እርሱ እስር ቤት ገብቶ ሳለ መቼም ማቁለጭለጩ አይቀርም:: አቤቱታውም፣ ማባበሉም፣ መለማመጡም አለ፤ እያስለሰም ቢሆን ልብን የማማ ለል አቅም አለው:: ጩካኝ ልብ ያሻል::

ይህ አሮጌው ሰዋችን ሞተ የምንለው በመሠረቱ ከዚህ ሕይወት ስንላቀቅ ብቻ ነው:: ስለዚህ አንዱ ዋና ጠላታችን አሮጌው ሰው



ነው:: ችግሩን አስመልክቶ ብዙ ጊዜ አንዱ በሌላው ያሳብባል፤ እገሌ በእነገሌ ያሳብባል፤ አንዳንዴ ሚስት በባል ታሳብባለች ባል በሚስት ያሳብባል:: ግን ቁጭ ብለን ረጋ ብለን ስናስበው ትልቁ ጠላት አቶ እንትና፣ ወ/ሮ እንትና፣ እገሌ፣ እከሊት አይ ደሉም:: ትልቁ ጠላት እኛው ውስጥ ነው ያለው:: ከሌሎች ሰዎች ጠላትነት ይልቅ በውስጣችን ያረገው አሮጌው ሰው ነው ትልቁ ጠላታችን::

ሰይጣን የታወቀለት ጠላት ነው:: በጌታ ስም ስንገስጸው ከእኛ ይሸሻል፤ አሮጌው ሰው ግን ምንጊዜም አብሮን ነው:: በአጭሩ የአሮጌው ሰው ከእኛ ይወገዳል ብለን አናስብ:: ግን እስር ቤት መዋል ማደሩን እንድናረጋግጥ እግዚአብሔር ይርዳን::

ይህን ማስር በየዕለቱ የምናደርገው ነገር ነው እንጂ አንድ ሁለት ሦስት ቀን አግተነው ኋላ ግን የምንተወው አይደለም:: ከተው ነው ብድግ ብሎ ጉድጉድ ሲል፣ ሥራውን ሲያከናውን እናገኘ ዋለን:: ከየት መጣህ ማን ጠራህ እንለዋለን፤ ለካ ያለው አብሮን ነው:: ምግብ በየዕለቱ እንደምንበላ ለሥጋ ሕይወታችን ለመ ንፈሳዊ ሕይወታችንም ጤንነት ይህ የማሠር ወይም የመስቀል ርምጃ መረጋገጥ ያለበት ነው:: ምክንያቱም የአሮጌው ሰው ማኅበርተኝነቱ ከዓለም፣ ከሰይጣን ጋር ነው::

*"ነገር ግን መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ ቢኖር ኮራት አይሰማችሁ፤ እውነትንም አትካዱ:: እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር ከሥጋና ከአጋን ንት ናት"* (ያዕ 3፥14-15)::

## ሌላው ጠላታችን ይሄ አሮጌው ሰው የሚወዳጀው ዓለም ወይም የዓለም ሥርዐት ነው::

አሮጌው ሰውና የዓለም ሥርዐት የተያያዙ ናቸው:: መቼም ዓለም

የአንድ ሰው ጉዳይ አይደ ለም። የአንድ የአሮጌው ሰው ጉዳይ ሳይሆን የአሮጌው ሰዎች ስብስብ ሥርዐት ነው፤ ስለ ሆነም ሥርዐቱ አሮጌው ሥርዐት ነው።

«ዓለምም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን።» (ዮሐ 5፥19 ነባሩ ትርጉም) ደግሞ እኛ በዓለም ውስጥ አለን። ከነኝህ ሦስቱ ጣምራ ጠላቶቻችን በእኛ ዘንድ የ24 ሰዓት ተወካይ የቅርብ ተጠሪ ሥጋ (አሮጌው ሰው) ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ዓለም ነው። ዓለም ደግሞ በክፉ ተይዛለች። በክፉው ቊጥጥር ሥር ወድቃለች። ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ የተባለ ነው።

ክርስቶስ ኢየሱስ ከዚህ ከአሮጌው ሥርዐት፣ ከዓለም ሥርዐት ወደ ዐዲስ ሥርዐት እንድንመጣ ነው የጋበዘን። በአሮጌው ሥርዐት ውስጥ የነገሮች ሁሉ ማዕከል «እኔ» ነው። በዐዲሱ ሥርዐት የነገሮች ሁሉ ማዕከል እግዚአብሔር ወይም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

የአሮጌው ሥርዐት ማንቀሳቀሻ ኀይሉ ዲናሞው መጎምጀት (Eros) ነው። ራስን የሚያልቅ፣ ለራስ የሚሆነውን መጐምጀት፣ እርሱ ነው ማንቀሳቀሻ ኀይሉ።

ኢሮስ (Eros) በግሪክ ቃል ከአራቱ የፍቅር ዐይነቶች አንደኛው ነው። ይሄ ኢሮስ የሚባለው ማናቸውንም ጠቃሚ የተባለን ነገር ለእኔ የሚል ነው። እኔን ያልቀኛል፣ እኔን ከፍ ያደርጋል፣ ለኔ ይበጃል የምንለውን ነገር ለራስ መፈለግ፤ መጎምጀት፣ ለማግኘት መጣር ነው። ምንም ዐይነት ሊሆን ይችላል። ገንዘብ ሊሆን ይችላል፤ ዕውቀት ሊሆን ይችላል፤ የተቃራኒ ጾታ ሊሆን ይችላል፤ ብቻ ዐላማው የራስ ማድረግ ነው። ተቃራኒ ጾታን ከሆነ እርሷን ወይም እርሱን ካላገኘሁ ብሎ በኢሮስ ልቤ ጠፋ የሚል ሰው ፍቅሩ እውነተኛ ፍቅር አይደለም። ለእርሱ እስካል ሆነች ድረስ ክፉ ቢያገኛት ግድ የለውም። ለእርሷ እስከ አል



ሆነ ድረስ ምንም ቢደርስበት ግድ የላትም። በእንደዚህ ዐይነቱ ፍቅር ውስጥ ዋናው 'እኔ' የሚለው ነው።

*ዐዲሱ ሥርዐት በዐዲሱ ሰው ዘንድ የሚታይ ነው።* በወዲያኛው፣ በዐዲሱ ሥርዐት ውስጥ የነገሮች ሁሉ ማዕከል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም እግዚአብሔር ነው። ጳውሎስ እንዳለ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ አሁን የምኖረው ኑሮ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምንኖረው ኑሮ ነው»።

2ቆሮ 5፥15 «በሕይወት ያሉት ለእነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለሁሉ ሞተ» ይሄ ነው የነገሮች ሁሉ መነሻ። የሚኖሩት ለርሱ ነው። በሮሜ 14ም ላይ ጳውሎስ እንደሚናገር ራሱንም በዚያ መንገድ ሲያመላልስ እንደቆየ *«ከኛ አንድስ እንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን»* (ሮሜ 14፥7) ያሳየናል።

በየዕለቱ እርሱን ስናስቀድም ሕይወታችን የሚረካ ይሆናል። በዐዲሱ ሰው ሥርዐት የማንቀሳቀሻ ኀይሉ ከእግዚአብሔር የሚመጣ በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚፈስ ፍቅር ነው።

ለዚህ የግሪኩ ቃል «አጋፔ» ነው። በአሮጌው ሥርዐት ውድድር፣ ፉክክር፣ እሽቅድድሞ ነው ያለው። በዚህኛው ግን የሚኖረው ኅብረት፣ መተሳሰብ፣ መተባበር ነው።

በእግዚአብሔር ሕዝብ መኖር ስለሚገባው ኅብረት በ1ቆሮ 12 በአካል ብልቶች አንፃር ተገልጿል።

በአሮጌው ሥርዐት ፉክክር እና እሽቅድቅድም ባለበት መፋለጥ እንዳይኖርና መረጋገጥ፣ መጨፈላለቅ እንዳይመጣም፣ መቈጣጠሪያ ኀይሉ ሕግና ዱላ አለ። ምክንያቱም ሁሉም ሳይጨፈላለቅ የሚቻለውን ጥቅም እንዲያገኝ በሕግና በዱላ ይጠበቃል።

ሕግ ያለ ዱላ ተግባራዊነት ስለሌለው ሕግና ዱላ፣ የግድ በዓለም ሥርዐት ማስጠበቂያ ሆኗል:: በአሮጌው ሰው ሥርዐት ፀጥታ ማስጠበቂያ ሕግና ዱላ ነው:: በአዲሱ ሰው ሥርዐት ግን ሰላም ማስፈኛው የመንፈስ ቅዱስ ተቈጣጣሪነት ወቀሳ ወይም የመንፈስ ፍሬ ነው፤ ይቅርታ ነው::

የመንፈስ ፍሬ በገላትያ 5፣2 ሳይ ተዘርዝረዋል:: እነኝህን የሚከለክል ምንም ዐይነት ሕግ የለም:: የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ፣ በራስ መናዘዝ፣ ይቅርታ መጠየቅ፣ ማድረግም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው:: በዐዲሱ ሥርዐት መቈጣጠሪያ ኀይሉ ያው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው::

አምልኮ ነፃነትን እንጂ የመንፈስን ፍሬ የሚከላከል ሕግ ሊወጣ ይቻላል እንዴ? በዓለም ዙሪያ መውደድን፣ ደስታን፣ ሰላምን፣ ትዕግስትን የሚከላከል ሕግ ይወጣል እንዴ? ደስታን የሚከላከል ሕግ ይወጣል እንዴ? ሰላምን የሚከለክል ሕግ ይወጣልን? ክርስትናን የሚቃወም የትም አገር ቢኬድ በኮሚኒስትም፣ በእስልምና አገርም ቢኬድ ይሄን ዐይነት ሕግ አይወጣም::

በአሮጌው ሥርዐት ሕግና ዱላ ደግሞ በአንድ አገር ውስጥ ሲሠሩ በአገሮችም መካከል ከሆነ ደግሞ የኀይል ሚዛንን የመጠበቅ ስልት ፍቱን ዘዴ ነው:: ምክንያቱም የአንድ አገር ሕግ ለሌላው ስለማይሠራ አንዱ ሌላውን እንዳይጨፈልቀው የኀይል ሚዛን ያስፈልጋል::

የአሜሪካንን ኀያልነት ሚዛን ማስጠበቂያው የሶቭየት ዩኒየን ኀይለኝነት ነበር:: አሁን የሶቭየት ዩኒየን አለመኖር በኀይል ሚዛን ጥበቃ አኳያ ትንሽ ስጋት አስከትሏል::

በአሮጌው ሥርዐት ጥርስ ለጥርስ ነው፤ ዐይን ለዐይን ነው:: በዐዲሱ ሥርዐት ግን ይቅርታ ነው:: ከራስ ይልቅ ባልንጀራ እንደሚሻል በትሕትና መቍጠር ነው::



በአሮጌው ሥርዐት የምንመለከተው የሰው ጽድቅ ሲሆን፣ በዐዲሱ ሥርዐት ግን የምንመለከተው ለሰው በጸጋ የተሰጠ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ነው::

## 2. ዓለምና መልኮቿ

"በተስፋ ደስተኞች ሁኑ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ" (ሮሜ 12፥2):: "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም:: ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል" (1ዮሐ 2፥15-17)::

የሚያልፈው ነገር ከማያልፈው ነገር ሊያስቀረን የሚችልበት የራሱ ኀይል አለው:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው የምንጎመጀው የዐይን አምሮት ይቅርና የእኛ የሥጋ ሕይወትም ያልፋል:: ይህች ዓለም በፍጻሜው እንደማትጠቅም ዕቃ ትጣላለች:: ዓለምም ምኞቱም ያልፋሉ:: እውነታው እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ በነዋሪው በዘላለሙ እሴት አንጻር እንናቃት፤ በዚችም ዓለም የምንጠቀም እንደማንጠቅም እንሁን:: በዚች ዓለም ያለው ነገር ሁሉ ኀላፊ ነው (1ቆሮ 7፥31)::

ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ቁርጥ አቋምና የእግዚአብሔር ወገንነት ያስፈልገናል::

ሰውን መካከለኛ ባደረገው (በአማክሎተ-ሰብ ላይ በሚያጠነጥነው) በዓለም ሥነ-ልቦናዊ አስተሳሰብ ወይም ከፖለቲካዊ ፍልፍስና ጋራ አመሳስላ ቤተ ክርስቲያን የትምህርቷን ንዘረትና አካሄዷን ብትቃኘው አይበጃትም::

- ዓለም ኅበረተ ሰባዊነት ስትል ቤተ ክርስቲያን ያንኑ ብትል፤
- ዓለም የሴቶች መብት ስላለች ብቻ ቤተ ክርስቲያንም

ያንኑ ተቀብላ የእህቶች መብት ብላ ብታስተጋባ፤ እግዚ አብሔር "አንተ" ብቻ ሳይሆን "አንተ አንቺም" ይባል ብትል፣

- ዓለም መብት ለሰዶማውያን እያለች ስትጮኽ ቤተ ክር ስቲያንም ቢቀስሱ ምን አለበት ብትል፣
- ዓለም በፋሽን አዙሪት ቀልቧ ሲጠፋ፣ ቤተ ክርስቲያን እንደዚያው ብትቦዝ፣
- ዓለም የገበያ አዳራሽን እንደ መቅደስ እየቈጠረች በሸመታ አባዜ ስትያዝ ቤተ ክርስቲያንም በዚያው ብትለከፍ፣
- ዓለም የሥነ ምግባርን ቋሚነት ገፍትራ ጥላ፣ የጋራ እውነትን እያሟሸሸች፣ የእኔም እውነት እውነት ነው፣ የአንተም እውነት እውነት ነው፣ የእኔም መለኪያ ልክ ነው፣ የአንተም መለኪያ ልክ ነው ስትል ቤተ ክርስቲያንም ዘመነኛው ከቤተ ክርስቲያን እንዳይሸሽ በሚል ፈሊጥ የሞራልን ማክረር እንተው ብትል፣ መለ ኪያዋን ብትደብቅ ወይም ብትሰብር ወዘተ ...

የትምህርቷንና የሥልጣኗን ምንጭ ዘንግታ የዓለም አቀንቃኝ አስተሳሰብ ገደል ማሚቶ ሆነች ማለት ነው።

እንደ ቃሉ፣ የእውነት አምድና መሠረት፣ የፍትህና የጽድቅ መግለጫ፣ ክፉውን የምታስር መልካሙን የምትፈታ ሆና መገ ኘት ሲኖርባት፣ የየዘመኑን የዓለም አስተሳሰብ እና አደራረግ ከኮረጀች፣ ከእውነተኛው ሀለት የተለየች በአሸዋ መሠረት ላይ የታነጸች ትሆናለች - አትጸናምም።

የሕይወት መልሕቅ ነቃይ፣ አቋምዋ ዥዋዥዌ የሆነባት፣ ጉዞዋ ወትሮ ተደናብሮ የሆነባት፣ በሮቿ የተበረጋገዱ የትኛውም ፍልስፍና በመረጠው በር ዘው ብሎ የሚገባባት፣ የሕይወት ዐላ ማና ትርጕም ወለብላባ የሆኑባት፣ በውሸት እውነት በተባለ የድህረ ዘመናዊ (post modernism) ቅኝት የተጋዘች ትሆናለች።

ዓለም በቀለም፣ በዘር፣ በነገድና በቋንቋ ስትከፋፈል፤ ታዳጊዋ፣ ነውር እንደሌለው በግ ደሙን አፍሶ፤ ከነገድም ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ ዋጅቶ ለአባቱ ለእግዚአብሔር የካህናት



መንግሥት ለማድረግ የተቤዣት ቤተ ክርስቲያን፤ የዓለምን ጥያቄ ጥያቄዋ አድርጋ፣ በዘርና በነገድ ብትከፋፈል ጌታዋ በሥ ጋው መቈረስ ያፈረሰውን የጥል ግድግዳ በዘረኝነት፣ ለወገኔ ይጠቅማል በሚል ከንቱ ውዳሴ መልሶ እንደ መገንባት ይሆናል። ዓለም በቀዘፈችበት እየቀዘፈች ዓለም በለቀመችበት እየቃረመች መሄድ የለባትም።

ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያንነቷ ከማንኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብ በላይ ሆና የማይናወጥ መንግሥት ዜግነቷንና አባል ነቷን አክብራ መያዝና መጽናት አለባት እንጂ የየትኛውም ፖለ ቲካ ክፍል መሣሪያ ለመሆን ተንሸራታ መውረድ አይገባትም። የነቢይነት አገልግሎቷ ተኮላሽቶ እንዳይቀር።

ቅድሚያ መስጠት ያለብን ለዓለም ሳይሆን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ይህም ደግሞ መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነው። በእግዚአ ብሔር መንግሥት የሚደረገው የራስ ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአ ብሔር ፈቃድ ነው። ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆንነው ፈቃ ዱን ዐውቀን እንድናደርግ ፈቃዱንም እንድንደገፍ ነው። መል ካምና ፍጹም ደስ ከሚያሰኘው ነገር አንዱ ጌታን ኢየሱስ ክር ስቶስን ማመን ነው። የጌታን ፈቃድ እያደረጉ በየዕለቱ እር ሱን ደግሞ መከተል የደቀ መዝሙር ጥሪ ነው።

በቤተ ክርስቲያን፡-

እውነት ከፍቅር ሲያብር
ዕውቀት ትህትናን ሲላበስ
ኀይል በርኅራኄ ሲቃኝ
ብልህነት ከየዋህነት ጋር ሲዳበል
ኀይለ መለኮት ከትምህርተ መለኮት ጋር ሲጣመር

የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ጥልቀትና ውበት ያበ ራል፤ ሕይወት አልጫ ለሆነባቸውም የሕይወት ጨው፣ ለጨለ መባቸውም ብርሃን ይሆናል (ማቴ22፥29፤ ኤፌ4፥15፤ 1ቆሮ 8፥1-3)።

**ዓለም ምን ትመስላለች ከሚለው ጥያቄ ይልቅ ዓለም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ያህል ገባች ወይም ቤተ ክርስቲ ያን ዓለምን ምን ያህል መሰለች የሚለው ጥያቄ እጅግ አሳሳቢ ነው። ይኸው ሁኔታ በ2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 እና 4 ላይ በሰፊው ተንጸባርቋል።**

*"ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በከንቱ በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና። ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤ ኀይሉን ግን ክደዋል። ከእነዚህ ራቅ"* (2ጢሞ 3፥1-5)።

### ሀ) ራስ ወዳድነትና ትምክህት

ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና ዘመኑ ክፉ የሚሆነው ከዚህ የተነሣ ነው። እዚህ ላይ ሰዎች የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ሰዎችን የሚጨምር ነው። በእግዚአብሔር ስም የሚጠራው ሕዝብም ራሱን ካልጠበቀ በዚህ ውስጥ ያልፋል። ዓለምም በዚህ ውስጥ ትገኛለች። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን እኔ ማለት የምንችል የራስ ሕልውና ግንዛቤ ያለን አድርጐ ፈጥሮናል። ግን ራስ ወዳድነት እግዚአብሔርን ከመንገዱ በሚያስወግድ፣ ሰውን ከሰውነት ደረጃ አንሥቶ ወደ መለኮትነት በሚለውጥ መልኩ፣ የነገሮች ሁሉ ማዕከል ራስን በሚያደርግ መልኩ፣ እኔያዊነትን የሚያራምድ፣ የእኔ ሀሳብ፣ የእኔ ፈቃድ፣ የእኔ ፍላጐት ከሌላው ሁሉ ይቀደም የምንልበት፣ ከእግዚአብሔርም ይቅደም የምንልበት ዐይ



ነት ሁኔታ ስለሚሆን ዘመኑ ክፉ ነው።

ሰዎች ገንዘብን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ትምክህተኞች በትዕቢት የተነፉ ትዕቢተኞች ይሆናሉ። ምንጊዜም ሰዎች ትምክህተኞች ሊሆኑ መሠረት የላቸውም። በ1ቆሮ 4፥7 «ያልተቀበልከው ምን አለህ? የተቀበልክ ከሆንክስ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለምንድን ነው?» ያልተቀበልከው ነገር የለህም፣ በራስህ ያመጣኸው አንዳችም ነገር የለም። ይህንንም ቢሆን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወዳንተ የመጣ ያለህ ሁሉ የተቀበልከው ነውና ልትመካ መብት የለህም ይላል። ይሁንና ሰዎች ትምክህተኞች ይሆናሉ። ከዚህ የተነሣ በትዕቢት የተነፉ ይሆናሉ። በፊት የማንጠብቀው በእግዚአብሔር ስም፣ በክርስትና ስም በሚጠራው ሕዝብ ዘንድ እንኳ ራስን ወደ ላይ የማውጣት ነገር፣ ከክርስቶስ ጋር የማስተካከል ወደ መለኮትነት የማስተካከል ነገር አምላክ ነኝ የማለት ኩፍታ እየተሰራጨ ነው።

### ለ) አፍቅሮተ ንዋይ

ሰዎች ገንዘብን የሚወዱ ይሆናሉ። ይህም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ነው። የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ራሱ በገንዘብ ዙሪያ እየተሽከረከረ ነው። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በብዙ ስፍራ በተለይም በምዕራቡ ዓለም ዋናው ነገር ሰማያዊ ሳይሆን ምድራዊ ሆኗል። ስብከታችን ስለ ገንዘብ፣ ስለ ብልጥግና ሆኗል። በእግዚአብሔር ሀይን ማየት ቀርቶ በዓለም ዐይን ማየት ጀምረናል። ጌታ ኢየሱስ በእስያ የነበሩትን ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ሲገመግም፣ ስለ ሰምርኔስ ሲናገር «መከራህን ድኽነትህን ዐውቃለሁ» ይልና *«ይሁንና ባለጠጋ ነህ»* (ራእ 2፥9) ይለዋል።

ስለ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር ደግሞ ሎዶቅያ ሀብታም የበለጠገች ነበረችና ባለጠጋ ነኝ ስትል ድኻ የተራቈተች መሆኗን

ስለማታውቅ የእግዚአብሔር ቃል ነቀፋት:: በእግዚአብሔር ዐይን ከማየት ይልቅ በዓለም ዐይን ማየት እጅግ እየበዛ መጥቷል:: የቤተ ክርስቲያን ዐይን በኀላፊ ብልጥግና ላይ እየሆነ ነው::

በዓለም ስንመለከት ብዙ ነገር በገንዘብ ዙሪያ እየተሽከረከረ ነው:: ድሮ ስፖርት በስፖርትነቱ ነበር የሚካሄደው፤ አሁን ግን ስፖርት የሚካሄደው ከገንዘብ አኳያ ነው:: በቤተ ክርስቲያንም ሁኔታው ያው እንደ ሆነ ስናገር ብዙዎችን ላሳዝን እችላለሁ:: አገልግሎት በገንዘብ ዙሪያ እየተሽከረከረ ነው:: የመዝሙር አገልግሎት፣ የወንጌል አገልግሎት በገንዘብ ዙሪያ እየተሽከረከረ ነው:: ከገንዘብ በኋላ የምንሮጥ ከሆነ፣ የራስን ነገር በማሳደድ የምንሄድ ከሆነ፣ ጕዳዩ አሳሳቢ ነው::

ይህንን ስል ገንዘብ አያስፈልግም ማለቴ አይደለም:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስፍራ ገንዘብ መውሰድ የለበትም:: ሰማያዊውን ስፍራ ምድራዊው ነገር፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ቦታ መንግሥተ እኔ መተካት የለበትም::

አብዛኛውን ጸሎታችን በራሳችን ምድራዊ ምኞት ኋላ የሚሯሯጥ ነው:: በሰማያዊ አጀንዳ አይደለም የምንጸልየው:: ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ብንጓጓ ልዩ መገለጥ ብንጠብቅ ስለኛ ምድራዊ ነገር ጓጕተን ነው እንጂ የምንጠብቀው ስለጽድቅ ነገር ስለ ሰማያዊ ነገር ጓጕተን አይደለም::

«አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም እሹ» (ማቴ 6፥33):: በቤተ ክርስቲያን እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማናስቀድም ከሆነ እንጠፋለን:: ቤተ ክርስቲያን ዘማዊ ትሆናለች:: እግዚአብሔር ንፉግ አይደለም:: የእግዚአብሔር መንግሥት አጀንዳ የእኛ አጀንዳ ቢሆን እግዚአብሔር ስለ እኛ ጕዳይ ይገደዋል:: ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ቸር ነው::



እዚህ ላይ የሰሎሞንን ጸሎት ማንሣት ደስ ይለኛል:: እግዚአብሔር ወደ ሰሎሞን መጣና ምን ትለምነኛለህ አለው? ሰሎሞን የለመነው ነገር ሕዝቡን በጽድቅ እንዲያስተዳድር ጥበብ እንዲያገኝ፣ ማስተዋል እንዲያገኝ ነበር:: የእግዚአብሔር ሕዝብ በመልካም ለመተዳደር መብቃቱን አስቀደመ:: ይህም እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበት ጸሎት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ሰሎሞን ይህን ነገር ስለለመነ ነገሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ዛሬ ግን የሚሰበከው ምድራዊ በረከት ነው::

በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ *"በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ተባረክን"* ነው የሚለው፤ *"የልባችሁ ዐይኖች ሲበሩ በሰማይ ያላችሁን መዝገብ ታያላችሁ"* ነው የሚለን:: በእውነት ቤተ ክርስቲያን በኀላፊ ጠፊው እየታወረች ነው ያለችው፤ ሰማያዊውን ነገር መመልከት አልቻለችም:: በምድራዊ ነገር ዙሪያ ነው ያለ ነው:: የምድር በረከት ስበኩልን ነው የምንለው:: የበረከት ምንጭ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ታማኝ ነው:: ስናስቀድመው፣ ስንደገፈው አይጎድልብንም::

ሰሎሞን ተራ ነገር ስላልለመነ ነገሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው:: እግዚአብሔርም አለው *«ፍርድን ትለይ ዘንድ፣ ለራስህ ማስተዋልን ለመንህ እንጂ ለራስህ ብዙ ዘመናትን፣ ባለጠግነትን የጠላቶችህንም ነፍስ ሳትለምን ይህን ነገር ለምነሃልና እንደ ቃልህ ይህን አድርጌአለሁ»* (1ነገ 3፥10-13)::

በየትኛው ጸሎታችን እግዚአብሔርን ደስ የሚለው ይመስላችኋል? በምድራዊ ፍላጎታችን አኳያ መጸለይ ኀጢአት አይደለም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት የእግዚአብሔርን ክብር፣ የሌሎችን ጥቅም ስናስቀድም ነው:: ጳውሎስ «ለኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው» ሞትም ጥቅም ነው ይላል:: ጳውሎስ ሰማያዊውን ነገር የሚያይ ነው:: ዐይኑ ተከፍቶለታል:: «ለኔ ወደ ክርስቶስ መሄድ ይሻለኛል:: ነገር ግን መኖሬ ለናንተ የሚጠቅም በመ

ሆኑ» በማለት አገልግሎትን መርጧል (ፊል 1፥21-24)::

«በሕይወት ያሉ ለነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለሁሉ ሞተ» ስለሚል የመኖራችን ዐላማ ይህ እንደ ሆነ ነው የሚነግረን የእግዚአብሔር ቃል (2ቆሮ 5፥15)::

ሰሎሞን ረጅም ዕድሜን አልለመነም:: በምድር ብዙ ለመኖር አልጸለየም:: በእኔ ቋንቋ በጸሎቱ ጣቢቅ ምድር አልነበረም:: በሌላ መልክ ደግሞ ባለጠግነትን አላስቀደመም:: በአንድ በኩል እንደዚህ ብሎ ሊጸልይ ይችላል:: መቼም እኔ ያንተ ሕዝብ ንጉሥ ነኝ፤ ያንተ ሕዝብ ደግሞ ከአሕዛብ ሁሉ የተለየ ነው:: የአንተ ሕዝብ መሆን ማለት ክብሩ እንዴት እንደ ሆነ መታየት አለበት:: ከዓለም ነገሥታት ይልቅ ለኔ ምን የመሰለ ቤተ መንግሥት ነው የምትሠራልኝ? የተንደላቀቀ ቤት ሥራልኝ አላለውም:: ቢለው ያስኬድ ነበር::

አንዳንድ ቋንቋ አለን፤ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን የንጉሥ ልጆች ነን፤ ራስ እንጂ ጅራት መሆን የለብንም እንላለን:: ስለዚህ ትልቁ ነገር እግዚአብሔርን ማስከበር ሳይሆን እኛን በትምክህት ውስጥ ማስገባት ነው:: ይህ በእግዚአብሔር የመመካት ቋንቋ አይደለም:: እኛ በመረጥናቸው የምቾት መስመሮች እንጂ በጽድቅ፣ በቅድስና፣ ይቅር በማለት፣ በፍቅር፣ በትሕትና፣ በልግስና ጅራት ሳይሆኑ ራስ የመሆን ነገር ላይ አናተኩርም:: ቅኝታችን እንደ ዓለም ቅኝት ነው::

ሌላው ደግሞ "የጠላቶችን ነፍስ ሳትለምን" ይላል፤ እኛ የሚቃወሙንን እንዲደፉልን አንመኝም? በምንጠላቸው ላይ መቅሰፍት እንዲመጣ የሟርት ጸሎት የምንጸልይ የለንም? በእግዚአብሔር ስም ውሸታሞች አልሆንንም? ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ጆሮአችንን በሚያሳክክ፣ በዙሪያችን በሚፈላ ትንቢት



እውነተኛነቱን፣ ከእግዚአብሔር የመነጨ መሆኑን ሳንፈትሽ ለሥጋችን እስከ ጣፈጠ ድረስ እንመራበታለን:: እውነተኛ ትንቢት ሆኖ ሳለ ደግሞ ለሥጋችን ካልተመቸ እንገፈትረዋለን::

አንዳንድ ነገሥታት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለመንገሥ ሲፈልጉ ነቢያትን ያስቀድማሉ:: ስለ ንግሥናቸው ትንቢት ያስነግራሉ:: እግዚአብሔር ያልጠራቸው ግን አይጸኑም፤ ይከሽፋሉ::

ወደ ጌታ ከመጣሁ ጊዜ ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት አሁን እጅግ ተለውጧል:: ብዙ የተፋጠነ መሽቀልቀል ነው የማየው::

በአንድ ጕዳይ አንድ ሰው ልክ ያልሆነ ሲመስለን እንጸልይ እንደ ነበር አስታውሳለሁ:: እኔ ሳበላሽ ስስት ወይም የሳትኩ ሲመስል ሌላው ያነባ ነበር:: አሁን ግን እንደዚህ አይደለም:: አስወግድልን፤ አንሳልን ነው:: እኔ አነሳሳችኋለሁ ቢባል «አሜን» ነው የሚባለው፤ መማለድ የለም:: ጸሎታችን የሟርት ጸሎት ነው:: በንስሓ መመለስ፣ የወደቀው መነሣት እጅግ ያስደስተን ነበር::

የምድር ብልጥግናን እንንጓጓለን፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጎች ከሆንን በኋላ ሌላው ብልጥግና ከመጣ ይምጣ:: እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: ካልመጣ ደግሞ በጢሞቴዎስ እንደምናነበው ይህ ያለን ይበቃናል (1ጢሞ 6፥8):: ያየነውን ሁሉ አምጥተን አጋብሰን የእግዚአብሔር ሰላም ከእኛ ከራቀ ምን ዋጋ አለው? ግን አንዳንድ ጊዜ ገንዘብን የምንፈልገው ዋስትና ወይም ዘብ እንዲሆነን ነው:: ገንዘብ ከመጣ በኋላ ደግሞ ዘብ መሆኑ ቀርቶ እኛ ለገንዘቡ ዘብ እንሆናለን:: ለገንዘብ ዘብ መቆም ስቃይ ነው:: እኛ ጓጕተን ዐይናችን ቀላውጦ ምን የመሰለ ዐልጋ፣ ፍራሽ ብንገዛ እንሶላውም ብርድ ልብሱም ልዩ ቢሆን እንቅልፍ ከሌለን ምን ዋጋ አለው?

በረከት በሚሰበክበት በአሁኑ ወቅት ይሄ ነው መልእክቱ:: አስ

ቀድማችሁ የእግዚአብሔር መንግሥት ፈልጉ ከዚያ ሁሉ ይጨመርላችኋል:: ጭማሪው ብዙ አይታይም:: ከመጣ እግዚአብሔር ይመስገን:: ከሄደም ይሂድ:: እግዚአብሔር ብቻ ከእኛ አይራቅ:: ጤናችንን የሚጠብቅ ሰላምን የሚሰጠን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሁን:: ምን የመሰለ ቤት ሠርተን በባልና ሚስት መካከል ሰላም ከሌለ ትርፉ ምንድን ነው? የሰሎሞን ጸሎት የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስቀደመ ጸሎት ነው:: ግን እግዚአብሔር አስቀ ድሞ አያይ ይመስለናል? የፈጠረን አምላክ መሻታችንን አያው ቅም? እኛ ለምነን ነው የምንፈልገውን ነገር ከእግዚአብሔር እጅ የምናስረግፈው? እርሱ ምንም ሳንጠይቀው እንኳን የምን ፈልገውን እንዲሁ አይሰጠንም?

«እነሆ ማንም የሚመስልህ እንዳይኖር ከአንተ በፊትም በኋላም ጥበበኛ አእምሮና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ:: ደግሞም ከነገ ሥታት የሚመስልህ ማንም እንዳይኖር ያልለመንኸውን ባለጠ ግነት ክብር ሰጥቼሃለሁ::» ያልለመንኸውን ባለጠግነትና ክብር የሚሰጥ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን:: ስለዚህ እኛ ካልጨቀ ጨቅነው አይሰጠንም ብንል ጉዳያችን ምድራዊ ነው:: ለዚሁ ደግሞ አልተጠራነም:: ምንም እንኳ በሥጋ ውስጥ ብንኖር ጥሪ ያችን ሰማያዊ ነው:: ይሁንና በሥጋ ውስጥ መኖራችንን የሚ ያውቅ አምላክ ለማናቸውም ይጠነቀቃል:: ለዕለት እንጀራችን ይጠነቀቃል::

ገንዘብ ሲኖር ተምክህት ይመጣል፤ ትዕቢት ይመጣል፤ በእግዚ አብሔር ከመመካት ይልቅ ባለን ነገር እንመካለን:: እግዚአ ብሔር ከዚያ ያስጥለን:: የጠራች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ይዋጅ::

ሐ) ፍቅር አልባነት

ስለሚመጣው ዘመን በተነገረው በዚሁ ቦታ "ልጆች ለወላጆቻ ቸው የማይታዘዙ ይሆናሉ" ይላል:: "ፍቅር የሌላቸው" ይላል::



ልጆቻችንን አስተምረን፣ አንቆጥቁጠን አሳድገን ልጆች ለወላጆ ቻቸው የማይታዘዙ ሲሆኑ ወላጆች ደስ ይለናል? በብዙ ቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ሐዘን አለ:: ብዙ ወላጆች በልጆቻቸው ሁኔታ ልባቸው በሐዘን ይሰበራል:: ልጆች ብርቅ ቢሆኑልን፣ ብንንከባ ከባቸው በጣም ጥሩ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱን እናስቀድማቸውና እነርሱም ለእኛ አይሆኑም:: እግዚ አብሔር ቤተ ሰብን ካልባረከ ምን ዋጋ አለው? ልጅ ወልደን ልጆች ግን አብረውን የማይሆኑ ከሆነ ምን ዋጋ አለው? እግዚ አብሔር ልጆቻችንን እንደ ይስሃቅ ያድርግልን:: በእርሱ ስንታ መን እርሱ ነገሮችን ይቀይራል::

አሁን በቤተ ሰብ ውስጥ ልጆች ወላጆቻቸውን አያከብሩም:: የቤተ ክርስቲያን ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲያ ከብሩ መጠበቅ አለብን ወይ? በቤት ውስጥ ያሉትን ወላጆች ካላከበሩ በቤተ ክርስቲያን ያሉትን፣ ወላጆቻቸውን መስል የሆ ኑትን እንዴት ያክብሯቸው? ስለዚህ በቤት ባህሉ የለምና በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አልበኝነት ቢኖር አያስደንቅም:: ይህ ብቻ አይደለም:: 'ፍቅር የሌላቸው' ይላል:: እዚህ ላይ ፍቅር ተብሎ የተተረጐመው የግሪኩ ቃል 'ስትሮጌ' ነው:: ይህ ፍቅር ወላጆች ለልጆች የሚኖራቸው ፍቅር ነው:: ይህ ፍቅር በእንስሳም ዘንድ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ያሳደረው ፍቅር ነው::

ይህ ፍቅር ለምንድን ነው የሚጠቅመው? ወላጆች ልጆች ወል ደው ልጆቻቸውን የማይንከባከቡ እንዳይሆኑ ለዚህ ጕዳይ እግ ዚአብሔር የሰጠው ነው:: ይሄን ሀይነት ፍቅርም ነው ይጠፋል የሚለው:: ምናልባት ይሄ ማስወረድ መብት ነው የተባለው፣ የዚህ ነፀብራቅ ይሆን? በአንዳንድ አገር ማስወረድ መብት እየ ሆነ ነው፤ ልጁን ከማህፀን ከመውጣቱ በፊት መግደል ነው:: እንደዚህ ሀይነት ጊዜ ላይ ነው ያለነው ስለዚህ ወደ እግዚአ ብሔር መሮጥ ያስፈልጋል::

ይህን የሚቋቋም ጸጋ ከእግዚአብሔር ለመቀበል መሮጥ ያስፈልገናል። አብርሃም አንድ ልጅህን ሰዋልኝ በተባለ ጊዜ የወሰደው ርምጃ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ለኔ የበለጠ የሚያስደንቀኝ ግን ይስሐቅ ነው። አባቱ እየዋሸ ነው የወሰደው፤ መሥዋዕት እናቀርባለን አለው የበግ መስዋዕት እንደሚያቀርቡ፤ በጉ የት አለ? ሲለው አለ ወዲያ እያለ እያታለለ ነው የወሰደው። ከዚያ ነገሮችን ሁሉ አመቻችቶ ይስሐቅን ዕንጨት ላይ አጋድሞ ሰይፉን መዘዘ። ከመታረድ ይስሐቅን ያስጣለው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። ይስሐቅ ከዚያ በኋላ እያታለለ ወስዶ በሰይፍ ሊጐምደው ያሰበውን አባቱን፣ እግዚአብሔር አትርፎት ሲመለሱ አባቴ ብሎ መከተሉ የሚደንቅ ነገር ነው።

በሕይወታችን በቤተ ሰብ ኑሮአችን እግዚአብሔር ሲቀድም ልጆቻችንን እግዚአብሔር ለኛ ይሰጠናል። እግዚአብሔርን ለመከተል ስንል የሚያስመርር ነገር እንኳ ያደረግን ቢመስልም ልባቸው ግን መራራ አይሆንብንም፤ እንዲያው መንፈሳቸው ከመንፈሳችን ጋር ይጣመራል።

*መ) አለማመስገን*

እግዚአብሔር ሊመሰገን የሚገባው ነው። ብዙ ጊዜ ጎልቶ የሚታየው ከማመስገን ይልቅ ብሶት፣ ማጉረምረም ነው። ቃሉ የማያመሰግኑ ይላል። መቼም ማመስገን አለ። ይሁንና የማመስገን ይዘቱ ምን ዐይነት ነው? ብዙ ጊዜ የምናመሰግነው ተጨማሪው እንዲመጣልን በማሰብ አስልተን ነው። ተጨማሪ የማንጠብቅ ከሆነ ምስጋና ከእኛ ዘንድ ይተንናል። አንድ ሰው አንድ ነገር ሲያደርግልን በተወሰነ ደረጃ እናመሰግነዋለን፤ ምስጋናችን ግን ቍጥብ ነው። ወይም ጊዜያዊ ነው ወይም ከልብ አይደለም።

አንዳንዴ እግዚአብሔርን እናመሰግነው የምንለው አንዳንድ ነገ



ሮችን ደርድረን አሁን ብናመሰግነው እነዚህን ነገሮች ደስ ብሎት ይሰጠናል በሚል ነው። ስለ ወደ ፊቱ ምንም ሳናስብ ስለ ሆነው ነገር ብቻ ብናመሰግነው ግን እውነተኞች ነን። እግዚአብሔር ልባችንን ያውቃል። የምስጋና ጊዜ የምንለው ነገር በእውነት ምስጋና አይመስልም። አንዳንዴ እንዲያውም የምስጋና ጊዜ የመመጻደቂያ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም።

ወደ ቤተ መቅደስ ፈሪሳዊና ቀራጭ ሄደው ነበር። ፈሪሳዊው ያመሰግን ነበር የሚያመሰግነው እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ እያለ ነበር። ይህ መመጻደቅ እንጂ ማመስገን አይደለም። ደግሞ እግዚአብሔር አያውቅ ይመስል በሳምንት ሁለት ጊዜ እፆማለሁ ይላል። ራስን መካቢያ ነው። የምስጋና ጊዜ የምንለው የመመጻደቂያ ጊዜ እንዳይሆን እግዚአብሔር እንዳይታዘበን። ልጆቻችን ትምህርታቸውን ቢጨርሱ ማመስገን ይገባል። ግን ምስጋናዬ እኔ ለእግዚአብሔር የተለየሁ እንደ ሆን ለማሳየት ከሆነ ልክ አይደለም (ሉቃ 18፥9-14)።

በተጨማሪም "የሚያጉረመርሙ" ይላል። ይህም ማለት የሆነላቸውን ከማየት ይልቅ የጐደላቸውን የሚያዩ ማለት ነው። ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሲያያዝ በጣም ነው የሚያሳስበኝ። ብዙ ጊዜ ዐይናችን ምድራዊ ነገር ላይ ሲሆን የሚታየን የጐደለብን እንጂ የተሰጠን ነገር አይደለም።

ነገር ግን ለእግዚአብሔር ምን ጊዜም የተፈጥሮ ጸጋው ባለዕዳ ነን። እግዚአብሔርን ይህንን አጕድለህብኛል ብለን ልንወነጅለው በቂ ምክንያት የለንም። ምናልባት እንደሚባለው በሰውና በእግዚአብሔር መሃል ነፃ ፍርድ ቤት እንዲኖር ቢፈቀድና እኛና እግዚአብሔር ተካሰን፣ እኛ እግዚአብሔርን ከሰን ብንሄድ ማን ይረታል? በታሪክ ውስጥ ከማንም ይልቅ የክስ ፋይል የተከፈተበት ማን ይመስላችኋል? እግዚአብሔር ነው። እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ላይ የክስ ፋይል ከፍተናል። ይህንን አጉድሎብ

ኛል እንላለን:: ይሁንና ሁሉም የክስ ፋይላችን የከሸፈ ነው:: ምናልባት የግራ እጅ አጥቼ እግዚአብሔር የግራ እጅ ወሰደ ብኝ ብየ ብከሰው፣ እግዚአብሔር ደግሞ ግራ እጅ ብቻ ሳይ ሆን ቀኝ እጁም የእኔ ነው፣ እግሩም የእኔ ነው፣ ይለናል:: ፈጣ ሪነቱ ቸርነቱ ነውና::

ከሳሹ ሰው ይህንን ሲሰማ ቶሎ ብሎ ክሱን ዘግቶ ነው የሚሄ ደው፤ ለአንድ እጅ ሲከራከር ሌላውን እንዳያጣ:: ምን ጊዜም ላለማመስገን ምክንያት የለንም:: ውድድር ውስጥ ካልገባን በስተ ቀር ሁላችንም የምናመሰግንበት ምክንያት አለን:: የተቀበልና ቸው አያሌ ነገሮች አሉን፤ ሁልጊዜ የጸጋው ባለ ዕዳዎች ነን:: ተቀብለናልና ሁልጊዜ የምናመሰግንበት ምክንያት አለን:: እኛ ግን እናመሰግነዋለን የምንለው አጥተን ስናገኝ ወይም ታመን ስንፈወስ ነው::

እንዲሁ ያገኘን ከሆነ አናመሰግነውም:: ታመን ካልተፈወስን አናመሰግነውም:: ስለዚህ እግዚአብሔር ከእኛ ምስጋና እንዲያ ገኝ እኛ ታመን መፈወስ አለብን ማለት ነው:: አጥተን ማግ ኘት አለብን ማለት ነው::

አንድ ሌሊት ጥርሴን አመመኝና በዚያን ሌሊት «አንተ ፈዋሽ ነህ፤ ና ፈውሰኝ» እያልሁ ጸለይሁ:: ሻል ሲለኝ እንደ ገና ሕመሙ ሲመጣብኝ መለስ ቀለስ ሲል ነጋ:: ሲነጋ አንድ የታመነ ሐኪም ጋ ሄድኩና አስነቀልኩት::

በሚቀጥለው ቀን ማታ ያለፈውን ችግሬን አሰብሁና እፎይ ስላ ልኩ ደስ አለኝ፤ አመሰገንሁ:: ኋላ ሳስብ እነዚህ ጥርሶቼ ሁልጊዜ ሳያስቸግሩኝ ሲኖሩ እግዚአብሔርን አመስግኛለሁ ወይ? እኔ እግዚአብሔርን የማመሰግነው ታምሜ ሲሻለኝ ነው ወይ? አንድ ሰው ልቡን ሲታመም እንጸልያለን:: ግን አንድ ሰው ሀ ብሎ ከጀመረ ጀምሮ በቀንም በሌሊትም ልቡ ሲደበድብ ሲደበድብ



እኛ ተኝተን ልብ ግን ሳያርፍ ለሚሠራው፣ ለዚያ ጸጋ እግዚ አብሔርን እናመሰግ ናለን? እና ምስጋናችን ምን ሀይነት ነው?

## ሠ) ቅድስና አልባነት

የሚቀጥለው ዐሳብ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ቅድስና የሌ ላቸው፣ ራሳቸውን የማይገዙ ወይም በፍላጐታቸው የሚነዱ፣ ተድላን የሚወዱ ይላል::

በአንድ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ስብከት ከተሰበከ ብዙ ቆይቶ ስለነበር ተከታታይ የቅድስና ስብከት ተሰበከ:: ከዚያ በኋላ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በዚህ ኀጢአት የወደቃችሁ ተነሱ ሲባል ብዙ ሰዎች ተነሱ:: የሚገርመው ነገር የሳተ ይመለስ የወደቀም ይነሳ የሚለው ተገቢ ነገር ሆኖ ሳለ ንስሓ ገቢው ሰው ሁሉ ምን ልሁንልህ ሲል ሲያዜም፣ ሲያሸበሽብ የኖረ መሆኑ ግን ያስገርማል:: እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን እንዲቀድሰልን የፈቃድን ኀይል ብርታት ይስጠን:: ለሥጋ ልቅ ነት መንገድን እንዳንሰጥ::

ምንጊዜም ቢሆን ምንም ብንወድቅ ከወደቅንበት እንድንነሣና ወደ እርሱ እንድንመለስ ነው እግዚአብሔር የሚወደው:: እርሱ እንድንጠፋ አይፈልግም፤ ግን ኀጢአትን እንድንለማመድና በዚያ ውስጥ እንድንመላለስ አይሁን:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ እንግዳ ትምህርት እየገባ ነው:: ይህ የተሳሳተ "ወንጌል" መን ፈስ ነን ስለሚል መንፈሳችን ድኗል ተዋጅቷል፤ ስለዚህ ሥጋና ደም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም:: መንፈ ሳችን እስከዳነ ድረስ በሥጋችን ላይ የሚደረገው ፎምጃ ቍጥር ውስጥ አይገባም:: ስለዚህ በሥጋችን ላይ የሚደረግ ኀጢአት ጥያቄ ውስጥ አይገባም::" የሚል የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረት የለቀቀ አስተሳሰብ ይነዛል:: እንደዚያ ዐይነቱ ትምህርት በእን

ደዚህ ዐይነት መንገድ ለሚመላለስ ሰው አቤት እንዴት ያለ የምስራች ነው!

ረ) ይቅርታ ቢስነት

በተጨማሪም እርቅን የማይሰሙ ከዳተኞች ይላል። ይቅር ማለት አስቸግሮን የለ እንዴ? ታዲያ ወድቀናሳ። ከመስቀሉ እኮ ርቀናል። መስቀሉን ማየት ከኛ ሸሽቷል። «በዐይናችን ፊት ኢየሱስ እንደ ተሰቀለ ተስሎ ነበር፤ አሁን ግን ማን አዚም አደረገባችሁ?» እንደሚል የመስቀሉ ነገር ከእኛ ተደብቋል። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ ያደረገውን ማየት ስላዳገተን ይቅር መባላችንን ማየት ስለማንችል ይቅር ማለት ከብዶናል፤ እርቅ አስቸግሮናል። በቤተ ክርስቲያን የማስታረቅ አገልግሎት ከሌላው አገልግሎት በጣም ጉልበት የሚጨርስ፣ የሚያታክት አገልግሎት ሆኗል። ለምን? መታረቅን እምቢ ብለናልና። እርቅን አንሰማም ብለናል።

ሰ) ኀይሉን የካደ ሃይማኖተኛነት

ከዚያ በኋላ ደግሞ "የአምልኮ መልክ አላቸው ኀይሉን ግን ክደዋል"። የሚል መግለጫ አለ። ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን ይወዳሉ። የመለወጥ ኀይሉ፣ የመቀደስ፣ የመንፈስ ፍሬን የማምጣት ኀይሉ በተለያዩ መንገዶች በክፋት ኀይል ላይ በጨለማ ሥልጣን ላይ የመገለጥ ኀይሉ በአምልኮት ሁኔታ ውስጥ ተሰውሯል።

ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላ ይወዳሉ ይላል። በአምልኮአችን አካባቢ የተድላ ጣዖት ነው ስፍራውን የያዘው? የአምልኮ መልካችን ተድላንና የሚሰማንን ስሜታዊ ደስታ ነው ማዕከል ያደረገው? የመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያንም አካባቢ እንደ ዚሁ እንደ ሆነ ይናገራል። እውነትን የሚቃወሙ መልካምን የማይወዱ ከእውነት ጋር ኪዳንን የማይገቡ፣ እውነት የሚያንገ



ሸግሻቸው ይሆናሉ። ስለ እውነት ደንታ አይሰጣቸውም የጥቅም ጉዳይ ከእውነት ይበልጣል። ጳውሎስ ይህንን ካለ በኋላ «አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግስቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ» ይለዋል። ጳውሎስ ምሳሌ ሆኖለታል። ተከተልህ ይለዋል። ይህን ካለ በኋላ እንደ ገና አንተ ግን በተማርክበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር። ብዙኃኑ በሚሄዱበት በሰፊው መንገድ አትሂድ በዚህ በጠባቡ መንገድ ሂድ ይለዋል(2ጢሞ 3፥10-15)።

"ለሕይወትህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ" የሚለውን ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ያስተላለፈውን ትምህርት ዘንግተን ሕይወታችንንና ትምህርታችንን ብንሸቃቅጥ አገልግሎታችንም በወርቅ ወይም በብር ወይም በከበረ ድንጋይ በማንጽ ፈንታ በእንጨት ወይም በአገዳ ወይም በሣር ብንገነባ፣ ያ ፈታኝ የፍርድ እሳት ይበላዋል። ይህ እንዳይሆን ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን ትእዛዝ ማክበር ይበጀናል (1ጢሞ 4÷16፤ 1ቆሮ 3÷10-15)።

"ይሁዳ፣ በምኞትዋ ነፋስን እንደምታሸትት በምድረ በዳ እንደ ለመደች የሜዳ አህያ ከምኞትዋ የሚመልሳት ማነው?" እንደ ተባለች (ኤር 2:24) እኛም በአገልግሎት ሽፋን በ"ጌታ ሆይ" "ጌታ ሆይ" ስልት ከገንዘብ ኋላ፣ ከዝና ኋላ ብንሮጥ ፍጻሜአችን መጥፋትም ማጥፋትም ነው።

የ"ጌታ ሆይ"! "ጌታ ሆይ"! መኰርኰድኰድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ፣ "እነሆኝ እነሆኝ!" ማለት ከጐደለበት እንደ መንፈሳዊ የሚያስቈጥረን ትንቢቱም፣ አጋንንት አውጭነቱም ተአምራት አድራጊነቱም ከእግዚአብሔር መንግሥት ወግድ ዞር በል ከመባል አያስጥለንም (ማቴ 7÷21-23)።

በኤርምያስ ዘመን እንደ ታየው ለእውነት፣ ለጽድቅ የማይገደው አማኝም ሆነ አገልጋይ የሥጋን መጥገብና ምቾትን በሚያስተና

ግድ ትምህርት፣ የመንፈስ እንቅስቃሴ ወይም ትንቢት ወዘተ በቀላሉ ይጠፋል፣ ይወሰዳል። ከተለማመደውም በኋላ ወደ እንግዚአብሔር ቃል እውነት መመለስ ያዳግተዋል።

መቼም አማኝም ሆነ አገልጋይ፣ ምንጩ ከእውነት ይሁን ከሌላው፣ ስለ ራሱ መልካም ንግርት የተናገረለትን ነቢዩ ሲያደርገው፣ የተናገረበትን ደግሞ ከይሲ ያደርገዋል። ከዚህ ወጥመድ የሚያመልጥ እውነቱም ክብሩም እግዚአብሔር አምላክ የሆነለት የጽድቅ ሰው ብቻ ነው። "የሰው ነቢያትም" የሚበዙት የሚታጀቡትም ከዚህ የተነሣ ነው። እውነተኛ ነቢያት በዘመናቸው መቼ ደልቷቸው ነበር? መቃብራቸው ግን ተጊጦላቸዋል (ማቴ23÷29)።

መጥፎውን ረብ ከመመኘት በኃይል ከመግዛት በመራቅ ለጽድቅና ለፍቅር መጨከን ያሻናል።

"ለሠራተኛ ደሞዙ ይገባዋል" የሚለው ተከብሮ ሳለ፣ "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር" ተጠብቆ ሳለ፦

- ዓሣ አጥማጅነት ለኪስ "እስታቴር ፍለጋ" ከሆነ (ማቴ 17÷27)፣
- እረኝነት በጎችን ከማሰማራት፣ የደከመውን ከማጽናናት፣ የተሰበረውን ከመጠገን፣ የታመመውን ከማከም፣ የባዘነውን ከመመለስ፣ የጠፋውንም ከመፈለግ ይልቅ፣ በኃይል ለመግዛት ከሆነ "ጸጉራም ጸጉራሙን" ለመሸለት "የወፋፈሩትን" ለማረድ ከሆነ (ሕዝ 34፤ ማቴ 10÷6-10፤ ሉቃ 10÷7)፣
- ነቢይነት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጣዖት አምልኮ ከመመለስ፣ ጽድቁን ከማጽናት፣ ስለ መበለቲቱ ከመሟገት፣ ለደሃ አደጉ ከመቆም፣ ለመጻተኛው ከመናገር፣ ስለ ሞያተኛው ከመገደድ ፈንታ "ጥርስ ሲነክስ" ሰላምን መናገር አለበለዚያ ሰልፍን ከገዛ ልብ እያወጡ መተንበይ፣ ከንቱ ራእይ ማየት፣ ምዋርት ማሟረት፣ ስለ "ጭብጥ ገብስ" እና ስለ "ቁራሽ እንጀራ" ተብሎ፣ "ይላል የሠራዊት አምላክ" ማለት፣



*የእግዚአብሔርን ስም የሚያስረክስ ስለ ሆነ፣ ወዮ ነው* (ሚክ 3÷5-8፤ ሕዝ 13፤ ኤር 23÷13-18)!

*"የምታስደንቅና የምታስደነግጥ ነገር በምድር ላይ ሆናለች፤ ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፤ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ፤ በፍጻሜውስ ምን ታደርጋላችሁ?"* (ኤር 5÷30-31)

## 3. ሰይጣን - የጨለማ ኀይላት

### 1) ሰይጣን ማን ነው?

ሰይጣን ከመውደቁ በፊት በሰማይ ከፍተኛ ማዕረግ የነበረው ውብ መልአክ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ሲናገር እንዲህ ይላል *"ጥበብን የተሞላብህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ። በእግዚአብሔር ገነት በኤድን ነበርህ፤ ዕንቁ ሁሉ ሰርድዮን ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ፣ ልብስህ ነበር፤ የከበሮህና የእምቢልታህም ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤ በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር። አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ እየኖርህ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ። ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ"* (ሕዝ 28÷13-18)። በዚህ ሁኔታ የነበረው መልአክ በእግዚአብሔር መመሪያ መኖር ባርነት መስሎ ታየው። ከራሱ በሚወጣ ሀሳብ ለራሱ ፍላጎትና ፈቃድ በመገዛት ለመኖር ፈለገ፤ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሁሉ ራስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሌላ ራስ ለመሆን ተመኘ። ልብ ብሎ ራሱን አየ፤ ውበቱን አስተዋለ፤ በራሱ ተገረመ። ራሱንም አደነቀ፤ በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ለብቻው የያዛቸው ነገሮች ለእኔም ይገባኛል አለ። በውበቱም ምክንያት በልቡ በእግዚአብሔር ላይ ኮራ (ሕዝ 28÷17)። እግዚአብሔር በሰጠው ጥበ

ግድ ትምህርት፣ የመንፈስ እንቅስቃሴ ወይም ትንቢት ወዘተ
በቀላሉ ይጠፋል፣ ይወሰዳል:: ከተለማመደውም በኋላ ወደ እን
ግዚአብሔር ቃል እውነት መመለስ ያዳግተዋል::

መቼም አማኝም ሆነ አገልጋይ፣ ምንጩ ከእውነት ይሁን ከሌላው፣
ስለ ራሱ መልካም ንግርት የተናገረለትን ነቢዩ ሲያደርገው፣ የተ
ናገረበትን ደግሞ ከይሲ ያደርገዋል:: ከዚህ ወጥመድ የሚያመ
ልጥ እውነቱም ክብሩም እግዚአብሔር አምላክ የሆነለት የጽድቅ
ሰው ብቻ ነው:: "የሰው ነቢያትም" የሚበዙት የሚታጀቡትም
ከዚህ የተነሣ ነው:: እውነተኛ ነቢያት በዘመናቸው መቼ ደል
ቷቸው ነበር? መቃብራቸው ግን ተጊጦላቸዋል (ማቴ23÷29)::

መጥፎውን ረብ ከመመኘት በኃይል ከመግዛት በመራቅ ለጽድ
ቅና ለፍቅር መጨከን ያሻናል::

"ለሠራተኛ ደሞዙ ይገባዋል" የሚለው ተከብሮ ሳለ፣ "የሚያበ
ራየውን በሬ አፉን አትሰር" ተጠብቆ ሳለ:-

- ዓሣ አጥማጅነት ለኪስ "እስታቴር ፍለጋ" ከሆነ (ማቴ 17÷27)፣
- እረኝነት በጎችን ከማሰማራት፣ የደከመውን ከማጽናናት፣ የተ
  ሰበረውን ከመጠገን፣ የታመመውን ከማከም፣ የባዘነውን ከመ
  መለስ፣ የጠፋውንም ከመፈለግ ይልቅ፣ በኃይል ለመግዛት
  ከሆነ "ጸጉራም ጸጉራሙን" ለመሸለት "የወፋፈሩትን" ለማ
  ረድ ከሆነ (ሕዝ 34፤ ማቴ 10÷6-10፤ ሉቃ 10÷7)፣
- ነቢይነት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጣዖት አምልኮ
  ከመመለስ፣ ጽድቁን ከማጽናት፣ ስለ መበለቲቱ ከመሟገት፣
  ለደሃ አደጉ ከመቆም፣ ለመጻተኛው ከመናገር፣ ስለ ሞያተ
  ኛው ከመገደድ ፈንታ "ጥርስ ሲነክስ" ሰላምን መናገር አለ
  በለዚያ ሰልፍን ከገዛ ልብ እያወጡ መተንበይ፣ ከንቱ ራእይ
  ማየት፣ ምዋርት ማሟረት፣ ስለ "ጭብጥ ገብስ" እና ስለ "
  ቁራሽ እንጀራ" ተብሎ፣ "ይላል የሠራዊት አምላክ" ማለት፣



*የእግዚአብሔርን ስም የሚያስረክስ ስለ ሆነ፣ ወዮ ነው* (ሚክ
3÷5-8፤ ሕዝ 13፤ ኤር 23÷13-18)!
"የምታስደንቅና የምታስደነግጥ ነገር በምድር ላይ ሆናለች፤ ነቢ
ያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፤
ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ፤ በፍጻሜውስ ምን
ታደርጋላችሁ?" (ኤር 5÷30-31)

## 3. ሰይጣን - የጨለማ ኀይላት

### 1) ሰይጣን ማን ነው?

ሰይጣን ከመውደቁ በፊት በሰማይ ከፍተኛ ማዕረግ የነበረው
ውብ መልአክ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ሲናገር እን
ዲህ ይላል *"ጥበብን የተሞላብህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደ
ሚያ አንተ ነህ:: በእግዚአብሔር ገነተ በኤድን ነበርህ፤ ዕንቁ
ሁሉ ሰርድዮን ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቤርሌ፣ መርግድ፣ ኢያስ
ጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ፣ ልብስህ
ነበር፤ የከበሮህና የእምቢልታህም ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤ በተ
ፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር:: አንተ ልትጋርድ የተቀባህ
ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ
በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ:: ከተፈጠርህበት ቀን ጀም
ረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ"* (ሕዝ
28÷13-18):: በዚህ ሁኔታ የነበረው መልአክ በእግዚአብሔር መመ
ሪያ መኖር ባርነት መስሎ ታየው:: ከራሱ በሚወጣ ሀሳብ ለራሱ
ፍላጎትና ፈቃድ በመገዛት ለመኖር ፈለገ፤ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ
የሁሉ ራስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሌላ ራስ ለመሆን ተመኘ::
ልብ ብሎ ራሱን አየ፤ ውበቱን አስተዋለ፤ በራሱ ተገረመ:: ራሱ
ንም አደነቀ፤ በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ለብቻው የያዛቸው
ነገሮች ለእኔም ይገባኛል አለ:: በውበቱም ምክንያት በልቡ በእ
ግዚአብሔር ላይ ኮራ (ሕዝ 28÷17):: እግዚአብሔር በሰጠው ጥበ

ብና ውበት ለራሱ ለማትረፍ ተነሣ (ሕዝ 28፥16):: "በልቡም ወደ ሰማይ አርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ እቀመጣለሁ፤ ከደመናዎችም ከፍታ በላይ አርጋለሁ:: በልዑልም እመሰላለሁ አለ" (ኢሳ 14፥1-13):: በዚህ ጊዜ እንደ ርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ተራራ ተጣለ (ሕዝ 28፥16):: ከፍ ባለችው በእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እግዚአብሔር እጅግ ተጠግቶ የነበረ ይህ መልአክ በተቃራኒው እጅግ ርቆ ተጥሎ ማየት የሚደንቅ በመሆኑ "አንተ የንጋት ልጅ የአጥቢያ ኮከብ ሆይ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ?" ተባለ (ኢሳ 14፥12):: እግዚአብሔር ያደረገው ሆኖ መኖርን መቀበል ባለመቻሉ በሰማይ መንግሥት የማያስፈልግ ሆኖ እንደማይጠቅም ዕቃ ተጣለ::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን ማን እንደ ሆነ ባይገልጸው ስለ እርሱ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆን ነበር:: ሁላችንም ስለ ሰይጣን ያወቅነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ማንነት ስለ ገለጠልን ነው:: እንዲህ ባይሆን ኖሮ ማናችንም ስለ እርሱ ማንነት የምናውቀው በስውር ሁኔታ እንጂ ራሱን በመግለጥ ስላልሆነ ነው:: ራሱን ገልጦ የሚሠራ ጠላት በቀላሉ አሠራሩ ይታወቅበታል:: ጠላት ግን እንደ ሌለና እንደማይሠራ አድርጎ ራሱን ያቀርባል:: ስለዚህ ነገር ማናችንም መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው ውጭ መሆን አንችልም::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን ጠላት ባላጋራ ክፉ እያለ ገልጦታል:: ስለዚህ አንድ አማኝ ሰይጣንን እንደ ጠላቱ፣ እንደ ባላጋራው ማየት መቻል አለበት:: አለበለዚያ በመረጃነት (በዕውቀት) ብቻ ስለ ሰይጣን ከማወቃችን በላይ፣ አጥብቀን እንደ ጠላታችን የማንቃወምና የማንከላከል ከሆነ ጥቃት ሊያደርስብን ይችላል:: አንዳንዶች ዲያብሎስ ጠላታችን ነው ይላሉ፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያላችሁን ሁኔታ እንዴት ትመለከቱታላችሁ ሲባሉ፣ ምንም



ሊያደርገኝ አይችልም ይላሉ:: ምንም ሊያደርጋቸው ካልቻለ እንዴት ጠላታቸው ሊሆን ቻለ? ጠላቱን በመንገድ አግኝቶ በመልካም የሰደደ ማነው? ማንም ሊኖር አይችልም:: መጽሐፍ ቅዱስም ሰይጣንን ባላጋራ ነው የሚለው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ጠላት ነው ካለ በማንኛውም ሁኔታ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ "በመጠን ኑሩ ንቁም፣ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያንን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት" ይላል (1ጴጥ 5፥8-9):: ይህ ክፍል በጠላት ላይ ምን ዐይነት አቋም መውሰድ እንዳለብን ይናገራል:: እንደዚህ ክፍል አባባል ዲያብሎስ ባላጋራ (ጠላት) ነው:: ሆኖም አንዳንድ ወገኖች ምንም ሊያደርገኝ አይችልም ሲሉ አንድ ነገር ማድረግ መቻሉን በትክክል ያስተዋሉ አይመስሉም:: ምክንያቱም ምንም ሊያደርጋቸው ካልቻለ ወዳጃቸው እንጂ ጠላታቸው ሊሆን አይችልም:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ጠላት እንደ ሆነ ስለሚናገር "... ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል" ይላል (ያዕ4፥7):: ባንቃወመው ግን ሊያደርግ ያለውን ያደርጋል::

በአዲስ ኪዳን ከ27ቱ መጻሕፍት 19ኙ ሰይጣንን በተለያያ መልኩ ገልጠውታል:: ይኸውም ክፉ ጠላት ስለ ሆነ የራሱን ክፋት ለማሳየትና ለማሳወቅ ነው:: አሠራሩ ካልታወቀና በጥንቃቄ ካልተያዘ እንዲሁም ተከላካዮችና አጥቂዎች በምንሆንበት ሁኔታ ራሳችንን ካላስገባን የቀድሞ ጥፋቱን አሁንም ሊፈጽም ይችላል:: ሰይጣን በአዲስ ኪዳን ከሃያ ሰባቱ፣ ስምንቱ፤ ክስምንቱ ደግሞ በአራቱ ክፉ በሚል ወይም በሌላ ስያሜ ገልጠውታል:: እንዲሁም በወንጌላት ውስጥ ደግሞ 28 ጊዜ በተለያየ ስም እርሱና አጋንንቱ ተጠቅሰዋል:: ከሃያ ስምንቱ ሃያ አምስቱን ደግሞ የጠቀሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን ሕያው ፍጡር እንደ ሆነ ይናገራል::

የማሰብ፣ የማስተዋል ችሎታ ያለው፣ ፈቃድ ያለው፣ ስሜት ያለው ፍጡር አድርጎ ገልጦታል:: ፈቃዱ ደግሞ ያለ ማቋረጥ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚቃወም ነው:: 2ቆሮ12፥11፤ 11፥3፤ ማቴ 4፥6፤ ራእ 2፥9፤ 12፥1፤ 12፥4፤ 12፥12፤ 13፥5-7፤ 20፥7-9፤ 2ጢሞ2፥26፤ ሉቃ22፥31፤ 1ጢሞ3፥6፤ 4፤ ኢዮ2፥1-2፤ ኤፌ6፥11-12::

## 2) የሰይጣን የማጥቂያ መንገዶች

ስለ ሰይጣን ተቃዋሚነት ሲነሣ አብሮት የሚነሣው ጥያቄ እንዴት ነው የሚቃወመው? የሚለው ነው:: እርሱ እንዴት እንደሚቃወም ካልገባን አሠራሩን ልንስተው እንችላለን:: ስለዚህ ጒዳይ ከእግዚአብሔር ቃል አንዳንድ ነጥቦች አንስተን እንመለከታለን::

### ሀ) በማጥፋት/በማውደም

*"ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"* (ዮሐ 10፥10)::

ሰይጣን ጥቃት ከሚያደርስብን መንገዶች አንዱ በሰው ሕይወት፣ ጤንነትና ንብረት ላይ ውጊያ በማካሄድና በማጥቃት ነው:: በዚህ ጒዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው ኢዮብ ነው:: ኢዮብ እግዚአብሔር ራሱ እንደ መሰከረለት *"ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋትም ሁሉ የራቀ ነበር"* (ኢዮ 1፥8):: ሰይጣን ግን በእርሱ ላይ ተነሣ፤ ያለውን ንብረት ሁሉ አወደመ፤ ልጆቹንም ገደለ፤ በመጨረሻም ከራስ ጠጒሩ እስከ እግር ጥፍሩ በቍስል በመምታት ጤንነቱን አሳጣው:: እንዲያውም በምዕራፍ 2፥6 ላይ እግዚአብሔር ሰይጣንን ሕይወቱን ተወው ብሎ ተአቅቦ ባያደርግበት ኖሮ አመጣጡ ለመግደል ነበር:: እዚህ ላይ አንድ ልብ ሊባል የሚገባ ነገር አለ:: ይኸውም ሰይጣን በኢዮብ ላይ ይህን ሁሉ ሊያደርግበት የቻለው እግዚአብሔር ፈቅዶለት እንጂ በራሱ ባለ ሥልጣን ሆኖ አይደለም:: ዛሬም ቢሆን ባሕርይው እንደ ጥፋቱ ነው:: ጌታችን እንዳለው እርሱ *"ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም"*:: ሰይጣን ሰይጣን ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አጥፊና ነፍሰ ገዳይ ነው:: ይሁን እንጂ በልዑል መጠጊያ የሚኖር ግን ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ስለሚያድር ከአጥፊው ጥፋት ይድናል (መዝ 91፥1):: ነገር ግን እምቢ ብሎ ቅጥሩን የሚያፈርስ ግን እባቡ ትነድፈዋለች:: ደሙ ቅጥራችን ነው:: ማንም ከዚህ ቅጥር ቢወጣ ምንም መከላከያ የለውም፤ ምክንያቱም ከደሙ የተነሣ አጥፊው ወደ እናንተ አይቀርብም ተብሏልና (ዘፀ 12፥23):: ለማሰቃየት ቢመጣ እንኳ "ከበጉ ደም የተነሣ፣ ከምስክራቸው ቃል የተነሣ ድል ነሱት" ስለሚል አይሆንለትም (ራእ 12፥10):: ቀደም ብለን ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እንደ ተመለከትነው ሰይጣን ኢዮብን ሊፈትን እግዚአብሔርን ጠየቀ (ኢዮ1፥10-13):: ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ደግሞ "ደቀ መዛሙርቱን እንደ ስንዴ ሊያበጥራቸው ለመነ" እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለስምኦን ጴጥሮስ "ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ" ሲለው ሰይጣን ቅዱሳንን ለማጥፋት ይለምናል ማለት ነው? በክፍሉ የተጻፈ ነገር ባይኖርም የእኛ ጸሎት ከእርሱ ልመና በልጦ መገኘት አለበት::

### ለ) በማስታበይ

*"እግዚአብሔር ትእቢተኞችን ይቃወማል ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣልና"* (ያዕ 4፥7)::

የእግዚአብሔር ቃል የትዕቢትን መጥፎነት እየደጋገመ ይናገራል:: ሆኖም ሰዎች እንዲታበዩም ሆነ በዐመፅ እንዲነሡ የሚያደርግ

ሰይጣን ነው። እርሱ በእነዚህ እኩይ ተግባራት ተሞልቶ ሰዎችም እንዲሞሉ ያደርጋል። ከሚያስታብይበት መንገዱ አንዱ ስኬት ነው። እርሱ ሰዎች አስቀድሞ እንዳይሳካላቸው ወይም እንዳይሆንላቸው ይጥራል። ነገር ግን አልሆን ብሎት መሳካትና መከናወን ሲሆንላቸው ደግሞ ለማስታበይ ይሞክራል። በዚህ ጕዳይ ላይ በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 28 ላይ የተጠቀሰው የጢሮስ ንጉሥ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ከታሪክ እንደምንረዳው ጢሮስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በደሴት ውስጥ የተከተመች ከተማ ነበረች። የዚህች አገር ንጉሥም የአካባቢውን ንግድ ተቈጣጥሮት ስለ ነበር በልጥጎ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ እብሪተኛ ሆነ። ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከል ጀመረ። በዚህም ትዕቢቱ እግዚአብሔር ትጠፋለህ ሲል ከቍጥር 3 ጀምሮ እንዲህ ይለዋል፤

*"ከዳንኤል ይልቅ ጠቢብ ነህን?*
*ከአንተስ የተሰወረ ምስጢር የለምን?*
*በጥበብህና በማስተዋልህ የራስህን ሀብት አከማችህ፤*
*ወርቅም ብርም በግምጃ ቤትህ አጠራቀምህ፤*
*በንግድ ሥራ እጅግ ከመራቀቅህ የተነሣ በሀብት ላይ*
*ሀብት አካበትህ፤*
*ከሀብትህ ብዛት የተነሣም ልብህ በትዕቢት ተወጠረ፤*
*ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤*
*እንደ አምላክ ጥበበኛ ነኝ ብለህ ስለምታስብ፣*
*ከአሕዛብ መካከል እጅግ ጨካኞች የሆኑትን ባዕዳን*
*በአንተ ላይ አመጣለሁ፤*
*በጥበብህ ውበት ላይ ሰይፋቸውን ይመዛሉ፤*
*ታላቅ ክብርህንም ያረክሳሉ፤*
*ወደ ጕድጓድ ያወርዱሃል፤*
*በጥልቁ ባሕር ውስጥ በባሕሮችም ልብ ውስጥ አስከፊ*



*ሞት ትሞታለህ።*
*ታዲያ በገዳዮችህ ፊት አምላክ ነኝ ትላለህን?*
*በገዳዮችህ እጅ ስትገባ አንተ ሰው እንጂ አምላክ*
*አይደለህም" አለው።*

በመጨረሻም እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት ይቺ ጢሮስ የምትባል አገር እንደወደመች የትንቢትን አፈጻጸም የሚያስረዱ መጻሕፍቶች ይነግሩናል። እዚህ ላይ ከዚህ ጋር አያይዘን የምናነሣው ነጥብ አለ። ይኸውም የትንቢት መጻሕፍት የሚያስተምሩ ሰዎች አንዳንድ ትንቢቶች ተደጋጋሚ ፍጻሜ እንዳላቸው ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ታሪካዊ ከሆነው ነገር ተነሥተው ከበስተ ጀርባው ስላለው መንፈሳዊ እውነታ ይናገራል ይላሉ። በዚህ መሠረት ይኸ ክፍል ታሪካዊ ከሆነው ከንጉሥ ጢሮስ ይነሣና በስተ ጀርባው ስላለው ስለ ታብዮ አስታባዩ ሰይጣን ይናገራል። ይህ ንጉሥ ልቡን አሳምጾ በትዕቢት እኔ አምላክ ነኝ እንዲል ይገፋፋው የነበረው ሰይጣን ነበር።

ቀደም ብለን ጠቅሰን እንዳለፍነው ሰይጣን ከመውደቁ በፊት ጥበብ የተሞላና ውበቱም የተፈጸመ መደምደሚያ ነበር። ሆኖም ይህ ነገር እግዚአብሔር የሰጠው እንጂ በራሱ ያመጣው አልነበረም። በመጨረሻ ላይ ግን ይህንን ዘንግቶ በጥበቡና በውበቱ ታብዮ ራሱን እንደ አምላክ ቈጠረ። ስለዚህም ነበር ረክሶ ከእግዚአብሔር ተራራ ወደ ምድር የተጣለው።

ሰይጣን ለመውደቁ ምክንያት ትዕቢቱ ነው። ልክ እንዲሁ እኛም በእርሱ ቅያሽ ውስጥ ገብተን እግዚአብሔር የሰጠንን መንፈሳዊም ሆነ ተፈጥሮአዊ ጸጋ ወደ እኛነታችን አምጥተን በትዕቢት እንድንሞላ ግፊት ያደርጋል። ትዕቢት ወደ ውድቀት ያደርሳል (ምሳ 16፥18)። መጽሐፍ ቅዱስ ትዕቢት ሲል ማሰብ ከሚገባው በላይ ራስን ከፍ አድርጎ ማሰብ ወይም መገመት ከሚገባው በላይ

ለራስ ዋጋ ሰጥቶ መሄድ ማለት ነው። ሰይጣን እግዚአብሔር ባጎናጸፈው ውበትና ጥበብ ስለ ራሱ ያለው ግምትና አስተሳሰብ ከፍተኛ ሆነ፤ በዚህ ታበየ። ሰዎችም እግዚአብሔርን መቋቋም የሚጀምሩት እርሱ የሰጣቸውን ተፈጥሮአዊም ሆነ መንፈሳዊ ጸጋ ወስደው የራሳቸው ንብረት ማድረግ ሲጀምሩ ነው።

በትንቢተ ዳንኤል ላይ እንደምንመለከተው አንድ ጊዜ ንጉሡ ናቡከደናፆር በሰገነቱ ላይ ወጥቶ ከተማዪቱን አየና *"ይቺ እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥቴ መኖሪያ እንድ ትሆን የሠራሁዋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን?"* በማለት በትዕቢት "እኔ" አለ። በመሠረቱ ያቺ ከተማ ብትሠራ በሕዝቡ እንጂ በእርሱ አልነበረም። ሆኖም ቃሉ በንጉሡ አፍ ገና ሳለ ከሰማይ ድምጽ መጣና "ንጉሥ ናቡከደናፆር ሆይ፤ መንግሥትህ ከአንተ ፀለፈች ተብሎ ለአንተ ተነግሮአል፤ ልዑልም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሰለጥን እስከታውቅ ድረስ ከሰዎች ተለይ ተህ ትሰደዳለህ" አለው። ንጉሡም ወዲያው ተሰደደ፤ በመጨረ ሻም ጤናውንና ዙፋኑን አጥቶ ሰባት ዓመት እንደ በሬ ሳር በላ (ዳን4፥28-33)። የመማሪያው ዘመን ከተፈጸመ በኋላ ግን ዐይ ኑን ወደ ሰማይ አንሥቶ እንዲህ አለ " ... *አሁንም እኔ ናቡ ከደናፆር የሰማይ ንጉሥን አመሰግነዋለሁ፤ ታላቅ አደርገዋለሁ፤ አከብረዋለሁ፤ ሥራው ሁሉ እውነት መንገዱም ፍርድ ነውና፤ በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና"* አለ (ቍ 37)።

ሐዋርያው ያዕቆብ እንዳለ *"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወ ማል"* ትህትና ከእኛ ርቆ ትዕቢት በውስጣችን የሚታይ ከሆነ ክፉው እየተጠናወተን እንዳለ ልብ እንበል። እግዚአብሔር የሚ ኖረው ከትዕቢተኞች ጋር ሳይሆን ከትሁታን ጋር ነው። ስለ ትህ ትና ጥዳይ ሲነሣ ሙሴ በጣም ትሁት ሰው እንደ ነበር የእግ ዚአብሔር ቃል ይናገራል። ይህ ሰው በእጁ ብዙ ታምራትና



ድንቆች ሆነዋል፤ በእርሱ በኩል ቀይ ባሕር ተከፍሎአል። ይሁ ንና ሙሴ ግን የማስተዳደር ችሎታ ስላልነበረው፣ ከእስራኤል ወገን ያልሆነ ሰው አማቱ ዮቶር የአምሳ አለቆች፣ የመቶ አለቆ ችና የሺህ አለቆችን እንዲሾም መከረው። ነገር ግን እንዲህ ሲለው ምክሩን ሰማ እንጂ አንተ ተራ ሰው በእኔ እኮ በእጄ ብዙ ታምራትና ድንቅ ሆኖአል ብሎ አልታበየም። በእኛም ውስጥ አንድ መልካም ነገር ሲያልፍ ወይም ደግሞ ነገሮች ሁሉ የተሳ ኩልን ስንሆን ትሁት ካልሆንን ከእኛ ጋር ተባባሪ፣ ሰልፈኛ የሚሆነው ሰይጣን ነው።

ሐ) በመክሰስ

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን በራእ 12፥10 ላይ "የወንድሞች ከሳሽ" ይለዋል። እርሱ በዚህ ሥራው ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ቅዱሳንን ይከስ እንደ ነበር ዘካርያስ 3፥1-10 ካለው ክፍል መረዳት እን ችላለን። የዚህ ክፍል ታሪካዊ ዳራ ከቤተ መቅደሱ ጋር የተያ ያዘ ነው። ይኸውም ቤተ መቅደሱ በባቢሎን ወረራ ከፈረሰ በኋላ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ በኩል ከሰባ ዓመት በኋላ እመልሳችኋለሁ ብሎ ተስፋ ሰጣቸው። ይህ ተስፋ በዳንኤል የን ስሓ ጸሎት በኩል ሲፈጸም ሕዝቡ በምርኮ ይኖሩበት ከነበረው አገር ወደ ይሁዳና ኢየሩሳሌም ተመለሱ (ኤር 39፤ ዳን9፥1-23፤ ዕዝ1፥1)። በዚህ ጊዜ ሕዝቡን በዋነኛነት ሲመሩ የነበሩት ዘሩ ባቤልና ኢያሱ ናቸው (ዕዝ 2፥2)። የቤተ መቅደሱ መሠረት ተጠናቆ ሳለ ተቃዋሚዎች እንደ ገና ተነስተውባቸው ለዐሥር ዓመት ያህል ሥራው ተቋረጠ (ዕዝ 4)። የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዲተጓጎል ምክንያት የሆነው ንጉሥ ከሞተም በኋላ ሥራው ቸል ስለ ተባለ፣ ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ላይ ሐጌና ዘካርያስ ተነሥተው የቤተ መቅደሱን ሥራ እንደ ገና እንዲቀ ጥሉ ሕዝቡን አነሳሷቸው (ዕዝ5፥1-2)። በዚህ መሠረት ሥራው ቀጠለ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር ነቢዩ ዘካሪያስ በምዕራፍ 3 ላይ

*ያለውን ራእይ ያየው:: ክፍሉ እንዲህ ይላል፤ "እርሱም ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ፤ ሰይጣንም ይከሰው ዘንድ በቀኙ ቆሞ ነበር:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ ሰይጣን ሆይ፤ እግዚአብሔር ይገስጽህ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገስጽህ፤ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን? አለው:: ኢያሱም እድፋም ልብስ ለብሶ በመልአኩ ፊት ቆሞ ነበር:: እርሱም መልሶ በፊቱ የቆሙትን፣ እድፋሙን ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቁ አላቸው:: እርሱም እነሆ አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ፤ አለው:: ደግሞም ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድርጉ አለ:: እነርሱም በራሱ ላይ ንጹሕ ጥምጥም አደረጉ፤ ልብስንም አለበሱት የእግዚአብሔር መልአክ በአጠገቡ ቆሞ ነበር"::*

ኢያሱ በዚህ የቤተ መቅደስ ሥራ ላይ ግንባር ቀደም እንዲሆን የተሾመ ካህን ነበር:: ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሠራ በተነሣበት በዚህ ወቅት ሕይወቱ በኀጢአት ተልኮስኩሶ ስለ ነበር፣ ሰይጣን ይህ ሰው አይበቃም ብሎ ለክስ ተነሣ:: ደግነቱ ግን እግዚአብሔር ይገስጽህ፣ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ይገስጽህ፤ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን? በማለት ተሟገተለት::

ዛሬም ቢሆን ሰይጣን ወደ ኀጢአት እንድንገባ አስቀድሞ የተለያዩ ነገሮችን በማሳየት ያባብለናል:: ከዚያም በኋላ በኀጢአት ወድቀን ከተርመጠመጥን በኋላ ኅሊናችንን በክስ ለማስጨነቅ የክስ ፋይሉን ይዞ ይመጣል፤ ኅሊናችንን ያሰቃያል:: የዚህ ሁሉ ዋነኛ ዐላማ በክስ ብዛት ከእግዚአብሔር እንድንለይ ወይም ራሳችንን እንድንገድል ለማድረግ ነው:: በዚህ አኳያ ራሳቸውን የገደሉ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዳሉ ይነገራል:: እርሱ ስንደክም ንስሓ ገብተን እንዳንመለስ የእግዚአብሔርን ምኅረት ሸፍኖ ወደ ሞት እንድንጣደፍ ያደርጋል:: እግዚአብሔር ግን



የሚፈልገው ካለንበት ጨለማ ወጥተን ወደ እርሱ እንድንመጣ እንጂ እንድንጠፋ አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ሰይጣን በሠሩት ኀጢአት ከሶ ወደ ሞት ከነዳቸው ሰዎች መካከል አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው:: ይሁዳ ሰይጣን ኢየሱስን ስለ ብር ዐሳልፎ እንዲሸጠው በልቡ ዐሳብ አስገባበት (ዮሐ13፥2):: ይህንን ሰው የሰው ሕይወቱ በገንዘብ ብዛት ነው ያለው ይመስላል:: ነገር ግን ያንን የተመኘውን ገንዘብ ሲያገኝ ደግሞ ስለ ሠራው በደል ወደ ሞት እንዲሄድ ከሰሰው:: በመጨረሻም በክሱ ብዛት በዕንጨት ላይ ታንቆ እንዲሞት አደረገው (ማቴ 27፥3-5):: "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን፣ ጸጸት የሌለበት ወደ መዳን የሚያደርሰውን ንስሓ ያደርጋልና፤ የዓለም ጸጸት ግን ሞትን ያመጣል" ይላል (2ቆሮ 7፥10-11):: መንፈስ ቅዱስ ይወቅሳል፤ በሚወቅሰን ጊዜ አብሮ የንስሓን መንገድ ያሳየናል:: ሰይጣን ሲከሰን ግን ሞትን ሊጋብዘን ነው:: ንስሓ ገብተን ራሳችንን ባናጠፋ እንኳ በእግዚአብሔር መንገድ እንዳንሄድ ያኮላሽናል::

የእግዚአብሔር ቃል አማኞች በጸጋ ስም ኀጢአትን እንደ ውሃ እንዲጨልጡት ፈቃድ አይሰጥም:: ይሁን እንጂ ኀጢአት ሊሠሩ እንደማይችሉም አይናገርም (1ዮሐ2፥1-2):: ስለዚህ ምንም ዐይነት በደል ቢኖርብን በንስሓ መንገድ እየሄድን የተበላሸውን ነገራችንን በጽድቅ ሥራ መበቀል አለብን እንጂ ከእግዚአብሔር መሸሽ የለብንም:: ለዚህም ደግሞ እግዚአብሔር ይረዳናል:: የሰይጣን ክስ ወይም የዓለም ጸጸት ወደ ሞት ሲገፋፋ የእግዚአብሔር ወቀሳ ግን ወደ ንስሓ ያመጣል:: በሠራነው በደል ተጸጽተን ንስሓ ስንገባ እግዚአብሔር ኀጢአታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይቅር ይላል፤ አበሳችንንም ከእኛ ያርቃል:: በመስቀሉ ላይ የፈሰሰውም የሕይወት ምንጭ ኅሊናችንን አንጽቶ ሰላም ሊሰጠን ይችላል::

ቀደም ብለን ባየነው በዘካሪያስ መጽሐፍ ላይ ኢያሱ በእግዚአ ብሔር ፊት እድፋም ልብስ ለብሶ ቆሞ ነበር። እግዚአብሔር ግን ይቅር ስላለው መልሶ በፊቱ የቆሙትን "እድፋሙን ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቁ አላቸው"። እርሱም አበሳህን ከአንተ አር ቄአለሁ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ አለው። ደግሞም ንጹሕ ጥም ጥም በራሱ ላይ አድርጉለት አለ። እነርሱም በራሱ ላይ ንጹሕ ጥምጥም አደረጉለት፤ ልብስንም አለበሱት (ቍ ጥር 3-5)።

ይህ ጥምጥም ምንድን ነው? የነላፊነትና እንደ ገና የመሾም ምል ክት ነው። በመቀጠልም ወደ ቦታህ ለመመለስ ተመለስ ሲል የእግዚአብሔር መልአከ እንዲህ ሲል አዳኘበት *"የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመንገዴ ብትሄድ ትእዛዜንም ብትጠብቅ በቤቴ ላይ ትፈርዳለህ፤ አደባባዮቼንም ትጠብቃ ለህ፤ በዚህም ከቆሙት ከእነዚህ ጋር መግባትን እሰጥሃለሁ"* አለው። ተመለስ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ተደጋግሞ ከመጣ በኋላ ለኀሊናችን ታውቆን እምቢ ካልን መቄረጥ ይመጣል። ነገር ግን በመታዘዝ እሺ ብለን ወደ እግዚአብሔር ከተመለስን ግን እርሱ ንጹሕን ልብስ ያለብሰናል፤ በአደባባዮቹም (በቤቱ) ላይ መንጋውን ለማሰማራትም ሆነ ለመጠበቅ እንሾማለን።

በአጠቃላይ ሰይጣን ከሳሽ ከመሆኑ የተነሣ ሁል ጊዜ በቅዱሳን ላይ የክስ ፋይል ይከፍታል። በቀድሞው ዘመን እግዚአብሔርን በቅድስና ያመልኩ የነበሩትን ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፊት ይከ ሳቸው የነበረው "አንተን የሚያመልከህ እኮ ዙሪያውን ስላጠር ክለትና ስላከበርከው ነው" እያለ ነበር። ልክ እንደዚሁ ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ በእግዚአብሔር ፊት ጥሩ ሕይወት ያላቸ ውን ቅዱሳን አንተ ጸሎተኛ የሆንከው ስላጣህ ነው፤ አንተ ደግሞ የምታመሰግነው ስላገኘህ ነው እያለ በግራና በቀኝ ያዋክባል። ስለዚህ ይህንን ሽንገላ ለመቃወም የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልንለብስ ያስፈልጋል።



## መ) የሚያምኑትን ልብ/ አእምሮ በማሳወር - ቃሉን በመስረ ቅና እንዳይነገር/ እንዳይገለጥ በመከላከል

መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዓለም ገዥና አምላክ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ የሚሠራ አለቃ እንደ ሆነ ይናገራል (ዮሐ12፥31፤ 1ቆሮ4፥4፤ ኤፌ1፥2)። ሆኖም እርሱ የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው በሕጋዊ ንጉ ሥነት ሳይሆን፣ በኀይል (በግድ)፣ በኀጢአት፣ በሀመፅና በሞት ፍርሃት ነው። ድነትን በተመለከተ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ለማያምኑ እንዳያበራላቸው ዐሳባቸውን ያሳውራል ወይም ደግሞ ቃሉ ደርሷቸው ከሆነ በልባቸው የተዘራውን በመንጠቅ ይዋ ጋል (ማቴ13፥3፡19)። ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ላይ *"ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስታወት የሚያይን ሰው ይመስላል። ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያው እን ደምን እንደ ሆነ ይረሳል"* ይላል (ያዕ 1፥23)። አንዳንድ ጊዜ ቃሉን ስንሰማ ልባችን በጣም ይነካል፤ ወይም ሰው በፊታችን ላይ ያለውን ቆሻሻ አይቶ ከሚነግረን ይልቅ በመስታወት እንደ ምናየው ይሆንብናል። ከዚያ በኋላ ግን በውስጣችን የለም፤ የዚህ ምስጢሩ ከፉው የሰማነውን ቃል በልባችን እንዳይኖርና ወደ ሌላ እንድናዘነብል ማድረጉ ነው። ይህም ብቻ አይደለም ቃሉ እንዳይነገር ተቃውሞና ስደትም በማስነሣት የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይስፋፋ ይገዳደራል (1ተሰ2፥18)።

## ሠ) በማሳት

*«ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፤ እርሱም ዲያቢሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው፣ ዓለምን፤ ሁሉ የሚያስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ»*(ራእ 12፥9)።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ሕዝብ ከሚቋቋምበት መን ገዶች ውስጥ ዋነኛው ማሳት ነው:: ይህንን የሚያደርገው የተ ለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሲሆን፣ ሀይነተኛ ስልቶቹን ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን::

### 3) የማሳቻ ስልቶቹ

#### ሀ) በተቈርቋሪነት/ በነፃ አውጭነት ስልት

ሰይጣን ወደ ሰው የሚቀርበው የተጨቈኑትን ነጻ እንደሚያ ወጣ ሀይነት ተቈርቋሪ ሆኖ ነው:: ሆኖም በዚህ ውስጥ ዐላ ማው ሰዎችን በሞቱ ወጥመድ ውስጥ ለመክተት ነው::

ይህን ሀሳብ ለመግለጥ የሚረዳን በዘፍ 3፥1-8 ያለው ክፍል ነው:: በዚህ ክፍል ውስጥ ሰይጣን በእባቡ በኩል ወደ ኤደን ገነት በመምጣትና ለሴቲቱ ያልተረዳውን ለመረዳት እንደሚፈልግ በመምሰል «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዞ አልን?» ብሎ ሲጠይቃት እንመለከታለን:: ጥያቄው በውስጡ ተንኮል የተሞላበት ነበር:: ከዚህ ጥያቄ ይልቅ እግዚአብሔር ምን እንድትበሉ ፈቀደላችሁ ቢሆን ኖሮ መልስዋ ብዙ የእግ ዚአብሔርን ቸርነት የሚያሳይ ይሆን ነበር:: ምክንያቱም እግ ዚአብሔር ከዚች ዛፍ ውጭ ሁሉን እንዲበሉ ፈቅዶላቸው ነበር:: በዚህ ውስጥም እርሱ ለሰው ልጆች ያደረገው ቸርነቱ ይተረክ ነበር:: ስለዚህ «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዞአልን?» በማለት የወጥመድ መረቡን ዘረጋ:: የዚህ ጥያቄ ዐላማ ያልገባውን ጠይቆ ለመረዳት ሳይሆን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የቀረበና የጠለቀ ግንኙነት (ሕብረት) እንዲ ያጡ ለማድረግ ነበር:: ሔዋንም በአካል በኩል ሊያነጋግራት ከመጣው ሰይጣን ጋር ውይይት ለማድረግ እሷነቷን ሰጠች:: በመቀጠልም ለጥያቄው እንዲህ ስትል መልስ ሰጠች:: «በገነት ካለው ዛፍ ፍሬ፣ «እግዚአብሔር አለ እንዳትሞቱ ከእርሱ አት



ብሉ አትንኩትም::» በዚህ ጊዜ እባቡ ሞትን አትሞቱም ከእ ርሷ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብ ሔርም መልካምንና ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብ ሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ አላት:: እንግዲህ በዚህ ውስጥ ቀድሞ ስትቀበለው መልካም የነበረው የእግዚአብሔር ትእዛዝ አሁን ጭቆና ያለበት ነጻነት የሚገፍ ሆኖ ታያት:: በተጨማሪ በዚህ ቦታ ሄዋን እግዚአብሔርን ርዕስ አድርጋ መነጋገር መጀ መሯን እንመለከታለን:: ይህም የሚጠቁመን በእግዚአብሔር ብርሃን ስንመላለስ ቆይተን ከምንመላለስበት ብርሃን ስንወጣ ወዲያው የብዙ ቀናትና ርቀት ያህል ከእግዚአብሔር ፈቀቅ ብለን መገኘታችን ነው:: እንግዲህ ይሄኔ ነው እባቡ ሞትን አት ሞቱም ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምና ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ እግ ዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ ሲል ለመናገር የደፈረው::

ሔዋን የተሰጣት መልስ ፍጡር ለፍጡር የሚሰጠው ነጻነት የኑሮ መመሪያ ነው:: ፍጡር ለማንነቱ ለሕይወቱ እውነተኛ ሀላማና ግብን ከራሱ ወይም ከሌላ ፍጡር ለማግኘት ቢሞክር አደጋው ይህ ነው አይባልም:: «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኀጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ በእግዚአብሔር ህግ ደስ ይለ ዋል ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል» (መዝ 1፥1-8):: ሰይጣን ለፍጡር ሁሉ ያለውን የኑሮ መመሪያ አቀረበላት በማሳት ስል ቱም፦ እናንተ የሰው ልጆች ሆይ ለራሳችሁ በራሳችሁ ኑሩ አለ:: ለራሳቸው ዐሳብ ፈቃድና ስሜት ለምኞታችሁም ጭምር ልትኖሩ ይገባችኋል፤ አምላክ የሚሆነውንና የሚያደርገውን ለመ ሆን ለማድረግም እግዚአብሔር አያስፈልግም፤ በራሳችሁ፣ ካለ እግዚአብሔር፣ እንደ አምላክ ለመሆን ትበቃላችሁ፤ ማንነታችሁ አምላክ ሊሆን እንደሚችል ዕወቁ፣ ይህንንም ምስጢር ማወቃ ችሁ እንደ እግዚአብሔር ያደርጋችኋል አላቸው::

ዛሬም ሰይጣን ለፍጡር ሁሉ ይበጃል የሚለው «በራስ ለራስ ብቁ ሆኖ መኖር» የሚል ከራሱ ያመነጨው የኑሮ መርህ አለው:: እርሱ ፍጡር በራሱ ሀሳብና ፈቃድ ለራሱ ካልኖረ ኑሮው የባርነት ነው፤ ነጻ ሊወጣም ይገባዋል ይላል:: እግዚአብሔር ፍጡራን ከአገዛዙ እንዳይወጡ በሚያደርግላቸው ነገር ያባብላል ጥቦም እየሰጠ እንዲያመልኩት ያደርጋል ባይ ነው (ኢዮ 1፥9-11፤ 2፥4-5):: እኛ ፍጡራን እንደ እግዚአብሔር ያለ ምንም አዛዥና ኀላፊ ሳይሰለጥንብን በፍጹም ነጻነት ለምን አንኖርም? አምላክ፣ አምላክ የሆነው በራሱ ሀሳብና ፈቃድ ሁሉን በማድረጉ አይደለምን? እንደ እርሱ የማንሆንበት ምን ምክንያት አለ? ሰይጣን ክብርና ባለቤትነት እግዚአብሔር እንደሚለው በመሆን የሚገኝ ሳይሆን፣ በጥረት የሚደረስበት ነው:: ስንመራመርና ስናውቅ አምላክ ሆኖ የምናየውን እንሆናለን:: ዕውቀትም ፍጡር በራሱ ጥረት የሚያገኘው ከእኔነት የሚመነጭ ቁልፍ ነው ይላል::

የሚገርመው ፍጡር በራሱ መንገድ ቢሄድ ሰይጣን አምላክ ሊሆን ነው:: በዚሁ በረከሰ ፍጡራዊ ሀሳብና ሀላማው ማርኮና አሳስቶ ሲሶ መላእክትን ከእግዚአብሔር መንግሥት አወጣቸው (ራእ 12፥4-9):: በጅራቱ መሳባቸውም የእርሱን ፈለግ መከተላቸውን ያሳያል::

ሄዋን ሰይጣን ባላት፣ በመከራት ነገር ቆማ ዐዲሱን ማንነቷን በምናቧ በአድናቆት ተመለከተች:: ፍጹም ነጻ ሰውም ለመሆን ናፈቀች:: በዚህ ጊዜ ዐዲስ ማንነት እንደሚያስገኝ ወደ ተነገራት ዛፍ አየች ዛፉንም የዕውቀትና የጥበብ ምንጭ አድርጋ ቈጠረችው ከፍሬውም ወሰደችና በላች::

ማናችንም ብንሆን እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ላይ ስንመጣ ተመሳይ ነገር ሊገጥመን ይችላል:: እግዚአብሔር ከሚኖርበት ብርሃን ወጥተን በጨለማው ሥርዐት ሥር ስንሆን የትላንትናውን የበረከት ሕይወት ማሰብ ያቅተናል:: በብርሃን ሳለን ይጥመን የነበረው መንፈሳዊ ነገር ይሸሽናል:: አልፎም ሞኝነት ይሆንብናል:: የሌለ ነገር ስናምን የኖርን የተበደልንና የተታለልን ይመስለናል:: ምን ጊዜም ወደ ውሳኔ የሚያደርሰን ሀሳብ ምኞትና ምርጫ ከየት አቅጣጫ በምን ዐይነት ግንኙነት የት ላይ ቆመን በምን መነፅር ተመልክተንም እንደ ደረስን መመርመር ይኖርብናል:: በኀጢአተኞች መንገድ ላይ ቆመን በወንበራቸው ተቀምጠን በመነፅራቸው የምናየውና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሕብረት ጠብቀን እያለን የምንረዳው መረዳት ትልቅ ልዩነት አለው::

እግዚአብሔር ለአዳም «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» ብሎ ሲያዘው በምድር ላይ ከሰጠው ነገሮች ውስጥ የአንድ ዛፍ ድርሻ እንደሌለው ለማሳወቅ ነው:: አዳም ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ ከመጠበቅ ይልቅ ለእግዚአብሔር አንድም ዛፍ መቅረት የለበትም ሲል ወስዶ በላ:: ሰይጣንም በእባቡ በኩል መጥቶ ለሴቲቱ «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዞአልን?» ብሎ ሲጠይቃት ጥያቄው የእግዚአብሔር ቸርነት ታይቶ ምሥጋና ከሚበዛ ይልቅ ንፉግ እንደ ሆነ ለማሳየትና መራራቅን ለመፍጠር ነው:: ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር የሰጠን ብዙ ነገር ነው:: ስናስብ ግን ስንት ነገር የጎደለን መስሎ ይታየናል ሰይጣን ሁል ጊዜ ራሱን እንደ አዛኝ አድርጎ ወደ እኛ ሲመጣ ይዞት የሚመጣው የመጀመሪያው ጥያቄ እግዚአብሔር ምን ያጎደለብህ ነገር አለ? የሚለውን ነው:: እርሱ ፈታኝ ስለ ሆነ ለአንዱ በትምህርት፣ ለአንዱ በገንዘብ፣ ለአንዱ በሥልጣን ጉዳይ ለሌላው ደግሞ በጤናነክ ጉዳይ ጥያቄ ይዞ ይመጣል:: ከዚያም ያ ነገር ካልተከናወነልን 'አባት ማለት ይህ ነው?' 'አምላክ ማለትስ ይህ ነው?' 'የምታመልከውና የምታገለግለውስ እንዲህ ዐይነቱን አምላክ ነው?'

ይለናል። በዚህን ጊዜ ማጕረምረም እንጀምራለን። ማጕረምረም ማለት የእግዚአብሔርን ቸርነት አለማየት ማለት ነው። በመሠረቱ እኛ ብዙ የተቸረን ነን፤ ሆኖም የጎደለብንን ነገር ስና ስብ ግን በተቸረን ነገር ላይ ግርዶሽ ይፈጠራል፤ ሆድ ይብሰናል። ይሆን እንጂ ካስተዋልነው ማንኛውም እኛ ዘንድ ያለው ነገር እግዚአብሔር የሰጠን እንጂ የእኛ አይደለም። እጃችን፣ እግራችን ሁለንተናችን ከእርሱ የተቀበልነው ነው። የእግዚአብሔር ቃል አንተ የምትመካ ስለ ምንድን ነው? ያልተቀበልከው ምን አለ? የተቀበልክ ከሆነስ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ለምንድን ነው? ይላል (1ቆሮ 4፥7) ብዙ ጊዜ ነገሮች የእኛ ሲሆኑ ጠባቂዎች እንሆናለን። ነገር ግን የእርሱ እንደ ሆነ ህውቀን ጥበቃችንን ስንተው እርሱ ያለንን ነገር የንብረቶቻችን ጠባቂ ይሆናል።

### ለ) ሐሰትን ከእውነት ጋር በመደባለቅ

ሰይጣን እውነትን ከሐሰት ጋር በመደባለቅ ይቀርበናል። ዘፍ ምዕራፍ 3 ላይ ስንመለከት «እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበር። ሴቲቱንም በእውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዚልን? አላት። ሴቲቱም ለእ ባቡ አለችው በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን። ነገር ግን በገነቱ መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር አለ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፣ ሞትን አትሞቱም ከእሷ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካሙና ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ» (ዘፍ3፥1-5)።

በዚህ ክፍል ውስጥ ሰይጣን ወደ ሴቲቱ ሲመጣ የተናገራት ነገር ሙሉ በሙሉ ሙልጭ (ሽምጥ) ውሸት አይደለም። ሞትን አትሞቱም ያለው ውሸት ሲሆን፣ እንደ እግዚአብሔር መልካሙንና



ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ ያለው ግን እውነት ነው። ምክንያቱም በምዕራፍ 3፥22 ላይ እግዚአብሔር ራሱ «እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» ብሏል። እርሱ አዳምና ሔዋንን በሞት የነገሠባቸው አትሞቱም ብሎ ነው። ዛሬም ቢሆን አትሞቱም ብሎ በሰዎች ላይ በሞት ለመንገሥ ሞትን ደብቆ የምሥራች ብሎ የሚሰብክ ነው። እርሱ ሰው እስከሞተለትና ከሕይወት እስከተቋረጠለት ድረስ በምንም ዐይነት ዕውቀት ቢራቀቅ ጕዳዩ አይደለም።

በ2ቆሮ 2፥17 ላይ ጳውሎስ *«የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እን ደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና። በቅንነት ግን ከእ ግዚአብሔር እንደተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን።»*

እዚህ ጋ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ነገር ለማጨለም በሚሆን መልኩ ሲቀርብ ነው የምናየው። የመናፍቅ ትምህርት (Heresy) እን ደዚሁ ውሸትን ከእውነት የሚደባልቅ ነው። መናፍቅ የሚባለው ከግዕዝ የመጣ ነው። ነፈቀ (ናፈቀ) ማለት ከፈለ ማለት ነው፤ ግማሹን እውነት ግማሹን ውሸት አደረገ ማለት ነው። ስልቱ በመደባለቅ ነው።

ብዙ ጊዜ እኛ የምንሳሳትበት ነገር ቁንጽል እውነት የሆነ ነገር ካየን ያችኑ ይዘን «ይህ እውነት አለ አይደለም እንዴ? ይኽ ካለ ታዲያ ምን ልትለው ነው?» በማለት እውነቱንም ሐሰቱንም አንድ ላይ ጠቅልለን እውነት አድርገን እንድንወስድ እንገፋፋለን። በዚህና በዚያ ምክንያት ውሸቱንም አግበስብሰን ለመውሰድ እንፈተናለን። ትንሽ ልክ የሆነ እንደ ምልክት ስናይ ሌላው ግን አጥፊ የሆነ የተሰወረ መርዝም ቢኖርበት በተለይም ለህሳባችን፣ ለፍላጎታችን፣ ለጊዜው ሁኔታችን የሚመች ከመሰለን አጥፊ

ውንም አብረን የምንወስድ እንሆናለን::

የሰይጣን ዐላማ እውነትና ሐሰትን በመደባለቅና በተደባለቀው ውስጥ መልካም የሚመስለውን፣ ልክ የሚመስለውን ግን ልክ ያል ሆነውን አብረን እንድናስተናግድ ነው:: አይሆንም ላለማለት እጃችን፣ ዐሳባችን፣ ልቡናችን እንዲታሠር በጕጕታችን እንዲ ሸፈን በማድረግ በዚህ መልክ ይቀርባል::

ሐ) በማባበል ስልት (ገላ 5፥7፤ ቈላ 2፥4፤ ማቴ 4፥8-9)

ቀደም ብለን ሰይጣን ሐሰትን ከእውነት ጋር በመደባለቅ በመ ሸቃቀጥ ስልት የእግዚአብሔርን መንግሥት መስፋፋትና የእ ግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚያጠቃ ተመልክተናል:: ከዚህ ጋር በማያያዝ ደግሞ በማባበል ስልት እንዴት እንደሚያስት እንመ ለከታለን:: ማባበል ማለት መደለል ሰዎች የሚጓጉለትን በመ ስጠት ወይም እንደሚያገኙት ተስፋ በመስጠትና ከዚያም በኋላ ተገዥ እንዲሆኑ ማድረግ ማለት ነው:: ልጆች በነበርንበት ጊዜ በሆነ ነገር ካለቀስን ዝም እንድንል ቤተሰቦቻችን ብስኩት ወይም ከረሜላ እንገዛልሃለን ብለው ያባብሉን ነበር:: ወይም ደግሞ አንድ ቦታ ሊልኩን ሲፈልጉ እዚህ ቦታ ሂድልኝ ስትመጣ ይህ ንን አደርግልሃለሁ ይሉን ነበር:: ልክ እንዲሁ ሰይጣንም በሥ ጋዊ ፍላጎቶቻችን ያባብለናል:: ለማባበልም ወደ እኛ ሲመጣ፣ ይድረስ ለሥጋ ፍላጎት፣ ይድረስ ለክብር ፍላጎት፣ ይድረስ ለጤና ፍላጎት እያለ ነው:: ይህንን በማሳየት ወደ ራሱ መን ገድ ያስገባናል::

ለሰይጣን የማይታለሉ (የማይባበሉ) ዓለምን ወይም በዓለም ያለ ውን የማይራቡና የማይጠሙ ናቸው:: ዓለምን የሚጠሙና የሚ ራቡ ግን ይታለላሉ (ይባበላሉ)፣ በወጥመዱም ውስጥ ይገባሉ:: አስቀድመን እንዳልን የሚያስፈልጋቸውን ከእግዚአብሔር እንጂ ከዓለም የማይቃኙ ግን ከሰይጣን ማባበያ ያመልጣሉ:: ሰይጣን



ሰዎችን የሚጠብሳቸው ሥጋዊ ፍላጎታቸውን እንደ መጥበሻ እጀታ ተጠቅሞ ነው:: እኛም ይህ ነገር እንዳይደርስብን ሥጋዊ ፍላጎቶቻችንን በመንፈሱ ኀይል እንቈጣጠር:: ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን የዓለምንም መንግሥታት ከነክብራቸው አሳይቶት ወድ ቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ ብሎ ሲፈትነው የተጠቀመበት ስልት የማባበል ነው::

ሰይጣንን ድል የሚነሱት እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው የማይሳሱ ናቸው (ራእ 12፥10-11):: የሰይጣን መሣሪያው፣ በባ ርነት መግዣው የሞት ፍርሃት ነውና፤ ሞትን የናቁ የሚይዛቸ ውን ኀይል (ምድራዊ) ጠረማምሰው የሚወጡ ናቸው :: ከነገ ወዲያ የሚሞት ሰው ነገ ቢሞት፣ ብርቁና ድንቁ ምንድን ነው? ከጊዜ ተራምዶ በጊዜ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እዚህ ሆኖ ማየት የሚችልና ለአንድ ቀን ተጨማሪ ዕድሜ የማይታለል ሰው ሰይ ጣንን ድል ይነሣል:: ከዚህ ይልቅ ነፍሱን ጣዖት የሚያደርግ ግን ድል ይደረጋል፣ ይሸነፋል (ዕብ 2፥14-15):: ሰይጣን ነፍሱን ጣዖት ያደረገን ሰው አይፈራም:: ለምድራዊ ነገር የሚጓጉና የሚሸነፉ ትንም ይገዛቸዋል፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው የማይሳ ሱት ግን ታሪክ ይለውጣሉ::

መ) መልካም ስም በመሰየም ስልት (2ቆሮ 11፥4፤ ዘሁ 32፥3-7፤ 2ዜና 18፥23፤ ራእ2፥2:9፤ 3፥9)

ወላጆቻችን፣ "መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ" እንዲሉ ሰይጣንም ከማሳቻ ስልቶቹ ውስጥ አንዱ መልካም ስም በመስጠት ስልት ነው:: እርሱ ሰዎችን ለማሣት በእግዚአብሔርና በእኛ ዘንድ ሀይ ነተኛ ስፍራ የምንሰጣቸውን የነገሮችን ስያሜ ይጠቀምባቸዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ ኢየሱስ፣ ወንጌል፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ክርስቶስ፣ ሐዋርያት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር ማኅበ ርና የእግዚአብሔር በዓል የሚሉት ናቸው:: እነዚህን ነገሮች

ወስዶ በሐሰት አሠራሩ ላይ በመለጠፍ የተለጠፈበትን እንድን
ቀበል ያደርጋል:: በመጨረሻ ላይ ግን ውስጡ ተከፍቶ ሲታይ
ልዩ ኢየሱስ፣ ልዩ መንፈስ፣ ልዩ ወንጌል፣ ልዩ ሐዋርያ የሚል
ይሆናል::

ሰይጣን ክርስቶስ፣ ኢየሱስ ተብሎ እንዲሰበክ ያደርጋል:: ውስጡ
ተከፍቶ ሲታይ ግን በመስቀል ላይ የተሰቀለው እጆቹና እግሮቹ
የተቸነከሩት የናዝሬቱ ኢየሱስ ወይም የተሰቀለው ክርስቶስ
ሳይሆን፣ ልዩ ኢየሱስ፣ ልዩ ክርስቶስ ይሆናል (2ቆሮ 11፥4፤ ዮሐ
20፥24):: ይህም ብቻ አይደለም ሰዎችን ኀይል ኀይል ያሰኛል::
ነገር ግን ውስጡ ተከፍቶ ሲታይ ልዩ መንፈስ ወይም ኀይል
ነው (2ቆሮ11፥4):: ለእኛ ግን የተሰጠን መንፈስ የእውነት መን
ፈስ፣ የቅድስና መንፈስ ነው (ዮሐ 16፥13):: ይኽ መንፈስ ኀይ
ልን ይሰጠናል:: በተጨማሪም ኀይል ስላለው ከበሽታችን እንድ
ንፈወስ፣ አጋንንቶችም ከሰው ሕይወት ለቀው እንዲወጡ ያደር
ጋል:: ያለዚህ መንፈስ ቤተ ክርስቲያን አቅመቢስና ደካማ፣
ሕይወት አልባም ናት:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ኀይል ተገ
ለጠ እየተባለ ኀጢአትና ዓለማዊነት ከናኘ፣ የክፉ ኀይል እንዳ
ይሆን መመርመር ያስፈልጋል (1ተሰ5፥19):: ወንጌልንም በተ
መለከተ ልዩ ወንጌል እንዳይሰበክልን መጠንቀቅ ያስፈልገናል
(2ቆሮ 11፥4፤ ገላ 1፥6):: ይህም ብቻ አይደለም ሐዋርያት ሳይ
ሆኑ፣ ሐዋርያት ነን ባዮችንም በመሰየም (ራእ 2፥2) የእግዚአ
ብሔርን መንግሥት መስፋፋት ይገታል፤ ዘማዊቷን ቤተ ክር
ስቲያን ያስፋፋል::

ሰይጣን የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ለመቋ
ቋም ሐሰተኛ አሠራሮችን መልካም ስም በመስጠት እንደ ቫይ
ረስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሳድራል:: ብዙ ጊዜ በዚህ ቫይ
ረስ የሚለከፉ ዓለማዊና ሥጋዊ መሻት ያላቸው ናቸው:: እነዚህ
ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሰይጣን መሣሪያ ይሆናሉ::



ቫይረሳቸውንም የሚያስራጩት ሁኔታ ሲመቻቸው ነው:: እንደ
ጳውሎስ በጸጋ የተሞላ ሰው ካለ ግን ሁኔታው እስኪመቻችላ
ቸው ያደባሉ:: ግን እርሱ ዘወር ሲል ይፈላሉ፣ ይወጣሉ:: ጳው
ሎስ ከኤፌሶን ከሄደ በኋላ የሆነው ይሂ ነው (ሐዋ 20፥29-30)::
ይሁን እንጂ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ነገር እጅ አል
ሰጠችም ነበር:: ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ይቺን ቤተ ክርስቲ
ያን ሲገመግም፦ ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተ
ኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ ብሏልና:: ኤፌሶናውያ
ኑን እውነትን ይዘዋል ይሁን እንጂ የቀደመውን ፍቅራቸውን
ግን ጥለዋል:: ጌታ ግን የፈለገው እውነትን ከፍቅር ጋር እንዲ
ይዙ ስለ ነበር ንስሓ ግቡ አላቸው::

ሐኪሞች በሰውነታችን ውስጥ ለበሽታ የሚዳርጉ ብዙ ቫይረሶች
እንዳሉ ይናገራሉ:: ሆኖም እኛን ለመጣል ግን ወቅት ይጠብ
ቃሉ፤ በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ ሳንወስድ ስንቀርና ሰውነታ
ችን ሲደክም የዚያን ጊዜ ይነሡና ይሰለጥኑብናል፤ ይሁን እንጂ
ሰውነታችን ጤነኛ በሚሆንበት ጊዜ ግን ዐቅም አይኖራቸውም፤
በቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው:: ቤተ ክርስቲያን በቃሉ እው
ነት፣ በስሙ ሥልጣንና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ስትመራ ሰይ
ጣን ኀይል አይኖረውም:: ነገር ግን ከዚህ ሽርትት ተብሎ መድ
ረኩን የሥጋ ነገር ሲቈጣጠረው በተጨማሪም በበደለን ወንድ
ማችን ላይ ባለን ጥላቻ ልባችን ተመርዞ ይቅርታ ስናጣ፣ የዚ
ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ኀይል ያገኛል (ኤፌ 4፥26)::

በዘፀ 32፥1-7 ባለው ክፍል ላይ ስንመለከት የእግዚአብሔር ሥራ
ለጣዖት ሲሰጥ እናያለን:: ይህ ነገር ሲሆን ሙሴ የእግዚአብሔር
ሕግ የተጻፈበትን ጽላት ሊያመጣ ወደ ተራራው ወጥቶ ነበር::
በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ወደ አሮን መጥተው «ይህ ከግብፅ ምድር
ያወጣን ሰው ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን
የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት::» አሮንም ለጥያቄያቸው

ምላሽ ለመስጠት በጆሮዎቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብ ስበው እንዲያመጡለት ጠየቀ:: ሲያመጡለትም የወርቅ ጥጃ ሠራላቸው:: አሮንም ጥጃውን ባየው ጊዜ መሠዊያን በፊቱ ሠራ፤ በመጨረሻም ነገ የእግዚአብሔር በዓል ነው ሲል ሀወጀ:: በነጋ ውም ማልደው ተነሥተው የሚቃጠል መሥዋዕት ሠዉ፤ የደ ህንነትም መሥዋዕት አቀረቡ:: ሕዝቡም ሊበሉና ሊጠጡ ተቀ መጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ:: በዚህ ቦታ የቀረበው መሥዋዕት ለእ ግዚአብሔር የሚቀርበው መሥዋዕት ዐይነት ይሁን እንጂ፣ እንደ አውነቱ ግን የቀረበው የእግዚአብሔርን ቦታ ለያዘ ለጥጃ ጣዖት ነበር:: በዚህ መሀል አንዱ ተነሥቶ በውኑ ይኸ የእግዚአብሔር በዓል ነውን? ተነሡ ንስሐ ግቡ ቢል ወዮለት:: ምክንያቱም ዘፈ ኑና ጭፈራው፣ መብሉና መጠጡ፣ ለሥጋ የሚመቸው ነገር ሁሉ ሊበላሽ ነው:: እግዚአብሔር ግን ለሙሴ «ከግብፅ ምድር ያወ ጣኸው ሕዝብህ ኀጢአት ሠርተዋል፤ ሂድ ውረድ ካዘዝኋቸው መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ፤ ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል ለራ ሳቸው አደረጉ፤ ሰገዱለትም እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አሉ» ሲል ተናገረ:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች አሜን ብለው በቀላሉ እንዲቀበሉት፣ የጣዖት በዓልን፣ መል ካም ስም በመስጠት የእግዚአብሔር በዓል ነው ለማለት ይቻላል:: በዚህ ቦታ ላይ አደናጋሪውና አደገኛው ነገር በምሰባኩ (በመድረኩ) ላይ ታላቁ ካህን አሮን መኖሩ ነው:: ዋናው ሲስት ሕዝቡም በቀላሉ አብሮ ይስታል:: አሮን እንደ ተቀበለው ኀላፊነት ጥያቄያ ቸውን እንደሰማ ሃይ ማለት ሲገባው እንዲያውም ወርቃቸውን ሰጥተውት ጥጃውን እንዲሠራ አበረታታቸው:: ዛሬም ቢሆን ሰይ ጣን እንዲህ ዐይነት ለእውነት ጸንተው የማይቆሙ፣ ለዝና የሚ ያድሩ፣ ጊዜያዊ መታጀብ የሚያሳሳቸው መሪዎችን ከጨለማው ጋር አመሳስሎ በመሥራት ተጠቅሞ ያስትባቸዋል::



ሠ) በብርሃን መልአክ መልክ በመገለጥ ስልት

ብዙ ጊዜ በአስተሳሰባችን ሰይጣን ወደ እኛ የሚመጣው ጨለማ ለብሶ፣ ቀንዳምና ጥፍራም ሆኖ ይመስለናል:: ነገር ግን እርሱ በተለይም ለማሳት እንደዚህ ሆኖ እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም:: እርሱ እንደ ብርሃን መልአክ ራሱን ለውጦ ይቀ ርባል (2ቆሮ 11፥14) እርሱ ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ ሁኔታ ማስተዋል እንዳለው በ2ቆሮ 11፥3 ተገልጾ እናያለን::

ቀደም ብለን ሰይጣን እኛ እንደምንገምተው ዐይነት መልክ እን ደሌለው አንስተናል፤ እንዲያውም እርሱ ከመውደቁ በፊት ውብ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ሕዝ 28፥12):: ከወደቀም በኋላ ቢሆን ሰዎችን ለማሣት ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ እንደሚለውጥ በ2ቆሮ 12፥13-14 ባለው ክፍል ተጽፎ እናገኛለን:: እርሱ ምንጊዜም ለማሣት ሲነሣ ራሱንና ሥራውን ከእውነተ ኛው ነገር ጋር ያመሳስላል:: ከእግዚአብሔር ዘንድም ኩልል ያለ ቃል ከመጣና ያ ቃል ከተነገረ በሚቀጥለው ጊዜ በዚያ ቃል ላይ ይነሣል:: አንዳንዴም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ ሰባኪ ይሆናል:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4፥1-11 ያለው ክፍል ነው::

ሰይጣን ኢየሱስን ወደ ቅድስት ከተማ ወስዶ በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ «መልአክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህም ከቶ አይሰና ከልም በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ወደ ታች ራስህን ወርውር» በማለት ሲቀርበው የብርሃን መልአክነትን ስልት ተጠቅሞ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ ወስዶት ሳለ፣ እርሱ ግን ከምድረ በዳ ወደ ቅድስት ከተማ መውሰዱ፣ ወደ ቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ማውጣቱና ቃሉን መጥቀሱ መልካም መንፈሳዊ አቋም እንዳለው የሚያስመስለው ነው:: ይህም የሚያሳየን አንድን ጥቅስ ከአውደ ምንባቡ ዘንጥሎ

በማውጣት አጣሞ በመተርጐም የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንድ ንጥስ ወይም እንድንስት የሚያደርግ መሆኑን ነው።

በማቴ 24፥24-25 *"ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ። እነሆ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።"* የመጨረሻው ዘመን አንዱ ምልክት የማሳት ሥራ እና አሠራር እየጐላና እያደገ ኀይልም እያገኘ መሄድ ነው።

እነዚህ የተመረጡ እንኳን ሊያመልጡ የሚችሉት በመጠንቀቅ ነው። ጌታ ኢየሱስ እዚህ ጋ ደግሞ አበክሮ ሲናገር «እነሆ አስቀድሜ ነገርኳችሁ አንግዳ አይሁንባችሁ። ስለዚህ ታምራት፣ ምልክት፣ ድንቅ ማየት ልክ እንዳልተጠበቀ ነገር አይሁንባችሁ ነው የሚለው።

በማቴ 7፥15-20 *"በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ከእሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል። ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም። ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህ ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ።"* ይላል። ይሀ አይመችንም። ወዲያው ብናውቅ ነው ደስ የሚለን እዛው በዛው ለማወቅ መናፍስትን የመለየት ጸጋ ይጠይቃል።

ሌላው የምናውቅበት መንገድ ግን ፍሬአቸውን በማየት ነው። ፍሬ ደግሞ ጊዜ ይጠይቃል። የአገልጋይን ሕይወት ማየት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በሩቁ ብቻ ሳይሆን ጠጋ ብሎ ሕይወታቸውን መመልከት አስፈላጊ ነው። *"ከእሾህ ቁጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ*



*ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል"* ቍጥር 21 ላይ *«በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም»* ይላል።

እዚህ ዋና ነገር አድርጐ የሚያቀርበው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግን ነው። በጣም ዋና ነገርና ሊሰመርበት የሚገባ ነገር ነው። «የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት አይገባም» ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ጌታ ማለት ብዙ ሊሆን ይችላል። ብዙ 'ጌታ ሆዮች' ሊሰሙ፣ ሊደመጡ፣ ሊያስተጋቡ ይችላሉ። ነገር ግን ዋናው ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው።

በሕይወታችን እግዚአብሔርን የሚነካው የሚዳስሰው ነገር ቁጥብ ነው። ብዙዎች መባ በሚጣልበት ቋት ሲጥሉ የጌታን ልብ የነካው ያች ሁለት ሳንቲም የጣለችው መበለት ናት። ብዙዎች ሲዳስሱት የጌታ ኢየሱስን ልብ ዐሳብ የያዘችው ያች ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት ናት። ብዙ 'ጌታ ሆዮች' ሊኖሩ ይችላሉ። ከዚያ ውስጥ ስንቱ ነው ወደ ጌታ ልብ የሚደርስ? በየዕለቱ በሕይወታችን ከምንለውስ ስንቱ ነው ጌታን የሚነካው?

*"በዚያ ቀን ብዙዎች፣ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። በዚያ ጊዜ ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ·ክፉዎች ከእኔ ራቁ! ብዬ በግልጽ እነግራችዋለሁ"* (ማቴ 7፥22-23)።

ይህን እያለ ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው እንጂ የማያደርገው ለሕይወቱ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ያስገነዝበናል። ይኸ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ማምለጫ አይሆንም። በዚያን ቀን ጌታ ሆይ ይሉኛል። መግቢያ ማለፊያ አድርገው የሚያቀርቡት ማስረጃ

አድርገው የሚያቀርቡ አንዱ በስምህ ትንቢት አልተናገርንም? በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህ አንድ ሳይሆን ብዙ ታምራት አላደረግንምን? ይሉኛል:: የዚያን ጊዜ ከቶ አላወቅ ኋችሁም እላቸዋለሁ ይላል::

አላውቃችሁም አይደለም:: ቀደም ሲል ከኔ ጋር በነበራችሁ ጊዜ አውቃችሁ ነበር በኋላ ግን ወደ ኋላ ተንሸራትታችሁ እኔን ትታችሁ ሂዳችሁ የሚል አይደለም:: ቃሉ የሚለው ፈፅሞ እኔ እናንተን እውቄአችሁ አላውቅም:: በእንግሊዝኛው ላይ ከቶ አላ ወቅኋችሁም (I never knew you ) ነው የሚለው:: የኔ ምንጭ ነት የላችሁም:: እኔ አልቀበላችሁም::

በጌታ ዘንድ ሁለት ሀይነት ስፍራ ማጣት አለ:: አንዳንድ ጊዜ በመልካም ጀምሮ ወደ ስህተት መሄድና መለየት አለ:: አንዳ ንዴ ደግሞ ገና ከምንጩ፣ ያለምንም ግንኙነት ከጌታ የራቀ መሆን አለ:: 'ከቶ አላወቅኋችሁም' ይሄ ከባድ አባባል ነው:: እና ቃሉን ማክበር ፍሬ ማሳየትን ግድ የሚል ነው፤ ለኛም እን ዳንዴ ግራ ያጋባናል:: እንዴት ነው? እነኝህ አጋንንትን እንዳ ወጡ፣ ታምራትን እንዳደረጉ ያስቈጠሩ ወይም የቈጠሩም ናቸው:: ወይስ ራሳቸው ተታለዋል ወይ? እነዚህን ጥያቄዎች የሚያስነሳ ክፍል ነው::

ረ) ድንቅና ምልክትን በማድረግ ስልት

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አጭበርብሮ ከሚያስትባቸው መንገዶች አንዱ ድንቅና ምልክትን በማድረግ ስልት ነው:: በማ ቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 እንደምንመለከተው ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ ጌታ ኢየሱስ ቀርበው "ንገረን፣ ይህ መቼ ይሆ ናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?" ብለው ሲጠይቁት እርሱ ምልክትም ማስጠንቀቂያም አድርጎ የሰጣቸው መልስ፣ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ:: ብዙ ዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም



ያስታሉ" የሚለውን ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው:: በዚህ ምዕራፍ በቍጥር 24-25 "ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ነቢያት ይነሣሉ ቢቻ ላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምል ክትና ድንቅ ያሳያሉ እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ" የሚል ተጨማሪ ማስገንዘቢያ እናገኛለን::

እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ እነዚህ ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ነቢያቶች የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ ካለ በኋላ "እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ" ማለቱ የተመ ረጡት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው:: በተ ለይ በዚህ ክፍል "ተጠንቀቁ" የሚለው ቃል የሚያስገነዝበን ነገር ትንቢትም ሲነገር ሆነ ታምራትና ድንቅ ሲደረግ ምንጩ ማን ነው? ብለን እንድንጠይቅ ነው:: በአንድ መንፈሳዊ ስብሰባ ላይ የትንቢት መነገር፣ የድንቅና የታምራት መደረግ አድራ ጊው የክርስቶስ ወገን ነው፤ የተደረገውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው፤ ለማለት አያስችልም:: ምናልባት በምልክት፣ ለድንቅና ለታምራት ሆ ብሎ የሚሰለፈውን ሕዝብ ለማሳት ሊሆን ይች ላል (2ተሰ 2፥9-10፤ ራእ 13፥14)::

በመሠረቱ እግዚአብሔር የድንቅና የታምራት አምላክ ነው:: በድ ንቅና በታምራት ድኻ አይደለም:: ቅዱሳን ግን እግዚአብሔር የሚሠራው ታምራት ሳይሆን፣ ራሱን ታምር ሠሪውን እግዚአ ብሔርን መቀበል፣ መፈለግ አለባቸው:: በርግጥ ድንቅና ታምራት ሲሆን የሰው ችግር ሊፈታ ይችላል:: ሆኖም ግን በራሱ ልብን አይለውጥም:: ከእዚህ ይልቅ እኛ መጓጓት ያለብን ሰዎች ድን ቅና ታምራት ካዩ በኋላ ልባቸውን ለእግዚኢብሔር ከፍተው ይህ እግዚአብሔር የሚባለው አምላክ እውን ነው እንዴ? ሕያው ነው እንዴ? እንዲሉና ከዚያም ቀጥሎ ሕይወታቸው ከእርሱ ጋር እንዲጣበቅ መሆን አለበት:: ይህ ምልክት የሚለው ቃል የሚያመለክት ማለት እንጂ በራሱ ፍጻሜ አለው ማለት አይደ

ለም። ለምሳሌ በአንድ መንገድ ላይ የእገሌ ቤተ ክርስቲያን የሚል ተጽፎ ብናይ፣ ያ የተጻፈው ጽሑፍ ያመለክታል እንጂ በራሱ ቤተ ክርስቲያን አይደለም። ልክ እንዲሁ ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የሚደረጉ ምልክቶች ወደ እግዚአብሔር እስካላመለከቱ ድረስ ሰርከስ ብቻ ሆነው ነው የሚቀሩት። ወዲያውኑም ሊረሱ ይችላሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በድንቅና በታምራት የተንበሸበሸ የእስራኤል ሕዝብ ነው። ይህ ሕዝብ በግብፅ ምድር ታምራታዊ መቅሰፍቶች ሲወርዱ፣ ዘፀ 14 መራራው ውሃ ጣፋጭ ሲሆን፣ ከዐለት ውስጥ ውሃ ሲፈልቅና ከዚያም በላይ መና ከሰማይ ሲዘንብ አይቶአል። ግን መልሶ ተጠራጣሪና ጣዖት አምላኪ ሕዝብ ሆነ (ዘፀ 15፥22-26፤ 16፥4፤17፥4፤ 32፥1-35)። ምን ጊዜም ድንቅና ምልክት ተመልካች ሕዝብ አይጠግብም። ለምሳሌ ዜና የሚሰማ ሰው ዛሬ ዜና ሰምቶ ከሆነ ነገ ደግሞ ምን አለ ብሎ ሬዲዮን እና ቴሌቪዥን ይከፍታል። ምልክትንና ድንቅንም የሚራብ ሰው እንዲሁ ነው። በ1ቆሮ 1፥22 ላይ *"አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ የግሪክ ሰዎች ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን"* ይላል። ሐዋርያው በዚህ ክፍል ላይ ሊለው የፈለገው፣ የእኛ መጨረሻ ምልክት ሳይሆን፣ የመስቀሉ ቃል ነው የሚለውን ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀልን ያላማከለ ድንቅና ምልክት በአሜንና በሃሌ ሉያ ቀኋጥቋጠ ታጅቦ ቢገለጥ የክርስቶስ ወንጌል አይደለም። ሰይጣን በድንቅና በምልክት ብንቆይ ጉዳዩ አይደለም። እግዚአብሔር ግን ከዚያ በላይ ዐልፈን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንድናውቅ ይፈልጋል። የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚጋርድ ወይም በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ጥላ የሚያጠላ ታምራትና ድንቅ ሊፈተሽ ይገባዋል። መንፈስ ቅዱስ ሥራ በሚባልበት መንፈሳዊ ስብሰባዎች ላይ የሚሆኑ ታምራትና ድንቅ፣ በመስቀሉ ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን ሸፍ



ነው ራሳቸውን የሚያጎሉ እንዳይሆን ልብ መባል አለበት። እነዚህ ክስተቶች የአማኞችን ትኩረት ከኢየሱስና ከመስቀሉ ሥራ የሚያርቅ መሆን የለበትም። እንዲህ ከሆነ አትራፊው ሰይጣን እንጂ ቤተ ክርስቲያን አትሆንም።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ የተገለጠው ሕዝብ ኢየሱስ ታምራት አድርጎ ከመገበው በኋላ፣ እንደ ገና ፈልገውት ምን ታምር ታደርጋለህ ብለው ይጠይቁት ነበር። ከቍጥር 24-31 ያ ያዩት ታምራት በእርሱ እንዲያምኑ አልረዳቸውም። እንዲያውም በእርሱ እንዲያምኑ ጌታ ሲጠይቃቸው፣ ሌላ ምልክት አድርግና ይሉት ነበር። የእስራኤል ሕዝብ መና በመካከላቸው እየወረደ ነው ጣዖት ሊያመልኩ የተነሡት (ዘፀ 32፥1-35)። እስራኤላውያን በመካከላቸው የእግዚአብሔር ታምራት እየሆነ ሳለ ለጥጃ እንዲሰግዱ ያነሣሣቸው የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም። ሰይጣን አንዱና ትልቁ የማሳቻ ስልቱ ታምራትና ድንቅ በማድረግ ነው። እኛም ልባችን ሙሉ በሙሉ በዚህ ላይ የሚወድቅ ከሆነ በቀላሉ ሊያስተን ይችላል። እርሱ በፍጻሜው ዓለምን የሚያስተው በድንቅና በምልክት ነው( 2ተሰ2፥9-10፤ ራእ 13፥3-4፤14)። አሁንም ቀደም ብለን እንዳየነው በሰይጣን እንዳንታለል አንድ ታምራት ሲሆን፣ የዚህ ታምራት ወይም ትንቢት ምንጩ ማን ነው ብለን መጠየቅ አለብን (1ተሰ5፥19፤ 1ዮሐ4፥1-2)።

ታምራትን ስንሻ የእግዚአብሔርን መንግሥት መስፋፋት እየናፈቅን መሆን አለበት። ጌታ ኢየሱስ ብዙውን ታምራት ያደረገባቸው ከተሞች ንስሓ ባለመግባታቸው ወቅሷቸዋል። ከዚህም የምንረዳው የታምራት መታየት ግቡ ሰዎችን ለንስሓ ማብቃቱ ላይ ነው። በወንጌል ስርጭት የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስፋፋት አኳያ ታምራት መናፈቅ ያለበት በትንግርት መታየቱ ላይ ሳይሆን፣ ሰዎች ለንስሓ መብቃታቸው ላይ ነው።

*"ወዮልሽ፥ ኮራዚን፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሓ በገቡ ነበር:: ስለዚህ እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀልላቸዋል:: አንቺ ቅፍርናሆም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት ፈለግሽ? ነገር ግን ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ታምራት በሰዶም ቢደረግ ኖሮ፣ እስከ ዛሬ በቆየች ነበር"* (ማቴ 11፥21-24)::

ሰ) በማስፈራራት

ሰይጣን ሰዎችን በተለያየ የችግር ቀንበር ይከብብና ስለ ሕይወት፣ ስለ ራስ፣ የወደፊቱን እያሰቡ እንዲጨነቁ ያደርጋል:: ከዚያ በኋላ እንዲህ ብታደርግና እንዲህ ብትሆን ደግሞ ከዚህ ችግር ታመልጣለህ በማለት የመፍትሔ ሀሳብን በመሰንዘር ወደ ራሱ ክልል የማስገቢያ ስልቱን ይዘረጋል:: በመጨረሻም ሰዎችን በዚህ ያጠምዳል:: ለምሳሌ ራእ 13፥14-17 ባለው ክፍል ስለ አውሬው ቍጥር ተጽፎ እናገኛለን:: ይህ ቍጥር የሌለው ማንም መሸጥም መለወጥም አይችልም:: የግድ እንዲሸጥና እንዲለውጥ ካስፈለገ ይህን ቍጥር መቀበል አለበት:: ደግሞም ሰው መግዛትም መሸጥም ካልቻለ የመኖር ዕድሉ ጠባብ እየሆነ ይመጣል:: ስለዚህ ሰይጣን በሰዎች የመኖር ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ልትኖሩ ትፈልጋላችሁ? ይላል፤ ልትኖሩ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ይህን ቍጥር መቀበል አለባችሁ፤ እስካልተቀበላችሁ ድረስ ግን መግዛትም መሸጥም አትችሉም በማለት በማስፈራራትና በእንዲህ ታመልጣለህ ስልት ያስታል:: ምናልባትም የዘመናችን አካሄድ ወደ ዚሁ ያመራ ሊሆን ይችላል::

*"አንድ ቀን ቤቱ በላዩ ተዘግቶበት ወደ ነበረው ወደ መሔጣብኤል ልጅ ወደ ድልያ ልጅ ወደ ሸመያ ሄድሁ፤ እርሱም ሰዎች*



*ሊገድሉህ ይመጣሉ በርግጥም በሌሊት ሊገድሉህ ይመጣሉ በእግዚአብሔር ቤት ባለው በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንገናኝ የቤተ መቅደሱንም በሮች እንዝጋቸው አለኝ:: እኔ ግን እንደ እኔ ያለ ሰው ሸሽቶ ይደበቃል? ወይም ደግሞ ሕይወቱን ለማዳን ሲል ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ይገባዋልን? አልሄድም! አልሁ"* (ነህ 6፥10-11)::

ነህምያ በመሠረቱ በዚህ መልክ ወደ መቅደስ መግባት የሚፈቀድለት ዐይነት ሰው አይደለም:: ነገር ግን በዚህ መንገድ እንዲስት ከመስመር የወጣ አካሄድ እንዲሄድ ይመጣሉ፤ እንዳያጠቁን ወደ ቤተ መቅደስ እንግባ ብሎ ሸማያ ሀሳብ ይሰጠዋል:: ሸማያ በአገልጋይነት፣ በነቢይነት የሚታወቅ ሰው ነው?::

*"በእኔ ላይ ትንቢት የተናገረው ጦቢያና ሰንበላጥ በገንዘብ ስለ ደለሉት አንጂ፣ እግዚአብሔር ወደ እኔ እንዳልላከው ተረዳሁ"* (ነህ 6፥12):: ጥሩነቱ ይህን ማወቅ የሰጠን እግዚአብሔር ስሙ የተባረከ ይሁን:: እግዚአብሔርን መታዘዝ እንፈልጋለን፤ እግዚአብሔር የሚለውን ለማድረግ እርሱን ደስ ማሰኘት እንወዳለን:: እና በዚያም ደግሞ ክብረት እንደ ሆነ እናምናለን:: ነገር ግን ችግሩ ያ ልናደርገው ያለ ነገር በእውነት እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ ነው አይደለም ብሎ መለየቱ ላይ ነው::

ነህምያ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሰው ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል የሚያከብር ሰው ነው:: አሁን ግን እግዚአብሔር እንደላከው መስሎ የተናገረ ሸማያ ያን በተናገረበት ጊዜ ግን ነህምያ መረዳትን አገኘ:: *"በእኔ ላይ ትንቢት የተናገረው ጦቢያና ሰንበላጥ በገንዘብ ስለ ደለሉት እንጂ፣ እግዚአብሔር ወደ እኔ እንዳልላከው ተረዳሁ"*::

ምንጊዜም በትንቢት መልክ ከሚነገረን ቃል ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሠፈረው የእግዚአብሔር ቃል የከበረ መሆን አለ

በት:: ይህን መጽሐፍ የጻፈ ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ከተናገረ ይህን የተጻፈውን ቃል አይቃረንም:: ከተቃረነ ጥያቄ ማንሣት አግባብ ነው:: መልእክቱን ከመቀበል መቈጠብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው::

*በእኔ ላይ ትንቢት የተናገረው ጠቢያና ሰንባላጥ በገንዘብ ስለ ደለሉት እንጂ፣ እግዚአብሔር ወደ እኔ እንዳልላከው ተረዳሁ"::* የእግዚአብሔርን ነቢያትም በዕለት ጥቅማ ጥቅም ጕዳይ ሊገዙ ይችላሉ:: በገንዘብ ሊገዙ ለገብስ እንጀራ ቃላቸውን ሊያወላክፉ ሊያጣምሙ ይችላል:: በነቢያት መጻሕፍት ላይ እንደምናየው:-

*"በገንዘብ የተገዛው እኔን ለማስፈራራት ነው፤ ይኸውም ይህን በመፈጸም ኀጢአት እንድሠራና በዚህም መጥፎ ስም ሰጥተው ተቀባይነት እንዳይኖረኝ ለማድረግ ነው"* (ነህ 6፥13)::

የተገለጠልንን፣ የተነገረንን ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ላለማድረግ መወሰን ልብ ማግኘት ነው፤ ራሱ ትልቅ ብርሃን ነው::

*"አምላኬ ሆይ ስለ ፈጸሙት ድርጊት ጠቢያንና ሰንባላጥን ዐስብ፤ ሊያስፈራሩኝ የሞከሩትን ነቢያቱን ኖዓድያንና ሌሎቹን ነቢያትም ዐስብ"* ብሎ ይጸልያል (ነህ 6፥14)::

ሸማያ ብቻ አይደለም፤ ሌሎችም ናቸው የተሰለፉበት ነቢያት ተሰለፉ:: ይሄ የሚያስገርም ነገር ሊሆን አይገባም:: እውነተኛ ነቢያት እንዳሉ የሐሰት ነቢያት ይኖራሉ:: ለሥጋ የሚያድሩ ነቢያት ይኖራሉ:: ሰውም ዘመኑም ያው ነው:: እውነተኛ እንዳለ ሁሉ ተቀናቃኙ አሳሳቹም አለ:: እርሱ የለም ብለን ስናስብና ስናሳስብ ለመሳትና ለማሳት አንድ እርምጃ ሄደናል ማለት ነው::

በነህምያ ላይ የተሰለፉት ብዙ ነበሩ:: ሸማያ ተነስቶበታል፣ ነቢይቱ ኖአድ ተነስታበታለች:: እነዚህን ነቢያት የማይሰማ ፀረ መንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ሊባል ይችላል በዛሬ፣ በአሁኑ ቋንቋ:: ነገር ግን ሐቁ ከነህምያ ጋር ነበር::



እነርሱ የመጡበትም መንገድ አሳሳች ነበር:: ይሄን ብታደርግ ታመልጣለህ፣ ትተርፋለህ፣ ከጠላት እጅ ትድናለህ አለበለዚያ ጉዳት ይደርስብሃል አንዱ የሰይጣን የማሳቻው ስልት ነው::

ወደ ዳንኤል መጽሐፍ ስንሄድ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል እንዲሰግዱ ተጠየቁ:: በመጨረሻ አንሰግድም ባሉ ጊዜ፣ እንዲሰግዱ ያስገደዷቸው በማስፈራራት ነበር:: እነርሱ ግን አንሰግድም በማለት በእምነታቸው ጸኑ:: ሰይጣን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ሕዝብ ከሚቋቋምበት መንገድ አንዱ በማስፈራራት ወይም እሺ በማለት ከዚህ ታመልጣለህ በሚል ስልት ነው::

ዳንኤል ላይ እንደምናነበው ምስል ተዘጋጅቶ ለዚህ ምስል ያልሰገደ *"አሁንም ቢሆን የመለከቱንና የእምቢልታውን፣ የመሰንቆውንና የክራሩን፣ የበገናውንና የዋሽንቱን፣ የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ፣ እኔ ላቆምሁት የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ ለመስገድ ዝግጁ ከሆናችሁ መልካም! ባትሰግዱለት ግን ወዲያውኑ ወደሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ትጣላላችሁ፤ ታዲያ ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማን ነው?"* መባሉን እናውቃለን (ዳን 3፥15)::

ቀደም ብለው አልሰገዱም ነበር:: አሁን ሌላ እድል ተሰጥቷቸዋል:: ሕዝቡ ሁሉ በተሰበሰበበት አሁን መለከቱን ሲሰሙ እንዲሰግዱ ነው:: በትንሽ ስብሰባ እንኳ ሌሎች ሁሉ በአንድ ላይ ሲሆኑ አንድ ሁለት ሆነን ስንቀር የማይመች ሁኔታ፣ ራሱ እንደ ወላፈን ነው::

እነኚህ ሰዎች ሌላው ሲጎነበስ እነርሱ እንደ ቆሙ ቀሩ፤ ጥሩ

ነው። አሉታዊ ቃል መናገርም አልፈሩም። ያድነናል ብለው ብቻ አላቆሙም፤ ባያድነንም እንኳ ላቆምከው ምስል አንሰግድም አሉ።

በአጭሩ እዚህ ላይ ለማሳየት የተፈለገው በማስፈራራት ይሄን ባታደርጉ ይሄ ይደርስባችኋል የሚለውን ስልት ከፉው እንደ ሚጠቀምበት ነው። ይሄ አንዱ የሰይጣን ዘዴ ነው። ራእይ 13 ላይ በግንባራቸው ላይ ምልክት ያላደረጉ መግዛት መሸጥ አይ ችሉም። ነገር ግን የጻድቃን ፈተናቸው ብዙም ቢሆን ከሁሉም እግዚአብሔር ያወጣቸዋል። ሰይጣን ከጽድቅና ከእውነት ጋር ኪዳን የሌላቸውን ሰዎች በቀላሉ ያስታል። ለእውነት ዋጋ የማ ይሰጡትን ለእውነት አክብሮት የሌላቸውንና ከእውነት ጋር ኪዳን የሌላቸውን ሰዎች ያስታል። በቍጥጥሩ ሥር ያደርጋቸዋል፤ ይነዳቸዋል፤ ያስገብራቸዋል።

ብዙ ሰዎች ስለእውነት ብዙ ደንታ የላቸውም እውነት ከሆነ ጥሩ ነው። ካልሆነ ደግሞ ብትተውስ፣ ምን አስጨነቀህ የሚሉ ሞል ተዋል። ሌላው ራሳቸውና የራሳቸው ነገር ጥቅማቸውን የሚያስ ቀድሙትን በቀላሉ ያስታል። መኖሪያቸው የዘላለም አምላክ ያልሆኑትን በቀላሉ ያስታል። መኖሪያቸው ምድር የሆነውን ምድራውያንን በቀላሉ ያስታል። መሣሪያውም ራሱ ምድራዊ ስለ ሆነ ያስታል። የእግዚአብሔር ዐላማ ከነዓን የኪዳን ሕዝቡ ዋነኛ ማደሪያው እንድትሆን አይደለም። በመጀመሪያ ማደሪያው እንዲሆን የሚፈልገው የዘላለም አምላክን ነው። ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣቸውን በምድረ በዳ ከመራቸው በኋላ ትው ልድ አልፎ ሌላው ተተክቶ ከነዓንን ተስፋ ሲያደርጉ ቆይተው፣ ማርና ወተት የምታዘንበዋን አገር ተስፋ ሲያደርጉ ቆይተው፣ ዘመን ተቆጥሮ ጊዜው ደርሶ ዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ሊገቡ ሲሉ "መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው" ብሎ ተናገራቸው።



# V. ድል በሰይጣን ላይ

## 1. ጌታ ኢየሱስ ዲያብሎስን እንዴት ድል አደረገ?

*"ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ። ፈታኙም ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ አለው። ኢየሱስም፣ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል ሲል መለሰለት። ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ ቅድስት ከተማ በመውሰድ ከቤተ መቅደሱም ዐናት ላይ አውጥቶ የእግዚአብ ሔር ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና። እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል። ኢየሱስም እንደዚሁም በመጻሕፍት እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል በማለት መለሰለት። እንደ ገናም ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓለምንም መንግሥታት ከነክብራቸው አሳየውና ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰ ጥሃለሁ አለው። ኢየሱስም አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ! ለአምላ ክህ ለእግዚአብሔር ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽ ፎአልና አለው። ከዚያም ዲያብሎስ ትቶት ሄደ፤ መላእክትም መጥተው አገለገሉት"* (ማቴ 4፥1-11)።

በክርስቶስ ኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ የተከናወነ ነገር አለ። በዮሐንስ መጥምቁ እጅ ተጠምቋል። በዚያን ጊዜ ሰማይ ተከፍቶ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በእርሱ ላይ አርፏል። «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከላይ መጣ። ወደ ምድረ በዳ ተወስዶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ። ዲያብሎስ ስለ ጌታ ኢየሱስ የተነገረውን

እውነት ለመጣል ጌታ ኢየሱስ የነበረበትን ሁኔታ መጠቀሚያ ለማድረግ ፍቱን ስልት ቀይሶ ሊፈትነው ቀረበ።

ሰይጣን ሊገዳደር የመጣው የእግዚአብሔር አብን ቃል ነው። እግዚአብሔር አብ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። ሰይጣንም እንግዲያስ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ" አለው። የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አሁን አሳይ፣ አረጋግጠህ ግለፅ። ማረጋገጫውም ሥጋዊ ፍላጐቱን ለማርካት መለኮታዊ ኀይሉን ተጠቅሞ ድንጋዮን ወደ እንጀራ ለውጦ እንዲበላና ከዚህ ፍላጐቱ እንዲረካ ነው።

እርሱም መልሶ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» አለው። ባጭር መልሱ በማናቸውም ሁኔታና ወቅት የእግዚአብሔር ነገር ይቀድማል። የሥጋ ፍላጐት አንገብጋቢ በሆነበት በዚያ ቅፅበት እንኳን ከፍተኛውና የከበረውን ደረጃ የሚይዝ የእግዚአብሔር ነገር የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህን ከሕይወታችን ጋር እያዛመድን ለመሄድ ብዙ ጊዜ ይወስድብናል።

ነገር ግን በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን የእግዚአብሔር ነገር ከሥጋ ነገር ከምድራዊ ነገር የከበረና የላቀ መሆኑ እያተምን እንድንሄድ ይጠበቅብናል። ሥርዐተ እሴታችን ይሄንን እንዲያመለክት ይጠበቅብናል።

በሌላኛው ፈተና የምንገነዘበው ነገር እግዚአብሔር ከተናገረ ይህንን ማስረገጥ የእኛ ኀላፊነት አለመሆኑን ነው። ለማረጋገጥ መሄድ ራሱ ገና አልተረጋገጠም ማለት ነው። አንዳንዴ እንደ ዚያ ያለ ፈተና ሰይጣን ወደኛ ይዞ ይመጣል። እግዚአብሔር ራሱ ከተናገረ ተቀብሎ ማመን ነው እንጂ ወደ ሙከራ ጓዳ ለፍተሻ መግባት አግባብ አይደለም።



ዲያብሎስ ጌታ ኢየሱስን ሲያይ በጣም መንፈሳዊ ሆነበት። ስለዚህ ስልቱን ለወጠ። አቀራረቡ መንፈሳዊ መልክ መያዝ እንዳለበት አሰላ። የብርሃን መልአክ መልክን የመያዝ ስልት ተጠቀመ። ወደ ቅድስት ከተማ ከዚያም ወደ ቤተ መቅደስ ወሰደው፤ ከቤተ መቅደስም ወደ ቁንጮ፣ ወደ ጫፍ ወደ ከፍተኛው ስፍራ አወጣው።

መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፤ የሚገርመው ነገር ሰይጣን ደግሞ የብርሃን መልክ ይዞ ይመጣና በምድረ በዳ በጾም የደከመውን ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደው፤ አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከፋች፣ ከአትርኖስ (ፑልፒት) ጓላ ቋሚ፣ ጥቅስ አንባቢ ይሆናል። «መላእክቱን ስለአንተ ያዝልሃል እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሱሃል ተብሎ ተጽፏል።» ብሎ በእግዚአብሔር የተሰጠን ተስፋ ያነባል ወይም ይናገራል።

ይህ የቀረበው ጥቅስ ግሩም ተስፋ ቢሆንም፣ ነገር ግን ከዐውዱ ተገንጥሎ የወጣ ነው። ይህ የተጠቀሰው ከመዝ 91 ሲሆን፣ ተስፋነቱ ለችግር ጊዜ ነው እንጂ ለጀብደኝነት ወይም ለሰርከስ ትርኢት አይደለም። በችግር፣ በአደጋ ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት መጥተው ያድኑሃል እንጂ እንደ ጀብዱ እየወሰድክ ራስህን ለመፈጥፈጥ እየጣልህ ሳለ የምትጠብቀው ተስፋ አይደለም። ሰርከስ እየተለማመዱ አይደለም። ነገር ግን በአደጋ ጊዜ ሊታደጉህ መላእክት ይመጣሉ ለማለት ነው።

አለበለዚያ ግን እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። «የሚያምኑቱም እባብ ቢይዙ አይገድላቸውም» የሚለውን አንዳንድ ጓደኞቻችን ሞክረውታል። አንዳንዶችም ተጽፏል በሚል መነሻ ጥዳት ላይ የወደቁ አሉ። የሚገድል መርዝ ቢጠጡም እንኳ አይጐዳቸውም የሚለውን ይዘን ከፋርማሲ ወደ ፋርማሲ እየተዘዋ

ወርን መርዝ ብንጠጣ ዋጋችንን ከመቀበል አናመልጥም:: ይህ በርግጥ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው::

ሁለት ጊዜም "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ" እያለ ነው የተገዳ ደረው:: የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ነው ሰይ ጣን በጽኑ ጌታ ኢየሱስን የተሟገተው:: ጌታ ኢየሱስ ግን ለተ ግዳሮቱ በር አልከፈተለትም:: እግዚአብሔር ከተናገረ ተናገረ ማለት ነው:: ተመሠረተ ጸና ማለት ነው:: አሻሚ ነገር ይመ ስል የተናገረውን ለማስረገጥ ምንም ዐይነት ማረጋገጫ ከባለ ጉዳዩ የሚሻ አይደለም:: ምን ጊዜም መረጋገጥ የሚኖርበት ነገር አጠራጣሪና አጠያያቂ ጉዳይ ሲኖር ብቻ ነው:: ከእግዚአብ ሔር የበለጠ ማስረጃ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ አይኖርም:: ስለ ሆነም ለሰይጣን ፍጥጫ ጌታ ኢየሱስ አልተበገረም፤ ሰይጣን በቀደደው መንገድ ወይም መስመር ቅንጣት ያህል አልተንቀሳ ቀሰም:: እግዚአብሔር ካለ አለ ተደመደመ:: እኛ ስናመነታ ሰይጣን ቀዳዳ ያገኛል፤ አምነን ስንቆም እርሱ መንገድ ያጣል::

ሰይጣን ወደ ፊት እንዳንሄድ ከኋላ ይይዘናል፤ ወደ ኋላ ይዞ ለማስቀረት የማይችለን ከሆነ ያለው አማራጭ ወደ ፊት መገ ፍተር ነው:: ጌታ ኢየሱስን ወደ ኋላ ለመያዝ ሞክሮ አልሆን ሲለው ደግሞ አንደርድሮ ወደ ፊት ሊገፋው ሞከረ::

የሚቀጥለውን ክፍል ደግሞ ስንመለከት «ደግሞም ዲያብሎስ እጅግ ረዥም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው የዓለምንም መንግሥ ታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ» ይላል:: ይኸ በምን መልኩ እንደ ሆነ ነው የምናስበው? አካላዊ በሆነ መልኩ ወይስ በዐ ሳብ፣ በዐይነ ሕሊና፣ በምናብ ደረጃ? ይህን ጥያቄ ክፍት አደ ርገዋለሁ::

በዐሳብ ደረጃ ከሆነ፣ ሁሉንም በምናብ ወደ እርሱ አመጣበት፣ በዐሳቡም አየ፤ በዐይነ ልቡናው ላይ ቀረጸበት እንደ ማለት ነው::



ካሳየው በኋላ የፍላጎትን መነሣሣት ለመጫር ሞከረ:: ከዚያም ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ ማለት የማባበል ስልት ነው:: ብዙ ጊዜ የምንጓጓው ስናይ ነው:: ሰይጣን ልንጓጓ የምንችላቸውን ነገሮች በየትኛውም መልኩ ልናይ ወደምንችል በት ደረጃ እንድንመጣ ያደርጋል:: ከመፈተኑ በፊት ምናል ባት በዚህ በሥጋ ዐይናችን እንድናይ ወይም በዐሳብ ዐይናችን በምናባችን እንድናይ ያደርጋል:: እንደቀረጸው ከዚያ በኋላ ያ ለእኔ ይሁን እንድንል፣ መሻት፣ ጉጉት፣ መጐምጀት እንዲያ ድርብን ይቀሰቅሰናል::

የእኔ ይሁን በምንልበት ጊዜ ግን ለእኛ የሚሆንበት መንገድ ቅድመ ሁኔታ እንዳለ ይናገራል:: እዚህጋ ክብራቸውንም አሳ ይቶ «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ» ይላል:: በማባበል ስልት ሲመጣ ነው የምናየው:: ይህን ሁሉ እሰጥሃ ለሁ፤ አንተ ብቻ ወድቀህ ስገድልኝ አለው፤ አንዴ ሰግዶ በመ ሄድ ምናለበት ይህን ሁሉ ማግበስበስ ከተቻለ ምን አለበት ያሰ ኙናል:: ያን ጊዜም ኢየሱስ «ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላ ክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል» አለው::

በመጐምጀት ሰዓት፣ በምድራዊ ፍላጐት፣ በፍቅረ ሲመት፣ በፍ ቅረ ንዋይ፣ ለተድላ ደስታ በምንገባበት ሰዓት ለእግዚአብሔር ብቻ መስገድ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ ቀላል ነገር አይደ ለም:: ከባድ ነገር ነው:: በእኛም ሕይወት ቢሆን በቀደመው በእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝብም ቢሆን ለእግዚአብሔር ብቻ መስገድ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ ከባድ ነገር ሆኖ እናየ ዋለን:: የእስራኤልን ነገሥታት ብንመለከት ብዙዎቹን ቀብቶ፣ ወደ ስልጣን ላይ ካወጣቸው በኋላ፣ እግዚአብሔር ሰላምን ከሰጣቸው በኋላ፣ መንግሥታቸውን ካደላደለላቸው በኋላ ወደ ባዕድ አምልኮ ሲሄዱ እናገኛቸዋለን::

ብዙዎቹ እግዚአብሔር ነቢያቱን ልኮ፣ ትንቢት ተነግሮላቸው፣
የእግዚአብሔር ጥበብ፣ የእግዚአብሔር እጅ ከፍ አድርጋቸው፣
ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ለእግዚአብሔር የሚሆነው አምልኳ
ቸው ተበላሽቶ ለጣዖት ሲሆን፣ ለእጃቸው ሥራ ሲሆን እናያ
ለን:: ለምንድነው ብለን ብናስብ በጣም የሚያስገርም ነገር
ነው:: አንዳንዴ ስናየው ምንም ምክንያት የለም እንላለን:: ነገር
ግን ጠጋ ብለን ስንመለከተው ብዙ ምክንያቶች በስተጀርባው
ይኖራሉ:: በጥቅሉ የሞራል ግዴታ ሳይኖርባቸው በምድራዊ
ሕይወት ለመከናወን በመሻታቸው፣ በመፈለጋቸው ነው:: ስለዚህ
"ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" ተብሎ ተዕ
ፏልና:: ያን ጊዜም ዲያብሎስ ተወው:: እነሆም መላዕክት ቀር
በው ያገለግሉት ነበር» ይላል::
ያለወቅቱ መላእክትን አልተጣራም:: በዲያብሎስ ተግዳሮት አይ
ደለም መላእክትን የጠራቸው ወይም መላእክት እንዲመጡ ተስፋ
ያደረገው፤ ሆኖም ግን በጊዜው መላእክት መጥተው አገለግ
ሉት::

«ራስህን ጣል መላዕክት መጥተው በእጆቻቸው ያነሡሃል» ነበር
ያለው:: እንደዚህ ያለ ነገር ቢያደርግ የእግዚአብሔር ልጅ
ነቱን ለማሳየት ለሰይጣን ሀሳብ ራሱን አስገዝቷል ማለት ነው::
እና ነገሮች ይበላሹ ነበር:: ሰይጣንም ከዚያ በኋላ፣ የያሚላ
ጥያቄውን፣ ማስገደዱን እየቀጠለ ይሄድ ነበር::

## 2. የክርስቲያን /የአማኝ ድል በሰይጣን ላይ

ክርስቲያን "በራሱ" ዓለምን የማሸነፍም ሆነ ሰይጣንን የመቋ
ቋም ኀይል የለውም:: በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15፥1-5 ላይ
ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍሬ በማፍራት ጉዳይ
በእርሱና በአማኞች መካከል ያለውን አንድነት፣ በወይን ግንድ
መስሎት ሲናገር "*እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ አትክል*



*ተኛውም አባቴ ነው እርሱም በእኔ ያለውን የማያፈራውን ቅር
ንጫፍ ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውን ቅርንጫፍ
ሁሉ ግን የበለጠ እንዲያፈራ ይገርዘዋል:: ከነገርኋችሁ ቃል
የተነሣ አሁን ንጹሓን ናችሁ:: በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ እኖ
ራለሁ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ
ሊያፈራ አይችልም፤ እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ
አትችሉም:: እኔ የወይን ተክል ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች
ናችሁ:: ማንም በእኔ ቢኖር እኔም በእርሱ ብኖር እርሱ ብዙ
ፍሬ ያፈራል፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና::*" አለ::
ከዚህ ክፍል አጽንኦት ሰጥተን እንድናየው የምፈልገው "ያለ
እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" የሚለውን ነው:: ይህንን
ቃል ልብ ማለታችን ያለ ክርስቶስ በራሳችን አቅመ ቢሶችና
ምንም ማድረግ የማንችል መሆናችንን እንድንቀበል ያደርገ
ናል:: ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ለመደገፍ፣ ለጸሎት፣
ለልመና ያነሳሳናል:: ምክንያቱም የሚጸልይ ወይም የሚለምን
ሰው "በራሱ ምንም ማድረግ የማይችል" መሆኑን የተቀበለ ነው::
ምክንያቱም ራሱን ብቁ እንደ ሆነ የሚቈጥር ሰው ሊጸልይ፣
እግዚአብሔርን ሊለምን አይችልምና::

በርግጥ ሰዎች በጊዜ ጥበት ምክንያት ሳይጸልዩ ይችሉ ይሆናል::
ሆኖም አንድን ነገር በራሳችን እንደምናደርገው መቀበል፣ በራሴ
በቅቻለሁ የማለት አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል:: የእግዚአብሔር
ቃል እንደሚለን ግን ምንጊዜም አንበቃም:: በራሳችን ምንም
ማድረግ አንችልም፤ ከዚህ ተነሥተን ስለ ክርስቲያንም ድል
ስናስብ ድላችን የተገኘው የእኛን ብቃት በመጫን ሳይሆን፣
በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት ነው:: ሰይጣን በዚህ መስቀል
ላይ አንዴ ለዘላለም ድል ተመቶአል:: ስለዚህ እኛ ክርስቲያ
ኖች ድላችን መነሣት ያለበት ከመስቀሉ እንጂ ከራሳችን ልም

ምድና እውቀት መሆን የለበትም። በራሳችን ብቃትና ልምምድ ሰይጣንን ለማሸነፍ ብንነሣ ድል አናደርገውም።

ከብሉይ ኪዳን ዳዊትን ስንመለከት ምንም እንኳ የራሱ የሆነ የጦር ዘይቤና ልምምድ ቢኖረውም፣ ሁል ጊዜ ወደ ስልፍ ሲወጣ እግዚአብሔርን ልውጣን? ብሎ ይጠይቃል (1ሳሙ 23፥1-2፤ 30፥8፤ 2ሳሙ 2፥1)። ይህ ሰው ያለ እግዚአብሔር እንደማይሆንለትና እንደማይከናወንለት ያውቃል። ዛሬም እኛ ያለ ክርስቶስ ምንም ማድረግ አንችልም። ይህን ሁል ጊዜ ለራሳችን ማስረዳት፣ ለሌላውም መናገር አለብን። ኀይላችንም ሆነ ድላችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሌላው ክርስቲያን በራሱ ድል ማድረግ እንደማይችል አያይዘን የምናየው በሮሜ 7፥24-25 ያለውን ክፍል እንደ አብነት በመውሰድ ነው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ የሥጋውን ኀይል (የአሮጌውን ሰው ባሕርይ) ለማሸነፍ ስላልቻለ "እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" ሲል እንመለከተዋለን። ወዲያው ይህን ካለ በኋላ ግን *"በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፣ በሥጋዬ ግን ለኀጢአት ሕግ እገዛለሁ"* ሲል እንመለከተዋለን። ይህ ሰው ኀጢአትን በራሱ ለማሸነፍ የተነሣ ሰው ነበር። በኋላ ላይ ግን በውድቀት ሲሞላ፣ ካለበት የተስፋ መቍረጥና ማጣት የጨለማ ሕይወት ለመውጣት "ማን ያድነኛል" ብሎ ጮኸ፣ ተጣራ። በዚህ ጊዜ አዳኙ ኢየሱስ በድምቀት ከተፍ አለለት፤ ወዲያው ብርሃን በራለት ተስፋ ከማጣትም ቋንቋ ወደ ምስጋና ተቀለበሰ።

በአንድ ችግር ውስጥ ሆነን "ማን ያድነኛል" ብለን ስንጮኽ ወይም እኔ ከዚህ ነገር ለመውጣት ይህንን የመጣብኝን ወገን ለማሸነፍ በራሴ ኀይል የለኝም ስንል ለዘላለም አዳኝ የሆነው ጌታ እኔ



አዳኝ ነኝ ብሎ ወደ እኛ ይመጣል። ይህን ርምጃ በራሳችን እንዳንመካ ማጤን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ክርስቲያን የሚሸነፈው ድሉን ከክርስቶስ ውጪ መፈለግ ሲጀምር ነው። በዚህ ጊዜ ለከፉ ጥቃት ይጋለጣል። ነገር ግን በክርስቶስ ውስጥ ድላችን እንዳለ ሀውቀን ለማጥቃት ብንነሣ "በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" (ሮሜ 8፥37፤ 1ዮሐ4፥4፤ ፊሊ.4፥13፤ ዮሐ 16፥33፤ ገላ2፥20)። እንዲህ ከሆነ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ድል አድራጊነት መንፈስ ብርቱ ይሆናል።

**(1) የክርስቲያን የማሸነፊያ ስልቱ/ዝግጅቱ**

ስለ ስልት ስናስብ ብዙ ሰዎች አንድን ነገር በጥሩ መልኩ ለማቅረብ የሚጠቀሙበት የተለያዩ ስልቶች አሉአቸው። ለምሳሌ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾችን ብንመለከተ የሰሚዎቻቸውን ጆሮ ወደ ሙዚቃ አጨዋወታቸው ለመሳብ የተለያዩ የአጨዋወት ስልቶችን ይጠቀማሉ። በንግግሩም እንዲደመጥ የሚፈልግ ሰው የአድማጮቹን ትኩረት ለመሳብ የተለያዩ የንግግር ስልቶችን ይጠቀማል። እኛም ራሳችን በአንድ ነገር ጥሩ ውጤት እንድናመጣ ስንፈልግ የተለያዩ ስልቶችን እንጠቀማለን። ልክ እንዲሁ ወደ መንፈሳዊው ነገርም ስንመለስ የእግዚአብሔርን ቃል ጠላታችን የሆነውን ሰይጣን ለማሸነፍ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንዳለብን ይናገራል። እነርሱም፦ በያዕቆብ ምዕራፍ 4፥7-10 ባለው ክፍል የተጠቀሱት ሦስት ነገሮች ናቸው። አንደኛ፣ ራስን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ማድረግ (ማዋረድ)፤ ሁለተኛ፣ ሰይጣንን መቃወም፤ ሦስተኛ፣ ከራስ ትምክህት መራቅ ወይም ትሁት መሆን ናቸው። እነዚህ የክርስቲያን የማሸነፊያ ስልቶች ሲሆኑ ማንም ክርስቲያን ያለ እነዚህ ስልቶች ሰይጣንን ማሸነፍ አይችልም።

ሌላው ከዚህ ጋር አያይዘን የምንመለከተው ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 6፥10-18 ባለው ክፍል ላይ ከመንፈሳዊ ውጊያ ጋር

አያይዞ ዖተናገራቸውን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ነው:: በዚህ
ክፍል አማኝ መንፈሳዊ ውጊያ ከማድረጉ በፊት ስድስት ዐይ
ነት መንፈሳዊ ዕቃ ጦር መልበስ እንዳለበት ተጽፎአል:: እነዚ
ህም ስድስት መንፈሳዊ ዕቃ ጦር መከላከያና ማጥቂያ ዕቃ
ጦሮች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ:: መከላከያ የሚባሉት እው
ነት፣ ጽድቅ፣ ወንጌል፣ እምነትና የመዳን ራስ ቍር ሲሆኑ፣
ማጥቂያ ደግሞ የመንፈስ ሰይፍ ሆኖ የተመሰለው የእግዚአ
ብሔር ቃል እና ጸሎት ነው:: እነርሱንም ከዚህ በታች እንመ
ለከታለን::

(2) መከላከያ

ሀ) እውነትን መታጠቅ

*"እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ዝናር ታጥቃችሁ፣ ..."* ኤፌ. 6፥14

እውነትን መታጠቅ ማለት በቃሉ መኖር ማለት ነው:: በዮሐ
ንስ ወንጌል ምዕራፍ 8፥32 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ያመኑትን አይሁዶች "እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ
መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም ሀርነት
ያወጣችኋል አላቸው"::

ይህ ክፍል እውነት አርነት ያወጣችኋል ሳይሆን፣ ያለው እው
ነትን ታውቃላችሁ፤ እውነትም ሀርነት ያወጣችኋል ነው ያለው::
እንግዲህ እውነትን ማወቅ በልብም መያዝ አስፈላጊ ነገር ነው::
አንድ ሰው አርነት እንዲወጣ የሚረዳው እውነትን ማወቁ፣
ካወቀው እውነትም ጋር መጣበቁ ወይም ሊኖርበት ኪዳን ማድ
ረጉ ነው:: አለበለዚያ እውነት መኖሩ ብቻ በራሱ ሊረዳው
አይችልም:: ከዚህ አኳያ ለእውነት ራሳችንን መስጠት ያስፈ
ልገናል:: ሰይጣን የሚዋጋው የእውነት ሰዎች መሆናችንን
እንጂ እውነትን በአእምሮ ደረጃ ማወቃችንን አይደለም:: ስለ



ዚህ እርሱን ለመቃወም ስንነሣ ግብዝነትትንና ማስመሰልን ከላያ
ችን ላይ አውልቀን እውነትን መታጠቃችንን ወይም በቃሉ
መኖራችንን ርግጠኞች መሆን አለብን::

በውሸት የተሞላ ኑሮ እየኖሩ ሰይጣንን መቃወም አይቻልም::
እርሱ የሚፈራው የእውነት ሰዎች ስንሆን ብቻ ነው:: ስለዚህ
በሰይጣን ላይ ባለ ሙሉ ድል ለመሆን በአንደበታችንና በሀሳባ
ችን በተጨማሪም በልባችን እውነተኞችና ለእውነት የቆምን
መሆን አለብን:: ብዙ ጊዜ በእውነት ስለ መኖር ሲታሰብ እኛ
የምንመርጠው ትክክለኛ የሆነውን ሳይሆን፣ ምቹ የሆነውን
ነው:: ይህንንም ስንፈልግ መዋሸት ካስፈለገ እንዋሻለን፤ ለእው
ነት መቆም ግን በየትኛው ቦታና ጊዜ ዋጋ የሚያስከፍል ነው፤
ወይም ጊዜያዊ ጥቅምን መተው ግድ የሚል ነው:: ለጊዜአዊ
ጥቅም ነው ብዙ ጊዜ የምንዋሸው:: ይህም ጥቅም በገንዘብና
በቍሳቍስ ወይም በዝና አኳያ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ስለ
እውነት ደንታ የሌለን ሰዎች የምንሆን ከሆነ ግን ለሰይጣን
እንመቸዋለን፤ ያሸንፈናል::

በትንቢተ ዳንኤል 11፥32 ላይ ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ ሲናገር
*"ኪዳኑን የሚተላለፉትን በማታለል ያስታል፤ አምላካቸውን የሚ
ያውቁ ሕዝብ ግን ጸንተው ይቃወሙታል፤ ርምጃም ይወስዳሉ"*
ይላል:: በዚህ ቦታ ላይ ኪዳን ተብሎ የተቀመጠው የእግዚአብ
ሔር ሕግ ወይም ቃል ነው:: ሰይጣን ይህን ኪዳን የሚበድሉ
ትን ወይም የማይታዘዙትን በማታለል ያስታል:: እንደ ገናም
በ2ተሰ 2፥11-12 *"በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በሐሰት እን
ዲያምኑ የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል፤ ይህም የሚሆነው
እውነትን ያላመኑት ነገር ግን በክፋት ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ
እንዲፈረድባቸው ነው"* ተብሎ ተጽፎአል:: በ2ዜና 18 ላይም
ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን:: ሰዎች እውነትን ሲገፉ ለሰይጣን
አሠራር አልፈው ይሰጣሉ:: ማንም ሰው ሰይጣንን ለመቃወም

እውነትን ማወቅ ያወቀውን እውነት የራሱ ማድረግና በዚያም እውነት ላይ መደገፍ ይገባዋል:: ከዚህ ውጪ ክፉውን ማሸነፍ አይቻልም::

ቤተ ክርስቲያን በሐሰት ትምህርት መታወኳ የዚህ ዘመን ክስተት ብቻ አይደለም:: ከተመሠረተችበት አዲስ ኪዳን ከተጸፈበት ጊዜ አንስቶ ስትታወክ ቆይታለች:: ርግጥ በዘመኑ መጨረሻ እሳቶች ይበዛሉ:: ብዙ ሐሰተኛ ነቢያቶችና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ፣ ብሎ ጌታችን በማቴዎስ ምዕራፍ 24 እና በሉቃስ 21 ላይ ተናግሮአል፣ አስጠንቅቋልም:: እንግዲህ ጆሮ ያለው ይስማ::

የሐሰት መልእክተኞችና አስተማሪዎች በብሉይ ኪዳን ዘመንም ነበሩ:: እንዲያውም ከእውነተኛ ነቢያት ይልቅ የሚበዙት ሐሰተኛ ነቢያት ሆነው እናገኛቸዋለን::

የተሳሳተ ትምህርትን ለይቶ ማሳየት የሚስቱትንም መገሰጽ አግባብነት ያለው ነው:: ጳውሎስ የወንጌልን መሠረታዊ እውነት ባለ አደራ፣ ጠባቂ፣ ተማጣኝ ሆኖ እናየዋለን:: ሆን ብለው የሚያስቱትንም ሲዘልፍ እንመለከታለን::

*". . . የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ:: ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን::"* ገላ 1÷7-8

የሐሰት አስተማሪዎች የወንጌልን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ሳይሆን፣ ብዙውን ጊዜ የሚያደርጉት ነገር፣ ወንጌልን ጠመም ማድረግ ነው:: የተጣመመ ወንጌል፣ የወንጌል ሀሳብ ፈጽሞ የተወገደበት፣ ዱካው የማይታይበት አይደለም:: የተጣመመ ስንል ከወንጌል እውነት ላይ የተቀነሰ ወይም በወንጌል እውነት ላይ ሌላ የታከለበት ወይም ልዩ ፍቺ የተሰጠው ማለት ነው::



ጳውሎስ ይገደው የነበረው "ወንጌል በማን ተጣመመ?" ሳይሆን "ወንጌል ተጣመመ" ነበር:: በማንም ይሁን በማን ወንጌል ከተጣመመ ይገደዋል:: ያ ታላቅ ሰው፣ ያ የተከበረ ሰው፣ ያ ወዳጄ ነውና ወንጌልን ጥቂት ቢያጣምም ምንም አይደል፣ እርሱ እስ ከሆነ ድረስ ይሁን ግድ የለም የሚል አቋም አልነበረውም:: ራሱንም ቢሆን የሚያጣምም ከሆነ ይቃወማል:: የሰማይ መልአክ / ያ፣ በኀይል የተሞላ ፍጡር፣ የሚያበራ፣ የሚያንጸባርቅ፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያይ/ ቢሆንም እንኳ ምንም አይገደውም:: ሰይጣንስ እስከወደቀበት ሰዓት ፍጹም አልነበረምን? የሐዋርያው ጳውሎስ ኪዳን ከእውነት ጋር ነበር:: ለእውነትም ዋጋ ለመክፈል ምን ጊዜም ዝግጁ ነበር፤ ስለዚህም ነው *"አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም"* ያለው (ገላ1÷10)::
የእኛስ አቋም ምን ይመስላል? ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል አኳያ እንዴት እንፈትሸዋለን? ከእውነት ጋር ያለን ኪዳን ምን ያህል የጠበቀ ነው?

አንደኛው ጥያቄ እውነትን ማወቅ ከእውነት ላለመሳትም መጠንቀቅ ነው:: ሌላው ከእውነት ጋርና ለእውነት መቆም ስለ ጽድቅ መሟገት ነው:: ለእውነት ቀዋሚያን መሆን ነው::

በሕይወት ለመኖር መብላት ያስፈልገናል፣ መጠጣት ያስፈልገናል፣ አየሩም ያስፈልገናል:: ሌሎችም የሚጠቀሱ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን እነዚህ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን የምንወስዳቸውን ነገሮች ስንወስድ በምድራችን ላይ ኩልልና ጥርት ብለው አናገኛቸውም::

ከሚበላው ጋር የሚበላም ነገር አለ፤ ከሚጠጣውም ጋርም እኛንም የሚመጥ ነገር ሊኖር ይችላል:: ከምንወስደውም አየር ጋራ ምናልባት ካልተጠነቀቅን ለሕይወት ሕልፈት የሚያበቃን ምርዝ አየር አብሮ ሊገባ ስለሚችል ይህንን ከኑሮ እየተገነዘብን ስለመጣን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እናደርጋለን::

የምንጠጣውን ውሃ በተለያየ መንገድ እናጠራለን:: ወይ እናፈ ላለን፣ እናጠላለን፤ ልዩ ልዩ ኬሚካል ይጨመራል፤ ምናልባት እንደዚህ ሀይነቱን ሥራ ሌላው ክፍል ስለሚሠራልን እኛ ልብ አንለው ይሆናል:: ግን ይኸ ሁሉ እየተካሄደ ነው:: ስለምንበ ላውም ምግብ እንጠነቃቀለን:: ሕይወታችንን ማቆየት ይችላል ብለን ከምንወስደው ምግብ ጋር ሕይወትን የሚቀጭ ነገር እን ዳይኖር፣ ጤናን የሚጠናወት ነገር አብረን እንዳንወስድ፣ በም ንበላው ምግብ ላይ ጥንቃቄ እናደርጋለን::

እንዲሁም የማይሆን አየር ከወሰድን ለምሳሌ ከምንስበው አየር ውስጥ እንደ ካርቦን ሞኖክሳይድ ሀይነቱ ከገባ አደገኛ ነው እንባላለን:: እና ምርዝ (ፖሉዩትድ) አየር እንዳይኖር እንጠነ ቀቃለን::

በመንፈሳዊው መልክ ደግሞ ስንመለከት እንደዚሁ ነው:: «ዓለም በክፉ እንደተያዘች እናውቃለን» ይላል ዮሐንስ በመልዕክቱ:: እንደ ገና በራእይ ምዕራፍ 12 ላይ «ዓለም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደ መው እባብ ተጣለ:: ወደ ምድር ተጣለ፤ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» (ቍጥር 9)::

መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ እንዳለ ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ ክፉ መንፈስ ሰይጣን የክፋት መንፈሳዊ ሰራዊት ደግሞ በዙ ሪያ እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል:: ስለዚህ ይህቺ የምን ኖርባት በመንፈሳዊው ረገድ የምንመላለስበት ምድር ሁለት ሀይ ነት ክፍል የያዘች ናት፤ ቅዱሱ መንፈስና ርኩሱን መንፈስ የያዘች ናት::

ለሥጋ ሕይወት የምንወስደውን ምግብ ተጠንቅቀን እንደም ንወስድ ሁሉ ለመንፈሳዊውም ሕይወት የምንወስደውም ምግብ ተጠንቅቀን እንድንወስድ ኑሮአችን ራሱ ያስተምረናል:: መጽሐፍ ቅዱስም ደግሞ ይህንኑ ይናገራል:: «ሁሉን ፈትኑ መልካሙን



ያዙ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ::»

«ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ ፈትኑ» እንኝህና ሌሎችም አያሌ ጥቅሶችን ስንመለ ከት የጥንቃቄ ጥዞ እንድንሄድ ያሳስቡናል::

መቼም መጠንቀቅ የሚባለው ነገር አይመችንም:: እኛ የምንፈ ልገው ተዘለን መኖር፣ ያለ ሀሳብ መመላለስ ነው:: ነገር ግን እንደዚያ ሆኖ አልተገኘም፤ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ጌታ ኢየሱስም ይህንኑ ሀሳብ ለደቀ መዛሙ ርቱ ተናግሯል:: በአንድ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታ ኢየ ሱስ ይመጡና «ንገረን ይህ መቼ ይሆናል:: የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?» (ማቴ 24፥3) አሉት ይላል:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው «ማንም እንዳያስታ ችሁ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ»::

የሚያስቱ ባይመጡ ጥሩ ነበር:: ነገር ግን የነቢያት ሁሉ ነቢይ የሆነ ጌታ ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲናገር እንደ ምልክትም አድርጐ ያቀረበው ይህንኑ ነው:: ጌታ ክርስቶስ ኢየ ሱስ እንድንጠነቀቅ ያሳስበናል::

ስለዚህ ጌታችን እንደዚያ ካለ እንደ ዘበት ልንወስደው አይጠ ገባም:: ጥዳዩ አሳሳቢ ነው፤ የሕይወትና የሞት ወይም የሽረት ጥዳይ ነው ማለት ነው::

መጠንቀቅ ማለት ደግሞ መናወጥ መሸበር መፍራት አይደ ለም:: ወታደር በግዳጅ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ይጠ ነቀቃል:: ስለዚህ እኛን የሚፋለሙ ነገሮች እንዳሉ ያሳስበናል::

ዮሐንስ "*ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም*" ይላል(3ዮሐ 4)::

*"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ"* (ሐዋ 20፥28)። የተባለውን ማስብ በተግባርም መተርጎም ይኖርብናል።

ለ) ጽድቅን መልበስ

*"... የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ"* ኤፌ 6፥14

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽድቅ በሁለት ዐይነት መልኩ ተገልጧል። ይኸውም አንደኛው፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚገኘው ጽድቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ደግሞ አማኞች ከዳኑ በኋላ በሕይወታቸው መታየት ስለሚገባ የጽድቅ ሥራ ነው። ቅድሚያ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ስለሚገኘው ጽድቅ ጥቂት እናነሳለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1 እና 2 ላይ ሕግ ያልተሰጣቸው አረማውያንና ሕግ የተሰጣቸው አይሁዳውያን በባሕርያቸው ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ ከተናገረ በኋላ በምዕራፍ 3፥21-25 ላይ እንዲህ ይናገራል። *"አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጪ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል፤ ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለም። ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል። በደሙ በሆነው እምነት እግዚአብሔር የማስተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው"*

ሐዋርያው እንደሚል የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል። ይህንን ጽድቅ ለመቀበል ማንም ምንም ዐይነት ቅድመ ሁኔታ ማሟላት የለበትም። ይህንን የተገለጠውን ጽድቅ ሕግ ስላልተከተለው ማንም ኀጢአተኛ መጥቶ የራሱ ሊያደርገው ይችላል። እግዚአብሔር ኀጢአተኛ የሆነውን የሰው ልጅ ሕግ ባልተከተለው ጽድቅ ማጽደቅ የፈለገው በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት ላይ ተመስርቶ በጸጋው ነው። ከዚህ ተነስተን ስለ ድነታችን ስናስብ ሁለት ነገር መገንዘብ እንችላለን። ይኸውም በአንደኛ ደረጃ የድነታችን ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑንና መሠረቱ ደግሞ መስቀሉ (ደሙ) እንደ ሆነ ነው።

እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን የሚያጸድቀው በጸጋው በክርስቶስ ደም ነው። አንድ ሰው ኀጢአተኛውን የሚያጸድቀውን እግዚአብሔርን "አንተ እኔን ከኀጢአቴና ከበደሌ በክርስቶስ ደም አጥበህ ልታጸድቀኝ ትችላለህ" ብሎ ሲያምን እግዚአብሔር ያንን ሰው ከኀጢአቱና ከበደሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም አጥቦ ከፍርድና ከኩነኔ ነጻ ነህ የሚል ፍርድ ይፈርድለታል ወይም ያጸድቀዋል (ሮሜ 4፥4-5፤ ቆላ 24-25)። ይህም ብቻ አይደለም በዚህ በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም ከሕግ ርግማን ይዋጀዋል (ገላ 3፥13-14)።

እኛ ሁላችን በክርስቶስ ደም ከኀጢአታችን ጸድቀናል፤ ከሕግ ርግማንም ተዋጅተናል። እዚህ ላይ ከሕግ ርግማን ተዋጅተናል ስንል ከሕግ ሥራ ወይም ከከንቱ ኑሮ ተዋጅተናል ማለታችን ነው። በዘጸ 21፥23 ላይ እንደተጻፈው በዕንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ የተረገመ ነው። በዚህ መሠረት ክርስቶስ ኢየሱስ በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ ከሕግ ርግማን ዋጀን፤ ለመዳን ሕግንም በመጠበቅ ከመጽደቅ ግዴታ ነጻ አወጣን። በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም ከሕግ ሞግዚትነትም ሆነ፣ ከምንም ዐይነት ርግማን ነጻ ወጥተናል።

የቀደመው የኪዳን ሕዝብ ወደ ክርስቶስ ለመምጣት የግድ በህግ ሞግዚትነት ሥር ማለፍ ነበረበት አሁን ግን እኛ በእርሱ በኩል የማለፍ ግዴታ የለብንም። በመስቀሉ ሞት ሁሉ ነገር

ስለተመቻቸ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በቀጥታ ወደ እግዚአብ ሔር ልንገባ እንችላለን (ዕብ 10÷19-20)፡፡ በፈሰሰውም ደም መዋ ጀት፣ ሥርየት፣ በእምነት መጽደቅንና ልጅነትን ተቀብለናል፡፡ ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ሰላም አለን፡፡

ይህን ሀሳብ በዚህ ከማጠቃለላችን በፊት እግረ መንገዳችንን አንድ መታወቅ ያለበት ነገር ስላለ አንስተን እናያለን፤ ይኸ ውም እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት አማካይነት መዋ ጀት፣ ሥርየት፣ ጽድቅና የጸጋ ልጅነት አግኝተናል፡፡ እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት የድነታችን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ነው፡፡ ለምሳሌ መዋጀት የሚለው ቃል የገበያ ቋንቋ ነው፣ ሥርየት የሚለው ደግሞ የቤተ መቅደስ፣ እንዲሁም ልጅነት የሚለው ደግሞ የቤተ ሰብ ወይም የማኅበረ ሰብ ቋንቋ ሲሆን፣ ጽድቅ ደግሞ የፍርድ ቤት ቋንቋ ነው፡፡ በመስቀሉ ላይ በተከናወነው ሥራ ድነታችን ይህንን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የድነትን እውነት ስናነሳ እነዚህን ልብ ማለት አለብን፡፡ እነዚህ ሀሳቦች ግልጥ ሆነው ወደ እኛ ሲመጡ ሰይጣንን ለመቃወም ይረዱናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እኛ አማኞች ከኀጢአት፣ ከሕግ፣ ከሰይጣንና ከሞት ኀይል ነጻ እንደወጣን ይናገራል፡፡ ነጻ ስለመውጣታችን ጉዳይ ከቈላስይስና ከዕብራውያን መልእክት ሁለት ክፍሎችን ወስደን እንነጋገራለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ እንዲህ ይላል፡፡ *"ሲቃወመንና ሲጻረ ረን የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ በመደምሰስ በመስ ቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ ላይ አስወገደው፡፡ የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትን ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደ ባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ"* (ቈላ2÷14-15)፡፡

ይህ ክፍል የራሱ የሆነ የታሪክ ዳራ አለው፡፡ ከዚህ ተነስተን ክፍ ሉን ለማየት ብንሞክር የበለጠ ትርጕም ሊሰጠን ይችላል፡፡



በዛን ዘመን አንድ ሰው ከሌላ ሰው ብዙ ገንዘብ ቢበደርና የተበ ደረውን ገንዘብ መክፈል ቢያቅተው፣ አበዳሪው ሰውዬ ይህንን ሰው ገንዘቡን (ዕዳውን) እስኪከፍል ድረስ ባሪያ አድርጐ ይወ ስደው ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ መካከል ተበዳሪው ሰውዬ ለአበዳ ሪው ገንዘቡን መክፈል ካልቻለ አበዳሪው ይህንን ሰው ገበያ አው ጥቶ ሊሸጠው መብት ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ አበዳሪው ይህ ንን ሰው ከመሸጡ በፊት የሚያደርገው ነገር አለ፤ ይኸውም የዚህን ሰው ዕዳ ከፍሎ ነጻ የሚያወጣው ሰው ካለ አስቀድሞ በአደባባይ ዕዳውን በላዩ ላይ ጽፎ ይለጥፍበት ነበር፡፡ ከዚያም ይህንን ሰው ዕዳውን ሊከፍል የሚችል ሰው ካለ፣ ከመሸጡ በፊት ዕዳውን በመክፈል ነጻ ያወጣው ነበር፡፡ ልክ እንዲሁ ክር ስቶስ ኢየሱስም በእኛ ላይ የተጻፈውን ዕዳ በመስቀል ጠርቆ አስወገደው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም የአለቆችንና የባለ ሥልጣና ትን ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያ ዞራቸው እንዲታዩ አደረገ ይላል፡፡ ይህም አባባል ልክ እንደ ላይኛው የራሱ የሆነ ታሪካዊ ዳራ አለው፡፡ በዚያን ዘመን ሁለት አገሮች በጦርነት ቢጋጠሙና አንደኛው ቢሸነፍ፣ አሸናፊው ወገን የተሸናፊውን አገር የጦር መሪውን ወይም መሪዎችን ማዕ ረግ ገፎ በአደባባይ እያዞረ ያሳይ ነበር፡፡ ልክ እንዲሁም ክር ስቶስ ኢየሱስም አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ በሰማያዊ ስፍራ እያዞረ አሳያቸው፡፡ በተጨማሪም የዕብራውያን ጸሓፊ በምዕ 2÷14 ላይ *"... በሞት ላይ ኀይል ያለውን ዲያብሎስን በሞቱ ኀይል እንዲደመስስ ነው"* ይላል፡፡ እዚህ ላይ አሠራሩ ምስጢራዊ ነው፡፡ እሾህን በእሾህ እንደሚባለው የአበው ብሂል፣ ኢየሱስ ክርስቶ ስም በመስቀል ሞቶ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ሰይጣንን ሻረ፡፡ በዚህም ከጨለማው ሥልጣንና ከኀጢአት ኀይል ነጻ አወ ጣን፡፡ የእኛንም ጽድቅ ሽሮ የራሱን ጽድቅ አለበሰን፡፡ እንግዲህ ሰይጣንን የምንዋጋው ይህንን ጽድቅ በመልበስ ነው፡፡

ሁለተኛው፣ ጽድቅ ደግሞ አማኞች ከዳኑ በኋላ ሊሠሩት የሚገባው የጽድቅ ሥራ ነው:: ክርስቲያኖች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ከጸደቁ በኋላ በጽድቅ የመመላለስ ግዴታ እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አበክሮ ይናገራል:: በጽድቅ መመላለስ ማለት ደግሞ ትክክለኛ የሆነ ነገር እያደረጉ መኖር ማለት ነው:: እኛ ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመን ጸደቅን ስንል፣ ጻድቅ ሆነን ተሠራን ማለት ሳይሆን፣ የክርስቶስ ጽድቅ ተቈጠረልን ማለታችን ነው:: እያንዳንዳችን የክርስቶስ ጽድቅ የተቈጠረልን ከሆነ ደግሞ በጽድቅ የመመላለስና ጽድቅን የማድረግ ግዴታ አለብን:: ከዚህ ውጪ ከኖርን ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል አመጻ ነው:: ለጽድቅ ኑሮ ደንታ ከሌለን በክርስቶስ አምነን ለመጽደቅ ንስሓ መግባታችን መሠረታዊነት የሌላው መሆኑን መግለጣችን ነው::

ጳውሎስ በኤፌ. 6÷15 ላይ ከዲያብሎስ ጋር በሚደረግ ውጊያ በአሸናፊነት እንድንወጣ የሮማውያንን ወታደሮች የአለባበስ ሥርዐት በማምጣት "የጽድቅን ጥሩር ልበሱ" ይላል:: ጥሩር የሮማውያን ወታደሮች ደረታቸውን ለመሸፈን ከፊት ለፊት ከአንገት እስከ ወገብ ድረስ የሚያደርጉት የጦር እቃ ነው:: አገልግሎቱም ልብን ለመከላከል ነው:: ይሁን እንጂ ጳውሎስ ከመንፈሳዊ ውጊያ ጋር አያይዞ ሲናገርበት ምሳሌነቱ የጽድቅ ነው::

አንድ ሰው ከሰይጣን ጋር ለመዋጋት ጽድቅን መልበስ አለበት:: ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚለውን ስናስብ በጽድቅ ሕይወት መሞላት ወይም መመላለስ የሚለውን መዘንጋት የለብንም:: ሰይጣንን የምንቃወመው በክርስቶስ ኢየሱስ ስም በመገሰጽ ብቻ ሳይሆን በጽድቅ ሕይወት በመመላለስም ጭምር ነው:: በጽድቅ ሳንመላለስ ሰይጣንን በክርስቶስ ስም ብቻ ብንቃወም ድላችን ላይቆምም፤ እንዲያውም ኀይል የሌለው አርቲፊሻል ጥይት ይሆንብናል:: የጽድቅ ሕይወት፣ ኀጢአትን የሚጠላ የክ



ርስቶስ ኢየሱስ ስምን ከመጥራት ጋር ግን ይገፈትረዋል:: ይህ አልቦ በሆነበት በአንደበት ብቻ እንከላከላለን ብንል ግን ውርድ በራስ ይሆናል:: ከዚህ አኳያ የጸደቁ ሰዎች በጽድቅ የመመላለስ ግዴታ አለባቸው:: ስለዚህ በጽድቅ እየኖርንና እየተመላለስን ሰይጣንን ብንዋጋ ኀይላችንና ጕልበታችን ብርቱ ይሆናል::

### ሐ) ወንጌልን መጫማት

"*በሰላም ወንጌል ዝግጁነት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ*" (ኤፌ. 6÷15)::

ሰይጣንን ለማሸነፍ ሶስተኛው ስልት በሰላም ወንጌል ላይ ተጫምቶ መቆም ነው:: በሰላም ወንጌል ላይ ተጫምቶ መቆም ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ማድረግና በእርሱ ሰላም በመሞላት፣ ሌሎችም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን የጠብ ግድግዳ አስወግደው ሰላምን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያደርጉ የሰላምን መምጣት ማብሰር ለሰላም ሕይወት መጣራት ነው::

2ቆሮ 5÷18-20 ባለው ክፍል ላይ ሰውን ከሰው፣ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን የምንማልድ አምባሳደሮች እንደሆንን ይናገራል:: እኛ ከጠላታችን ጋር ሰልፍ ለማድረግ የምንወጣው በእግዚአብሔር ሰላም ተሞልተንና ከሰዎች ጋር ሰላም ሆነን ማለትም ጥላቻን አስወግደን ነው:: ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሳንሆን ከሰይጣን ጋር ለመዋጋት ብንወጣ ኀይላችን የከሰመ ይሆናል:: ይቅር አለማለት ሰይጣን በሕይወታችን ስፍራ እንዲያገኝ ያደርገዋል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል በኤፌ. 4÷26 ላይ "*ተቈጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ፤ በቍጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፤ ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት*" ይላል:: ለሰይጣን እግር መቆሚያ ስጥተን እርሱን እንዋጋ ብንል አይሆንም:: እርሱን ለመቃወም አስቀድመን ያንን የሰጠነውን መቆሚያ፣ በንስሓ መንገድ በመሄድ ወይም ጥላቻ፣ ቂም ይዘን

ከነበረ፣ በማስወገድ፣ ይቅር በማለት ማፍረስ አለብን:: ይቅር በማንልበት ጊዜ ግን ሰይጣን በሕይወታችን ለእግሩ ማረፊያ ያገኛል:: ይህንን ያገኘውን የእግሩን ማረፊያ ደግሞ እያሰፋው ይሄዳል:: ቍጣ ውሎ ሲያድር ምሬት ሆኖ ወደ መንፈሳችን ዘልቆ ይገባል:: ጥላቻ ወደ መንፈሳችን ዘልቆ ሲገባ ደግሞ መራራ እንሆናለን፤ መንፈሳችንም ይጨልማል:: ሰይጣን ደግሞ የጨለመ መንፈስ ማኅበርተኛ እና አጋፋሪ ነው:: በጨለማ መንፈስ ውስጥ ሰይጣን መግቢያ መውጫ ያገኛል::

ቀደም ብሎ ጌታ ያስተማረው ጸሎት እስመልክቶ በተሰጠው ሀሳብ ላይ የይቅርታ ጉዳይ ዘርዘር ባለ መልኩ እንደተገለጠው ሁሉ፣ አሁንም ከጠላት ጋር በሚኖረን መንፈሳዊ ውጊያ ለድሉ አስተማማኝነት ለሌሎች ያለን የይቅርታ ልብ እጅግ ወሳኝ ነው:: ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲጣሉ፣ መጨረሻ ላይ በጣም መራራ በመሆን ከእግዚአብሔርም ጋር ያላቸው ግንኙነትና ሰላም ሲበላሽ ይስተዋላል:: የዚህ ምክንያቱ በተማረሩበት ሰው ላይ ለምን እግዚአብሔር አንድ ክፉ ነገር አላደረገበትም የሚል ነው:: በመጨረሻም እነርሱ የጠሉትን እግዚአብሔር እንዲጠላላቸው ፈልገው እግዚአብሔር እሺ ሳይል ሲቀር፣ የጠላቴ ወዳጅ ጠላቴ ነው በሚል ሀሳብ በእግዚአብሔር ላይ ያኮርፋሉ:: በዚህም ሰላማቸው ይበጠበጣል:: ማንኛችንም ብንሆን እንዲህ ዐይነት ሕይወት ይዘን ሰይጣንን መቃወም አንችልም:: በጠላታችን ላይ አመርቂ ድል እንድናገኝ ካስፈለገ አስቀድመን ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሆነን በሰላም መሞላትና በተጨማሪም ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት በይቅርታ ማበጀትና ሰላምን መመሥረት አለብን::

መ) የእምነት ጋሻ ማንሣት

"*ከእነዚህም ሁሉ ጋር፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ*" (ኤፌ.6፥16)::



ጥንት የሮማውያን ወታደሮች ከነበሩአቸው የጦር እቃዎች ውስጥ አንዱ ጋሻ ነበር:: ይህ ጋሻ የሚሠራው ከቄዳ ሲሆን፣ ወደ ጦርነት በሚወጡበትም ጊዜ በእሳት ተለኩሶ የሚወረወርን ፍላጻ ለማጥፋት በውሃ ይነከር ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስም ከዲያብሎስ ጋር የሚደረገው መንፈሳዊ ውጊያ ላይ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሱ ይላል:: እምነት በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ አማኝ እንዳይጎዳ ወይም ጥቃት እንዳይደርስበት የሚረዳ መንፈሳዊ እቃ ጦር ነው:: ያለዚህ እቃ ጦር እየተንበለበሉ የሚመጡትን የክፉውን ፍላጻዎች ማጥፋት አይቻልም:: እምነት ሲጠፋ ከእግዚአብሔርም ጋር ያለ ሕያው ግንኙነት ጠፋ ማለት ነው:: አንድ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን እንዲህ አለው:: "*ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ*" (ሉቃ 22፥31-32):: የሰይጣን ፈተና የሚያነጣጥረው እምነታችንን በማናጋት፣ በማጥፋት ላይ ነው::

የሰይጣን ማጥቂያዎቹ ፍላጻዎቹ ናቸው:: እነዚህ ፍላጻዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ምን እንደሆኑ አልተጠቀሱም ሆኖም ከሚሠራቸው ክፉ ሥራዎች ተነስተን ግን መገመት እንችላለን:: ይኸውም ትካዜ፣ መከራ፣ ጸጸት፣ ተስፋ መቍረጥ፣ ተስፋ ማጣት፣ የኀሊና ክስ፣ ጥዳት ... ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ በእነዚህ ፍላጻዎች በቀላሉ የሰዎችን ስሜትና አእምሮ ሊጎዳ፣ እምነትንም ሊያስጥል ስለሚችል የሚወረወርብንን የክፉ ፍላጻ እንደየ አመጣጡ ለመመለስ የእምነት ጋሻ ማንሳት ያስፈልጋል:: ይህም እምነት የሚገኘው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት፣ በልብም በመሰወር ነው::

ሠ) የመዳን ራስ ቍር

"የመዳን ራስ ቍር ..."

የራስ ቍር የራስን ዙሪያ የሚሸፍን የጦር ዕቃ ነው። አገልግሎቱም እራስን ለመከላከል ሲሆን አእምሮአችን በጠላት እንዳይጠቃ በእግዚአብሔር ተስፋ መሞላት መቻል አለበት። ይህም ብቻ አይደለም ስለ ድነታችን በቂ ግንዛቤ ሊኖረን የተረዳነውንም አጥብቀን ልንይዝ ይገባል (1ተሰ5÷8)።

(3) ማጥቂያ መንፈሳዊ የጦር ዕቃ

ሀ) በመንፈስ ሰይፍ ወይም በእግዚአብሔር ቃል መዘጋጀት "የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው" ኤፌ 6÷17

በዚህ በኤፌሶን 6÷10-18 ላይ ከተገለጠው መንፈሳዊ እቃ ጦር ውስጥ በማጥቂያነት የተቀመጠው ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ በአማኙ ውስጥ ሆኖ በኀይል መሥራት ቢፈልግ ለእርሱ ሰይፉ በአማኙ ዘንድ ያደረ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከዚህ አኳያ የእግዚአብሔር ቃል በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ሀይነተኛ ቦታ ያለው ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በቈላ 3÷16 ላይ "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" የሚለን። ጠላት ለውጊያ በእኛ ላይ በሚነሳሳበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ የመጣብንን ውጊያ ለመመለስ ወይም ለመመከት የሚጠቀመው በውስጣችን በሙላት ካለው ቃል ነው። ይህንን ልብ ብለን በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ መዋጋት ብንጀምር መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ቃል እንደሚሰጠን ማስተዋል እንችላለን። ሆኖም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተቈራኘ ነገር እስካልኖረን ድረስ ይህ ነገር አይሆንም። ሌላው ቢቀር ቃሉን ባነበብንበት ወይም በሰማንበት ጊዜና ባላነበብን



በት ጊዜ እንኳ ያለን መንፈሳዊ ጉልበት ይለያያል። ቃሉን ስናነብ ወይም ስንሰማ ጠንካራ ጕልበት ይኖረናል በዚህን ጊዜ ውጊያ ቢመጣብን እንኳ ቀድመን ያነበብነውን የእግዚአብሔርን ቃል መንፈስ ቅዱስ ለድል እንደ ድልድይ ይጠቀምበታል። ሳናነብ ከቀረን ግን ሽንፈታችን ይበዛል። የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን መኖሩ በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ ወዲያውኑ ተነስተን ለመዋጋት ይረዳናል። ለምሳሌ በውጊያ ውስጥ በጣም ደክመንና ጠውልገን ከርመን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኛ ቢመጣ ወይም መልእክት ብንሰማ ወዲያውኑ ብድግ እንላለን፤ ካለንበት ሁኔታ እንወጣለን። የዚህ ምስጢሩ ቃል በሕይወታችን መሥራቱ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። ቃሉ ወደ እኛ ሲመጣ በውስጣችን የመንፈስ ሠይፍ ይሆንና ያለንበትን ፈተና ይቈራርጣል፤ ወዲያውም ከአጠገባችን ብዙ ነገር ገለል ይልልናል። የሰማነው ቃል ግን በውስጣችን ኖሮ ቢሆን፣ ካለንበት ጦርነት ለመውጣት ሰባኪው እስኪሰብክም ድረስ አንጠብቅም ነበር።

በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንደ ሰይፍ ይጠቀማል፤ እኛ ግን ብዙ ጊዜ "መንፈስ ይሙላባችሁ" የሚለውን ቃል ይዘን "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" የሚለውን ቃል ግን እንረሳለን (ኤፌ 5÷18፤ ቈላ 3÷16)። ሆኖም በሐዋርያው ጳውሎስ ውስጥ ሆኖ "መንፈስ ይሙላባችሁ" ያለን እግዚአብሔር እንደ ገናም በቈላስይስ መልእክት ላይ "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" ብሎ ያስተምረናል።

መንፈስ ቅዱስ አለኝ ብሎ መኩራትና መመጻደቅ አደገኛ ነው። መንፈስ ቅዱስን ከወደድን እርሱ የደረሰውን ቃል አብረን መውደድ አለብን። ደራሲው ከመጽሐፉ፣ ከቃሉ ጋር ማደር ይፈልጋል። የእግዚአብሔርን ቃል ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ጻፉት (2ጴጥ2÷21)። መንፈስ ቅዱ

ስም በእኛ ውስጥ ሲያድር ቃሉንም በፍቃዳችን ወደ ልባችን አስገብተን ከእርሱ ጋር ማሳደር ያስፈልጋል:: በእኛ አድሮ ሥራ የሚሠራውና የጠላትን አሠራር የሚያፈርሰው በውስጣችን የኖ ርነውን ቃሉን በመጠቀም ነው::

**ለ) በመንፈስ መጸለይ**

ጸሎት ራሱ ሰይጣንን የምንዋጋበት መሣሪያ ነው:: መንግሥ ትህ ትምጣ ብለን ወደ እግዚአብሔር ስንጣራና ይኸ ጸሎት መልስ ሲያገኝ የአጋንንት ምሽጎች ይፈራርሳሉ::
በጸሎት አማኞች ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ፤ በእምላካቸው ክንፍ ሥር መሸሸጊያ ያገኛሉ፤ በላባዎቹ ይጋረዳሉ፤ ከክፉ ይጠበቃሉ፤ እባቡና ጊንጡን ይጫማሉ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ይረግጣሉ (መዝ 91)::


መንፈስ ቅዱስ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ያሳየናል፤ ያግዘ ናል፤ ይመራናልም፤ በማይነገር መቃተት በውስጣችን ይማል ዳል:: በልሳን ስንጸልይም በግል እንታነጻለን (ሮሜ 26-27፤ 1ቆሮ 14÷4)::



# ድል በመስቀሉ

*"እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል፣ ድል ነሡት፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ፣ ለነፍሳቸው አልሳሱም"* (ራእ 12÷11)::

ሥጋ፣ ዓለምና ሰይጣን በመስቀሉ ድል ተመተዋል::




**ድል በሥጋ ላይ፤**

*"ከእንግዲህ የኀጢአት ባሮች እንዳንሆን፣ የኀጢአት ሰው ነት እንዲሻር አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን"* (ሮሜ 6÷6)::

**ድል በዓለም ላይ፤**

*"ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰ ቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ ይሁን"* (ገላ 6÷14)::

**ድል በሰይጣን ላይ፤**

**ቈላ 2÷14-15፤ ዕብ 2÷14-15**

*"እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተ ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል፤ እናንተ ኀጢአተኞች እጃችሁን አንጹ፣ እናንተ በሁለት ዐሳብ የምትዋልሉ ልባችሁን አጥሩ"* (ያዕ 4÷7-8)::

## VI. አንተ ግን

«ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ
ይህን ዕወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን
የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆ
ቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር
የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይ
ገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣
ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን
የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኀይሉን ግን
ክደዋል ከእነዚህ ደግሞ ራቅ። ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ
ኀጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትንም የሚወሰ
ዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ
ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ ከእነዚህ ዘንድ
ናቸውና። ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፣
እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ከእምነትም
የተጣሉ ሰዎች ሆነው እውነትን ይቃወማሉ። ዳሩ ግን የእነዚያ
ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ ሞኝነታቸው ለሁሉ ይገለጣ
ልና ከፊት ይልቅ አይቀናላቸውም።

አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግ
ሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተ
ልህ፤ በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥ
ሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታም ከሁሉ አዳነኝ። በእውነ
ትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚ
ወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች
እያሳቱና እየሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ» (2ጢሞ 3፥1-13)።

በጢሞቴዎስ መልእክት «አንተ ግን» የሚለው ሐረግ ተደጋ
ግሞ ይገኛል። በ1 ጢሞ 6፣ ከላይ በተጠቀሰው ሁለት ጊዜ፣
በምዕራፍ 4 እንደገና እናገኘዋለን። «አንተ ግን» የሚለው ጥሪ



በአንድ በኩል የሕይወትን አቅጣጫ በሌላ በኩል የትምህርቱን
አቋም በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የአገልግሎቱን የስምሪቱን የጥሪ
ውን ጉዳይ የሚመለከት ነው።

ጳውሎስ ዘመኑን ሊያጠናቅቅ ሲዘጋጅ በጢሞቴዎስ ላይ ብዙ
አደራ ይጭን ነበር። ስለዚህ ዋና ዋና ነገሮችን ይነግረዋል።
በተለይ በ2ኛ ጢሞቴዎስ ላይ መሄጃው እንደተቃረበና በዚህ
ሥጋ ውስጥ የሚኖርበት ዘመን ሊያከትም የተጠጋበት ወቅት
መሆኑን ተረድቶ ታላቁን አደራ ጢሞቴዎስ ላይ ይጥላል።
በዚህ አኳያ ደግሞ ስለሚመጣው ሁኔታ ስለዘመኑ ይነግረዋል።

ጊዜ በተለያየ መንገድ ይለካል። ጊዜን በዓመት፣ በወር፣ በቀን፣
በሰዓት፣ በደቂቃ ወዘተ እንለካለን። ነገር ግን ደግሞ ጊዜ የሚ
ለካበት ሌላ ጠባይ አለው። በውስጡ በታጨቀው፣ በውስጡ
በሚካሄደው እንቅስቃሴ፣ በውስጡ በሚገለጠው ክስተት፣ ባሕ
ርይ አኳያ ጊዜ ይለካል። በዚህ ምዕራፍ ስለጊዜ ሲናገር
በዚህ ሀሳብ ነው።

«ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን … »
እንደዚህ ሀይነት መልዕክት መስማት ደስ አይልም። በተለይ
ለእኛ አይመችንም። ምክንያቱም ከጢሞቴዎስ ይልቅ በመጨ
ረሻው ዘመን ላይ ነው ያለነው። የመጨረሻው ቀን ብሎ የሚና
ገረው የምስራች የሆነ የሚጓጓ ነገር አይደለም የሚናገረው፤
የሚያስቆዝም ነገር ነው የሚናገረው፤ ደስ የማይል ክፉ የሚ
ያስጨንቅ ዘመን ይመጣል ይላል።

እግዚአብሔር ካለ የተባለው እውነት ነው። ከእኛ ምኞት ምንም
ተቃራኒ ቢሆን እግዚአብሔር ከተናገረው እርሱ እውነት ነው።
ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር መስማማት ይበጀ
ናል።

ጳውሎስ ስለዚህ ክፉ ዘመን ሲናገር ከሰው ማንነት ውጪ በሆኑ

ነገሮች ላይ አይደለም:: በርግጥ ጌታ በማቴ 24 ስለመጨረሻው ዘመን ሲናገር የምድር መናወጥ ረሓብና ቸነፈር እንደሚኖር እነኝህን የመሳሰሉ ነገሮች ተናግሯል::

እዚህ ግን ዘመኑ ክፉ የሚሆነው ከእንደዚህ ዐይነት ጉዳዮች የተነሣ ሳይሆን በሰው ውስጥ ከሚገለጠው ከሰው ውስጣዊ ሁኔታ፣ ባሕርይ፣ ጠባይ የተነሣ እንደ ሆነ ይናገራል:: የተመረዘ የውስጥ ሰውነትን ይመለከታል::

## 1. እግዚአብሔር ለተከታዮቹ የሚያደርገው ጥሪ

ይህ «አንተ ግን» የሚለው ሐረግ አንተ የተባለለት ወይም አንተ የተባለው ከሌሎች ጋር የሚነፃፀር ከሌሎች ጋራ በተለያዩ ሁኔታዎች ተቃርኖ ውስጥ የሚገኝ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው:: ልዩነትን የሚጠራ ሐረግ ነው፤ የተቃርኖ ይዘትን ያመለክታል፤ በማንነት ወይም በእቋም ደረጃ፣ በአመለካከት ደረጃ፣ በዋጋ አሰጣጥ ደረጃ፣ በአደራረግ፣ በአሠራር ሁኔታ፣ በአካሄድ፣ በአኗኗር ዘይቤ ልዩነትን የሚያመለክት ነው::

«አንተ ግን» ከሌሎች ይልቅ የሚል ዐሳብ አለው፤ «አንተ ግን የተለየህ ሁን» የሚል ሐሳብ አለው:: ይህን ዐይነት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ እናገኛለን፤ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን በተለይም ደግሞ ወደ ጢሞቴዎስ በተጻፈው መልእክት ውስጥ ተደጋግሞ እናያለን::

በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ኤርምያስን «አንተ ግን ወገብህን ታጠቅ ተነስም ያዘዝሁህንም ሁሉ ንገራቸው በፊታቸው እንዳላስፈራህ አትፍራቸው» (ኤር 1፥17) ሲል እንሰማለን:: ይህ ሀይነቱ አባባል ከሌሎች ሰዎች ሁኔታ ጋር ይነጻጸራል:: እዚህ ጋ ከራሱ የሚነጻጸረው ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር ነው:: በኤር 1 ቍጥር 16ም «ስለ ክፋታቸውም ሁሉ እኔን ስለተዉ ለሌሎችም አማልክት ስላጠኑ ለእጃቸውም ስራ ስለ



ሰገዱ ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ» ይላል::

እግዚአብሔር ይህን የሚለው ስለ አዘነበት ሕዝቡ ነው:: የተለየ ሆኖ መመላለስ የተገባው ይሄ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ሸሸ፤ ክፉን በማድረግ መንገድ ተጓዘ:: የሕያው ውሃ ምንጭ አምላኩን ተወ፤ ለሌሎች አማልክት፣ አማልክት ናቸው ብሎ ለሰየማቸው፣ ላሰባቸው ለእጁ ሥራ ሰገደ፤ ኪዳኑን ተላለፈ፤ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ» የሚለውን የመጀመሪያ መመሪያ ስለ ተላለፈ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚአብሔር እየራቀ ስለ ሄደ፣ የእግዚአብሔርን ማዕከላዊነት እያስወጣ ራሱን ዋና እያደረገ ስለ ሄደ፣ ሕያው እግዚአብሔርን እየተወ ጣዖታትን በመካከሉ ስላስቀመጠ፣ ስላጠነ ነው:: ሕይወቱ የዘቀጠ፣ ጀርባውን ለእግዚአብሔር የሰጠ ሆነ:: በሕዝቡ መካከል ላለው ለኤርምያስ እንዲህ ይለዋል- «አንተ ግን ወገብህን ታጠቅ፣ ተነስም ያዘዝሁህን ሁሉ ንገራቸው፤ በፊታቸው እንዳላስፈራህ አትፍራቸው»::

## 2. ጥሪው ከባድ ቢሆንም መታዘዝ አማራጭ የለውም

ከብዙሃን ተለይቶ መውጣት፣ ከአጀቡ ውስጥ መውጣትና ለብቻ መቆም፣ አጀቡ በአንድ መንገድ ሲነጉድ ያንን መንገድ ተቃርኖ በተቃራኒ አቅጣጫ መጓዝ ከባድ ነው:: ለእንደኔ ዐይነቱ፣ ለእንደኛ ሀይነቱ ለእያንዳንዳችን የሚከብድ ጥሪ ነው:: ወንዙ በሚፈስበት አቅጣጫ አለመቅዘፍ፣ አለመዋኘት፣ ወንዙ ቁልቁል ሲፈስ ሽቅብ እንዋኝ ማለት፣ በጣም ከባድ ነው፤ የሚያዳግት ነው:: ይሁን እንጂ እንዲህ ይለዋል "በፊታቸው እንዳላስፈራህ አትፍራቸው፤" እነርሱን ከምትፈራ ይልቅ እኔን ብትፈራ ይሻላል፤ ለእነርሱ ከምትመቻቸው ለእኔ የምትመች ብትሆን ለአንተ ይበጅሃል::

ለኤርምያስ የመጣለት በጣም የከበደ ጥሪ ነው:: ይሁንና ለዚህ

ጥሪ፣ ለዚህ ግብዣ፣ ኤርምያስ አዎንታዊ መልስ ባይሰጥ አሻፈረኝ ቢል አማራጩ የከፋ ነው:: ለሕዝቡ ሁሉ ከፊታቸው እየመጣ ያለው ነገር ከባድ ነውና፤ ይህ ሕዝብ ከእግዚአብሔር እየራቀ ስለመጣ በዚህ ሕዝብ ፊት የመጣው ክፉ ነገር ነው:: ረሓብ ነው የመጣው፣ ሰይፍ ነው የመጣው፣ የባቢሎን ሰይፍ እየመጣ ነው፤ ቸነፈር እየመጣ ነው፤ ካህናት ምግብ ፍለጋ ሲዞሩ በመንገድ ላይ በሰይፍ የሚወድቁበት ጊዜ እየመጣ ነው:: ከረሓብ የተነሣ ርህሩህ እናቶች እንኳን ልጆቻቸውን ቀቅለው የሚበሉበት ጊዜ እየመጣ ነው፤ ልጆች ደኻ አደጎች፣ ወላጅ የለሽ የሚሆኑበት፣ ምርኮኝነት፣ ባርነት የሚሰፍንበት ጊዜ እየመጣ ነው:: ስለዚህ ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ጥሪ ሸሽቶ ከሕዝቡ ጋር ቢደባለቅ የሚጠብቀው የባሰ ክፉ ነገር ነው:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ እስከተቻለ ጊዜ ድረስ ሕዝቡን ወደ መልካም ነገር እየተጣራ ቢመላለስ ነው የሚበጀው:: ዘመኑ ሲከፋ ጥሪያችንም የከበደ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ለሚደረግልን ጥሪ እሺታችንን ባንመልስ ጀርባን ብንሰጥ፣ በራሳችን መንገድ እንሂድ ብንል፣ የባሰ ክፉ ነገር ውስጥ ነው የምንገባው::

«አንተ ግን» ተለይ ይለዋል:: እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ በአንድ ወቅት ሲናገር «እኔ የተመረጠች ፍጹምም እውነተኛ ዘር አድርጌ ተክዬሽ ነበር፤ አንቺ ግን ክፉ የእንግዳ የወይን ዘር ሆነሽ እንዴት ተለወጥሽብኝ» (ኤር 2÷21) ይሄ ከሕዝቡ ፍቃድ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው:: የእግዚአብሔር ቸርነት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው በጎነት ስለ ተጓደለ ሳይሆን ሕዝቡ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከማስገዛት ይልቅ በራሱ መንገድ ለመሄድ ስለ ፈለገ ነው ሌላ ወይን የሆነው::

ጨው አልጫ ቢሆን ለምን ይጠቅማል? የእግዚአብሔር ቃል ለምንም አይበጅም ነው የሚለን:: ጌታ ኢየሱስ *«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም»* (ማቴ 5÷13) ይላል::



እዚህ ስፍራ ላይ ጨው ተብሎ የተገለጠው ዛሬ የምናየውን የጨው የተጣራ መልክ የያዘ ሳይሆን ዛሬ ቦሌ ብለን የምናውቀውን ኖራ መሰል ከምድር የሚታፈስ ልዩ የዐፈር ዐይነት ነው:: ይኸ ቦሌ መሰል ነገር ጨውነት ያለው ነው:: ይሁንና ሁለንተናው ጨው አይደለም፤ ግን እንደ ጨው ያገለግላል:: አንዳንድ ጊዜ ይህ ኖራማ መሳይ ልዩ ዐፈር ከውስጡ ያለው ጨው ሟሙቶ በውሃ ከተዋሐደም በኋላ ያንኑ ነጭማ መልክ ይይዛል:: በዚያን ወቅት እንደ ጨው ሊጠቀሙበት ቢሞክሩ ጨውነቱንም ያጣ ሆኖ ያገኙታል:: በዚህን ጊዜ ጨው አልጫ ሆነ፤ የጨውነቱን ጣዕም አጣ ይባላል::

ይህ ጨውነት የማይታይ ከሆነ ጨውነት ወደ አልጫነት ከተለወጠ ልዩ እንግዳ የወይን ግንድ ከሆንን ይህንን አልጫነት ይቀየር ዘንድ ለሕዝቡ እግዚአብሔር እንደገና ጥሪ ያቀርባል፤ ለእያንዳንዳችን ጥሪ ያቀርባል:: «አንተ ግን» ይላል ይህን ሀይነት አጠራር በየቦታው ተነግሯል ለምሳሌ ለዳንኤል «አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ድረስ ሂድ አንተም ታርፋለህ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ» (ዳን 12÷13) ተብሎ ተነግሮታል:: ስለሚመጣው ዘመን ተነገረው፤ ክፉዎች በክፋታቸው እየባሱ እንደሚሄዱ ተነገረው:: ደግሞም ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ እያስገኙ ራሳቸውን የሚያጠሩም እንደሚኖሩ ተነገረው፤ በዚህ መካከል፣ አንተ ግን በዚህ በያዝከው መንገድ 'አልጫ' ባልሆነው፣ ጨው በሆነው መንገድ እስከፍጻሜ ሂድ:: ከዚያ በኋላ ታርፋለህ፤ በመጨረሻም በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ ተባለ::

### 3. ይህ ጥሪ ለምሕረት የሚያበቃ የተመለሱ ጥሪ ነው

ይህ «አንተ ግን» የሚለው አጠራር እግዚአብሔር የራሱ ወገን

ሊያደርግ ሲፈልግ፣ ተስፋን ሊሰጠን፣ በፊታችን ሕይወትን ሊያ ለመልም፣ ሊፈርድብን ሳይፈልግ፣ ለእኛ የሚያቀርበው ጥሪ ነው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ አሁንም፣ ያንጊዜም ያው ነው፤ በብ ሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የምናየው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚአብሔር የመኰብለል ፈተና ይገጥመዋል:: ቀድሞውንም የኪዳኑን ሕዝብ፣ የእስራኤል ሕዝብ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት በአብዛኛው የሚታየው ከእግዚአብሔር ሲኮበ ልል፣ ሲሸሽ ነው:: ነገሥታትን እግዚአብሔር ቀብቶ በሥልጣን ላይ ሲያወጣቸው ጥቂት ከቆዩ በኋላ፣ ስልጣናቸው ከተደላደለ በኋላ፣ ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር ይሰጡ ነበር::

ይሁንና ሕዝቡ አልፎ ለጥፋት ከተሰጠ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ቢጮኽ እግዚአብሔር ይመልሰዋል፤ ሕዝቡ ሕይወቱ የተሟላ ሲሆንለት ጥቂት ቆይቶ አሁንም ደግሞ ለእግዚአብሔር ጀርባውን ይሰጣል፤ በዚህ ሀይነት መንገድ ሲመላለስ የታየ ሕዝብ ነው::

ከይሁዳ አውራጃ ከተሞች ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደሱ ይሰበ ሰባሉ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ግን ይጋፋሉ:: እውነተኛ የእግዚአ ብሔርን ቃል የሚያመጡ የእግዚአብሔርን ባሪያዎች ያሳድ ዳሉ (ኤር 26፥1-9):: ለጾምም ከየአውራጃው ከተሞች መጥተው በቤተ መቅደሱ ይሰበሰባሉ:: እውነተኛ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመጣውን ነቢዩ ኤርምያስን ያስወግዳሉ (ኤር 36፥1-7፥24-26):: ተሰባስበው ምንም ይሁን ምን እንታዘዛለን በማለት ከእግ ዚአብሔር ምሪት ይጠይቃሉ:: ምሪት ሲሰጣቸው አሻፈረኝ ይላሉ፤ መልእክተኞቹንም እፍነው፣ አግተው ይወስዳሉ (ኤር 42 እና 43)::

የአዲስ ኪዳን ሕዝብም እንደዚሁ ነው:: ሃይማኖታዊ መልኩን ይይዛል፤ ነገር ግን በነይማኖቱ መካከል ሊገኝ የሚገባውን ሕያው



እግዚአብሔርን ያጣል:: ለእኛም አዲስ ኪዳን ብንሆን «በመን ፈስ ብትኖሩ በመንፈስ ተመላለሱ":: በመንፈስ ዳግመኛ ብት ወለዱ በዚህ ዳግመኛ ልደትን በሰጣችሁ በመንፈስ፣ በእውነት መንፈስ፣ በቅድስና መንፈስ ተመላለሱ ነው የሚለው::

እምነታችን በክርስቶስ ዙሪያ ይጀምርና በሕይወታችን ክርስቶ ስን ማሳየት፣ ክርስቶስን ማየት፣ እግዚአብሔርን ማየት እየቀረ ይሄዳል:: ራስን ማየትና ማሳየት የሃይማኖታችን ማዕከል ይሆ ናል:: በዚህ ጊዜ ጨው አልጫ ይሆናል፤ ብርሃን ሰጪውም ጨለማ ይሆናል፤ እንደዚህ ሀይነት ችግር እናያለን ሃይማኖታዊ ሥርዐቱ ይኖራል፤ ሃይማኖታዊ ልምምዱን እንቀጥለዋለን፤ ልምምድ እስከ ሆነ ድረስ እንደበታችን ይደግመዋል፤ ነገር ግን በመሐል እንቡጥ መሆን የሚገባው፣ የነገሮች ሁሉ ማዕከል መሆን የሚ ገባው የፍጥረት ሁሉ ባለቤት እርሱ ይወጣል፤ ይሸሻል:: ለእያ ንዳንዳችን ሕይወት መስተካከል እግዚአብሔር ብርሃን ይስጠን፤ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት የምንቃኝበት ዐይን እግዚአብሔር ይስጠን::

በጌታችን ዘመን የነበሩት ፈሪሳውያንም የሃይማኖቱን ሥርሀት ማሟላት ሥራቸው ስለ ሆነ ሥርዐቱን ቢያደርጉትም የእግዚአ ብሔርን ቃል ይተዉ ነበር፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ቸል ይሉ ነበር:: ጸሎታቸው ውጫዊ ሆነ፤ የአምልኮ ሥርዐ ታቸው ውጫዊ ሆነ እንጂ የልብ ነገር ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ ነገር አልተገኘበትም::

የሃይማኖታዊ ሥርሀት ይፈጽማሉ፤ በጎ ትሩፋትንም ያሳያሉ፤ ነገር ግን የነገሩ ማዕከል እግዚአብሔር አይደለም፤ «እንግዲህ ምፅዋት ስታደርግ ግብዞች ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እን ደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ:: እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል»(ማቴ 6፥1-4) ብሎ ጌታችን ተናገረ:: በሃይማኖት ክልል ውስጥ በመንፈሳዊ ልምምዳችን ውስጥ ዋናው

ነገር እግዚአብሔርን ማሳየትና ማስከበር ነው ወይስ የራሳችን ክብር ነው?

እነኚህ የሃይማኖት መሪዎች ጥንት መጀመሪያ ላይ በጥሩ ጅማሬ የነበሩ ግን በኋላ ላይ ሕይወታቸው የዘቀጠ በእግዚአ ብሔር ፊንታ ራሳቸውን ማስገባት የጀመሩ ናቸው:: እግዚ አብሔር ከልባቸው ብዙ የራቀ፣ ለአንደበታቸው ግን የቀረበ ሆነ:: እነርሱ ምፅዋት አድራጊዎች ከሆኑ ዓላማው እግዚአብሔር የሚያዘውን ጽድቅ መፈጸም ሳይሆን ክብርን ማግኘት ነው:: ከምናደርጋቸው ነገሮች ውስጥ በሰዎች ለመታየት፣ መንፈሳዊ ተብለን ለመከበር የምናደርጋቸው ለእግዚአብሔር ከልብ ከምና ደርጋቸው ጋር ሲነጻጸሩ ምን ያህል ናቸው? «አንተ ግን ምፅ ዋት ስታደርግ ምፅዋትህ በስውር ይሁን፤ ቀኝ እጅህ የምታደ ርገውን ግራህ አትወቅ»::

መልእክቱ ምንድን ነው? የምታደርገው ለታይታ አይሁን፤ ራስን ለማሳየት አትነሣ፤ በሕይወትህ ሁሉ እግዚአብሔርን ማሳየት ይሁን ማለት ነው:: «ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ:: ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብ በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፤ አንተ ግን ስትጸልይ እልፍኝህን ዝጋ፣ በስውር ለሚያይ አባትህም ጸልይ» እንደሚለው ማለት ነው:: ሃይማኖታዊነቱ በሰው ዘንድ ቢታይ ይሄ እንዴት ዐይነት ግሩም መንፈሳዊ ሰው ነው፤ ልዩ 'የተቀባ' ሰው ብንባል ነው የምንናፍቀው ወይስ በእግዚአብሔር ፊት በትህትና ሄደን የእግዚአብሔርን ነገር ማሳየት እግዚ አብሔር ከፍ ከፍ እንዲል እኛ ግን በእግዚአብሔር ውስጥ እንድንሰወር፣ 'እርሱ ሊልቅ እኔ ላንስ ይገባል' እንዳለ እንደ መጥመቁ ዮሐንስ በዚያ ልብ ነው የምንመላለሰው?

ጸሎታችን የሚበዛው በየመንገድ ማዕዘን ማለትም ሰዎች የሚሰ በሰቡበት ቦታ ነው? ወይስ በጓዳችን? ከእግዚአብሔር ጋር የው



ስጥ ግንኙነት አለን?

"ስትጾሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ ለሰዎች ሊታዩ ፊታቸ ውን ያጠፋሉና ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: አንተ ግን ስትጾም በስ ውር ይሁን"፤ እዚህ ላይ ልብ እንድንል የሚያስፈልገው ነገር እግዚአብሔርን ከማየትና ከማሳየት ይልቅ በሃይማኖታዊ አድ ራጎታችን ራሳችንን ማየትና ማሳየት እግዚአብሔር የሚፈል ገው መንገድ ስላልሆነ አንተ ግን ከዚህ ውጪ ሁን፤ ስማያዊውን ነገር ምድራዊ አታድርገው፤ የልብን ነገር የታይታ አድርገህ አትለውጠው የሚለውን ዋና ምክር ነው (ማቴ 6፥16-8)::

ጌታ ኢየሱስ ለብዙኀን ሲናገር «እናንተ ግን ተጠንቀቁ አስቀ ድሜ ሁሉን ነገርኳችሁ» ስለ ዘመኑ መጨረሻ መልክም ሲና ገር «ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ፣ ብዙ ሐሰተኞች ክርስቶ ሶች ይነሳሉ» ብሎ ካለ በኋላ "እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኳችሁ" ይላል:: ሌላው በሚነጉድበት መን ገድ አትሂዱ ማለቱ ነው (ማቴ 24፥23-25)::

## 4. የወንጌልን እውነት ጠብቅ

"*ብዙዎች እያሳቱና እየሳቱ ይሄዳሉ፤ አንተ ግን በተማርክበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ቁም*" (2ጢሞ 3፥13-14):: በተለያየ ስልትም ቢመጣ አንተ ጸንተህ ቁም አንዳንዴ ሌሎች ሲከተሉ ሲተምሙ ከእነርሱ ተለይተን ብቻችንን መቆም በጣም ከባድ ነው:: እነ ሲድራቅ ሚሳቅ አብድናጎ ሌላው ሁሉ ሲጉነበስ እነርሱ ብቻ ሲቆሙ በጣም ከባድ ነበር:: "አንተ ግን" የሚለው ጥሪ ይህን ያስከትላል፤ ደግነቱ እግዚአብሔር አብሮ ይሆናል:: በዚያ ውስጥ የማዳን መንገድ ይመጣል:: ነገ የሚሞት ሰው ዛሬ ቢሞት ብርቅና ድንቅ አይደለም:: ከነገ ወዲያ የሚሞት ሰው ነገ ቢሞት ምንም አይደለም:: ባያድነንም እንኳ ስለ ማለ ታቸው የጸና አቋም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: እግዚ

አብሔር ደግሞ ታማኝ ነው፤ እነሲድራቅ ቆሙ:: ዐይንህ ላፈር ትባል ይሆናል፤ የምላስ ጅራፍ ይዥጐደጐድብህ ይሆናል፤ ስምህ ይጠፋ ይሆናል፤ ያልሆነ ነገር ይለጠፍብህ ይሆናል፤ ነገር ግን አንተ በቃሉ እውነት ከአምላክህ ጋር መቆምህን አረጋግጥ::

ጳውሎስ የወንጌሉን እምነት መዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ከዚያ ጋር ተደማሪ ከሰው ዘንድ የሚመጣ ምንም ነገር እንደሌለ ሲያስተምር አይሁዶች ግን ትምህርቱ ስላልተ መቻቸው ባሕላቸውም ስላስገደዳቸው እንደ ገና ከዚያ ጋር የሕግ ሥርዐት መገረዝ ያስፈልጋል ብለው ማስተማር ጀመሩ:: ያን ጊዜ ጳውሎስ ዞር በሉ አለ:: ድሮ ለዚያ ሕግና ወግ ይታገል የነበረ ይወጣ ይወርድ ያሳድድ የነበረ እውነቱ በራለት:: የዚ ህን ጊዜ የጳውሎስን ስም ለማጥፋት ተነሡ::

በገላትያና በቆሮንቶስ አካባቢ በነበረው አገልግሎት «እርሱ እኮ እንዲያውም ሐዋርያ አይደለም፣ እንደኛ ከጌታ ኢየሱስ ጋር የተመላለሰ እኮ አይደለም» ተባለ:: ይህም የእርሱ ትምህርት ተቀባይነት እንዳያገኝ ነበር:: ስለዚህ ጳውሎስ ማለት የማይገ ባውን ማለት ግድ ሆነበት:: በመገለጥ ብዛት ሰዎች የማይሆን ስፍራ እንዳይሰጡት የማይፈልገውን፣ የሚሸሸውን አንዳንድ ነገ ሮችን መግለጥ ነበረበት:: ግን ሲገልጥም ከ14 ዓመት በኋላ ነው:: እኛ አንድ ማታ የሆነ ነገር የተገለጠልን እንደ ሆነ በማ ግስቱ ሮጠን ተገለጠልን እንላለን፤ እንናገዋለን፤ እናዳርሰዋለን:: ብዙ ጊዜ «እኔ ምን ዐይነት ሰው ነኝ? ሰማያት የሚከፈቱልኝ፣ የሚገለጥልኝ ሰው ነኝ» በማለት እንታበያለን:: ጳውሎስ ግን 14 ዓመት ጠብቆ አስፈላጊ ሲሆን የቃሉን እውነት መናገር ግድ ሆነበት::

"በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው እግዚአብሔር አብ ሐዋ ርያ የሆነ እንጂ በሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ" ብሎ ስለ ራሱ ይናገራል:: በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ



ማለት ግድ ሆነበት (ገላ1፥1):: የገላትያ ሰዎች ከፍቅራቸው የተነሣ ዐይናቸውን እንኳ በሰጡት ነበር፤ ከእውነት ጋር ነበሩ ልባቸውን ከፍተው ነበር (ገላ 4፥15-16):: በኋላ ሌሎች መጡና አወነባበዱአቸው:: በእንደዚያ ዐይነት ግብዝነት ጴጥሮስም እንኳ እንዳፈገፈገ አይቶ ጳውሎስ ጴጥሮስን በሁሉ ፊት ገሠጸው (ገላ 2፥14):: ለምን? አንዳንድ ችግሮች በማኅበር ሲገሠጹ ሌሎችም ያ ችግር የያዛቸው ይለቃቸዋል:: በጸሎት ጊዜ አንዳንዴ እንዳ ንድ አጋንንት እንደዚያ ይሆናሉ:: እግዚአብሔር አንዱን ሲመታ ሌላው ለቆ ይሄዳል:: ገሠጸው ቢገሥጽም ጴጥሮስ ጥፋቱን አው ቋል:: ሌላ ጊዜ በጳውሎስ የሚሠራ ልዩ ጸጋ በማለት በአክብ ሮት ስለ እርሱ ጴጥሮስ ተናግሮአል (2ጴጥ3፥15-16):: አንዳ ንዴ የሚገሥጹን ሰዎች ሲኖሩ ስለገሠጹን አዋረዱን ብለን ስማቸውን ከማጥፋት እንደ ጴጥሮስ ጸጋቸውን ብናከብር እግዚ አብሔር ይወዳል:: እግዚአብሔር ይርዳን::

እውነትን የያዘ ሰው መስደዱ አይቀርም:: ላለመሰደድ እውነ ትን መጣል ይኖርብናል፤ አንድ እውነት ቢኖር አንተ ተናገር አንተ ተናገር እንባባላለን፤ ለምን? ሌላው ርምጃ ቢወስድ ደስ ይለናል:: እኛ ግን ስደቱን እንሸሻለን፤ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለመሰደድ ቁረጥ ይለዋል:: መከራ ተቀበል ይለዋል እየደጋ ገመ፤ አይቀሬ ነውና፤ መከራ ለመቀበል ያልቈረጠ ለውጥን ማምጣት፣ ታሪክን መቀየር አይችልም:: «ነገር ግን እኛ ብን ሆን ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለየውን ቢሰብ ክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላ1፥8) እያለ ሲናገር ራሱንም አያ ተርፍም:: በጳውሎስ ውስጥ የሠራ የእግዚአብሔር ጸጋ የተመ ሠገነ ይሁን:: ለራሱም አይሳሳም:: ይህንን የወንጌል ቃል ሽቃ ቅጠን በኋላ በሌላ መልክ ሌላ ወንጌል ይዘን ብንመጣ እኛም ብንሆን የሰማዩ መልአክም ቢሆን የተረገምን እንሁን:: ጽኑ ርግጠኛነት የተሞላ ቃል ነው::

በግጻዌ መለኮት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በሥላሴ ዘንድ በዘላለማዊ ዕቅድ የተደነገገውን ይህን የወንጌል የድነት መንገድ ለመበረዝ የሚፈልግ መልአክ እንኳ ቢኖር ምንም ዐይነት በብርሃን የተሞላ ይሁን ምንም ያህል በእግዚአብሔር ዘንድ እገኛለሁ ይበል፤ የእግዚአብሔርን ፊት በየዕለቱም ይይ፤ ነገር ግን ከዚህ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክ ይውደቅ፣ ይከስከስ ነው የሚለው። በዚህ ነገር እርሱ ከማን ጋር እንደ ሆነ ያውቃል፤ ምንም አይደራደርም፤ አያቅማማም። በዚህ ቦታ የሚናገረው ስለ ክፉ መልአክ አይደለም፤ ስለ ቅዱሳን መላእክት ነው።

በብርሃን የተሞላ፣ አንዴ ሲገለጥ ምድርን የሚያናውጥ፣ በአንድ ሌሊት 185 ሺህ ሬፍርፎ የሚያደርግ ጉልበተኛም ቢሆን፣ ይህንን ወንጌል ቢያጣምም የተረገመ ነው። ይህንን ሲል ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማት ነው።

«ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሠኛለሁኝ? ወይስ ሰውን ደስ ላሰኘው እፈልጋለሁ? ዓላማዬ እርሱ ነውን? አይደለም ነው» የሚለው። "አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም" (ገላ1፥10)። እንደ እሮን ሰውን ደስ በማሰኘት ከሄድኩኝ እንደ እርሱ ከሆነ የክርስቶስ ባሪያ አልሆንም።» ማለቱ ነው።

እንደምናውቀው፣ ቀደም ሲልም እንዳየነው የድነት ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። የድነታችን መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመስቀል መከራ በመታዘዝ የፈሰሰው ደም ነው፤ የድነታችን መሠረት። የድነት መንገዱ የእምነት መንገድ ነው። መተግበሪያ ኀይሉ ደግሞ የሥጋ ኀይል አይደለም፤ የዕውቀት ኀይል አይደለም፤ የዚህ ጉልበት አይደለም፤ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው። ይህንን አጥብቀህ ያዝ ይህንን የሚመርዝ ነገር ተከላከል ነው የሚለው።



በመስቀሉ ላይ በተከናወነው ነገር ከፈሰሰው ደም የተነሣ የኀጢአት ሥርየት እንዳገኘን ከበደልና ከኀጢአት ነፃ የሚያወጣ ስርየት እንደ ሆነልን ይናገራል። ከዚያ ደግሞ በዚሁ በመስቀል ላይ በተሠራው ሥራ ከፍርድና ከኩነኔ ነፃ የሚያደርግ ጽድቅ እንደ ታደለን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ያ ብቻ አይደለም ከሕግ ሥራ ከሕግ ርግማን ከሕግ ሞግዚትነት፣ ከከንቱ ኑሮ በደሙ ተዋጅታችኋል ይለናል። በእኛ ላይ ያለው የዕዳ ጽሕፈት ተደምስሷል፤ ዋጋው ተከፍሏል። በብርና በወርቅ ሳይሆን በከበረው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተገዝታችኋል ይላል። አሁንም ከሕግ ርግማን ከከንቱ ኑሮ በደሙ ተዋጅተናል፤ የአምላካችን የክርስቶስ ኢየሱስ ገንዘብ ሆነናል።

በዚሁ መሠረት ደሙ «ሰላማችን ነው» ይላል፤ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበት ነው። እርቅ ብቻ ሳይሆን ከዚያም አልፎ ተርፎ ለእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ሆነናል፤ ያ ሁሉ የተከናወነው በደሙ፣ በመስቀሉ ላይ በተሠራው ሥራ ነው።

በመስቀሉ ድልንም አግኝተናል። በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞቱ ሻረው፤ በመስቀሉ አለቅነትና ሥልጣናትን ስለ ገፈፈ የጨለማ ሥልጣን በእኛ ላይ ቦታ የለውም። ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀሉ በኩል እስከመጣን ድረስ በመጨረሻ በፍፅሙተ ድነት ወደ ዘላለም መንግሥት እንገባለን፤ ይኸ የድነታችን መሠረት ነው።

ግን በዘመናችን በመስቀል ላይ ክርስቶስ ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ የፈሰሰው ደም በዚያ ላይ ሥጋው መሰቃየቱ መቈረሱ ለኀጢአታችን ሥርየት አስተዋጽዖ አያደርግም የሚል ትምህርት እየተረጨ ነው፤ ከዚህም የባሰ የሚዘገንን ትምህርት እየሰማን ነው፤ ይህም «ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሰይጣናዊ ባሕርይ ወሰደ» የሚለው ትምህርት ነው። «ጌታ በጥላቻና በርኩሰት ተሞላ፤ በሰይጣን እጅ ወደቀ። በሲኦል ውስጥ ገባ እኛን

ለማዳን፣ ይኸውም ከሰዋዊ ባሕርይ አውጥቶ ወደ መለኮት ባሕርይ ሊያሻግረን» በማለት የማይሆን ጥቅስ ከሀውደ ምንባቡ ዘንጥለው ወስደው ያጣምማሉ:: «እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ እርሱን ስለኛ ኀጢአት አደረገው» የሚለው ጥቅስ ተወስዶ ነው፤ ነገር ግን መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ ነገር አይረክስም፤ በብሉይም ስንመለከት ንጹሕ የሆነ ነገር ነው የሚቀርበው:: ለኀጢአት ዋጋ ሆኖ ይቀርባል እንጂ ያ ነገር አይረክስም::

በእንደዚህ ሀይነት የምትቸገሩ ካላችሁ ምናልባት ይደግፉችሁ ይችላል ብዬ የማስበው አንድ ክፍል አለ:: (ዘሌ6፥25-27) «አሮንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ ተናገራቸው የኀጢአት መሥዋዕት ሕግ እንዲሁ ነው:: እርሱም ቅድስተ ቅዱሳን ነው:: ለኀጢአት የሚሠዋው ካህን ይበላዋል፤ በመገናኛው ድንኳን ዙሪያ ባለው አደባባይ በተቀደሰ ስፍራ ይበላል፤ ሥጋውን የሚነካ ሁሉ ቅዱስ ይሆናል፤ ማናቸውም ልብስ ደም ቢረጭበት የተረጨበትን በተቀደሰ ስፍራ ታጥበዋለህ::» በብሉይ እንኳ ለመሥዋዕት የሚቀርበው እንከን የሌለበት ነገር ለኀጢአት መስዋዕት ሆኖ ቢቀርብም ራሱ መስዋዕቱ አይረክስም::

"በመስቀል ላይ ተሰየጠነ" የሚለው የኢጋንንት ትምህርት ነው:: በዚህ መንገድ የሄድን ካለን ማንም ምንም ይበል ንስሓ መግባት አለብን:: *«የክርስቶስ ኢየሱስን ደም ያክፋፋ ወዮለት»* (ዕብ 10፥29) ይላል:: «ይሄ ስለኀጢአት ሥርየት የሚፈሰው ደሜ ነው» ያንን ብንለውጠው ድነታችን የመጣው ከሲኦል ውስጥ ነው ብንል ማኅበርተኝነታችን ከማን ጋር ነው? እስጊ ሁኔታ ላይ ነን::

*"በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ መግባቢያ ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ"* (ቈላ 2፥8)::



*"በልዩ ልዩ ዐይነት እንግዳ ትምህርቶች አትወሰዱ ..."* (ዕብ 13፥9)::

የድነት መንገዱ የእምነት መንገድ ነው:: እምነት ደግሞ ስንል ጳውሎስ በገላ 2፥20 ያለውን ብናስብ መልካም ነው:: *«እኔ አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም»* እያለ ከተናገረ በኋላ *«አሁን በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት ነው:: ስለ እኔ እራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ነው:: በእምነት የምኖረው ኑሮ ነው»* ይላል (ገላ 2፥20)::

ፍቅራችን፣ ግንኙነታችን ሁሉ በእምነት ነው፤ ማመን ይኖርብናል:: ሚስታችን የእኛ መሆኗን ለእኛ እንደምትጠበቅልን ማመን ከሌለ በጣም ችግር ነው:: በፍቅርና በወዳጅነት መካከል እምነት ያስፈልጋል፤ ያለ አባትና ያለ እናት የመጣ ሰው የለም:: እናቴ እናቴ ለመሆኗ ምንም ማስረጃ የለኝም:: ስጸነስ ማስረጃ ይዤ አልመጣሁም፤ የተፈጥሮ እናቴንና የተፈጥሮ አባቴን የምቀበለው በእምነት ነው::

የሔዋን ችግር የእምነት ችግር አልነበረም:: የእምነት ችግር ማንን ነው የምናምነው? የሚለው ነው:: የእምነታችን ማረፊያ ማን ነው? ሔዋን እግዚአብሔርን ከማመን ይልቅ ሰይጣንን አመነች እንጂ ያለ እምነት አልነበረችም፤ ማንን ነው የምናምነው? እምነታችን ማረፍ ያለበት ማን ላይ ነው? ነው ጥያቄው::

እምነታችን ክርስቶስ ተገልጧል ይላል:: ዳግም ልደት የምናገኘው ከሥላሴ አንዱ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ነው:: ይህ ወንጌል ለጢሞቴዎስ ብቻ አይደለም ለእኛም ነው የተጻፈው፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ይለዋል:: ይህንን የእውነት ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣል:: ይሄ የመስቀሉ ቃል እንደ ሞኝነት ይቈጠራል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንኳ እየገፉት ነው፡፡ የሚመቸው ወንጌል የማኅበራዊው ወንጌል (Social gospel) እየሆነ ነው፡፡ ወንጌል ምድራዊ ተድላ የሚሰጥ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ አንተ ኀጢአተኛ ነህ ተብሎ ወደ ንስሐ የሚጣራ ወንጌል አይወደ ድም፤ በብዙ ቦታ ስለ ፍቅር እንጂ ስለ በደል /ኀጢአት አትስ በክ፣ አትናገር ይባላል፡፡ በዚያ መንገድ ደግሞ የሄዱ ብዙ አገ ልጋዮች አሉ፡፡ «ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱ በት ዘመን ይመጣል፡፡» ይመጣል ከተባለ ይመጣል፤ ከመጣም መገረም የለብንም፡፡

አንዳንዴ የተጻፈውን ትንቢት እንደሌለ ለመቍጠር እንፈልጋ ለን፤ «ብዙ ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይመጣሉ» ይህን የተናገረው የነቢያት ሁሉ ነቢይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ይሆናል «እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ» ተብሏል፤ «ስለዚህ ስለ ትምህር ትህ ተጠንቀቅ፡፡ በጊዜውም ያለጊዜው ፅና፤ ቢመችህም ባይመ ችህም፣ ደጋፊ ቢኖርም ባይኖርም፣ የአዳማጩ ፊት ፈገግ ቢልም ቢኮሳተርም አንተ ግን ጽና፤ በዚያ ውስጥ የምታተር ፈው ሰማያዊ ትርፍ አለ» ነው የሚለን፡፡

«እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ» የምኞት ጣዖትን ያቆማሉ፤ ስለዚያ ለዚያ የሚያጥኑላቸውን አስ ተማሪዎች ይፈልጋሉ፤ ጣዖት ማቆም ማለት ምድራዊ ፍላጐታ ችን የሚያረኩልን ስለ ጽድቅና ስለ ቅድስና የማይሟገቱትን አማልክት ማቆም ማለት ነው፡፡ እንደ በዓል ዝናብ የሚያዘንቡ ልን ነገር ግን ስለ ጽድቅ ስለ ቅድስና ጥያቄ የማያነሱብን፣ የማያስቸግሩንን የምኞታችንን ጣዖቶች ማቆም ማለት ነው፡፡

እውነትንም ከመስማት ፈቀቅ ይላሉ ጆሮአቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረት ፈቀቅ ይላሉ»፡፡ ዘመነኛ ስብከት ምናልባት ከመ ጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር እንደ መነሻ ይጠቅሳል፤ የሚበዛው ግን ሰው ሠራሽ የፈጠራ ታሪክ ነው፤ መንፈሳዊ ይዘቱ ገለባ፣



ለጊዜው ስሜትን የሚያረካ ነው፡፡ የሚያሞቅ ነው፤ ዛሬ 'አዎን ታዊ' ነገር ተናገር 'አሉታዊ' (ኔጋቲቭ) ነገር አትናገር የስብ ከት መመሪያ እየሆነ ነው፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመለከት አሉታዊ ነገርን ይናገራል፡፡ አሉታዊውን ተናግሮ ግን አይቆምም ወደ አዎንታዊ ይሄዳል፡፡ «አንተ ኀጢአተኛ ነህ የእግዚአብሔር ፍርድ አለብህ» ብሎ ከተናገረ በኋላ ይሁንና ድነት በክርስቶስ ታውጆልሃል፤ የዘላለም ሕይወት ተዘጋጅቶል ሃል» ይላል፡፡ የዘላለም ክብር ተዘጋጅቶልሃል፡፡ ነገር ግን አሉታ ዊውን አትናገር ማለት ለንስሐ ጠላት፣ ለሰይጣን መመቸት ነው፡፡ ዛሬ የሚስማማቸውን የሐሰት አስተማሪዎች የሚያከማቹ ብዙ ቤተ እምነቶች ቢበዙ አይደንቅም፡፡

## 5. የጳውሎስ ምሳሌነትና ለጢሞቴዎስ የሚሰጠው አደራ

*"አንተ ግን ትምህርቴን፣ አካሄዴን፣ ዐላማዬን፣ እምነቴን፣ ትዕግ ሥቴን፣ ፍቅሬንና ጽናቴን ሁሉ ታውቃለህ"* (2ጢሞ 3፥10)፡፡

ጳውሎስ ሕይወቱን ለጢሞቴዎስ አሳይቶታል፡፡ ምክራችን የቃል ብቻ እንዳይሆን እግዚአብሔር ያድለንና ለሚያዩን ሰዎች የሚ ቀርላቸው የጽድቅ ትሩፋት በውስጣችን ያሳልፍ፡፡ ጳውሎስ ያንን አሳይቶአል፡፡ «አይተሃል» ይለዋል፡፡ በነዚህ ስፍራዎች በልስጥራ በአንፆኪያና በኢኮንዮን የሆነብኝን የታገስኩትን ትምህርቴን አካሄዴን ታውቃለህ፡፡ ከአንተ የተሰወረ አይደለም፡፡ ትምህር ቴን ፍቅሬን በመከራ ውስጥ መጽናቴን ታውቃለህ፡፡ ለማስረጃ ያህል በአንፆኪያ በኢኮንዮን በልስጥራ የሆነብኝን የታገስኩትን ስደት ታውቀዋለህ፡፡ አንተ ራስህ ምስክር ነህ ይህን ካለው በኋላ ነው አደራ የሚለው፣ 'አንተ ግን' የሚለው፣ ይቻላል ለማ ለት ነው፡፡ አንተ ግን ብሎ የሰጠው መመሪያ የሚቻል ነው፡፡ በእኔ ሕይወት ውስጥ ተችሎ አይተኸዋልና ትችላለህ፡፡

ቀደም ሲል ያነሣነውን ሀሳብ ደግመን እንየው፤ ጳውሎስ ጥሩ

ምሳሌ ነው:: በአገልግሎቱ የእግዚአብሔር ጸጋ በተለየ ሁኔታ
ሲገለጥ የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ አልነበረም:: በክርስ
ቶስ ላይ የሚያጠላ ነገር የለውም:: ክርስቶስን እንጂ ራሱን የሚ
ያጐላ አካሄድ ፈፅሞ የለውም:: ለቆሮንቶስ አማኞችም «እናን
ተን ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ» ይላቸዋል:: በዚያ ያሉ
በጳውሎስ ዙሪያ ሊሰባሰቡ ሲፈልጉ አንዳንዶቹ እኔ የኬፋ ነኝ፣
የአጵሎስ ነኝ የሚሉትን አላስጠጋቸውም:: እናንተ ብርሃኑ
በርቶላችኋል:: ወደ ፊት ተተኪ አገልጋይ እናንተ ናችሁ አላላ
ቸውም:: ዞር በሉ ነው ያላቸው «ጳውሎስ ምንድን ነው? አጵ
ሎስ ምንድን ነው? እኔ ተከልሁ፣ አጵሎስ አጠጣ:: በዚህ ውስጥ
የተከለም ያጠጣም ምንም አይደለም የሚያሳድግ እግዚአብሔር
እንጂ:: እኔ ብተክል ብዘራም ዘሩ የእግዚአብሔር ነው:: እርሱ
ቢያጠጣ ውሃው የእግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ አጵሎስ ምንም
አይደለም፣ እኔም ምንም አይደለሁም:: እግዚአብሔርን ጸጋ እን
ደበዛልን የሚመስለን ወይም በእኛ ውስጥ የተለየ ጸጋ የሚያል
ፍብንን እግዚአብሔር ይጠብቀን::

ብዙ ጊዜ የራሳችን ደቀ መዛሙርት በዙሪያችን እንዲሰባሰቡ
እናደርጋለን:: በያለንበት ደረጃ በቤተ ክርስቲያኖቻችን በራ
ሳችን ዙሪያ ሰዎች እንዲሰበሰቡ እናደርጋለን:: እኔ የእርሱ ነው
የሚስማማኝ ሲሉ ደስ ይለናል:: እነርሱን ነው እዚህ ቦታ
እንዲመረጡ የምናደርገው:: ጳውሎስ ሁሉን «ለአንድ ወንድ
አጭቻችኋለሁ::» ለጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት
አፍሪዎች እንጂ ለራሳችን ደቀ መዛሙርት ሰብሳቢዎች አይደ
ለንም:: ደቀ መዛሙርት ክርስቶስን ሲተውት እናያለን:: በአ
ንድ ወቅት ክደውታል፤ ተበትነዋል:: ክርስቶስ ቢተውት እን
ኳን ልቡ ሰፊ ነው:: ማቀፍ ይችላል:: የእኛ ደቀ መዛሙርት
ይተዉናል:: ስለዚህ በእኛ ዙሪያ ከምንሰበስብ ወደ እርሱ ብን
ገፈትር ይበጀናል::

በልስጥራ፣ ጳውሎስ ሲያልፍ አንድ ከማኅፀን ጀምሮ እግሩ



የሰለለ ሰው ያይና ያ ሰው እምነት እንዳለው ተመልክቶ በእግ
ዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ፈውስን እንዲያገኝ ምክን
ያት ይሆናል:: የልስጥራ ሰዎችን አማልክት ሰዎችን መስለው
ወደኛ ወርደዋል አሉ:: በርናባስን ድያ ጳውሎስ ደግሞ በመና
ገር ዋና ስለነበር ሄርሜን አሉት:: ሄርሜን ከግሪክ አማልክት
መካከል የአማልክቶችን ሀሳብ እያመጣ ለሕዝቡ የሚተረጉም
አምላክ ነው:: አማልክት ወርደዋልና ስለዚህ እንሰዋላቸው አሉ::
በከተማውም ፊት ቤተ መቅደስ ያለው የድያ ካህን ኮርማን
አምጥቶ ሊሰዋላቸው ወደደ::

«ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸ
ውን ቀደው በሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ::» ብዙ ሊያጥ
ኑልን የሚፈልጉ ታቦት ሊቀርጹልን የሚነሱ አሉ:: እንዴት
ነው የምንቀበላቸው? በፈገግታ ነው? እነ ጳውሎስ ግን ልብሳ
ቸውን ቀደዱ ስለዚህ የወንጌልን እውነት አፅንተው ያዙ::

የእርሱ ማንነት በክርስቶስ ኢየሱስ በአምላካችን ላይ አላጠ
ላም:: «ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ:: እንዲህም አሉ:-
እናንተ ሰዎች ይህን ስለምን ታደርጋላችሁ? እኛ ደግሞ እንደ
እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን ከዚህ ከንቱ ነገር ሰማይናን ምድ
ርን ባሕርንም ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር
ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን» ትንንሽ አማልክቶች ነን
አሉ እንዴ? አላሉም::

«ይህንንም ብለው እንዳይሠውላቸው ሕዝቡን በጭንቅ አስተዋ
ቸው» እንደዚህ ‘ዐይነት ልቡና እግዚአብሔር በየቤተ ክርስ
ቲያኑ ላሉት አገልጋዮች ይስጥ::

የሚሸሹ፣ የእነርሱ ነገር በክርስቶስ ላይ ጥላ የሚያጠላ መስሎ
ከታየ የሚደበቁ፣ ልብሳቸውን የሚቀዱ፣ እኛ ምንም አይደለ
ንም የሚሉ፤ የዚህ ዐይነት ሰዎች ቢበዙልን መንፈሳዊ እንቅስ
ቃሴው እየበራ ይሄዳል:: አለበለዚያ ሸንጋይ ገብቶ ስፍራውን

ይወስደዋል::

የሚገርመው ነገር ግን አይሁድ ከአንፆኪያ ከኢኮንዮን መጥ
ተው ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ሲወግሩትና የሞተ መስ
ሏቸው ከከተማው ውጪ ሲጐትቱት፣ "እንሰዋላችሁ" ያሉት
ሰዎች ምንም አልሆኑላቸውም፤ አልተከላከሉላቸውም:: ተመልካ
ቾች ሆኑ:: በሰዎች አንታመን፣ ከሰዎች ከብር ባንጓጓ መልካም
ነው:: ዛሬ ሰዎች ያጀቡን የሚመስለን አገልጋዮች ካለን በዚያ
ላይ አንደገፍ:: ጌታ ኢየሱስ ይህ ደርሶበታል፤ ሆሳዕና ብለ
ውለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስቀለው ብለውታል::

በእውነት መንገድ ስንሄድ የእውነት ሰዎች አብረውን ከተጓዙ
እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: ግን እነርሱ ድጋፋችን አይ
ሁኑ:: ምንጊዜም የሚደግፈን ታማኙ እግዚአብሔር ነው:: በዚህ
መንገድም የምጓዘውን አይተሃል ይለዋል:: «በእውነት በክርስ
ቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ
ይሰደዳሉ::» 6÷11 «አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ
ሽሽ፤ እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታ
ተል» ይለዋል:: ምንድን ነው? «አእምሮአቸውም በጠፋባቸው
እውነትንም በተቀሙ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚ
ሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ:: እንደዚህ ካሉት ራቅ፤ ኑሮዬ
ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማት
ረፊያ ነው» የሚል ነው::

ይህን ሲለው እርሱ በተግባር አሳይቶ ነው:: «በእውነት በክር
ስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ
ይሰደዳሉ:: ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች እየሳቱና
እያሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ:: አንተ ግን በተማርህበትና
በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር» ይለዋል::

"ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና፣ ከህፃንነትህም ጀምረህ



ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ
የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሀውቀሃል:: የእግዚአብሔር
ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአ
ብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብ
ንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል"::

"በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው
በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በመገለጡና በመንግሥቱም
እመክርሃለሁ:: ቃሉን ስበክ፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፤
ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም:: ሕይ
ወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣ
ልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደ ገዛ ምኞ
ታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ:: እውነትንም ከመ
ስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ::
አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፤ መከራን ተቀበል፤ የወ
ንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ አገልግሎትህን ፈጽም"::

"በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድ
በትም ጊዜ ደርሶአል:: መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫ
ውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ
አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ
ያን ቀን ለእኔ ያስረክ ባል፣ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት
ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም::» (2ጢሞ 3÷12-4÷8)

ለጢሞቴዎስ አካሄዱ ከሌሎች የተለየ እንዲሆን እንደ ተነገ
ረው አይተናል:: በአንድ በኩል በሕይወቱ አኗያ በሕይወቱ
የተለየ እንዲሆን ከጐልማሳነት ምኞት እንዲሸሽ በጽድቅ መን
ገድ በትህትና መንገድ፣ በእምነት መንገድ እንዲሄድ ለዚህም
ደግሞ ጳውሎስ ራሱ የሕይወት ምስክር እንደ ሆነ እየገለጸለት
መክሮታል::

ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ደግሞ በሁለት አቅጣጫ ይነግረዋል። ትምህርቱና አገልግሎቱን በተመለከተ መንገድ አንተ ግን በተማ ርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር። የምትሰማው፣ የሚነ ገረው፣ አንተ እንደ ተማርኸው በልብህም እንደተቀበልኸው አሜን ብለህ ከሕይወትህ ጋር እንዳዋሃድኸው ዐይነት ሳይሆን ሌላ ከሆነ፣ የተሳሳተ ከሆነ፣ ብዙም ቢባል፣ ብዙም ቢነገር ብዙ ድጋፍና ሆሆታም ቢያገኝ፣ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህ በት ጸንተህ ቁም።

ምነው ቢባል ብዙ ክፉዎች አሉ፤ አታላዮች አሉ። እያሳቱ የሚስቱ፣ እየሳቱ የሚያስቱ በዚያም ላይ እየጨመሩ የሚሄዱ፤ ክፉዎች ሰዎች አሉ፤ በክፋት እየባሱ የሚሄዱ አሉ። አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር። አንተ የተማርከው ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው። የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴና አገ ልግሎት ሁሉ የሕይወታችንም መመሪያ ማዕከል ሊሆን የሚገ ባው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። እንትና እንደዚህ ብሏል የሚለው አነጋገር መመሪያችን ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል በሰጠን በዚህ መጽሐፍ ምን ይላል? መለኪ ያችን የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት። ያንን ቻል ባልን ጊዜ በሕይወትም በትምህርታችንና በአገልግሎታችንም እንስ ታለን። ሰዎች ይስታሉ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን አንተ ግን በተ ማርህበት በተረዳኸው ነገር ጸንተህ ኑር፤ የተረዳኸውን ወንጌል አጥብቀህ ያዝ ይለዋል።

## 6. በሚገጥምህ ውጊያ ጽና

«እንደገዛ ምኞታቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ ጆሮአቸውን የሚያሳክክ ነገር ለጆሮአቸው የሚጣፍጠውን መስማት ይፈል ጋሉ»። ጆሮአችንን ሲበላን ስናከው ጥሩ ስሜት ይሰማናል። በደረቅ ነገር ማከክ ጥሩ አይደለም። ፈረንጆች ጥሩ ጥሩ ማከ ኪያ አላቸው፤ እኛ ግን ቢያንስ ቢያንስ የዶሮ ላባ አለን፣ ያን



ጊዜ ጥሩ ስሜት ይሰማናል። «ሰዎች እንደዚህ ዐይነቱን ይፈል ጋሉ» አንተ ግን በዚህ መንገድ ልትሄድ አትችልም። ስለዚህ በዚህ መንገድ ላለመሄድ ወስን ነው የሚለው።

አካሄድህ ከብዙዎቹ የተለየ ቢሆንም ደግሞ አትሸነፍም፤ የእ ግዚአብሔር ስም የተመሠገነ ይሁን፤ አትሸነፍም፣ ድል አለ ነው የሚለው፤ ኤርምያስን የጠራው አምላክ ተነስ ታጠቅም ያዘዝ ሁህን ሁሉ ንገራቸው ሲለው "ይዋጉሃል" አለው። የሚዋጉህ አን ድና ሁለት አይደሉም ብዙዎች ናቸው። ከኤርምያስ የሚወ ጣው ቃል አይመቻቸውም ነበር፤ ካህናቱ ይዋጉሃል የእግዚአ ብሔርን ቃል ጥለው ነበርና። ሕዝቡን መግዛታቸውን ነበር የሚያዩት። የሕዝብ አለቆችም አይወዱትም 'ጥቦ ንጥቂያ ይቅር'፣ 'ፍትህ ይስፈን' ይል ነበር። 'ቤታችሁ በሸንገላ ተሞል ታለች' ይል ነበር፤ ነውራቸውን ይገልጥ ነበር፤ ኑ ተመለሱ ይል ነበር። አይወዱትም፤ ማን ይወደዋል የዚህ ዐይነቱን ሰው? ነቢያቱም አይወዱትም ነበር ስንት የሰው/ የሐሰት ነቢያት ናቸው ኤርምያስን በመቃወም በኤርምያስ ሕይወት ዙሪያ የተ ንጋጋው?

እርሱ እግዚአብሔር የሰጠውን ሲናገር ረሓብ፣ ሰይፍ ቸነፈር እየመጣ ነው ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሳችሁ ፍርድ አለ ሲል ሌሎች ነቢያት ይነሡና ሰላም ነው ምንም የለባችሁም እግዚአብሔር ሰላም አሰጣችኋለሁ ይላል። ሰይፍም አታዩም ራብም አታዩም ይሏቸው ነበር።

ኤርምያስ በጣም ይጨነቃል «ጌታ ሆይ እንዲህ ትለኛለህ ነቢ ያት ግን እኮ ሰላም ነው ይሏቸዋል» እያለ አምላኩን ይጠይቅ ነበር። እርሱ "ሰባው ዓመት እስኪፈፀም ከባርነት አትመለ ሱም" ይላል፤ ንስሐ አልገቡምና። ሌላው ይመጣና "በሁለት ዓመት ውስጥ የምርኮ ቀንበር ይሰበራል" ይላል። «ይኸ እንዲያ ውም በጠላት የተገዛ ነው ተባለ፤ ይገደል ብለው ንጉሡን ጠየቁ።

ሴዴቅያስን ለመኑትና ጕድጓድ ውስጥ ተጣለ፤ እግዚአብሔር ግን ታደገው። ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክን ልኮ «ይዋጉሃል እኔ ከአንተ ጋር ለማዳን እሆናለሁና ድል አይነሡህም» ብሎ አፅናናው።

ውጊያ አይቀሬ ነው ለምቾት ብናፈገፍግ አይበጀንም። የሚመቸው በእግዚአብሔር ዘንድ መሆን ነው።

## 7. እርሱን ተማምነህ ኑር

*«በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል፤ እግዚአብሔርን አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ፤ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፤ በእርሱም እታመናለሁ ... በላባዎቹ ይጋርድሃል በክንፎቹ በታች ትተማመናለህ»* (መዝ 91፥1-2)።

እርሱን ተማምኖ ማደር ትልቅ ነገር ነው፤ እንዲህ ተማምኖ አለማደር አስቸጋሪ እንደ ሆነ አስታውሳለሁ፤ በተለይ እኔና ባለ ቤቴ እንደተጋባን አንዳንድ ዕቃዎች ገዝተን ቤት መሥርተን እንዳሳመርነውና ጥቂት እንደቆየን ሌሊት ሌሊት ሌባ እየመጣ አስቸገረን፤ በየዕለቱ ሊባው አጥር ዘሎ ይገባል፤ ስለዚህ አለመተኛት ጀመርን በተለይም እኔ። (ለማንም አትናገሩ እንጂ እኔ አንደኜ ከተኛሁ አልሰማም) ስለዚህ ያለኝ ምርጫ ፍጥጥ ብሎ ማደር ሆነ። ሲነጋ ሥራ እሄዳለሁ ችግር ነበር።

ርግጥ በዚያ ግቢ ውስጥ ደግሞ የአንድ ሌላ ሰው ቤት አለ፤ ባለቤቱም በጣም ንቁ ናት፤ ኳ ሲል ትነቃለች። እና በኋላ እንዳልታመን ደግሞ ድንገት ጅው አድርጎ እንቅልፍ ቢወስዳትስ እያልሁ ተቸገርሁ፤ ከዚያ በኋላ በጸሎት ነገሩን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚሻል አመንሁ። ማታ ስንተኛ «አንተ ጠባቂዬ ነህ፤ አንተ ፈቅደህ ከሆነ ቢወስዱት ይወሰዱት» ብዬ እየጸለይሁ ከዚያም ለጥ ብዬ መተኛት ጀመርሁ። ከዚያ በኋላ ምንም አልነበረም። የሚያስደነግጥ ነገር ድምፅም የለም፤ ኮቴም የለም፤ *«በላባዎቹ ይጋርድሃል በክንፎቹም በታች ትታመናለህ እውነት እንደ ጋሻ ይከብሃል፤ ከሌሊት ግርማ፣ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፣ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፣ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም። በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም በሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ ወደ አንተ ግን አይቀርብም። በዐይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፣ የኀጥአንንም ብድራት ታያለህ። አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ። ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፤ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፣ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ፤ በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፣ ስሜንም አውቋልና እጋርደዋለሁ»* (መዝ 91)።



## 8. የሕይወትን ዋና ነገር አጥብቀህ ያዝ

ስለዚህ አንተ ተመለስ በብዙሃኑ መንገድ አትሂድ በምቾት መንገድ አትሂድ የእውነተኛ ምቾት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ከብዙኀኑ ጋር ለመስማማት አትውጣ። «ንአምን በአሐዱ አምላክ» ብሎ በአንድ አምላክ ታምኖ መሄድ ነው የሚሻለው። በራሳችን አንሆንም፤ ኤርምያስ «ሰው ሕይወቱ በእጁ አይደለም፤ አካሄዱንም ማቅናት ከራሱ የሚመጣ አይደለም» ይላል፤ የእንግሊዝኛው የተሻለ ጉልህ ይመስለኛል፤ I know, O Lord  that a man's life is not his own. It is not for man to direct his steps ይላል። መንገድን ማቅናት በራስ አይደለም። ስለዚህ በእግዚአብሔር ማረፍ ይሻላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ ነው የተገለጠው። የሠራዊት አምላክ የእግዚአብሔር ለብ ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ነው፤ ጌታ ኢየሱስን ቸል ብለን፣ ይህን ጠባቡ መንገድ ቸል ብለን፣ በሰፊው መንገድ ሄደን እናተርፋለን ብንል አይሆንም፤

ጳውሎስ «ነፍሴ በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እቆጥራታለሁ» ይላል፤ ይሁንና በመጨረሻው «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል። ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክበኛል» ይላል። መቼ ነው ከጌታችን ጋር የምንገናኘው? በአፀደ ሥጋ ሳይሆን ከዚህ የሥጋ አካል ወጥተን ነው።

ሁላችንም እናልፋለን የዘላለም መንግሥት የክርስቶስ መንግሥት ይገለጣል፤ ሁሉ ያልፋል ትካዜውም ያልፋል፤ ፍንደቃውም ያልፋል፤ ችግሩም ያልፋል፤ ምቾቱም ያልፋል አጀቡም ያልፋል፤ ብቸኝነቱም ያልፋል ማማቱም መታማቱም ያልፋል፤ ሁሉ ያልፋል፤ እኛም እናልፋለን። «ዓለሙም ምኞቱም ያልፉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ እርሱ ለዘላለም ይኖራል፤ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ»።

በነገሥታት መጽሐፍ እንትና እንትና ነገሠ ይህን አደረገ፤ ሞተ፤ ልጁ ደግሞ በምትኩ ነገሠ፣ ሞት እያለ ሲያቀርብልን፣ በጥቂት ደቂቆች ውስጥ የስንቶቹን መወለድ፣ መንገሥና መሞት እናያለን፤ አሁንም እንደዚሁ ነው። የዕድሜን ዳገት በተስፋ ይዘን የዕድሜን ቍልቍለት ግን በፀፀት እንዳንሄድ ከእግዚአብሔር ጋር ብንስማማ ይሻለናል።

ለመኖር በመዘጋጀት ዛሬ የሕይወታችንን ወቅት እንዳናሳልፈው እግዚአብሔር ይርዳን። አንድ ጊዜ አንድ ቡድን ከጠላት ፊት ሸሽቶ ይሄድ ነበር። በሚሄድበት ጊዜ በዋሻ ውስጥ ማለፍ ግድ ሆነበት፤ ዋሻው ረዥም ነው ደግሞም ጨለማ ነው፤ ግን በዋሻ ውስጥ ሲሄዱ የሚረግጡት ለየት ያለ ጠጠር ሀይነት ስሜት ያለው ነገር ነበረ፤ የዚህን ጊዜ አንዳንዶቹ ዘገኑት ያዙት አንዳንዶቹ ደግሞ አይ ምንድን ነው? ብለው ተውት።



ከዘገኑት መካከል አንዳንዶች ጥቂት ተጮዘው በተኑት። አንዳንዶቹ ግን ይዘው ወጡ፤ ወደ ብርሃን ከወጡ በኋላ ጠላት ግን እየተከተላቸው ነው። ሲያዩ ዘግነው በኋላ የጣሉት ቈጫቸው፤ ዘግነው ይዘው የወጡትም ቈጫቸው፤ ያልዘገኑትም ቈጫቸው። ነገሩ ለካ ዋጋው ውድ የሆነ በአልማዝ ደረጃ የሚቈጠር የከበረ ድንጋይ ኖሯል። ያልዘገኑት እና ዘግነው የጣሉት «እንዴት እንዴት ይህን ያህል ሸክም እኮ አልነበረም ብንዘግነው፣ ብንይዘው ኖሮ» ብለው ሲቆጩ የዘገኑትም ደግሞ «ለምን ይህቺን ብቻ ዘገንን?» ብለው ተቈጩ። በሕይወት መንገድ እንድንሄድ ተጋብዘናል፤ በሕይወት መንገድ ያልገቡም እንደሚቈጫቸው፣ የገባንም፣ የተሠማራንም በሙላት እንድንይዘው፣ ደግሞ የሚቈጨን እንዳይሆን በተጠራንበት መጠራት መያዝ የሚገባንን እንድንይዝ፣ እስከ ፍጻሜም እንድንጓዝ እግዚአብሔር ይርዳን። ነገ ለመኖር በመዘጋጀት የሕይወታችንን ወቅት አናሳልፍ፤ በመክብብ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ «የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንስማ፤ ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና እግዚአብሔርንም ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ወደ ፍርድ ያመጣዋልና» «በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋን በሙታን ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በመገለጡና በመንግሥቱ እንዳታፍር እነግርሃለሁ» (2ጢሞ 4)።

ጌታችን ይገለጣል የዚያን ጊዜ ሐሴት ይሆንልናል፤ አሁንም ቢሆን የሚመቸው በአምላካችን ዘንድ ነው። እግዚአብሔር ለመልካም ፍጻሜ ያብቃን።

*"ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስና በበሮቿም በኩል ወደ ከተማይቱ ለመግባት መብት እንዲኖራቸው ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው"* (ራእ 22፥14)።

*"መንፈስና ሙሽራዪቱ፣ "ና" ይላሉ፤ የሚሰማም፣ "ና" ይበል፤ የተጠማም ሁሉ ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ በነጻ ይውሰድ"* (ራእ 22፥17)::

**ልመና/ምልጃ**

እንደሚታየው:- ደከመናል፤
ለዛችን ተሟጧል፤
የሕይወት ኀይል እርቆን ቀስስተኛ ሆነናል::

አሻፈረኝ ለፍርስራሽ አሻፈረኝ ለሽንፈት፣
የሚል ወኔ ከእኛ ተወስዷል፤
ልበ ሙሉነታችን ግዞት ወርዷል፤
የዕለት ጕዳያችን፣ የሐሳባችንን አድማስ፣
ገድግዶ ይዞታል፤
ከግል ጕዳያችን ተሻግረን ማየት ተስኖናል::

በዕለት ነገራችን ተወጥረን እርስ በርስም ተፎካክረን፣
በመነቃቀፍ በመናናቅ መጠላለፍን፣
ሥራችን አድርገን ተያይዘነዋል፤
በዚህ ነፍሳችን ተይዛ ትንፋሿ የሲቃ ሆኖአል::

በዚህ ጕስቍልና፣ ቀኖች ለጥቅም ከመዋል አፈትልከው፣
እየነጐዱ የዕድሜም ድውር እየሞላብን ነው::
ምን ይባላል ተስፋው ምኞቱ ታላቅ ሥራ፣
አክናውኖ የማለፍ ጕጕ ናፍቆቱ ሚሾብናል፣
ተጠልፎ ተወስዶብናል::

እንግዲህ ሁሉም ከአንተ ነውና ማጻኑም፣
ጽድቁም ከአንተ ነውና፣
የበጎነት ምንጭ ምን ጊዜም አንተና አንተ ብቻ ነህና፣
በምሕረትህ ተነሥ፤ ታደገን ተሐድሶንም ስጠን፣



በመካከላችን በውስጣችንም ስምህን አክብረው፤
እኛም አይተን ተገንዝበን በሁለንተናችን እንገዛልህና፣
እርስታችን ሁነን ስምህም ትምክሕታችን ይሁን፣
በሕይወት ኑሩ ብለህ ብርሃንህ ጨለማችንን ያስወግድ፤
ዐይናችንም ተከፍቶ፣ የዐይን መስታወታችንም አጥርቶ ይይ፤
ይሁን በል፤ ከአንተ ዘንድ ድንጋጌ ይውጣ::

የሳቱና ገለባ የሆኑ ትንቢቶች፣ ሚርቶች፣ ከክብርህ መገ
ለጥ የተነሣ፣
ወድቀው ይንኰታኰቱ፤ ተቃጥለው ይብነኑ፣
የተሸነገሉ የሕዝብህ እስረኞችም ይፈቱ፣
ነጻ ወጥተው በእውነትህ ኪዳን ተሐድሶ እንደ ኘ ይታነጹ፣
የከበረውን ከተዋረደው፣ ዘላለማዊውን ከጊዜያዊው፣
ከንላፊው፣ ከጠፊው ይለዩ፣
ክብር ለአንተ፣ ክብር ለአንተ ብለው ለሕያውነትህ
ለአምላክነትህ ይስገዱ::

ሁላችንም ሐሰቱን እውነት ነው ብለን፣
ራሳችንን ካግተብንበት ከበባ ከፍ ከፍ ብለን ምንጥቅ
ብለን እንውጣ፣
የብርሃኑ ሙላትም ሁሉን ፍንትው አድርጎ ያሳየን፣
የሸነገልንበትና የተሸነገልንበት ትብታብ ትባንትብ ይበጣጠስ፣
ከእጅ ከእግራችን ላይ ይርገፍ::

እባክህ ጌታ ሆይ እባክህ፣
ዘመናችንን እንደ ቀድሞው ዐድስ፣
መልሰህ አንጸን፣
መልሰህ በአንተ መሥርተን፣
መቆሚያ ዐለት ሁነን፣
ከአሸዋ መሠረት ከእንሽርት አውጣን፣

በከፍታ ላይ አቁመን፣
ሞታችንን በትንሣኤ ሕይወት ተክተህ ሙላን።

አንዛል፤ ይልቁንም:
አንላቅ፣ አንደርጅ፣ እንለምልም፣ አናብብ፣
ፍሬ እንያዝ፣ አንብዛ፣ አንትረፍረፍ፣
ሕይወት ይፍለቅ ይጕረፍም፣
የደረቁ ዐጥንቶች ይሰባሰቡ፣ በጅማት ይያያዙ፣
ሥጋም ይልበሱ በቈዳም ይሸፈኑ፣
በኀይለ ሕይወትም ይሞሉ፤ ይንቀሳቀሱ ይጐልብቱና፣
ታላቅ ሰራዊት ሆነው ይቁሙ።
ከዚያም:
ለአንተ ይጐንበሱ፤ ጠላትን ግን ያስጐንብሱ፣
የጠላትን ሰፈር ሁሉ ይውረሱ።

እንግዲያስ:
ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፣
ምድርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ያበጀ፣
ለሕዝቧ እስትንፋስን፣
ለሚኖሩባትም ሕይወትን የሚሰጥ እግዚአብሔር፣
አንደ ገና ያበጃጀን፤ ከእርሱ በሚመነጭ በእስትንፋሱ፣
ሕይወት ይሙላን፤ በድል ያመላልሰን።

ክብር ለእግዚአብሔር አብ
ክብር ለእግዚአብሔር ወልድ
ክብር ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ
አንድ አምላክ ይሁን አሜን!